# ልጅን እንዴት ላሳድግ

## በምዕራብ አገሮች

ረጅም ባልተጓዙበት ዕድሜ፣ ሠፊና ድንቅ ቁም ነገር መቋጨት ለሁሉም የተሰጠ ጸጋ አይደለም። የሐምራዊት መጽሐፍ ማንኛውም ቤተሰብ ሊያነበውና ሊጠቀምበት የሚገባ እውነታዎች ያዘለ ነው። ደጋግሞ ይባርካትና የተባረከ በረከት እንድትደጋግመን ያብቃት።

*ወይዘሮ አለምጸሐይ ወዳጆ*
*አርቲስት*

ወላጅነት አሳዳጊነት ውል እንደጠፋው ልቃቂት እየተውተበተበ ባለበት በዚህ የጭንቅ ሰዓት እንደዚህ መጽሐፍ ዐይነት አስተዋይና ደፋር ድምፅ ማግኘት እንዴት ጥሩ ነገር ነው! የሐምራዊት መጽሐፍ በጣም ብርቱ ርዕሰ ጉዳይ ይዞአል፤የያዘውን ጉዳይ በርጋታና በጨዋነት ያስተነትናል ፤ለዛሬ የሚሆን ተግባራዊ ምክር ይለግሣል፤ እቅጩን ለመንገር አይፈራም፤በሰሜን አሜሪካ ብቻ ሳይሆን ቁስ አምላኪነት (materialism) በገነነባቸው የትም ቦታዎች ለሚገኙ ሁሉ በጣም ጠቃሚ መጽሐፍ ነው፡፡ ምነው ቀደም ብዬ ባገኘሁት ለሚሉ አዛውንት ወላጆች; በተረፈው ጊዜም እንኳ ለመጠቀም ኢታመንቱ እላለሁ፡፡

*አቶ ንጉሤ ቡልቻ*
**ከቃለ-እግዚአብሔር አንባቢዎች ማኅበር**

ርእስ፧ ልጅን እንዴት ላሳድግ፧ በምዕራብ አገሮች
ጸሐፊ፧ ሐምራዊት ተስፋ

አሳታሚ ሞሪስ ቡክ ፓብሊሺንግ

Printed in the United States by Morris Publishing®
3212 East Highway 30
Kearney, NE 68847
1-800-650-7888

አስተያየት ወይም ጥያቄ ካለዎት፧በሚቀጥለው አድራሻ ይጻፉ
hamrawittesfa@yahoo.com

ያለ አሳታሚው ፍቃድ አብዝቶ ማሳተም የተከለከለ ነው። በማንኛውም መልኩ መረጃዎችን ለመውሰድ ከተፈለገ፣ ሥርዐቱን ጠብቆ ሊጠቀስ፣ በግርጌ ማስታወሻ ሊመላከት ይገባዋል።

All rights reserved. No part of this publication may be reproduced, stored in a retrieval system or transmitted in any form or by any means-electronic mechanical photocopying recording or other wise-without the prior written permission of the copy right owner.





# አበርክቶት



በሕይወቴ ውስጥ ትልቅ ቦታ ላለውና በሕይወት አካሄዱ አቅጣጫዬን ለቀረጸው ለአባቴ፣ ለአቶ ተስፋ ገብረማርያም ይሁንልኝ።



በሕይወቴ ውስጥ ትልቅ ቦታ ላለውና በሕይወት አካሄዱ አትጣጫዬን ለቀረጸው ለአባቴ፣ ለአቶ ተስፋ ገብረማርያም ይሁንልኝ።

# ምስጋና

መጀመርያ፣ አነሳሥቶ ላስጀመረኝ፣ አስጀምሮም ላስጨረሰኝ ቸሩ እግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው ማለት እወዳለሁ።

ቤተሰቦቼ ማለትም እናቴ ወይዘሮ ፍቅርተ ገብረ ማርያምና አቶ ንጉሤ መንገሻ ለሰጣችሁኝ ልባዊ ፍቅርና ድጋፍ ከልብ አመሰግናለሁ። ባገር ቤትም ሆነ በውጭ ያላችሁ ዘመዶቼ ለሕይወቴ ላበረከታችሁት አዎንታዊ ተጽእኖ በሙሉ፣ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፤ የቄራ ሰፈር ቤተሰቦቼ በልቤ ውስጥ ያላችሁን ትልቅ ስፍራ  ቃላት አይገልጸውም፤

አንቱ ስድሴ በሕይወት ገጠመኞቼ ሁሉ ከጎኔ ሆነሽ አብረሽኝ ስለቆምሽ፣ እንቴ ሰብለ፣ ደጋፊ አበረታቼ ስለሆንሽልኝ፤ አባቡ ሚንዳ በሕይወቴ ውስጥ ስላሳደርከው አዎንታዊ ተጋቦት፣ ዶ/ር ዓለሙ ቢፍቱና ወይዘሮ ውድነሽ ማሩ እምነታችሁ ከልባዊ ፍቅርና አገልግሎት ጋር የተቈራኘ ተምሳሌታዊ አገልግሎት በመሆኑ፣ አቶ በየነ ገብራይ አባታዊ ምክርህና ድጋፍህ ለዓመታት አብሮኝ ስለኖረ፣ ጸጋ ተስፋዬና ኢርምያስ ተስፋዬ በብዙ ስለደገፋችሁኝና ከጐኔ ስለቆማችሁ፣ ወይዘሮ ጸሐይነሽ መለሰቦ በጸሎትና ድጋፍ ከጎኔ ስለነበሩ ከልብ አመሰግናለሁ።

አቶ ብርሃኑ በላይነህ (ሻለቃ) ድጋፍህ ወሰን የሌለው ስለነበረ፤ የዚህ መጽሀፍ እዚ ደረጃ የመድረስ ምክንያቱ ስለሆነ፣ አቶ ተስፋዬ ሮበሌ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትል በአርትኦቱ ሥራ ስለረዳኸኝ፣ አቶ ዮናስ አስፋው በአርትኦት ሥራው ውስጥ ስለነበረው ትልቅ ተሳትፎ አቶ ወርቃፈራሁ ከበደ የእንግሊዘኛ ጽሁፎችን ባማረ አማርኛ በመተርጎም ስለተባበርከኝ፤ ከልብ አመሰግናችኋለሁ፤ ዕድሜና ጤና ያስጣችሁ ብል ያንስ ከሆን አይበዛም፡

የጊዜ ጥበት ሳይበግራችሁ፣ የጽሑፉን ረቂቅ በማንበብ አስተያየት የሰጣችሁኝን ውድ ወገኖቼን ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ::

የሚሺጋን፤አናርበር ኮሚኒቲ፣ በተለያየ መንገድ ያገዛችሁኝ ወገኖቼ፣ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ።

በአንዳንድ ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ ቃለ መጠይቅ አድርጌላቸው ሕይወታቸውንና ገበናቸውን ገላልጠው ላጫወቱኝ ወንድም እኅቶቼ ያለኝ አድናቆትና ከበሬታ እጅግ ታላቅ ነው:: የእናንተ ታሪከና ተሞክሮ ለሌላው ሕይወት ትልቅ ፋና ወጊ ብርሃን ፈንጣቂ እንደሚሆን አልጠራጠርም::

ባላችሁ በቻላችሁት ለሕዝብ ላገራችሁ እያበረከታችሁ ላላችሁ ለውድ ወገኖቼ፣በራሴና በአገሬ ሕዝብ ስም ሆኜ ልባዊ ምስጋናን አቀርባለሁ።

ሐምራዊት ተሰፋ





# ማውጫ


**መቅድም**------------------------------------9

**መግቢያ**------------------------------------11

**የውጭ አገሩ ሕይወታችን**-----------------16

**ምዕራፍ አንድ:– መልካም የልጅነት ሕይወት**------------------------------------22

**ምዕራፍ ሁለት:– የልጆች ለቁም ነገር መብቃት**------------------------------------41

**ምዕራፍ ሶስት:– የልጆች ራስን ችሎ መቆም**------------------------------------56

**ምዕራፍ አራት:–ፍሬያማነት በልጆች ሕይወት**------------------------------------72

**ምዕራፍ አምስት:–ተግጋሮቶችን የሚቋቋሙ ልጆችን ማፍራት**-------------------122

ምዕራፍ ስድስት:-ልጆቻችንን በሥነ ሥርዐት አስታጥቆ ማሳደግ----------155

ምዕራፍ ሰባት:-በቤት ውስጥ ችግር ቢገጥም--------------------------------170

ምዕራፍ ስምንት:-ልጆቻችን የባህሪ ለውጥ ሲያሳዩ------------------------------------181

ምዕራፍ ዘጠኝ:-የወላጅን የግል ሕይወት በተመለከተ--------------------------------199

ምዕራፍ አስር:-ወላጅን እና ልጆችን ለመርዳት የማህበረሰቡ ሚና ---------------204

ጠቃሚ ድረገጾች/መጽሐፍት-----------------227

ዋቢ መጽሐፍት----------------------------231






# መቅድም

ይህን መጽሐፍ መጻፍ ለምን አስፈለገ? በመሠረቱ ይህን መጽሐፍ የመጻፍ ዐላማ አልነበረኝም። በሌላ ርእስ ጉዳይ ዙሪያ፣ ሌላ መጽሐፍ የመጻፍ ዕቅዱና ፍላጎቱ ግን ነበረኝ፤ የተወሰነም ነገር በመጻፍ ላይ እገኝም ነበር። ዓመት ከመንፈቅ በፊት፣ ለወላጆች የሚሆን መልእክት ማዘጋጀት እንዳለብኝ፣ ሐሳብ ወደ ልቤ ይመጣ ጀመር። በየሰንበቱ ወደምሄድባት ቤተ ክርስቲያን በአንድ ገጽ ወረቀት የሰፈረች ለወላጆች የምትሆን መልእክት አዘጋጅቼ በታዳሚው ፊት አነበብሁ። ሁለት ሦስቱ ይህንኑ አደረግሁ።በውስጤ ያለው ሸክም ግን ከመቅለል ይልቅ እየከበደ መጣ።መልእክቱ የተወሰኑ ኢትዮጵያውያን ወላጆች ብቻ ሳይሆኑ ብዙ ሰዎች የሚሰሙበትን መንገድ ማውጠንጠን ጀመርሁ።

አንኳር አንኳር የሆኑትን ነጥቦች በአንድ ገጽ ወረቀት ላይ አስፍሬ፣ ኢትዮጵያውያን ወላጆች በብዛት ወደሚገኙበት ቦታ በኢሜል እንዲሁም በፋክስ መላክ ጀመርሁ። ወረቀቷን የላኩላቸው ሰዎች በአካል የማውቃቸው አልነበረም፤ እነዚህም ሰዎች ወረቀቱን እያባዙ እንዲያሠራጩ ነገርኋቸው። ዞሮ ዞሮ ቀዳማይ ዐላማዬ፣ በወረቀቱ ላይ የሰፈረውን ሐሳብ ሰዎች ገንዘባቸው እንዲያደርጉት መጓጓቴ ነው። ወደ ዐሥር የሚሆኑ ቦታዎች ላክሁ። ከላክሁባቸው ቦታዎች መካከል አንድ ሰው፣ "ይህን ጽሑፍ የበለጠ አፋፍተሽው፣ ወደ መጽሐፍ ለምን አትቀይሪውም" ሲል ሐሳብ አቀረበልኝ። ከዚህ በፊት አስቤው ያልነበረ ሐሳብ ስለሆነ፣ የተቀበልሁት በግማሽ ልብ ነበር። በሌላ ርእስ ጉዳይ ላይ መጽሐፍ ለማዘጋጀት እየሞከርኩ የነበረ መሆኑም፣ ምክሩን ወዲያው እንዳልቀበል ምክንያት ነበር። ለአእምሮዬ ይህን ልበለው እንጂ፣ ልቤ ግን ሊያርፍ አልቻለም።

የቅርብ ባልንጀራዬም ይህንኑ ሐሳብ በመድገም፣ "ይህን ጽሑፍ ወደ መጽሐፍ ብትቀይሪው መልካም ይመስለኛል" ስትል ለሁለተኛ ጊዜ ልቤን አንኳኳችው። እኔም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፣ እነዚህ ወገኖቼ የሰጡኝን ምክር በመቀበል፣ በርእሰ ጉዳዩ ላይ መጽሐፍ ማዘጋጀት እንዳለብኝ ውስጤ ተነሣሣ። በዚህ ጉዳይ ላይ ለወላጆች ተብሎ የተጻፈ ትምህርት ሰጪ መጽሐፍ እኔ በግሌ ያለማግኘቴ

***ስለ ልጆች የሚንጸባረቅ የተሳሳተ የወላጅ አመለካከት***

- "በምእራብያውያን አገሮች መኖራቸው በራሱ ጥሩ ሕይወትን ይሰጣቸዋል"::
- "የሚበሉት የሚጠጡት ይኑር፣ የሚለብሱት የሚተኙበት ይኑራቸው እንጂ ምንም አይሆኑም!"::
- "የምገዛላቸው ዘመናዊ ልብስና መጫወቻ የሚያስፈልጋቸውን ርካታና ሰላም ይሰጣቸዋል"::
- "የሌሎች ሰዎች ልጆች ያገኙትን ነገር ሁሉ የእኔም ልጆች ማግኘት አለባቸው"::

***ወላጅ ከልጁ ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ አዘውትሮ የሚያንጸባርቃቸው የተሳሳቱ ግንዛቤዎች***

- "ልጆቼ ናቸው፤ የእኔ ናቸው፤ እንደምወዳቸው ያውቃሉ፤ ሁሉን የማደርገው ለእነሱ እንደሆነ ይረዳሉ፤ ስለዚህም ልነግራቸውም ሆነ ላሳያቸው አያስፈልግም"::
- "ከልጆቼ ጋር አብሬ መዋሌ በራሱ ትስስሬን ያጠነክረዋል"::
- "ልጆች ቅሬታና ሐዘን አይሰማቸውም"::
- "ፍቅሬን መግለጼና ከልጄ ጋር መጫወቴ ልጄን ያሞላቅቃል:: ልጆቼ ያከብሩኝ ዘንድ ቆጠብ ኮስተር ብዬ መታየት አለብኝ"::
- "ወላጁ እስከሆንኩ ድረስ ሁለመናው ሆኜ፣ ላሳድገው ይገባል"::

***ልጆችን ትልቅ ቦታ ማድረስን በተመለከተ በወላጆች ዘንድ የሚንጸባርቁ የተሳሳቱ ግንዛቤዎች***

- "ጎበዝ ልጅ ማለት በዚህ የትምህርት ሞያ፣ የሚያተኩር፤ ወደዚህኛው የሥራ መስክ ለመጓዝ የመረጠ፣ ልጅ ብቻ ነው"::
- "እንደ ወላጅነቴ፣ ለልጄ የሚጠቅመውንና ሊወስደው የሚገባውን አቅጣጫ ሁሉ ጠንቅቄ ዐውቃለሁ::ሥራዬ ሊሆን የሚገባው፣ ያየሁለትን የእኔን ህልም እርሱ እንዲፈጽም ነው"::
- "ልጅን ከወንድም እህቱ ወይም ከሌላ ጋር እያስተያየሁ፣ 'እንደ እገሌ፣ እገሊት ጎበዝ አይደለህም'፤ 'ከእነርሱ ጋር ስትነጻጸር ይህ ይቀርሀል ብዬ ሳመላክተው በበጎ ቅናት ይነሣሣል"::





***ልጅን ሥነ ሥርዐት ማስያዝን በተመለከተ፣ የምንመራባቸው የተሳሳቱ ግንዛቤዎች***

- "ቁጣና አካላዊ ቅጣት ልጅን በማነበዙ ሂደት ላይ ዋነኛ ድርሻ አለው"::
- "ልጅን ካልጮኹበት አይሰማም"::
- "ወላጅ እንደ መሆኔ መጠን ልጄ ላይ ተጽእኖ የማምጣት ዕድሉ ዘወትር አለኝ"::
- "አትኩሮት መስጠት ያለብኝ እየተበላሸ ላለው ልጄ ብቻ ነው"::
- "ልጅ የጠባይ ለውጥ የሚያመጣው መስመር ሲለቅ ብቻ ነው"::
- "ወላጅ ሲናገረው የራሱን ሀሳብ የሚገልጽ ልጅ ተዳፍሯል።
- "ወላጅ ፊት ዝም የሚል ክፉ የማይናገር ልጅ ሁሉ ጨዋ ነው"::
- "ባጠፋ እንኳ፣ ለልጄም ሆነ በልጄ ፊት አጥፍቻለሁ ማለትና ይቅርታ መጠየቅ፣ ልጆቼ እንዲንቁኝ በር መክፈት ነው"::

*በአጠቃላይ ኑሮዋችንን በተመለከተ፣ በዚህ በምእራብያውያን ባህል ውስጥ የምንኖር ሰዎች ያለን ዋነኛ የተሳሳተ ግንዛቤ*

- *"አንድ ቀን ይህ የሚያሯሩጠኝ ነገር ይሳካና፣ እርፍ ብዬ ከቤተሰቤ ጋር እኖራለሁ" የሚል ነው።* ይህ መጽሐፍ ለእነዚህና ከእነዚህ ጋር ተዛማጅ ለሆኑ የተሣሣቱ ግንዛቤዎች መልስ ለመስጠት ሙከራ ያደርጋል::

> ቀጥሎ ልጅ ላይ ዋነኛ ተጽእኖ ያለው፣ አባትና እናት እርስ በእርስ ያላቸው ግንኙነት እና ከወጀብ ነጻ የሆነ ሰላማዊ ሕይወት መምራታቸው ነው። እነዚህ የቤተሰብ ልምምዶች ለልጅ በቀጥታ ከምናደርግለት ሌሎች ነገሮች የበለጠ፣ ለደህንነቱ ያበረክታሉ።”[3]

ባልና ሚስት እየተፎካከሩ፣ እኔ ዐውቃለሁ ብለው፣ እርስ በእርሳቸው እልህ እየተያያዙ፣ ልጄን ስለምወድ ብለው በተናጥል ብዙ ከሚያደርጉለት ይልቅ፣ አንድ ላይ ቆመው ሰላምን መያዛቸው፣ ለልጅ ሕይወቱ ዕጥፍ ደስታ ያመጣለታል:: በሌላ በኩል፣ በተናጠል ምንስ ነገር ቢደረግለት፣ በአባትና እናት መሀል ጥልና ፉክክር እስካለ ድረስ፣ ያ የምንሰጠው ነገር ሁሉ ሊያስደስተው ሀይል ያጣል:: ልጅ ሁሉን ያስተውላል:: እነዛ የሚወዳቸውና ወደላይ ከፍ አድርጎ የሚመለከታቸው ወላጆቹ ጤነኛ ባልሆነ ነገር ውስጥ እንዳሉ ሲያይ፣ ሰላምና ደስታው እንዲጠፋ፣ ከዕድሜው በላይ እንዲያስብና ውስጡ እንዲቆዝም ያደርገዋል::

## የሚያድሳቸውን ለማወቅ የልጅን ፍላጎት ማጤን

ልጆቻችን የሚፈልጉትን በትክክል ለመረዳት ማየትና ማዳመጥ፣ ልጆቻችን የእውነት የሚያድሳቸውን ነገር መስጠት እንድንችል ያደርገናል:: ብንሰማቸው፣ ብንገመግማቸው ልጆቻችን በአፋቸው ባይነግሩን እንኳ በተለያየ መንገድ ከእኛ የሚፈልጉት ምን እንደ ሆነ ያሳዩናል:: የሚያስደስታቸውን ነገር ስንል፣ ልጆች ጊዜያዊ ደስታ ሲፈልጉ “ይሄንን ብትገዙልኝ፣ ብታደርጉልኝ ደስተኛ እሆናለሁ” ብለው ለደቂቃ የሚናገሩትን ዐይነት ፍላጎት ማለት አይደለም:: የእውነት ውስጣቸውን የሚገነባቸው፣ ቀናቸውን የሚያበራላቸው ምን ስናደርግላቸው እንዴት ስናወራቸው እንደሆነ፣ በተለያየ መንገድ ያሳዩናል:: ጥንቃቄ ካልወሰድን፣ “ልጆቼ በእውነት የሚያስደስታቸው ነገር ምንድን ነው?” ብለን ቀስ ብለን በመገምገም

3 Epstein 2010 Robert Epsteing Scientific American Mind November 2010 issue page





ፈንታ፣ ያስደስታቸዋል ብለን በራሳችን በወሰንነው ነገር ውስጥ ልንራራጥ እንችላለን:: በዚያ መንገድ ከቀጠልን ደግሞ፣ ፍየል ወዲህ ቅምዝምዝ ወዲያ እንደሚባለው ከልጆቻችን ጋር በተለያየ አቅጣጫ ሮጠን በኋላ ልንነቃ እንችላለን::

ብዙ ያደጉ ልጆች “እኔ ልጅ ሆኜ የምፈልገው ነገር ይህ ነበር፤ ነገር ግን ቤተሰቦቼ ያንን ከልብ የሚያስደስተኝን ነገር ሳይሰጡኝ ዐደግሁ” ብለው ያወራሉ:: ምናልባትም እነዚያ ወላጆች፣ ደስተኛ ልጆች ካፈሩት ወላጆች እኩል ልጆቻቸውን ይወዱ ነበር ይሆናል:: ነገር ግን፣ “በዚህ ሂደት ውስጥ ልጅ ቦታ የለውም፤ የልጅ ነገር ልጅ ነው፣ለልጄ የሚሆነውን ነገር ሁሉ እኔ ዐውቃለሁ” ብሎ በራስ መንገድ ብቻ የመሮጥ ያመጣው ጣጣ ነው::

በአሜሪካ ውስጥ የታወቀ ፊልም ሰሪ የነበረ አረን ስፔሊንግ (Aaron Spelling) የሚባል ሰው ነበር:: ይህ ሰውና ቤተሰቡ የሚኖሩበት መኖርያ ቤት ትልቅነቱ በካሊፎርንያ ውስጥ አንደኛ ነው ይባል ነበር:: የዚህ ሀብታምና ታዋቂ ልጅ ዛሬ በእድሜ ትልቅ ሆና ስለ ሕይወት ታሪኳ የሚናገር መጽሐፍ ጽፋለች:: ቶሪ ስፔሊንግ (Tori Spelling) የምትባለው ይህች ሰው፣ “sTori TELLING” በሚለው መጽሐፏ ላይ፣ ስለልጅነት ጊዜ ትዝታዋ እንዲህ ስትል ታወሳለች:: ጓደኞቼ “እንዴት ታድለሻል” እያሉ ይቀኑብኝ ነበር:: እውነትም እናቴና አባቴ በጣም ብዙ ገንዘብ ነበራቸው:: በልጅነት ዘመኔ፣ ሊያስደስቱኝ ፈልገው በገንዘባቸው ተጠቅመው በጣም ብዙ ያደርጉልኝ ነበር:: አባቴም፣ “ልጄ አንቺን ስለምወድሽ ይህን ይህን አደርግልሻለሁ” እያለ ገንዘቡን ብዙ ነገር ላይ ያወጣ ነበር:: በዚያ በልጅነት ዘመኔ ከሚገዛልኝና ከሚያደርግልኝ ብዙ ነገሮች ሁሉ በላይ የሚያስደስተኝና በናፍቆት የምጠብቀው የነበረው ፣ በስንት ጊዜ አንዴ አብሮኝ የሚያሳልፋቸው ጥቂት ጊዜያት ነበሩ:: እነዚያ ጥቂት ጊዜያት ለኔ ምን ያህል ዋጋ እንደነበራቸው ቢያቅ ኖሮ፣ ከመሞቱ በፊት ቢረዳ ኖሮ ብዬ እመኛለሁ ብላ መጽሐፏ ላይ ታወሳለች:: ስለ እናቷም ስታነሳ፣ ከዚያ ያልተለየ ትዝታን ታወሳለች:: ከእሷ በላይ የጠቀመችኝ እና ብዙ ያደረገችልኝ

ውስጥ ሲኖሩ፣ ድጋፍ እናገኛለን፤ ከብቸኝነት ነጻ እንወጣለን፤ ሕይወታችንም ይበራል። ልጆቻችንም ከማኅበራዊ ሕይወት የሚገኘውን ፍቅር ቀምሰው ያድጋሉ። አጎቴ አክስቴ የሚሉትና የሚወዱት ቤተሰብ መካከል ከማደጋቸው በተጨማሪ፣ የዕድሜ ጓደኞቻቸውን ያገኛሉ። ዕድሜያቸው ተቀራራቢ የሆኑ ሌሎች ልጆች ጋር አብረው በማሳለፍ፣ የሚያገኙት የልጅነት ጊዜም የማይረሱት፣ጣዕም ያለው ትዝታ ያተርፍላቸዋል። ያ ማህበራዊ ሕይወት ከሌለ ቤተሰባችን ደስታና ሰላም አይኖረውም ለማለት አይደለም፤ ተጨማሪ ጣእምን ወደ ሕይወታችን ሲያመጣ ግን ትልቅ ሀይል አለው።

## ማጠቃለያ

በአሜሪካን አገር ካናዳ፣ አውሮፓና በተለያዩ ቦታዎች የሚኖሩ፣ ሕይወታቸውን በመጽሐፍ ያስቀመጡ ብዙ ሰዎች አሉ። የእነዚህ ሰዎች የግል ታሪክን ብናነብ፣ ብዙዎቹን የሚያያይዛቸው አንድ እውነት አለ። ጥሩ የልጅነት ጊዜ ነበረኝ ብለው የጻፉ ሰዎች፤ፍቅር፣ የቤተሰብ የጋራ ጊዜ፣ መከባበር፣ ወዘተ ዋነኛ ነገሮች እንደነበሩ ያወሳሉ።

በአንጻሩ ደግሞ ምድራዊ ንዋይ ኖሮአቸው እነዚህ ነገሮች ስላልነበሯቸው ሕይወታቸው ምን ያህል አሳዛኝ እንደነበር የጻፉ ብዙ አሉ። ከዚህ ተመክሮ እንማር። ማስቀደም ያለብንን ጥቂትና ዋና ነገሮች እንቀፍ፤የኛና የልጆቻችን ዘመናት የደስታ፣ የተድላና፣ የፍሥሐ ጊዜ እንዲሆን ጠንክረን እንሥራ።





# የሕይወት ተሞክሮ



## የእህት ጣእም

ዛሬ 23 አመት ሰው ሆኜ መለስ ብዬ ቤተሰቦቼ ያደረጉልኝን ሳየው ከድሮው በበለጠ በጣም አመሰግናቸዋለሁ። አንድ ነገር ምን ታውቂያለሽ ተብዬ ብጠየቅ፣ ወላጆቼ ሁሉን ያደረጉት "ለልጆቻችን ምን ይጠቅማቸዋል" ከሚለው ቦታ ተነስተው ነው። ከተወለድንበት ጊዜ ጀምሮ፣ ዋና አትኩሮታቸው የነበረው የደስታ ሰላም፣ ልምላሜ የተሞላበት ህይወት እንድንኖር በመጣር ላይ ነበር። የእኛ፣ ፍቅርን አግኝቶ ማደግ፣ ለቤተሰቦቼ ዋነኛ ነገር ነበር። ልዘርዝረው ብል ያደረጉልኝን አልቆጥርም፤ ግን አርቀው አስበውና አይተው ካደረጉልኝ ዋና ነገር ብዬ የምለውን ልጥቀስ።

እኔና እህቴ ከሚገመተው በላይ ተቃራኒ የሆንን ሰዎች ነን። እንደዛ ስል የማጋነን ሊመስል ይችላል። ግን እውነቱ ያ ነው። እህቴ፣ ፍጥነትን፣ እንቅስቃሴንና አዲስ ነገርን የምትወድ ሰው ናት። የተሰማትን ወዲያው የምትናገር፣ ካገኘችው ሰው ጋር ወዲያው ተግባብታ የምታወራ፣ ሰው ናት። ከሷ ጋ ተቀምጦ አንድ ሰው የድብርት ስሜት ይሰማዋል ለማለት ይከብደኛል።

በተቃራኒው፣ እኔ በተፈጥሮዬ እርጋታ ጋ የተዛመድኩ ሰው ነኝ። ስወስን ቀስ ብዬ ነው ፣ አዲስ ነገር ውስጥ ቶሎ መግባት አያስደስተኝም። ጊዜዬን ወስጄ ቁጭ ብዬ ነገሮችን መመልከት ማየትና መገምገም፣ ማጥናት ማብሰልሰል ውስጤን ያስደስተኛል።

የእኔና አንድ እህቴ ጸባይ፣ ልዩነቱ የታየው፣ ገና ከእናታችን ማህጸን ጀምሮ ነው። እኔ እናቴ ማህጸን ውስጥ እያለሁ እንኳ፣ ተመችቶኝ በእርጋታ ጸጥ ብዬ ከመተኛቴ የተነሳ፤ ቤተሰቦቼ፣ "ይህ ጽንስ አይንቀሳቀስም፤ ይህች ልጅ ደህና ነች እንዴ" ብለው፣ ከመጨነቅ ደረጃ ደርሰው ነበር። በተቃራኒው ታናሽቱ እህቴ፣ ገና ማህጸን ውስጥ እያለች እየተንፈራገጠች፣ መወለጃ ሰአቷ መድረሱን ለማስታወቅ ትሞክር ነበር። የመወለጃ ሰአቱ እንደዘገየበት ሰው ስትንፈራገጥ፣ ወላጆቼ ይህችኛዋ ፍጹም የተለየች እንደሆነች ገምተው ነበር።

ከገለጻዬ እንደሚታየው እኔና እህቴ በጸባይ በአሰራር አመለካከት በጣም ተቃራኒ የሆንን ሰዎች ነን፤ ህይወትንም የምናይበት መነጽር በጣም የተለያየ ነው። እንደዛም ሆኖ፣ እህቴ ዋነኛ የልቤ ጓደኛዬ ነች ብል ማጋነን አይሆንም። የጋራ የሆነ የሚያገናኘን አንድ ጸባይ ሆነ አመለካከት ባይኖረንም እህቴ ከህትነት ያለፈች ውዴ ነች።የልቤን የምነግራት በስቃይ ሆነ በደስታ ጊዜ ዞሬ የማማክራት ጓደኛዬ ናት። ከእህቴ ጋር ያለኝ ግንኙነት ከልቤ የምደሰትበት በህይወቴ የምረካበት ነው። ለዚህም ደግሞ፣ በዋነኝነት የማመሰግነው፣ ወላጆቼን ነው፤ ምክንያቱም እኔና እህቴ እንዲህ አይነት ግንኙነት ሁሌም አልነበረንም።

በእኔ እና በታናሽ እህቴ ሳራ መሀል የአራት አመት ልዩነት አለ። እውነቱን ልናገር ብል፣ በአስራዎቹ አመታት ውስጥ እያለሁ፣ ስራዋ ሁሉ ያናድደኝ ነበር። "እየረበሸችኝ ነው" ብዬ የምማረርባቸው ብዙ ጊዜዎች ነበሩ። ፍጹም የተለያየን ሰዎች





ነበርንና፣ የጋራ የሆነ መኝታ ቤት ውስጥ መተኛት፣ በጋራ መጫወቻዎች መጫወት በጣም ይከብደን ነበር። ብዙ ጊዜም እንጣላና እንጯጯህ ነበር። በተለያየ ጸባያችን ምክንያት እንደዛ ብንጣላም፣ ወላጆቻችን ሁሌ አብረን ጊዜ እንድናሳልፍ ያደርጉ ነበር። በእህትና እህት መሀል መዋደድ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ደጋግመው ይነግሩን ነበር። የሆነ ቦታ ልሂድ ብዬ ከተነሳሁ፣ ወይም የሆነ ነገር ላድርግ ብዬ ስነሳ ከወላጆቼ የሚመጣው ጥያቄ "እህትሽስ፣ እሷንስ ለምን አትወስጃትም" የሚል ነበር። በዛ ጊዜ የምማረርበት፣ ምንድነው የሚያስጨንቁኝ ብዬ የማስብበት ብዙ ወቅት ነበር። በኋላ ግን አብረን ጊዜ እንድናሳልፍ እኛን በማበረታታቸው፣ ዋነኛ ስጦታ እንደሰጡኝ ተረዳሁ። እኔ የሌለኝ ጠንካራ ጎን፣እህቴ አላት፤ እሷም የሌላት እኔ አለኝ። አብረን ብዙ ጊዜ ስናሳልፍ፣ ከእርስ በእርስ መማማር ጀመርን። ከእርስ በእርስ ከመማማርም አልፈን፣ እርስ በእርስ መከባበር ጀመርን።ቀስ በቀስ ጥላችን ወደ አብሮ መጫወት፣መጯጯሃችን ወደ ሳቅና ፈገግታ ተለወጠ። ያ አብቦ ዛሬ እህት ብቻ ሳይሆን ጓደኛም ሆነናል። በአሁኑ ጊዜ 80 ከመቶው የሚሆነው፣ የምዝናናበት ጊዜ ከእህቴ ጋር አብሮ መሆን ያስደስተኛል። የእኔ ጓደኞች የእሷም ናቸው። ሁሌ አብረን ነንና፣ አንድ ቦታ እንኳ ብቻችንን ከታየን፣ "እህትሽ የታለች" መባላችን አይቀሬ ነው።

አሁን መለስ ብዬ ሳስበው፣ ወላጆቼ ስራዬ ብለው በእኔና በአንድ እህቴ መሀል ያለው ግንኙነት እንዲያብብ እንደጣሩ አረዳለሁ። እናትና አባቴ፣ ከብዙ ቤተሰብና ወዳጅ መሀል ከነበሩበት፣ ከአገራቸው ርቀው እዚህ ፍጹም የተለየ ባህል ውስጥ መጡ። ኢትዮጵያ ያደጉበት አካባቢ ጎረቤት ወዳጅ ዘመዱ ተሰብስቦ ልጅን ያሳድግ ነበር። እዚህ ሲመጡ ግን እናትና አባቴ ሁሉን የተጋፈጡት ብቻቸውን ነበር። በዚህ ብቸኝነትን በሚያበረታታ ባህል ውስጥ ለእርስ በእርስ ያለነው እኔና እህቴ እንደነበር ይረዱት ነበር። እንደወላጅነታቸው ስራዬ ብለው፣ በእኔና እህቴ መሀል ትስስር እንዲኖር ካላደረጉ፣

ውጤታችን የሚሆነው ተራርቆ ማደግ እንደሚሆን እናቴና አባቴ ከመጀመሪያውኑ ተረዱት፤ ትልቁን የቅርርብ ስጦታ፣ በዛ መልክ ለእኛ ለልጆቻቸው አስረከቡን::

ወንድም እህት ሁልጊዜያቸውን አብረው እንዲያሳልፉ መጣሩ እነሱን ለማቀራረብ ብቸኛው መላ ነው ለማለት ብዬ አይደለም:: ወንድምና እህት ስለሆኑ ብቻ ይቀራረባሉ ብለን ደምድመን መተዉ ግን ጥሩ ላይሆን ይችላል:: እህት፣ ወንድም እንዲዋደዱ፣ እንዲቀራረቡና ለእርስ በርስ እንዲተሳሰቡ ወላጅ ስራዬ ብሎ ግንኙነታቸውን ማነጽ፣ ማነጋገሩ ትልቅ ጥቅም አለው ብዬ አስባለሁ፤ በልጅነት የታነጸ ግንኙነት ሲያድጉም ይቆይላቸዋል፤ እኔና እህቴ እንደሆንነው ለእርስ በርስ ድጋፍ እንዲሆኑ፣ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋልና::





# ምዕራፍ ሁለት

## የልጆች ለቁምነገር መብቃት

ልጆች እንዴት ለቁምነገር ሊበቁ ይችላሉ? የሚለው ጥያቄ መሰረታዊ ጥያቄ ነው። ልጆቻችን ለቁም ነገር እንዲደርሱልን ማድረግ ያለብንን በተመለከተ፣ ዋነኛው ነገር እኛ የምንሰጣቸው ድጋፍና እገዛ ነው:: ከእኛ የሚያገኙት ድጋፍ፣ የእነርሱ ወደ ሆነው ትልቅ ቦታ እንዲደርሱ ይረዳቸዋል::

### 1) *ወላጅ በልጁ ማመን አለበት*

"ልጅዎ ስለራሱና ስለችሎታው የሚኖረው አዎንታዊ አመለካከት፣ ከእርስዎ ዕለት ተዕለት በሚያገኘው ድጋፍ ይወሰናል።"[5]

ወላጅ በልጁ መተማመኑ፣ "አስፈላጊ እርዳታና ድጋፍ ያገኝ እንጂ ልጁ ሊደርስ የሚገባው ጥሩ ቦታ ይደርሳል" ብሎ ጉዞውን መጀመሩ፣ ሁሉን ይወስናል፤ እውነት ሆኖ የሚወጣው ከልብ ያመንበት ነገር ነውና::

ልጃችንን የማናምንበት፣ትልቅ ቦታ አይደርስም ብለን በውስጣችን የምናስብ ከሆነ፣ ከሁኔታችን ሊገነዘበው ይችላል:: እኛ አፋችንን አውጥተን ባንናገር እንኳ፣ ከውስጣችን ያለው የተደበቀ እምነት በተለያየ መልክ ተፈናጥቆ ወጥቶ ይታያል:: "አላምንብህም፤ ትልቅ ቦታ አትደርስም" እያለ፣ የልጃችንን አቅጣጫ ይመራል::

[5] Dyer Wayne (1985) what do you really want for your children, Addison Wesley publishing company.

አዎ፤ አንዳንዴ የልጃችንን ጠባይ፣ ፍላጎትና አደራረግ ከወዲሁ ገምግመን፣ "አይ፤ እንጃ ይህ ልጅ ትልቅ ቦታ የሚደርስ አይመስልም" ብለን እናስባለን። አንድ ትልቅ እውነት እናስታውስ። ማንም ልጅ ቢሆን ከተደገፈ ይለመልማል፤ከነበረበት ወደ ላይ ይነሣል። ይህ ሁሉንም ልጅ የሚያገናኝ እውነት ነው፤በራሱ በሆነውና በተወለደበት ችሎታው አሠራሩ ያብባል፤ የራሱ በሆነ መንገድ ያድጋል ይመነደጋል። እያንዳንዱ ስር ሊያብብ፣ልዩ ፍሬን ሊያወጣ እንደ ተፈጠረ፣ የሚጠብቀው የእኛን ድጋፍ እንደ ሆነ ተረድተን፣ በነገው ትልቁ ልጃችን ላይ እንበርታ።

ቃላት ኀይል አላቸው።ቃላቶቻችን ልጆቻችንን ፍቅር ማሳያ ብቻ ሳይሆኑ ወደ ላይ እንዲመጥቁ የሚያግዙ መሰላል ናቸው። አዎ፤ልጆቻችን ወደ ላይ እንዲመጥቁ ስንፈልግ፣ ቃላቶቻችን ለመገንባት ወይ ለመስበር ትልቅ ሀይል እንዳላቸው እንረዳ። ከሕፃንነታቸው ጀምሮ ለልጆቻችን፣ ያሰቡት ቦታ ሁሉ መድረስ እንደሚችሉ እንንገራቸው። "እንዲህ መሆን እፈልጋለሁ" ሲሉ አንሳቅባቸው። ሌላው ቀርቶ እንዲህ መሆን እፈልጋለሁ የሚሉት ነገር የማይቻል ቢመስለን እንኳ፣ በመሳቅ ፋንታ ያ ውስጣቸው የተቀመጠውን፣ ትልቅ ቦታ የሚያየውን ኀይል ማበረታታትና መደገፍ አለብን። ለምሳሌ ልጃችን መጥታ፣ "የዓለም አንደኛ እግር ኳስ ተጫዋች መሆን እፈልጋለሁ" ብትለን በልባችን ዋናው ማሰብ ያለብን "እንዴት የማይሆን ነገር ተናገረች"፣ የሚለውን አይደለም፤ይህ በውስጧ የተቀመጠውን ወደ ትልቅ ቦታ ለመመዘዝ የሚያስበውን ኀይል እንዴት ማበረታታት እንዳለብን ነው። ሲሆን፤ "አዎ ትችያለሽ ልንላት፤ አለበለዚያም ያንን ትልቅ ቦታ የሚያየውን፤ በውስጧ የተቀመጠውን ውድ የሆነ ኀይል መደገፍ ይኖርብናል። "ትልቅ ቦታ ታስቢያለሽ፣ የራስሽ የሆነ ህልም አለሽ፤ ያ በጣም ጥሩ ነው"፣ ብለን ማበረታታት አለብን። ዋናው የሚፈለገው ትልቅ ቦታ አነጣጥሮ የሚያይ ዓይን ልጃችን ያላት መሆኑ ነው እንጂ፣ እግር ኳሱ ነገ በሌላ ህልም ይተካል።



ልጅን እንዴት ላሳድግ? በምዕራብ አገሮች

ልጃችን እንዲህ እሆናለሁ ብላ ስትናገር ግን፣ አዬ ብለን ብንስቅ፣ ወይም ይህ ከንቱ ምኞት ነው ብንል፣ ሳናውቀው አፍራሽ መልእክት እየላክን ነው። እናስታውስ፤ ልጅ ሁሉን ነገር በውስጡ ይመዘግባል። የዛሬ ትንሿ ልጃችን፣ እራሷን ትልቅ ቦታ አይታ እንዲህ እሆናለሁ ስትለንና እኛ የፌዝ ሣቅ ስንስቅ፣ መልእክት እያስተላለፍንላት ነው። "ከሰው ለየት ያለና ትልቅ ቦታ ማሰብ ሞኝነት ነው" እያልናት ነው። ጭራሽኑ ትልቅ ቦታ ራስሽን አትይ እያልናት ነው፤ በድርጊትና በቃል ሳናስተውለው፣ ልጃችንን እየሰናከልን ነው። የልጅን ኅሳብ ከማጣጣል እንቆጠብ፤ ዋናው ነገር፣ በልጅ ውስጥ፣ ትልቅ ቦታ የሚያይ፣ ለትልቅ ነገር የሚያነጣጥር፣ኀይል መኖሩ እንደሆነ ተረድተን እናበረታታቸው፤ ጠንክረው ከሰሩ የማይቻል የለምና።

ልጆቻችን ሲጎብዙና በሆነ ነገር ሲመጥቁ ስናይ በቶሎ እናበረታታቸው። "ጎበዝ ልጄ በጣም በርትተሀል"፣ ብለን ምን ያህል እንደተደሰትንባቸው እናስታውቃቸው። እየሰሙ፣ ሰው ፊት ስለ እነርሱ ጉብዝና፣ ስላደረጉት ጥሩ ነገር እናውራ። "የእኔ ልጅ እኮ በዚህ ይህን ነገር አከናውኗል፤ልጄ እኮ ያንን ግሩም ጽሁፍ ጻፈች እያልን፣ ስለ ሁሉም ልጆቻችን ጥሩ ስለሰሩበትና ስለ ጎበዙበት ነገር ለዘመድ ወዳጅ እናውራ። እንዲህ ሰው ፊት ስለ እነርሱ ጉብዝና ስንወራ፣ ምን ያህል እንደኮራንባቸው፣ ባደረጉት እንደተደሰትን ያሳያቸዋል፤የበለጠ ለመስራትም ይበረታታሉ።

ልጆቻችንን ትልቅ ቦታ እንደሚደርሱ፣ በማሰብ እናውራቸው። ያ ማለት ምን ማለት ነው? ለምሳሌ ከአሁኑ ስለ ትልቅ ነገር እናውራቸው። " ልጄ፣ ወደ ፊት ምን ማጥናት ትፈልጊያለሽ" እንበላቸው፤ይህንንና ያንን ብለው ሲነግሩን፤ በጥሞና እናዳምጥ። "ለምን ይህን መሆን ፈለግሽ? እንዴት ያ ፍላጎት አደረብህ?" ብለን እንጠይቃቸው። የሚያስቡት ነገር እውን መሆን እንደሚችል በሚያስገነዝባቸው መልክ እናነጋግራቸው። ሰው ደጋግሞ ከአፉ የሚያወጣውን ነገር ያምናል። ለእኛ ሲመልሱ እነርሱም እያሰቡበትና የሚናገሩትንም ከልብ እያመኑ ይመጣሉ።

በእውቀቱና በስራው ዝናን እና ብዙ ታዋቂነትን ያተረፈው፣ አሉ ከሚባሉት ዋነኛ የቀዶ ጥገና ሀኪሞች አንዱ የሆነው ጥቁር አሜሪካዊው ቤን ካርሰን፣ (Ben Carson) ስለ አስተዳደጉ በጻፋቸው መጽሐፎቹ ላይ አንድ ነጥብ ደጋግሞ ያነሳል:: ያም እናቱ በሕይወቱ ምን ያህል አስተዋጽኦ እንዳደረገች ነው:: ድሃ እናቱ የተማረችው እስከ ሶስተኛ ክፍል ድረስ ብቻ ነበር። ልጆቿንም የምታሳድገው ያለ አባት ብቻዋን ነበር:: ይህች ሴት ግን አንድ የተለየ ነገር ነበራት:: ለሁለት ልጆቿ ትልቅ ህልም ነበራት:: በየቀኑ ቤታቸውን ልታጸዳ ስትሄድ የምታያቸውን ሀብታም ነጮችን በመመልከት፣ "ልጆቼም እነርሱ የደረሱበት ቦታ መድረስ ይችላሉ" ብላ ከልቧ ታምን ነበር::

ቤት መጥታም ለልጆቿ እንዲህ ብላ ታስታውሳቸው ነበር፤"እነርሱ ከእኛ ምንም አይለዩም:: እናንተም፣ እነርሱ የደረሱበት ትልቅ ቦታ መድረስ ትችላላችሁ ብላ ትገነባቸው ነበር:: ዝቅ የሚያደርጉ ቃላትን ልጆቿ ፊት ፍጹም አትጠቀምም ነበር:: "ባንድ ወቅት መምህሮች ተስፋ የቆረጡብኝ የማይገባኝ ልጅ ነበርኩ፤አምስተኛ ክፍል እያለሁ የክፍሉ የመጨረሻ ዝቅተኛ ውጤት የማገኘው እኔ ነበርኩ። በክፍሉ ውስጥ ቅጽል ስሜም " ያ ደደቡ ልጅ" የሚለው ነበር፤የክፍሉ መሳቂያም ነበርኩ። እናቴ ግን ህልሟ የተለየ ነበር። ታበረታታኝ ነበር። አንተ ደደብ አይደለህም፤ ጥሩ ጭንቅላት አለህ። በርታ ጠንክረህ ስራ እንጂ ያለምከው ቦታ ትደርሳለህ ብላ ታስታውሰኝ ነበር" ይላል:: "ሁዋላ ተበረታችቼ፣ ወደፊት ትልቅ ቦታ እደርሳለሁ ብዬ ስነግራትም፣ ምን ያስቆምሀል ትሆናለህ ብላ ታበረታታኝ ነበር"፣ ብሎ ያስታውሳል:: የህይወቱ እጣ ምን እንደደረሰ ሲያወሳ እንዲህ ይላል፤ "ከክፍሉ የመጨረሻ የተባለው ልጅ በዓለም ታዋቂ ቀዶ ጥገና ሀኪም ይሆናል ብሎ ማ ሊያስብ ይችል ነበር፤እናቴ ግን ያን ታምን ነበር። ይኸው እኔንም፣ ወንድሜንም ትልቅ ቦታ እንድንደርስ፣ ትልቅ ነገር አበረከተች" ብሎ በፍቅር ያነሳታል::[6]

[6] Carson, Ben; Gifted hands



ልጅን እንዴት ላሳድግ? በምዕራብ አገሮች

ልጅ ከማንም በላይ ወላጁን ያምናልና፣ ያለሙበት ትልቅ ቦታ መድረስ እንደሚችሉ በንግግራችንና በድርጊታችን ስናሳያቸው፣ እውነትም ያ እምነት በውስጣቸው እየተደላደለ ይመጣል፤ እምነቱ የሕይወታቸው ክፍል ሊሆን ትልቅ እድል ያገኛል::

ልጆቻችንን ማበረታታት ብቻ አይደለም፤ ምንም የማይችሉ አድርጎ የሚያሳያቸውን አነጋገሮች እናስወግድ:: እንዲሁ በግዴለሽነት የምንናገራቸውን ለምሳሌ፣ "አዬ አንተ የማትረባ ነህ፤ መቼም አንቺ ጥሩ ቦታ አትደርሽም፤ አንተ የማያልፍልህ ሰው ነህ፤ አንቺ ደደብ ነሽ" ...ወዘተ የሚሉ አባባሎች በጣም አደገኛ ናቸው:: ንግግሮቻችን ልጆቻችንን ሊቀርጹ የሚችሉ ነገሮች ናቸው:: የወላጆቹን ቃላት ከልቡ ያምናልና፣ በመጥፎ ቃላት ስንከበው፣ እውነትም ልክ እኛ እንደምንለው መቀረጽ፣ እና ያለውን ጥሩ ነገር ሁሉ ጭራሽ መተው ይጀምራል:: የሰደብነው ስድብ፣ አስተሳሰቡን፣ አካሄዱን፣ ውሳኔውንና ህልሙን መቅረጽ ይጀምራል:: በግዴለሽነት የምንናገራቸው ቃላቶች ልጆቻችንን እንደሚሰብሩ እና በቶሎ ተስፋ እንዲቆርጡ ሊያደርጋቸው እንደሚችል ተረድተን፣ ልጅን የሚያቆረቁዙ ስድቦችን ፍጹም እናቁም::

Carson Ben; Think big

## 2) የልጅን ማንነት አክብሮ መያዝ

ልጃችን እንዲያድግ እንዲያብብ ስንፈልግ፤ በችሎታ በዕውቀትና በአሠራር አንድ ልጅን ከሌላው እያስተያየን፣እንደሱ ብትሆን እንደሷ ብትሆኝ አንበላቸው። ልጅ የሚያብበው፣ ትልቅ ቦታ ለመድረስ የሚዘረጋው፣ በራሱ በሆነው፣ የተፈጥሮው በሆነው አሠራሩ፣ አደራረጉና ጠባዩ እንዲያብብና እንዲለመልም ስናበረታታው ነው እንጂ፣ የራሱ ነገር ዋጋ እንደሌለው ነግረን ሌላውን ልናስገለብጠው ስንሞክር አይደለም።

ልጃችንን፣ በራሱ መስፈርት በመለካት ፋንታ፣ ከወንድም እህት ወይም ከሌላ ከውጭ ልጅ ጋር በማነጻጸር፣ "አንተ በዚህ ነገር እንደ እርሷ ጎበዝ አይደለህም፤ በእዚህ ጉዳይ እንደ እነርሱ አይደለህም" እያልን ዝቅ በሚያደርግ ሁኔታ ስንነግረው ክፉኛ ይጎዳል። ስለ ራሱ፣ዝቅ ያለ አስተሳሰብ ሊኖረው ይጀምራል። "ከቤታችን ጥሩ ነገር የሌለኝ እኔ ብቻ ነኝ" ብሎ እንዲያስብ ይዳርገዋል።በዚህም ምክንያት የራሱ የሆነውንና ሊያብበት የሚችለውን፣ የራሱን የተፈጥሮ ችሎታ እርግፍ አድርጎ ይተዋል። ልጅ ደግሞ የራሱን የሆነውን የተፈጥሮ ነገር ትቶ ሌላን ለመገልበጥ መሞከሩ አድካሚ ብቻ ሳይሆን ጭራሽኑ ወደ ኋላ እንዲቀር የሚያደርገው ነገር ነው። ልጅን ከሌላ ጋር ደጋግመን ስናስተያየው ሲያይ፣ ምሬተኛ ሰው ይሆናል። ሌላ ሰው ለመሆን እየሞከረ ነውና ሁሌ ባለበት ነገር ደስ ሳይሰኝ እንደ ተደናቀፈ እንዲያድግ ይሆናል።

ሁሉ ልጅ ሲወለድ ጀምሮ የራሱ የተለየ አስተሳሰብ እና የራሱ የሆነ፣ ደረጃ አወጣጥ አለው። አንዳንድ ልጅ ሰው በቶሎ ይቀርባል፤ሌላው ደግሞ ዝምተኛ ነው፤አንዳንድ ልጅ በተፈጥሮው የተለያየ ነገር ማድረግ ፣መሯሯጥ ይወዳል ። ሌላው ልጅ ደግሞ፣ ቁጭ ማለት ይወዳል። አንዳንድ ልጅ ትምህርት ቤት ገብቶ በቶሎ መጻፍና ማንበብ ይጀምራል። አንዳንድ ልጅ ጊዜ ሊፈጅ ይችላል።



ልጅን እንዴት ላሳድግ? በምዕራብ አገሮች

በትምህርት ጉዳይ ላይ ጥናት ያደረጉ ብዙ ሰዎች እንደሚጠቅሱት፣ ልጆች ትምህርትን በቶሎ የሚቀስሙበት ዘዴም የተለያየ ነው። አንዳንድ ልጆች በማየት የበለጠ ይማራሉ። ሌሎች በመስማት የበለጠ ይማራሉ። በእንቅስቃሴ እጃቸውን በመጠቀም መማር የሚቀላቸው ልጆችም አሉ። ሁሉን ልጅ በአንድ አይነት የማስተማር ዘዴ እንዲበረቱ ከጠበቅን በራሳቸው በሆነው ጥንካሬ በመምጠቅ ፈንታ መካከለኛ ወይም ከዛም ያነሱ እንዲሆኑ መንገድ እንከፍታለን። በሌላ በኩል፣ ልጃችን በቀላሉ እውቀት የሚቀስምበትን ዘይቤውን ተረድተን በዚያ ላይ መደገፋችን፣ በራሱ መንገድ ወደ ትልቅ ቦታ እንዲያመራ ይረዳዋል። የልጆቻችንን ሁኔታና ነገሮችን በቀላሉ የሚማሩበትን ዘዴ ከገመገምን በኋላ፣ በተፈጥሮዋቸው መንገድ እንዲመጥቁም እናበረታታ። የልጅ፣ በቀላሉ የመማርያ ዘይቤውን በተመለከተ፣ ጠለቅ ያለ ግንዛቤ ማግኘት ከፈለግን "children learning style" ብለን ኢንተርኔት ውስጥ ብንፈልግ ጥሩ መረጃን እናገኛለን።

ተፈጥሮአዊ በሆነ ችግር ምክንያት የሆነ ነገር የሚከብደው ልጅ ካለን፣ "ለምን እንዲህና እንደዚያ አልሆነም" ብለን ከመቸገር፣ ትእግስትን ተላብሰን፣ ያ ልጅ ካለበት ሁኔታ መጀመሩ ትክክለኛው ምርጫ ነው። ያ ልጅ ጥሩ የሆነበትን ነገር ዐውቀን በእዚያ ላይ የበለጠ እንዲያብብ መርዳት እና ማበረታታት፣ የጥንካሬና የተስፋ ስሜት በውስጡ እንዲመሰረት፣ ሌላውንም ነገር እንዲያሻሽል የሚረዳው ውስጣዊ ጥንካሬ በውስጡ እንዲፈጠር ይረዳል።

ልጅ፣ "ወንድምና እህቴ እንዲህ ናቸው ፤እኔ ግን እንዲህ አይደለሁም" ብሎ ራሱን ሲኮንን ካየነው፣ እንዲህ አይነት ጎጂ ምግባርን እንዲያቆም እናበረታታው። ጉድለቱን ብቻ ነጥሎ እያየ ራሱን መኰነኑ፣ ትርፉ የሚሆነው ተስፋ ማስቆረጥ እንደ ሆነ እናስታውሰው። ሁሉ ልጅ፣ የየራሱ ችሎታ እና ጥንካሬ እንዳለው፣ ማንም በቻለው መጠን ጠንክሮ ከሰራ እና የድል ቃል ከተናገረ ሊደርስ የሚገባው ቦታ እንደሚደርስ፣ የራሱን ውብ ነገር ይዞ እንደሚዘልቅ፣ ለልጃችን እናስረዳ።

## 3) ጠንክሮ መስራት ወሳኝ ነው

ሁላችንም እንደምንስማማው ጠንክሮ መሥራት የግብ መድረሻ ዋነኛ መንገድ ነው። ልጆቻችን ጠንክሮ ለግብ መስራትን ካልተማሩ፣ የቱንም ያህል ትልቅ ነገር በውስጣቸው ቢኖር፣ ቀጭጮ ይቀራል። ለአላማቸው ተግቶ መሥራትን፣ ሰአታቸውን በአግባብ መጠቀምን፣ ተስፋ ሳይቆርጡ መሞከርን ካልተለማመዱ፣ ችሎታቸውና ተፈጥሮዋዊ ስጦታቸው ሁሉ እንዳልነበር ይሆናል።

የልጆችን የቀን ከቀን ልምምድ በዋነኝነት የሚቀርጹት፣ ጠንክሮ ለግብ የመስራት ባህል እንዲዋሀዳቸው መንገዱን የሚያመቻቹት፤ ወላጆች ናቸው። ወላጅ የሚወስነው ውሳኔ፣ ልጅ ጠንክሮ እንዲሰራ ወይም ትምህርትን ችላ እንዲል ትልቅ ድርሻን ያበረክታል። ተግቶ በመስራት ህግ ላይ የማያወላውል አቋም ከሌለን፣ ልጅም ይሳነፋል፤ የመካከለኛ ውጤት ተማሪም ሆኖም ይቀራል። ልጆቻችን ችሎታው፣ጉብዝናው እንዳላቸው፣ እንዲሁ ፈተናን እንደምንም ብለው ለማለፍ ብቻ ሳይሆን፣ ጠንክረው እንዲሰሩ እንዲያጠኑ እንደምንጠብቅባቸው እንንገራቸው።

### *ልጆቻችን ለግብ ጠንክሮ የመስራት፣ የማጥናት ባህል እንዲዋሀዳቸው፣ ወላጅ ምን ሊያደርግ ይችላል?*

- ✓ ለቤት ሥራ፣ ለጥናት የተመደበ፤ የተወሰነ ሰአት መኖር አለበት። ለምሳሌ "ከዚህ ሰአት እስከ እዚህ የቤት ስራ የሚሰራበት፣ ጥናት የሚጠናበት ጊዜ ነው" ብለን ካወጣን፣ ያ የተመደበ ሰአት ሁሌ ለጥናትና የቤት ስራ ለመሥራት መሆን አለበት። እንደዚህ የተወሰነ የጥናት ጊዜ ሲኖራቸው፣ ልጆቻችን ሠዓትን በአግባብ መጠቀምን ይማራሉ። ጠንክረው እንዲሰሩ፣ ለወደፊትም በዕቅድ መስራትን እንዲለማመዱ ይረዳቸዋል።





- ✓ ሁልጊዜ አንድ አይነት የሆነ ህግ ይኑረን። ዛሬ አጥኑ ብለን ተቆጥተን ነገ ይጫወቱ ብለን ዝም ካልናቸው ልጆቻችን በዚህ ጉዳይ ላይ የማያወላውል ህግ እንደሌለን ይረዳሉ። እነርሱም ነገሮችን በቀላል መውሰድ ይጀምራሉ። ካላጠናችሁ እንዲ አይነት ቅጣት ይመጣል ብለን አንዴ ከወሰንን በኋላ፣ የማይለዋወጥ አንድ አይነት አቋም ይኑረን።
- ✓ በልጆቻችን የጥናት፣ የቤት ስራ ጊዜ ቴሌቭዥን እናጥፋ፤ ወደ መጫወት የሚስቧቸውን ነገሮች ሁሉ ካጠገባቸው እናስወግድ። ለጥናት የተመቸ ቦታ እናዘጋጅላቸው። እንደዚህ ጸጥ ያለ ቦታ ሲቀመጡ፣ ሳይደናቀፉ ለማንበብና ሥራቸውን ለመሥራት ዕድል ያገኛሉ።
- ✓ ልጆቻችን ጥያቄ ሲጠይቁን ሁሉን በመመለስ ፈንታ፣ እንዲያስቡበት፣ ራሳቸው መልሱን እንዲያገኙ የሚረዳቸውን ምሪት እንስጣቸው።
- ✓ ልጆቻችን የሚያጠኑበት አካባቢ መዝገበ ቃላት፣ የሚያስፈልጋቸው ወረቀት፣ እርሳስ፣ እስክሪብቶ መኖሩን እናረጋግጥ።
- ✓ በልጅ ትምህርት ምጥቀት ላይ የሚያስተምሩ ብዙ ባለሙያዎች ለወላጆች ደጋግመው የሚያስገነዝቡት ነገር፣ ወላጆች ከልጆች አስተማሪዎች ጋር የማያቋርጥ ግንኙነት መፍጠር ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ነው። ልጃችን አዲስ ክፍል ሲጀምር፣ ከአስተማሪ ጋር እንተዋወቅ፤ አንዳንድ ጊዜ ከልጃችን አስተማሪ ጋር እየተገናኘን ስለ ልጃችን የትምህርት ጉዳይም እንወያይ። ልጃችን የደከመበት ነገር ካለ፣ ለአስተማሪ "ልጄን ለመርዳት ምን ማድረግ እችላለሁ" ብለን እንጠይቅ። ትምህርት ቤቱ ልጃችንን ለመርዳት ያለውን ፕሮግራም እናጣራ።

- ✓ የቤተሰብና የመምህር ስብሰባ ላይም በተቻለ መጠን እንገኝ። እንደዚህ በትምህርት ቤቱ ውስጥ መሳተፋችን፤ልጃችንን በምን በምን ልንረዳ እንደሚገባን ጠቃሚ ግንዛቤ እንዲኖረን ይረዳናል። ከዚያም በላይ አስተማሪዎቹ፣ የልጃችን ትምህርት ጉዳይን ስራዬ ብለን እንደምንከታተል ሲረዱ፣ እነርሱም ችላ እንዳይሉ፣ ጠንክረው እንዲሰሩ ያደርጋቸዋል።

- ✓ ልጃችን ከትምህርት ውጭ በሆነ እንቅስቃሴ ላይ እንድትሳተፍ እናበረታታ። ሙዚቃ ሆነ ስፖርት፣ ስእል በመሳሰሉት ነገሮች ችሎታዋን በሚያጎለብቱ ነገሮች ውስጥ መሳተፏ በጣም አስፈላጊ ነው። እንደዚህ ችሎታን በሚያጎለብቱ ከትምህርት ውጭ ያሉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ልጃችን መሳተፏ በተለያየ መንገድ ይጠቅማታል። ለግብ ጠንክሮ፣ ተስፋ ሳይቆርጡ መስራትን እንድትማር ይረዳል። በምትወደው፣ችሎታዋን በሚያጎለብት እንቅስቃሴ ላይ ስትሳተፍ፣ ትምህርቷ ላይም ለመጎበዝ እንድትበረታታ ዕገዛ ያደርግላታል። ከዚያም በላይ ደግሞ፣ በተፈጥሮ ችሎታዋ እንድትመጥቅ፣ ከሌሎች ጋር አብሮ መስራትን፣ ጥምረትን፣ እንድታዳብር ይረዳታል። እዚ ጋር፣ እነዚህ ከትምህርት ውጭ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች፣ ሰአታችንን ሁሉ አጣበው በሩጫ እንዳያስኖሩን ጥንቃቄ እንውሰድ። ሚዛን ባለው፣ ለሌላም የቤተሰብ ትስስሮች ጊዜ በሚተውልን መንገድ በእነዚህ እንቅስቃሴዎች ላይ ልጆቻችን እንዲሳተፉ ካደረግን ግን ለልምላሜያቸው በትልቁ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል።

ባጠቃላይ፣ ልጆቻችን፣ እንዲጎብዙ፣ ባላቸው አቅምና ችሎታ እንዲተጉ እናበረታታ። ከላይ ያነሳነው፣ ታናሽ ከሆነ ጅማሬ ጀምሮ የአለም ታዋቂ ቀዶ ጥገና ሀኪም ለመሆን የበቃው ቤን ካርሰን (Ben Carson) የተባለው ሰው፣ እርሱና ወንድሙ ጠንክረው እንዲሰሩና እንዲበረቱ እናቱ ምን ያህል ትጠብቅባቸው እንደ ነበር ደጋግሞ ይገልጻል። ባንድ ወቅት፣ ልጆቹ በትምህርት ቤት ዝቅተኛ ውጤት





ማምጣታቸውን ተመልክታ ይህች ቆራጥ እናቱ ቴሌቭዥኑን እንደዘጋች፣ ተግተው እንዲያጠኑ፣ በሳምንት ሁለት መጽሐፍ አንብበው እንዲነግሯት እንዳዘዘቻቸው ያወሳል። በውስጣቸው ያስቀመጠችው ተግቶ የማጥናት ባህል ወደ ትልቅ ቦታ እንዳሸጋገረውም ደጋግሞ ያነሳል። እኛም ይህንን ሁሌ ልብ እንበል። ልጆቻችን ምንስ የተፈጥሮ ጉብዝና ቢኖራቸው፣ ተግቶ ማጥናትን ካልተማሩ ሊመጥቁ የሚችሉበት ቦታ እንደማይደርሱ ተረድተን ጠንክሮ ለአላማ ግብ መስራት ላይ የማያወላውል ህግ ይኑረን።

## *4) ማንበብ የዕውቀት ቁልፍ ነው*

መጻሕፍ፣ ልጆቻችን ውስጥ ያለውን ዘር ለማፍካት ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው ተረድተን ልጆቻችን መጻሀፍ የማንበብ ልማድ እንዲኖራቸው እንጣር፤ መጽሐፍ እንግዛላቸው ቤታችን ሁሌ መጻሕፍት ይኑሩ። እንዲ ዐይነት መጽሐፍ ካላነበብክ ወይም ካላነበብሽ ብለን ብዙም አናስጨንቃቸው። ዋናው መጽሐፍ ማንበብ ይልመዱ፣ ይውደዱ እንጂ፣ የበለጠ ጥልቅ ነገሮች ውስጥ እየገቡ ይመጣሉ። መጥፎ ለልጅ የማይስማማ ነገር እስከሌለበት ድረስ፣ እንደየፍላጎታቸው የሚወዱት አይነት መጽሐፍ እንዲያነቡ በመፍቀድ፣ የመጽሐፍ ፍቅራቸውን እናሳድግ።

መጽሐፍ ማንበብ የማይወድ ልጅ ካለን፣ያ ፍቅር ቀስ በቀስ በራሱ እንዲገባው ቦታ መክፈት እንጂ ብዙም ጫና አናድርግባቸው፤በጣም መጫኑ ጭራሽ እንዲጠሉ ሊያደርጋቸው ይችላልና። ወላጅ ሲያነብ ሲያይ፣በንባብ ባህል ውስጥ ቤተሰብ ሲሳተፍ፣ ልጅም የማንበብ ፍቅሩ እንዲጨምር ያበረክታል። ቤተሰብ፣ የአንባቢያን ቡድን ብለን የራሳችንን መመስረት፣ አንድ ጥሩ ዘዴ ነው። አንድ የቤተሰብ አባል መጽሐፍ አንብቦ ከጨረሰ በኋላ፣ ወይም በቡድን አንድ መጽሐፍ ካነበብን በኋላ ቤተሰብ ተሰባስበን፣ ሻይ አዘጋጅተን ስላነበብነው መጽሐፍ መወያየት፣ ስላገኘንበት ቁምነገር ማካፈል የልጅ የማንበብ ፍቅርን ለመጨመር ትልቅ አስተዋጽኦ አለው።

## 5) የአስተሳሰብ አድማሳቸውን ማስፋት

በትምህርት ጠንክረው እንዲሰሩና የንባብ ልምድ እንዲያደርጉ መንገዱን ከማመቻቸት በተጨማሪ ልጆቻችንን እንዲመጥቁ የምናበረክትበት ሌላኛው መንገድ፣ የአስተሳሰብ አድማሳቸውን ማስፋት ነው። ልጆቻችን ትላልቅ ነገር እንደ እውነት ሆኖ በውስጣቸው እንዲሳልባቸው፣ ከትላልቅ ነገር ጋር ከአሁኑ ማስተዋወቅ ጠቃሚ ነው። ሙዚየም ቦታ ይዘናቸው መሄድ፣ መጻሕፍት ቤት መውሰድ፣ የተለያዩ የሳይንስ ግኝቶች ያሉባቸውን ቦታዎች ማሳየት አለብን። ኮሌጅ እንጎብኝ ብለን አብረናቸው እንጎብኝ። እንደ ግዴታ ነገር አድርገን ሳይሆን ቀስ በቀስ እያደረግን እድሜያቸው ከእነርሱ ከፍ ያለ፣ ኮሌጅ የገቡ የሚማሩ ልጆች ጋር እናስተዋውቃቸው። ከእነርሱ ጋር እንዲያወሩና ጊዜ እንዲያሳልፉ እናድርግ።

እነርሱ፣ "ወደፊት እደርሳለሁ" ብለው የሚመኙት ግብ ላይ ከደረሱ ሰዎች ጋር እንዲገናኙ እናድርግ፤ "ይኸውልህ እነኚህ ሰዎች፣ልክ አንተ ልትሆን የምትፈልገውን፣ አንቺ ልትደርሺበት የምትፈልጊው ቦታ ላይ የደረሱ ሰዎች ናቸው" እንበላቸው። ከዛም በተጨማሪ፣ ተስፋ ሳይቆርጡ ፣ ከባድ የሆነ የሕይወት ፈተናን ካሸነፉ በድል ከተወጡ ሰዎች ጋር እናገናኛቸው

በዓለም ትላልቅ ነገር ስለ ሠሩ ሰዎች እንንገራቸው። የወደፊት አላማቸው ምን እንደሆነ፣ እነርሱ ለየት ያለ ችሎታና ክህሎት አለኝ የሚሉት በምን አንጻር እንደ ሆነ እንጠይቃቸው። በአጠቃላይ በትላልቅ ሀሳብ ዘወትር እንክበባቸው፤ የሰው ልጅ የከበበው ነገር እውነቱ ይሆናልና።



ልጅን እንዴት ላሳድግ? በምዕራብ አገሮች

## 6) እኛ የምንተልምላቸውን ብቻ አንይ

ልጆቻችን እና የወደፊት ግባቸውን በተመለከተ፣ የእኛ የራሳችን በሆነ እቅድ፣ በምናስበው ነገር ልንቀርጻቸው እንዳንሞክር በጣም እንጠንቀቅ። "ልጆቼ ለመምጠቅ ይህንና ያንን ማጥናት አለባቸው" ብለን አናስብ። በተለይ እንደዚህ እንደ አሜሪካ ባለ፣ ለተለያየ ሥራ ምርጫና ሰፊ ማደጊያ አማራጭ ባለበት አገር፣ ለተለያዩ ፍላጎቶች እና የትምህርት ዐይነቶች ሰፊ ቦታ አለ። ልጃችን ይበርታ፣ ጠንክሮ ይስራ እንጂ ለማደጊያ ሰፊ ቦታ አለ፤ የራሱ ወደ ሆነው ወደተጠራበት ትልቅ ቦታ ይደርሳል።

"ለእኔ ትልቅ መስሎ የታየኝ ነገር ለእነርሱም መሆን አለበት" በማለት፣ ልጆቻችንን አስገድደን ልናስገባቸው ከሞከርን ግን፣ መጥቀው የማይሄዱ ሰዎች እናደርጋቸዋለን። "ያንን ዐቢይ ትምህርት ካላጠናችሁ፣ ይህንን ካልተማራችሁ፣" ብለን ቀንና ለሊት ስንጨቀጭቃቸው፣ በውስጣቸው ያለው ፍላጎት መነቃቃት እና ትልቅ እሳት ይጠፋል። ለማጥናት ቢነሳሱ እንኳ፣ እኛን ለማስደሰት ብቻ በማስመሰል ማድረግ ይጀምራሉ። እኛም እንደማናምንባቸው ይሰማቸዋል። በኋላ ጊዜ አልፎ፣ በትልቅነት እድሜያቸው፣ ያንን እኛን ለማስደሰት ብለው ያጠኑትን ትምህርት ይዘው ሲኖሩ፣ በእኛ ሁሌ እንደተናደዱና እንደተማረሩብን ይዘልቃሉ። "በዚያ ልባዊ ፍላጎት በነበረኝ ጥናት ብመረቅ ኖሮ ዛሬ የት እደርስ ነበር፤ እንዴት ደስ የሚለኝን ስራ እሰራ ነበር" በማለት፣ ሁሌ በቁጭትና በምሬት ያስቡናል፤ በራሳቸው ሳይሆን የእኛ ህልም በሆነው ነገር ውስጥ ናቸውና። በተለያየ የጥናት መስክ ላይ ምክር፣ አስተያየት መስጠቱ ጥሩ ነው፤ ከዚያ በተረፈ ግን፣ ሰው የሚያብበው በራሱ ህልም ሲዋብ መሆኑን አስታውሰን እንዲህና እንዲያ ዐይነት ዛፍ ካልሆናችሁ በማለት ፈንታ፣ የራሳቸው ማንነት፣ ሥሩ ጠንካራ በሚሆንበት ጉዳይ ላይ እናተኩር።

## *የልጆቻችን ትምህርት ቤት*

ልጆቻችን ትምህርት የሚያገኙበት ተማሪ ቤት የትምህርት አሰጣጣቸውን ይወስናል፤ ስለዚህም ለምጥቀታቸው ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል:: ይህንን እውነት ተረድተን፣ በተቻለን መጠን የትምህርት አሰጣጥ ጥራቱ የተሻለ ትምህርት ቤት እንዲሄዱ እንጣር:: እውነት ነው፤ ብዙዎቻችን፣ ልጆቻችንን የግል ትምህርት ቤት ለመላክ፣ አቅሙ ላይኖረን ይችላል፤ ስለዚህም ያለን ብቸኛ አማራጭ፣ በአካባቢያችን ያለ ትምህርት ቤት ልጆቻችንን ማስገባት ብቻ እንደ ሆነ ሊሰማን ይችላል:: ነገር ግን፣ ከዛ ያለፉ የተለያዩ ምርጫዎች አሉ:: መሰረታዊ የሆኑ እነዚህ ፕሮግራሞች በምንኖርበት አካባቢ ውስጥ እንዳሉ ማጥናትና ማጣራት ይገባል::

## ማጠቃለያ

የልጆች በትምህርት መምጠቅ ላይ፣ ወላጅ ትልቅ ቦታ እንዳለው ተረድተን፣ ከልጅነታቸው እንገንባቸው:: ጠንክሮ መሥራት፣ ትልቅ ነገር ማለምን፣ አደርገዋለሁ ብሎ ማመን፣ተስፋ አለመቁረጥ፤ በልጆቻችን ውስጥ እንዲቀረጽ ጠንክረን እንስራ፤ በራሳቸው በተጠሩበት ነገር አብበው ይወጣሉ::

**(የልጅዎን ትምህርት ቤት ምርጫ በማስመልከት ስላሉት የተለያዩ ፕሮግራሞች ለመገምገም፣ ከስር ይመልከቱ፤[7])**

---

[7] **የትምህርት ቤት ምርጫን አስመልክቶ ያሉ የተለያዩ ፕሮግራሞች**

Open enrollment፤ በዚህ ፕሮግራም ስር፣ ከመኖርያዎ አቅራቢያ ባለ ትምህርት ቤት አይወሰኑም። በእርስዎ ወረዳም ያሉ ሌሎች ትምህርት ቤቶች ሆኑ በሌሎች ወረዳዎች፤ ለልጅዎ ትምህርት ቤቶችን መምረጥ ይችላሉ።[7] (ስለዚ ፕሮግራም የበለጠ ለማወቅ ቢፈልጉ፣ኢንተርኔት ጉግል ውስጥ ገብተው open enrollment school ብለው በመፈለግ የበለጠ ገለጻ ያገኛሉ)

Charter school፤ እነዚህ በህዝብ የተመሰረቱ (የሚደገፉ) አንደኛ ደረጃ ፤ ሁለተኛ ደረጃና አጠቃላይ ትምህርት ቤቶች ናቸው። የህዝብ ትምህርት ቤት ቢሆኑም፣ ሌሎች የህዝብ ትምህርት ቤቶች በሚተዳደሩበት ህግ ሁሉ አይተዳደሩም። ብዙ ጊዜ ቻርተር ስኩልስ ልጆችን የሚቀበሉት





በዕጣ መልክ ነው። ቻርተር ስኩልሰ ክፍያ እንዲያስከፍሉ አየፈቀድላቸውም። አንዳንድ የቻርተር ትምህርት ቤቶች በተወሰኑ የትምህርተ መስኮች ብቻ ስርአተ ትምህርተ አላቸው። ለምሳሌ ስነ ጥበብ፣ ሂሳብ። ሌሎች ደግሞ፣ የተሻለና ከሌሎች የህዝብ ትምህርት ቤቶች በጠራ ሁኔታ ሁሉንም ትምህርት ይሰጣሉ።[7] በአካባቢዎ ያለ ቻርተር ስኩል ለማግኘት ቢፈልጉ (www.ederform.com) ብለው ይዩ Charterschoolcenter.org ብለው ቢገቡ ስለቻርተር ስኩል የበለጠ ገለጻ ማግኘት ይችላሉ።

Magnet schools፤ የህዝብ ትምህርት ቤት አካል ናቸው። ማግኔት ስኩል የተለየ ችሎታ ወይም ምርጫ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የተዘጋጀ ፕሮግራም አለው። ብዙ ጊዜ ትምህርት አሰጣጣቸው ጥራት ባለው መልኩ ነው። ትምህርት ቤቱ አመልካቾችን የሚመርጥበት የራሱ መስፈርት አለው።[7] (ስለዚህ ፕሮግራም የበለጠ ለማወቅ ኢንተርኔት ገብተው magnet.edu ብለው ይመልከቱ የበለጠ እርዳታ ለማግኘት 202-824-0672 ይደውሉ)

Voucher፤ ወላጆች የህዝብን ድጎማ (ፓብሊክ ፈንድ) ተጠቅመው የመረጡት ትምህርት ቤት ልጆቻቸውን ለማስገባት የሚረዳቸው ሰርተፊኬት ነው። አሪዞና፣ ፍሎሪዳ፣ ኦሀዮ፣ ኦታዋ ዊስከንሰንና ዋሽንግተን ዲሲ የቫውቸር ፕሮግራም አላቸው።[7] ስለ ቫዎቸር ፕሮግራም የበለጠ ለማወቅ ከፈለጉ
Schoolchoices.org/voucher
www.allianceforschoolchoice.org

Alternative schools በትምህርት በጣም ዝቅ ያለ ውጤት እያመጡ ያሉና በመውደቅ አደጋ ውስጥ ላሉ ተማሪዎች የተሻለ አካባቢ ለመፍጠር የተቋቋሙ ትምህርት ቤቶች ናቸው (በኢንተርኔት የበለጠ ገለጻን ማግኘት ይችላሉ)

No Child left behind (NCLB) የሚለው ህግ ይህን ይመስላል፤ የልጅዎ ትምህርት ቤት ከፌደራል የተለየ ድጎማ የሚቀበል (title 1) ትምህርት ቤት ከሆነ እና ለ2 ተከታታይ አመታት የሚጠበቅበትን ግብ ካልመታ፣ በዚያው ወረዳ (district) ላይ ልጅዎን ወደ ሌላ ት/ቤት የማዛወር መብት አለዎት። የፌዴራል ድጎማ የዚህ አይነቱን ዝውውር ወጭ ይሸፍናል። ልጅዎ ከነበረበት ት/ቤት ለተሻለ ለውጥ እስከተዘዋወረ ድረስ የወረዳው ትምህርት ቤት ለልጅዎ መጓጓዣ ወደ አዲሱ ትምህርት ቤት ያቀርባል።

ከላይ እንዳየነው፣ የትምህርት ቤት ምርጫን በተመለከተ፣ የተለያዩ አማራጮች አሉ። ወደ ልጅዎ ትምህርት ቤት ሄደው፣ ስለእነዚህ ፕሮግራሞች መጠየቅ ይችላሉ። በምንኖርበት ወረዳ (ዲስትሪክት) ውስጥ ትምህርት ቤትን በተመለከተ፣ የቱ አማራጭ እንዳለ ለማወቅ መሞከር በጣም አስፈላጊ ምርጫ ነው። በርስዎ ወረዳ (district) ምን አይነት ፕሮግራም እንዳለ ለማወቅ፣ ወደ ወረዳዎ ቢሮ ደውለው ማወቅ ወይም ዌብ ሳይታቸው ውስጥ ገብተው መመልከት ይችላሉ። ሌላው፣ የምንችል ከሆነ ያለን አማራጭ፣ የተሻለ የትምህርት አሰጣጥ ያለበት ወረዳ መግባት (ሰፈራችንን መለወጥ ነው)። በአካባቢያችን ያሉ የግል ትምህርት ቤቶች፣ ለልጆቻችን ስኮላርሺፕ ሊሰጡ የሚችሉበት አማራጭ ካለም ሄዶ መጠየቅ ሌላ ጥሩ አማራጭ ነው። በአካባቢዎ ያሉትን ወላጆች መጠየቅና ከእነሱ እይታ እና ምርጫ አንጻር ሁኔታውን ለመረዳት መሞከርም ይጠቅማል።

# ምዕራፍ ሦስት

## የልጆች ራስን ችሎ መቆም

ልጆቻችንን ከልብ የምንወድ ከሆነ፣ ይህንን እናስታውስ። ልጅን መጥቀም ማለት፣ በራሳቸው ጠንክረው መቆም ወደሚችሉበት ዐቅም፣ ቀስ በቀስ መምራት እንጂ፣ በእኛ ላይ ተጣብቀው ወደሚቀሩበት ቦታ መምራት አይደለም።ልጆቻችንን ምናሳድግበት ጊዜ፣ ከእኛ ውጭ ለሚኖሩበት ዘመን ጠንክረው መቆም እንዲችሉ እያዘጋጀናቸው ያለበት ወቅት እንጂ፣ እኛ ላይ በሁሉ ተመርኳዥ እንዲሆኑ የምናደርግበት አይሁን። እንዲጠነክሩ ስንል በሥራም፣ በአስተሳሰብም እንደሆነ ልብ ልንል ይገባናል።

### 1. *ሥራን በመውደድ እራስን መቻል*

> "የቤተሰብ ጥናት ምርምር እንደሚያመለክተው፣ ከ3 ወይም ከ4 አመት እድሜያቸው ጀምሮ፣ ልጆች ቤት ውስጥ እንዲያግዙ፣ ስራ እንዲሰሩ ማበረታታችን፣ ለወደፊት ችሎታ ጥንካሬያቸውና ማንነታቸውን በጥሩ ሁኔታ ለመቅረጽ፣ትልቅ ተጽዕኖ አለው።"[8]

ከፍቅር የተነሣ ቢሆንም፣ የልጆቻችንን እራስን ችሎ የመቆም ሂደት የምንገታ፣ በጣም ብዙ ወላጆች አለን። ሰበቡ ፍቅር ቢሆንም፣ልጆቻችን ያለ እኛ ጣልቃ ገብነት አንዳችም ነገር ማድረግ የማይችሉ የልጅ ጡረተኞች እንዲሆኑ አድርገን እያሳደግን ያለን ብዙ ሰዎች አለን። ይህን የምናደርገው ልጆቻችንን የተንከባከብን ስለሚመስለን ነው።

---

[8] (www. parent hood.com) wolf, Liz





ከልጅነት እስከ ዕውቀት ሁሉን ነገር እኛ እናደርግላቸዋለን። እነርሱ በራሳቸው አንድ ነገር እንዲያድርጉ አንገፋቸውም፤ በቤት ውስጥ የሚሠራ ሥራ አንሰጣቸውም። "ይህን ነገር መሥራት አቃተኝ" ባሉ ቁጥር ሁሉ፣ "እሺ ልጄ" ብለን እኛ የእነርሱን ሥራ እንሰራላቸዋለን። አንዳንድ ወላጆች፣ ብንችል እርምጃቸውን እንኳ እኛ ብንራመድላቸው ደስ ይለናል። ከላይ እንዳነሳነው፣ እንደዚህ የምናደርገው ለልጆቻችን ካለን ውዴታ የተነሳ ነው። ነገር ግን፣ ለእኛ ከፍቅር የሆነው ነገር፣ ለእነርሱ ማሰናከያ ኬላ ይሆንባቸዋል። ሕይወትን፣ ሁሌ በእኛ እቅፍ ሥር ሊኖሩ አይችሉም። ብርድ ካለበት ከውጩ መውጣታቸው አይቀሬ ነው። በዚያን ጊዜ፣ እኛ በሌለንበት ስፍራ ብቻቸውን ሆነው የውጩን አየር ሲቀምሱ፣ በእኛ ክንፍ ሥር ተጠልለው ያደጉት ልጆች መቆም ያቅታቸዋል፤ ይሰባበራሉ።

ከልጅነታቸው ጀምሮ፣ በራሳቸው እንዲቆሙ፣ ጠንክረው መስራት እንዲማሩ፣በገንዘብ ላይ የኀላፊነት ስሜት እንዲሰማቸው፣ መንገዱ ቀስ በቀስ እየተጠረበላቸው ያደጉ ልጆች፣ ውጭ ሲወጡ ግር አይላቸውም (መያዣው መጨበጫው አይጠፋቸውም)። ቀስ በቀስ ውስጣቸው እንዲቀመጥ በተደረገው በራስ የመተማመን ችሎታ ተመርተው፣ ወላጅ በሌለበት ሁኔታ ውስጥ ሁሉ ጠንክረው መቆም ይችላሉ። የራሳቸውን ሕይወት ለመምራትና ለመቆጣጠር ማድረግ ያለባቸውን ያውቃሉ።

ፍቅር በሚል ሰበብ በእኛ ክንፍ ሥር ተከልለው ያደጉ ልጆች ግን፣ ኋላ የሕይወትን ብርድ በግላጭ ሲጋፈጡ፣ ክንፏ እንደተመታ ወፍ መሆናቸው የግድ ይሆናል። ከፍቅር የተነሳ ነው ብለን ያደረግነው ነገር ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝንና፣ ልጆቻችንን ያጠፋል። ምእራብያውያን ከጥሩ ባህላቸው መካከል አንዱ፣ ልጆቻቸውን በራስ ቆሞ የማደግ ልምምድን ማስተማራቸው ነው። "ቆሻሻ አፌ ላይ አለ" ባሉ ቁጥር፣ ሄደው አይጠርጉላቸውም። "ከፍሪጅ ውስጥ ይህን አፈልጋለሁ" ባሉ ቁጥር፣ "እሺ ልጄ" ብለው ሄደው

አያመጡላቸውም:: እድሜያቸውን አቅማቸውን በተከተለ መልኩ፣ ከመጀመሪያው ጀምሮ ቀስ በቀስ፣ ራስን ችሎ የመቆም ባህልን ያስተምሯቸዋል:: በእነርሱ ዕድሜና ዐቅም የሚሰራ የቤት ሥራ ይሰጧቸዋል:: በራሳቸው ሊያደርጉ የሚችሉትን ነገር እንዲያደርጉ ዕድሉን ይሰጧቸዋል:: "እናትና አባቴ፣ እጄና እግሬ ሆነው፣ እኔ የምፈልገውን ሁሉ ያደርጉልኛል" ብለው እንዳያስቡ፣ ይልቁንም እራስን መቻል፣ በራስ መተማመንን በተግባር ያስተምሯቸዋል::

በሕይወት ዘመኑ፣ ሚኒስተር፣ ጸሐፊ፣ ለሌሎች መብት ተከራካሪና አስተማሪ ሆኖ፣ ብዙ ሰዎች የማይደርሱበት ግብ ደርሶና ስኬታማ ሆኖ ያለፈ ሬቨረንድ ሃሮልድ ዊይክ (Reverend Harold wilke) የተባለ ሰው ነበር:: ይህ ሰው የተወለደው ካለእጅ ነው:: እናቱ ልጇ የሚያጋጥመውን የህይወት ሳንካ ተረድታ፣ እንዴት ከልጅነቱ እንዳኅበዘችው ሲናገር እንዲህ ብሎ ነበር፤ "ልጄ አካለ ስንኩል ነው በሁሉ ልርዳው በማለት ፋንታ በራሴ መቆም መጠንከር እንዳለብኝ ተረድታ፣ በዛ መንገድ እንድራመድ ታበረታታኝ ነበር" ብሎ ይገልጻል:: የእናቱን አርቆ ማየት ሲገልጽ አንድ ምሳሌ ይሰጣል:: "የሁለት የሶስት አመት ልጅ ሆኜ አንድ ቀን፣ ካናቴራዬን ለማድረግ እየሞከርኩ (በአካለ ስንኩልነቴ ምክንያት) ከብዶኝ በጣም እፍጨረጨር ነበር:: እናቴ (እንደ ወላጅነቷ) እጇን ዘርግታ እንድትረዳኝ ውስጥዋ ቢያስጨንቃትና ቢገፋትም፣ ስሜቷን ተቆጣጥራ ካለችበት ቆማ ዝም ብላ ታየኝ ነበር:: የእናቴ ጓደኛ ይህን ሁኔታ አይታ፣ በንዴት አግርሞት፣ "አይዳ ለምን ልጅሽን አትረጅውም" አለቻት፤እናቴም እየረዳሁት ነው ብላ መለሰችላት" ብሎ ያነሳል::[9] እናት ገብቷት ነበር፤ልጇን መርዳት ማለት ልጇን ማጠንከር፣ ራሱን እንዲችል መንገዱን መጥረግ ማለት እንደ ሆነ ከወዲሁ ተገንዝባ ነበር:: ራሱን ችሎ፣ በራሱ ጠንክሮ

[9] Rigby Jill (2008) Raising unselfish children in a self absorbed world, Howard books.





መቆም የተማረው ልጇ፣ አንድም እጅ ሳይኖረው፣ ግን ሁለት እጅ ያላቸው ብዙ ሰዎች የማይደርሱበት ግብ ደርሶ፣ በሌሎችና በራሱ ሕይወት ትልቅ ለውጥ አምጥቶ አለፈ::

የአሜሪካ ፕሬዚደንት ባራክ ኦባማ ባለቤት የሆኑት ሚሼል ኦባማ፣ የልጆችን ራስን ችሎ ማደግ በማስመልከት፣ ይህ ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር፤ ልጆችዎ ዋይት ሀውስ ውስጥ እያሉ የፈለጉት ሁሉ እየተደረገላቸው በምቾት ነጻነት እየኖሩ ነወይ? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት መልስ ይህን ይመስላል፤ "እንዲህ አይነት፣ "ሌላው እኔን ያገልግለኝ" የሚል፣ የንግስትነት አስተሳሰብና ስሜት እንዲወርሳቸው ፍጹም አልፈቅድም፤ እኔ የማስበው አሁን እዚህ ዋይት ሀውስ ስላላቸው የምቾት ሕይወትና ጊዜ አይደለም፤ ስለወደፊት ኑሮዋቸው እንጂ፤ እንደማንም ልጅ፣ ወደፊት ለሚጠብቃቸው የሕይወት ጫና፣ እነሱንም ማዘጋጀት አለብን፤ ያ ማለት የራሳቸውን አልጋ ማንጠፍ፣ ቤት ውስጥ ማገዝ፣ ስነስርአት መያዝ፣ ለሌላ ሰው አክብሮት መኖር፣ ይጠበቅባቸዋል፤ ይህ ጊዜያዊ ቤታቸው ነው በውስጣቸው የተመሰረተው የሀላፊነት ስሜት፣ ቀና አስተሳሰብ እና አረማመድ ግን፣ ሁሌም አብሯቸው የሚቆይ ነው::" የሚለውን ምላሽ ሰጥተዋል::[10]

ወላጅ እንዲህ ራቅ አድርጎ አይቶ፣ ራሳቸውን እንዲችሉ ተደርገው ያደጉ ልጆች፣ እጅግ በሚያስደንቅ መጠን ልቀው ይገኛሉ፤ ሁሉን አድርገን ያሳደግናቸው የእኛ ልጆች ግን፣ ሁዋላ ውጭ ሲወጡ፣ ግራ ገብቷቸው ራቁታቸውን እንዳሉ ያህል ተሰምቷቸው፣ ሊቆሙ ግድ ይሆናል::

እኛ ሁሉን እያደረግን ስናሳድጋቸው፣ ልጆቻችን እኔነት ውስጣቸውን ሊወርሳቸው ትልቅ እድል አለው:: የቱንም ያህል በፍቅር ያደጉ ልጆች ቢሆኑ፣ በተግባር ሌላን ማገልገል

[10] December 2011- Jan 2012; Readers Digest; Michelle Obama Interview

አልተማሩምና፣ እኔ ሁሌ መገልገል አለብኝ የሚል እምነት የሚመራቸው ሰዎች ይሆናሉ። ወደፊት ሲያድጉ፣ እኔ እኔ የሚሉ፣ሁሌ መገልገል የሚፈልጉ፣ ከሌላ ሰው ጋር አብሮ ተስማምቶ የመኖር ችግር የሚኖራቸው ሰዎች እንዲሆኑ አስተዋጽኦ ያደርጋል። እቤት ውስጥ ቤተሰብን መርዳት፣ ወንድምንና እህትን ማገልገል ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ካስተማርናቸው ግን ራሳቸውን የቻሉ፣ከሌላም ጋር ተስማምተው መኖር የሚችሉ ሰዎች ይሆናሉ።

ሁሌ ልንንከባከባቸው እንደማንችል ተረድተን፣ ፍቅር ማለት ልጆቻችንን ማጠንከር፣ ለብርዱ ማዘጋጀት መሆኑን ተገንዝበን፣ ጠንካሮች የሚያደርጋቸውንና፣ በሁለት እግራቸው ለመቆም የሚያስችላቸውን ምርጫ እንምረጥ። ከልጅነታቸው ጀምሮ ቤት ውስጥ ኀላፊነት እንስጣቸው። ከመኝታ ቤት ጽዳት ጀምሮ በራሳቸው መሥራት እንዲለምዱ እናበረታታ። ቤት ውስጥም እንዲያግዙ እናድርግ።

ይህን ባህል ቤት ውስጥ ስንጀምር፣ መጀመርያ ላይ ከልጆች ዘንድ እንቢታ ሊመጣ ይችላል። ይሁንና፣ ይህ ጉዳይ ለልጆቻችን አስፈላጊ መሆኑን ተረድተን፣ በቃላችን እንቁም። "ይህ ቤት የእናታችሁና የአባታችሁ ቤት ብቻ አይደለም። የእናንተም ቤት ነው፤ ስለዚህ ሁላችንም የድርሻችንን ማበርከት አለብን" ብለን፣ የማይረሱትን ትምህርት እየደጋገምን እናስተምር። ልጆቻችንም፣ ባልነው እንደማናወላውል ሲረዱ፣ መሥራትን ልምዳቸው ያደርጋሉ።

በተለይ በሕጻንነት ዕድሜያቸው፣ ልጆቻችንን ለማነሣሣት ስንፈልግ፣ በትእዛዝ ወይም በጩኸት ይህን አድርጉ በማለት ፈንታ፣ እነርሱን በሚስብ መልክ ብናደርገው የበለጠ ጥሩ ውጤት እናገኛለን። ለምሳሌ የተለያዩ የስራ ክፍፍሎች ጽፈን፣ "ዕጣ እናወጣለን፤ ዕጣውን ሁላችሁም ታወጣላችሁ፤ ሁሉም ሰው የደረሰውን የሥራ ክፍል ያከናውናል ብለን ልጆች በዚህ ሂደት





ውስጥ እንዲሳተፉ ብናደርግ፣ ልጆችም ተነቃቅተው ይህ ልምድ ውስጥ እንዲገቡ ያበረታታቸዋል።

ከተለመደው የቤት ሥራ በላይም፣ ሠርተው ገንዘብ ሊያገኙበት የሚችሉት ዕድልም እንክፈትላቸው። አዎ፤ ልጆች እፈልጋለሁ ያሉትን ነገር ሁሉ በመግዛት ፈንታ ለሚፈልጉት ዕቃ መሥራት እንደሚችሉ ነግረን፣ ከተለመደው የኀላፊነት ሥራ ሌላ፣ ለገንዘባቸው መሥራት የሚፈልጉትን እንጠይቅ። ሠርተው ማግኘት እንደሚችሉም ሲረዱ፣ የስራን ጥቅም እያወቁ ይመጣሉ። እንደዚህ እያልን፣ ቀስ በቀስ የበለጠ ኀላፊነትን እየሰጠን ራሳቸውን የበለጠ ወደሚችሉበት አቅጣጫ እንምራቸው።

## *በአስተሳሰብ ራስን መቻል*

ልጆቻችን ራሳቸውን ችለው፣ ጠንክረው እንዲቆሙ የምናደርገው በድርጊታቸው ብቻ አይደለም። ልጆቻችን በአስተሳሰባቸውም ራሳቸውን የቻሉ፣አስተሳሰባቸው የበሰለና የጎለበተ እንዲሆን አድርገን ልናሳድጋቸው ያስፈልጋል። ለኋላቸውም የሚቆይላቸው አስታዋሽ መሪ የሚሆናቸው፣ የማመዛዘን ችሎታና የግንዛቤ ስሜት እንዲጠልቅባቸው ጠንክረን እንሥራ እንጂ፣ ራሳቸውን ችለው ማሰብ ያልተማሩ፣ እኛን ለማስደሰት ብቻ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ያወቁ "እንደ ሮቦት" የሆኑ ልጆች አናሳድግ። ልጆቻችን አርቀው እንዲያስቡ፣ ክፉና ደጉን ማመዛዘን እንዲችሉ፣ጠንክረን እንሥራ እንጂ፣ ወላጅን ለጊዜው ለማስደሰት ብቻ መሯሯጥ የለመዱ የልጅ ምርኮኛ አድርገን አናሳድግ፤ በግንዛቤ ደረጃ እኛ ላይ ተመርኳዥ የሆኑ ልጆች እንኳን ለሌላ ለራሳቸውም አይሆኑምና።

*ልጆቻችን በአስተሳሰብ ግንዛቤያቸው ራሳቸውን እንዳይችሉ፣ አርቀው ማየት እንዳይማሩ እክል የምንፈጥርባቸው እንዴት ነው?*

"ይህን አድርግ፤ ይህን መንገድ ተከተይ" እያልን እናዛቸዋለን። "እኔ ለእናንተ የሚበጃችሁን አውቃለሁ፤ ስለዚህ ይህን ምርጫ ምረጡ"

እንላቸዋለን። ግን ከዛ አልፈን፣ ያ ነገር ለሕይወታቸው ያለውን ጥቅም ወይም ጉዳት፣ ጊዜ ወስደን አናስረዳቸውም:: የአንድን ነገር ጥቅም ወይ ጉዳት እንዲያስቡበት ቦታና ዕድልን አንሰጣቸውም ::

ልጆች እኛ ፊት ሲሆኑ ብቻ ሁሉን ነገር ለይምሰል በማድረግ፣ ማስመሰልን ብቻ እንዲማሩ ማድረግ፣ የማንኛውም ወላጅ ግብ አይደለም፤እኛ በሌለንበትም የእውነት ለወደፊት ሕይወታቸው እንዲያስቡ፣ የሚጠቅማቸውንና የሚጎዳቸውን ነገሮች በእውነት እንዲረዱ፣ ምን ይበጀኛል ብለው እንዲያመዛዝኑ እንጂ::

"እኔ አጥኚ ስላልሁ አጥኚ፣ እኔ ስራ ስላልኩ ይህን ሥራ" እያልን ልንመራቸው ስንሞክር፣ ልጆቻችንን ያስተማርናቸው ሊመስለን ይችላል፤እውነታው ግን፣ የሚያደርጉትን ነገር የሚያደርጉት፣ እኛን ለማስደሰት ወይ እኛን ስለፈሩ ብቻ ነው፤ ያስተማርናቸው እኛን ማስደሰት ብቻ ነውና:: እኔ ስላልኩ ብቻ አድርጉ የሚለውን መርሆ ስንከተል፣ ልጆች ይህን ያን ማድረግ ያለባቸው፣ ለራሳቸው መሆኑን ሳይረዱት ይቀራል:: የሚያጠኑት ለቤተሰቦቻቸው ብለው ይመስላቸዋል:: ኮሌጅ የሚሄዱት፣ ሥራ የሚይዙት ወላጆቻቸውን ለማስደሰት ብቻ ይመስላቸዋል:: የሚያደርጉትን ሁሉ እኛን ለማስደሰት ወይም እኛን ዝም ለማስባል ብቻ ያደርጉታል::

ያቺ ልጅ በልጅነቷ፣ እኛን ስለፈራች አድርጊ የተባለችውን የምታደርግ ከሆነና፣ በኋላ ግን እኛ ሳንኖር አብሯት የሚቆየው ግንዛቤ በውስጧ ከሌለ ምን ፋይዳ ይኖረዋል? የተማረችው ብቸኛ ነገር እኛ ፊት መታዘዝ እንጂ፣ ጉዳዩን እውነት ይሁን ውሸት ካልተረዳች፣ ያ ምን ይጠቅማታል? ልጃችን እኛን ስለ ፈራ ብቻ ማጥናት ቢለማመድ፣ ኋላ ብቻውን ኮሌጅ ሲገባ የሚያቋቁመው የሚያጠነክረው፣ የሚገፋው የኀላፊነት ስሜት አብሮት ካልገባ ኪሳራ አይደለምን?

ልጆቻችንን ኋላ አጠንክሮ የሚያቆማቸው የእኛ ትእዛዝ አይደለም፤ በውስጣቸው እንዲተከል የተፈቀደለት የእውቀት፣ የሀላፊነት፣ የግንዛቤ ስሜት እንጂ፤ ያ ነው መሪ ሆኖ ከጥፋት የሚከልላቸው::





አድገው ከጓደኞቻቸው ይህንና ያንን ሲሰሙ፣ "እንዲህና እንዲያ አድርጉ" ሲባሉ አጠንክሮ የሚያቆማቸው፣ በጥሩ መንገድ የሚመራቸው፣ የእኛ ማስፈራራት አይደለም፤ በውስጣቸው ያለው የግንዛቤ ስሜት ምጥቀት እንጂ::

በሕይወት ተሞክሯችን አስፈላጊው ዕውቀት ገብቶናል:: ልጆቻችንም ይህንን ዕውቀት እንዲረዱ እንፈልጋለን:: ያ ጥሩ ሆኖ ሳለ፣ ዋናው ቁም ነገሩ ግን፣ ይህንን ዕውቀት ወደ እነርሱ የምናሻግረው፣ ግንዛቤ ሆኖ እንዲጠልቃቸው የምናደርገው እንዴት ነው፣ የሚለው መሰረታዊው ነጥብ ነው::

ግንዛቤን በሰው አእምሮ ውስጥ በግድ ልንወሽቃት አንችልም:: በሰው አእምሮ ውስጥ ግንዛቤ የሚተከለው፣ አንድን ነገር ማድረግ እና አለማድረግ የሚያስከትለውን መዘዝ በውል ሲመለከትና ልዩነቱን ሲያውቅ ብቻ ነው። አልፎ በመሄድ፣ እኛ በሌለንበት ጊዜ ሁሉ ወደ ጥሩ መንገድ የሚወስዳቸውን የጠለቀ ግንዛቤ፣ በውስጣቸው እንዲመሰረት፣ ታዛዥነታቸው ብቻ ሳይሆን ግንዛቤያቸውም እንዲጎለብት ማድረግ ይጠበቅብናል::

ምንነቱ ሳይነገር በግዳጅና በአፈና የሚደረግ ነገር፣ ምንስ ጥሩ ቢሆን መምረር እንደሚጀምር ተረድተን ልጆቻችን እውነተኛ ግንዛቤ በሚሰጣቸው መልክ እናነጋግራቸው፤የአንድን ነገር ስሕተት እና ትክክልነት ስንነግራቸው፣ እነርሱን ሊመስጥ በሚችል መንገድ እናቅርብላቸው:: "በትምህርትሽ ከወደቅሽ በሕይወት ልታሳኪ የምትፈልጊውን ነገር ልታጪ ትችያለሽ፣ ጠንክረህ ካልሠራህ ሌላው ካንተ በልጦ የፈለገው ቦታ ሲደርስ፣ አንተ ወደኋላ ትቀራለህ:: ጠንክረህ ስትሠራ፣ ያለምከው ቦታ ደርሰህ ደስ ትሰኛለህ፤ በርትተሽ ለግብሽ ስትሰሪ ሕይወትሽን ደስ በሚልሽ መንገድ ለመምራት እድል ታገኛለሽ፤ ነጻ ሆነሽ ህልምሽን ለማሳካት እድል ታገኛለሽ::" እያልን ልጆቻችንን እናስረዳቸው፤ ጥያቄያቸውን በትዕግሥት እናዳምጥ። ትክክለኛ መልስም እንፈልግለት:: ግንዛቤ ከፍርሐት የበለጠ ኀይል እንዳለው ሁሌ እናስታውስ፤ የጠለቀ

ዕውቀት እንዲኖራቸው ስንል፣ ጥያቄያቸውን ሰለቸኝ ሳንል እናዳምጣቸው፤ እናነጋግራቸው፤ እናበረታታቸው::

ኀላፊነትን የምናስተምርበት ሌላኛው ዋነኛው መንገድ፣ ሰው ሁሌ የሥራውን (ጥሩም ሆነ መጥፎ)፣ ውጤት እንደሚያገኝ ካሁኑ በግልጽ በማሳየት ነው:: እነሱ ሊገባቸው በሚችል መንገድ የምርጫቸው ውጤት ምን እንደሚያስከትል ከህጻንነት ጀምሮ እንዲረዱ፣ ተግተን መሥራት አለብን:: ብዙ ጊዜ የምርጫቸው ውጤት ምን ዐይነት ጥቅም ሆነ ጉዳት እንዳመጣ በግልጽ እንዲያዩ ዕድል አንሰጣቸውም:: ይህ ማለት ምን ማለት ነው? ለምሳሌ ልጅ ሊወስድ የሚገባውን ኀላፊነት ሳይወስድ ሲቀር፣ ተቆጥተን እዛው ነገሩን እናልፈዋለን፣ ወይም እኛው ተረክበን እናደርግላቸዋለን:: በዚያ ፈንታ፣ ምርጫቸው ምን መዘዝ እንዳስከተለ በግልጽ እንዲረዱት ቦታ መክፈት ያስፈልጋል፤የሥራቸውን ውጤት በግልጽ ሲያዩት ጥቅሙን ወይም ጉዳቱን ይገነዘቡታልና::

ለምሳሌ ልጃችንን ቁጭ አድርገን፣ "ኀላፊነት ወስደህ መኝታ ቤትህን በራስህ ማጽዳት የምትችልበት ዕድሜ ላይ ደርሰሀል:: ካሁን በኋላ ውል እንገባለን፤ ኀላፊነት ወስደህ መኝታ ቤትህን የምታጸዳ ከሆነ የምትወደውን ቴሌቭዥን ፕሮግራም እንድታይ ይፈቀድልሀል፤ ካላጸዳህ ግን፣ ያው አታይም" ብለን እንንገር:: ምርጫውን ለእነርሱ እንተውላቸው፤ አሰላስለው ራሳቸው እንዲወስኑ እናድርግ:: አላጸዳም ካሉ ወይም ህጉን ባግባቡ ካልጠበቁ፤ ረጋ ብለን "ምርጫህ ይህ ከሆነ በተነጋገርነው መሠረት የምርጫህ ውጤት ይሄ ነው፤ያንን የቴሌቭዥን ፕሮግራም አታይም"፣ ብለን ምርጫው ያስከተለውን ውጤት እናሳይ:: ልጅ ተናዶ "እንዴ፣ ይሄማ ልክ አይደለም፤ፕሮግራሜን ማየት እፈልጋለሁ ብሎ ከጮኸ ወይም የሙጥኝ ካለ፣ ይህ አጋጣሚ ትምህርትን ማስተማሪያ ጥሩ ሰአት መሆኑን ተረድተን፣ ምላሻችንን እንስጥ:: ስሜታዊ ሳንሆን፣ ይህ የሕይወት ገጽታ እንደ ሆነ በግልጽ ለልጃችን ማስረዳት አለብን:: "የዓለም አሠራር እንደዚህ ነው:: እኔ ለምሳሌ ካልሠራሁ አይከፈለኝም:: ሁሉ ሰው ለሚሠራው ሥራ ውጤት አለው:: በዚህ





ነገር ውስጥ የለሁበትም፤ ምርጫውን ላንተ ነው የሰጠሁት፤ አንተ ደግሞ አለማጽዳትን መርጠሀል፣ ስለዚህ ውጤቱ ደግሞ ይኸው፤"
"በትምህርትሽ ጥሩ እየሠራሽ አይደለም እና ይኸው ውጤቱ " ብለን መጽናት አለብን:: እንደዚህ ስናደርግ፣ ልጅ "ይህን ማድረጌ ወይም አለማድረጌ ጉዳቱና ጥቅሙ ምንድን ነው?"፣ የሚለው በጥልቅ እየገባው/እየገባት ይመጣል:: "አባቴና እናቴ ስለሚቆጡኝ" በሚለው ውስን እውቀት ፈንታ፣ እውነተኛ ግንዛቤ ይሰርጽባቸዋል::

በዚህ ሂደት ውስጥ በደንብ መገንዘብ የሚኖርብን ትልቁ ቁም ነገር፣ በአቋማችንና በቃላችን ጽኑና ታማኝ መሆናችን ነው:: ሐሳባችንን ለውጠን ልጅ ማየት በሚገባው ውጤት ፈንታ የፈለገውን መስጠት፣ የገዛ ልጃችንን መጉዳት ነው:: "ስንፍናዬ፣ግዴለሽነቴ መጥፎ ውጤት የለውም፤ ስለ ጮህኩ ወይም ስላስመሰልኩ ከሀላፊነት ልርቅ እችላለሁ"ብሎ እንዲደመድም እየዳረግነው ነውና

ከላይኛው ጋር ተያይዞ፣ አስፈላጊ በሆነ መልኩ ሌላ ማድረግ ያለብን ዋና ነገር ይህ ነው:: ልጆች የጥሩ ስራቸውንም ውጤት እንዲያዩ ቦታ መክፈት አለብን:: አንዲት ልጅ የተነገራትን ነገር አመዛዝና በትምህርቷ ብታሻሽል፣ "ግብሽ ላይ ለመድረስ ለፍተሻል፤ ለጥሩ ሥራ ደግሞ ጥሩ ውጤት አለው፤ ልክ እንደ ተናገርኩት ያ ቃል የገባሁልሽን ነገር ታገኛለሽ"፣ ብለን የሚገባትን እንስጥ:: ሀላፊነት ወስደው ለወሰዱት ጥሩ እርምጃ፣ መጠኑ ቢያንስ እንኳ መሸለም፣ ማሞገስን አንርሳ:: እንደዚያ ስናደርግ፣ ምርጫቸው ትክክል እንደሆነ እያስተማርናቸው፣ እንዲሁም የበለጠ እንዲራመዱ እያበረታታናቸው ነውና::

ልጆቻችን ከሕፃንነታቸው ጀምሮ፣ ለራሳቸው ማሰብ የሚጀምሩበትን ትናንሽ ዕድል እንክፈትላቸው:: "ስለዚህ ነገር ምን ማድረግ ትፈልጊያለሽ? ስለዚያ ነገር ምን ማድረግ ትፈልጋለህ?"፣ እያልን ለእድሜያቸው በተገባ መጠን፣ የራሳቸውን ምርጫ እንዲያደርጉ ዕድል እንስጣቸው:: ለምሳሌ የአራት ዓመትን ልጅ፣ መጫወቻህን እዚህ ቦታ አስቀምጥ በማለት ፈንታ፣"መጫወቻህን

የት ልታስቀምጣት ትፈልጋለህ?" እንበል፡፡ የሆነ ነገር ማጠራቀም የምትፈልግ ልጅ ካለችን፣ የልጅ ሥራ ነው ከማለት ይልቅ፣ ኀበዝ በርቺ እንበል፡፡ ነገሩ ከዕቃው ሳይሆን ኀላፊነትን መውሰድ ከመማሯ ነውና፡፡ "ይህን ጠብቅልኝ፤ይህን ነገር እስቲ ያዥልኝ፤ ይህንን ነገር ባንተ ኀላፊነት ሥር ትቼዋለሁ፤ ለዚህ ልደት በአል ይህን ክፍል እንዴት እንደምናሳምረው አንቺ ኀላፊነት ወስድሽ ዕቅድን አውጭ"፣ እያልን የራሳቸውን ትናንሽ ኀላፊነት እንስጣቸው፡፡ እኛም፣ አውቀንም ቢሆን እንኳ፣ ጥያቄ እንጠይቃቸው፡፡ እንዲማሩት ስለምንፈልገው ነገር፣ እንደ ጥያቄ አድርገን እንጠይቃቸው፡፡ "ስለዚህ ነገር ምን ትመክሪኛለሽ"? እንበላቸው፡፡ ለእኛ ጥሩ መልስ ለመስጠት ሲያሰላስሉ ለራሳቸው እየተማሩ ይመጣሉ፡፡

በትናንሽ ገንዘብ ላይ ኀላፊነት እንስጣቸው፡፡ ለምሳሌ "2 ብር በየሳምንቱ እሰጥሻለሁ፤ ያንን አጠራቅመሽ የፈለግሽውን መጫወቻ መግዛት ትችያለሽ፤ ወይንም "ይህን፣ ያንን ቤት ውስጥ ከሠራህ ይህን ያህል ደሞዝ ታገኛለህ፤ በዚያ ገንዘብ ያንን የፈለከውን እቃ መግዛት ትችላለህ" እንበላቸው፡፡ ይሄ ለገንዘብ ጠንክሮ መስራትን ያስተምራቸዋል፡፡ ገንዘብ እንደፈለጉት እንደማይገኝ ከማስተማሩም በላይ፣ ገንዘብን በብልሀት አወጣጥን ያስተምራቸዋል፡፡

ልጆቻችን በራሳቸው መንገድ እንዲራመዱ በሚፈልጉበት ጊዜ ፍርሐት አይሰማን፡፡ "እኔ ባልኩት ብቻ ሂድ" የተባለ ልጅ፣ የኀላፊነት ስሜት በውስጡ አያድግም፡፡ ራሱን ችሎ ማሰብን የተማረ ልጅ ግን ለወደፊትም በራሱ ጸንቶ መቆምን ይማራል፡፡ "እዚህ ቦታማ አትሄድም፤ እንደዚማ አታደርጊም" ብለን፣ በስጋት ከሁሉም ነገር ከልለን ለማሳደግ በመሞከር ፈንታ፣ ቀስ በቀስ እንደ ዕድሜያቸው መጠን፣ በራስ ለመቆሚያው ጊዜ እያዘጋጀናቸው ይሁን፡፡ ያ የምንሰጣቸው ፈቃድ ጓደኛ ቤት እንዲሄዱ መፍቀድ ይሆናል፤ወይም ይህን ያን እንዲያደርጉ መፍቀድ ይሆናል፡፡ ለእኛ እውነቱን መናገር፣ ቃላቸውን መጠበቅ እስከተማሩ ድረስ፣ በነጻነት አንዳንድ ነገሮችን እንዲያደርጉ እንፍቀድላቸው፡፡ እዚህ ጋር፣ ልጆቻችን ላድርግ ያሉንን ሁሉን እንዲሁ እሺ እንበል ለማለት





አይደለም፡፡ እኛ በራሳችን ማጣራት ያለብን ነገር ሊኖር ይችላል፡፡ የጓደኛቸውን ቤተሰብ መተዋወቅ፣ የት እንደሚሄዱ ማጣራት ሊኖርብን ይችላል፡፡ ያ እንዳለ ሆኖ፣ የማይጎዳቸው መጥፎ ያልሆነ ነገር እስከ ሆነ ድረስ፣ ለልጆቻችን በሕይወታቸው ኀላፊነት መስጠትን፣ በራሳቸው እንዲቆሙ መንገዱን መክፈትን እንጀምር፡፡ እንዲህና እንዲያ እያልን የኀላፊነት ስሜትን ማበረታታታችን፤

1. ልጆቻችን፣ በእነርሱ ዕውቀትና የማመዛዘን ችሎታ፣ እኛ እንደምንተማመን ያሳያቸዋል፡፡
2. እኔ ኀላፊነት መውሰድ የምችል ሰው ነኝ ብለው በራሳቸው እንዲተማመኑና ካሁኑ እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል፡፡
3. ለወደፊቱ ያዘጋጃቸዋል፡፡ ኋላ ሕይወትን ለብቻቸው ሲመሯት ከአሁኑ የለመዱት ኀላፊነት የመውሰድ ባህል፣አብሯቸው ይቆያል፡፡

በቤታቸው አንዲት ነጻነት አግኝተው የማያውቁት፣ ለራሳቸው ማሰብ አንዲት እድል ያላገኙት ልጆች ኮሌጅ ገብተው፣ "አሁን በቃ፣ እናቴ አባቴ አያዩኝም" ብለው "ታስሮ እንደተለቀቀ ጥጃ" ሆነው ሁሉን ልቀላቅል ሲሉ፣ እነዚህ ከልጅነታቸው ጀምሮ ለራስ ማሰብ፣ ኀላፊነት መውሰድን ቀስ በቀስ እንዲማሩ ሆነው ያደጉት ልጆቻችን፣ ምንም ነገር አዲስ አይሆንባቸውም፡፡ "እኔ ከድሮውም እናትና አባቴ ለራሴ ማሰብ እንድችል አድርገው ነው ያሳደጉኝ" ብለው፣ በዛው በኀላፊነት ስሜት ይቀጥላሉ፡፡ በውስጣቸው ተደላድሎ የተቀመጠው የግንዛቤ ስሜት፣ አሺጋሪ መርከብ፣ መሪ መስታወት ይሆንላቸዋል፡፡

# የሕይወት ተሞክሮ

## ልጆቻችንና ማንነታቸው

በውጭ አገር የተወለዱ ወይ የሚያድጉ ልጆችን በተመለከተ፤ አብዛኞች ልጆች፣ ንቅንቅ በማይል ስፍራ መካከል ሆነው፣ ተጨንቀው የሚገኙ መሆናቸውን አያለሁ፤ ይህም ማለት እነርሱ የሚኖሩት፣ በተለያዩት የወላጆቻቸው ዓለምና በጓደኞቻቸው ዓለም መካከል ነው። ይህ በበኩሉ በነርሱ ላይ የሚያስከትለው ውዥብርነትን ብቻ ሳይሆን የባይተዋርነትን ስሜት ጭምር ነው። ይህ ውጥረት የሚታየው በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ልጆች ላይ ብቻ ሳይሆን፣ እንደነሱው ወላጆቻቸው ከሌላ አገር በመጡ በሌሎችም ወጣቶች ነው።

ብዙ ወላጆች ለልጆቻችን ትላልቅ አላማና ህልም አለን፤ ያ እንዳለ ሆኖም፣ ልጆቻችን ሊደርሱበት የሚገባቸው ትልቅ ቦታ እንዲደርሱ፣ ወላጅ ሊይዝ የሚገባውን ቦታ መረዳት አለብን። ያ ምን ማለት ነው? ብዙ ሰዎች፣ ለልጆቻችን የምንወስነውን ውሳኔ ስንወስን፣ ነገሮችን የምንገመግመው ከራሳችን የግል እይታ ነው። "እኔ ልጅ ሆኜ ይህን እመኝ ነበር ስለዚህ እነሱም የሚመኙት ይህንን መሆን አለበት። እኔ ልጅ ሆኜ በእንደዚህ አይነት ችግር ውስጥ አልፌ ነበር፤ ስለዚህም ለልጆቼ ዋነኛ የሚያስፈልጋቸው ይህ ነው። እኔ ይህንን ነገር አያስፈልገኝም፤ ለእነሱም አያስፈልጋቸውም፤" ወዘተ። ባጠቃላይ አስበነውም ሆነ ሳናስበው፣ የራሳችንን ህይወት በምንመለከትበት መንገድ የእነሱንም ህይወት እንወስናለን። እንደዛ በማድረግ ፋንታ ግን፣ እነሱ የሚያስቡት የሚፈልጉት ምንድነው፣ 'በዚህ ጊዜ ለህይወታቸው ምንድነው የሚጠቅማቸው ምንድነው?' ብለን ቀስ ብለን ብናጠና፣ ለእነሱ የሚጠቅማቸው ነገር ላይ ሀይላችንን ልናወጣ እንችላለን።





የእኛ ግላዊ ምኞት፣ የልጆቻችንም አድርገን፣ መንገዳቸው ላይ አጋጅ ግድብ እንዳይሆን መጠንቀቅ አለብን። ለምሳሌ፣ ኮሌጅ ስትገቡ ይህንን ብቻ አጥኑ፣ ወደ ጥሩ ቦታ ለመድረስ መራመጃ አቅጣጫው ይህ ብቻ ነው እያልን እኛ በምናስበው አቅጣጫ ብቻ ልንመራቸው እንዳንሞክር እንጠንቀቅ። ይህ የሚያመጣው አደጋ የልጆቻችንን የተፈጥሮ ምጥቀት ያደመድማል፤ ራሳቸውን ችለው ማሰብን እንዳይለምዱ፣ በተፈጥሮ ችሎታቸው አብበው ደምቀው እንዳይወጡ ያደርጋቸዋል።

የእኛ ግላዊ ምርጫ፣ ልክ የልጆቻችንም እንደሆነ አድርገን ከሚጠቅማቸው ነገር እንዳንከላከላቸው ጥንቃቄን እንውሰድ፤ ለምሳሌ፣ ከትምህርት ውጭ ባለው የእንቅስቃሴ ፕሮግራም (extra curricular activity) ለልጆች ብዙ ጥቅም አለው። ልጆቻችን በዚህ ስፖርት ውስጥ ልግባ ወይ ይህንን አክቲቪቲ ላድርግ ሲሉን፣ እኛ ስለማናውቀው ወይ ስላለመድነው ብቻ "አይይ ምንም አያደርግልህም" እንላቸዋለን። እነሱ ያንን ስፖርት ሲጫወቱ፣ ወይ በትምህርት ቤት ያንን አርት ሲያሳዩ፣ ብዙ ወላጆች ሄደን አንመለከትም። እነዚህ አክቲቪቲዎች፣ ምንነታቸው ብዙም ባይረዳን እንኳ በዚህ ባህል ውስጥ ለሚያድጉት ለልጆቻን ምጥቀት አስፈላጊ እንደሆነ ተረድተን፣ የማናውቀው ከሆነ እንኳ ብንጠይቃቸው፣ ወይ አብረናቸው ብንለማመድ ልጆቻችንን ከማበረታታቱም በላይ ያለንን ትስስር በትልቁ ይጨምረዋል። ሌሎቻችን ደግሞ፣ በመጀመሪያ ላይ ስምምነታችንን ቢንገልጽም ልጃችን መሀል ላይ ሲደናቀፍ፣ ተስፋ ሲቆርጥ፣ ከዚያም ለመውጣት ሲወስን፣ ብዙ ጊዜ ውሳኔውን ያለማመንታት፣ እሺ ብለን እንቀበላለን። ልጆች ተስፋ አለመቁረጥን እንዲማሩ በምሳሌነት ማስተማር ያለበት ወላጅ ነው። ልጅ ትንሽ በደከመው ወይ ባስጠላው ቁጥር በቃኝ ብሎ ማቆም፣ ልጁ እንዲጎለምስ፣ ጠንክሮም እንዲጓዝ አይረዳውም።

ወላጅ ሊረሳው የሚችለው፣ ሌላው ልጅን በትልቁ የሚጠቅም ነገር፣ በበጎ አድራጎት ስራ ውስጥ መሳተፋቸው ነው። እኔ

አለመድኩም ወይ አላደኩበትም በማለት ፋንታ፣ ከልጆቻችን ጋር አብረን የበኅ አድራጎት ስራ ላይ ብንሳተፍ ከማንም በላይ የራሳችኑ ልጆች ህይወት እናሳብባለን። አብሮ መስራትን፣ መሪነትን፣ ለሌላ ማሰብን እና የመሳሰሉትን ያስተምራቸዋል። ከዚያም በላይ፣ ጠንካራ ያደርጋቸዋል ኮሌጅ ለመግባት ሲያመልከቱም በዚህ ውስጥ ተሳትፌያለሁ ብለው መጻፋቸው ለልጆቻችን ሬዚሜ በትልቁ ይረዳል።

የወላጅ ግላዊ ፍርሀት በምናደርገው ላይ ተፈናጥቆ፣ ልጆቻችንን እንዳይጎዳ ልንጠነቀቅ ይገባል. አገራችን ስናድግ በችግር ውስጥ አልፈን የመጣን ብዙ ሰዎች ልጆቼን ከችግር መከላከል እፈልጋለሁ ብለን እናስባለን፤እንደዛ ማሰባችን ጥሩም ትክክልም ነው። ከልክ ያለፈ ፍርሀትን ይዘን፣ በተሳሳተ ጎዳና እንዳናመራ ግን መጠንቀቅም አለብን። ልጅን ከችግር መከላከል ማለት ልጆቻችንን ማሞላቀቅ፣ ሀላፊነት ሳያስተምሩ ማሳደግ መሆን የለበትም። ለምሳሌ የኮሌጅ ተማሪ የሆኑ፣ እረፍት ጊዜ ሲመጣ የማይሰሩ ብዙ ልጆች አሉ። ልጆች ናቸው ብለን እየተውናቸው ብዙ ልጆች ራስን ስለመቻል፣ ገንዘብን በቅጡ ስለመያዝ ሳይማሩ ይቀራሉ። መስራት፣ ራሳቸውን መቻል ባለባቸው ጊዜ የሌላቸውን ገንዘብ እያጠፉ ጨዋታ ላይ ብቻ ማተኮር ልጆቻችንን በትልቁ ጎድቶ ሊያስቀር ይችላል።

ይህ ባህል የሚሰጣቸውን ብቻ ሳይሆን የእኛ ባህል የሚሰጣቸውን ጥሩ ነገርም ማጤን አለብን። ልጆች ምንጫቸውን ተረድተው ማደጋቸው ለህይወታቸው ምን ያህል ዋጋ እንደሚያመጣ ብዙ ጥናቶች መዝግበዋል።ማህበራዊ ኑሮ፣ ከሌላ ጋር መካፈል፣ ትልቅ ሰው ማክበር፣ ባህልን ማወቅ ለልጆቻችን መማራቸው በዚህ ባህል ውስጥ ሲያድጉ በጣም ይጠቅማቸዋል። ቤተሰብን ማክበር፣ እንግዳን ማክበር፣ ስነስርአት መያዝ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ማስተማር አለብን።ስራዬ ብለን ቋንቋ ባህላቸውን እንዲያውቁ መርዳት አለብን። ካልተጠነቀቅን፣ በራሳችኑ መነጽር አይተን፣





አያስፈልጋቸውም ብለን ወስነን፣ ይህን ለእነሱ ከፍተኛ ግምት ያለውን ጉዳይ ልንነሳቸው እንችላለን፤ የራሳቸው የሆነውን የቤተሰባቸውን ቋንቋ ታሪክ ልጆቻችንን ሳናስተምር የማሳደግ አደጋ ውስጥ ልንወድቅ እንችላለን። አንዳንዶቻችን ደግሞ የቤተሰባቸውን ቋንቋ ለመናገር መሞከራቸው ከእንግሊዘኛው ጋ ያምታታባቸዋል ብለን አስበን በጣም ከሚጠቅማቸው ነገር እንነሳቸዋለን። ወላጆች ማስተማር ባለብን ሰአት ስራዬ ብለን ስለማንነታቸው አላስተማርናቸውምና እነሱም ሲያድጉ በዛው መንገድ ይቀጥላሉ። የማንነታቸውን ክፍል የሆነውን ይህንን ቅርሳቸውን ሳናስተምር ካሳደግናቸው ባዶ ይቀራሉና ጠንክረን የሚጠቅማቸውን ነገር እንስጥ።

ልጆቻችን የሚያድጉት ከእኛ በተለየ ጊዜ፣ እንደሆነና የራሳቸው ብዙ ጫና እንዳለባቸው ተረድተን በግልጽ ልናናግራቸው ልንመክራቸው ይገባል። ከእነሱ ቦታ ሆነን፣ ሁኔታዎችን ለመረዳት ልንጥር ይገባል። በውጩ ያለባቸውን ግፊት ሳንረዳ፣ በግልጽ ሳናናግራቸው ፣ በደፈናው፣ እንዲህ አታድርግ እንዲህ አታጥፋ የሚለው ላይ ከማተኮር እንቆጠብ።

ባጠቃላይ ሁሉን ነገር በራሳችኑ መነጽር በመገምገም ፋንታ፣ እኛ በፈጠርነው አለም ውስጥ ልጆቻችን እንዲገቡልን ለመሳብ ከመሞከር ፋንታ፣ እነሱ ያሉበትን ሁኔታ አይተን ተረድተን ለልጆቼ ምን ማበርከት እችላለሁ፣ እንዲመጥቁ በምን ልረዳ እችላለሁ ብለን ብናይ በብዙ ሁኔታ ልንረዳቸው እንችላለን።

# ምዕራፍ አራት

## ፍሬያማነት በልጆች ሕይወት

ልጆቻችንን በተመለከተ፤ ፍሬያማነትን በአንድ በኩል ብቻ ከማየት እንቆጠብ። ምጥቀትን ስንለካ፣ ልጆቻችን በትምህርት መጎበዛቸውን፣ ጥሩ ውጤት ማምጣታቸውን ብቻ አናስብ። በትምህርት መጎበዝ አንድ አስፈላጊ የሆነ ምጥቀት ቢሆንም፣ ከትምህርት ቤት ውጤት ያለፉ፣ የሰው ልጅ ሊመጥቅባቸው የሚገባባቸው በጣም አስፈላጊ የሆኑ የሕይወት ክፍሎች አሉ።

ቀዳማይ የሕይወት ዐላማቸው፣ መብላት፣ መጠጣትና መተኛት የሆነ ልጆች ማሳደግ እንችላለን፤ ወይም ነገሮችን በጥልቅ የሚያስቡ፣ ራቅ ላለ ነገር የሚያነጣጥሩ ልጆችን ልናሳድግ እንችላለን። "ብዙኃንን የሚረዳ ጠቃሚ የሆነ ነገር አተረፉ" ተብለው የሚነሡ ልጆችን ልናሳድግ እንችላለን፤ ወይም "የ200 ብሩ ጫማ 150 ሲሆን እንዴት ነው የምገዛው" እያሉ ማሰላሰል፣ የሕይወት ዋነኛ እንቀሳቃሽ አላማቸው የሆነ የነገን ትላልቅ ሰዎች ልናሳድግ እንችላለን።

የሕይወት ዋነኛ ምሳሌያቸው፣ በቴሌቭዥን የሚያዩት ተዋናይ፣ የሆነ ልጆች ልናሳድግ እንችላለን፤ ወይም ከተብረቀረቀ ስእል አለፍ አድርገው የሚያዩ ልጆችን ልናፈራ እንችላለን። ዋነኛ ምኞታቸው፣ ጓደኛ ያደረገውን ሁሉ ለማድረግ በመጣጣር ላይ የተወሰነ ልጆችን ማሳደግ እንችላለን፤ ወይም ቆም ብለው በራሳቸው ማሰብን የማይፈሩ፣ በብዙ ዛፎች መሀል፣ ለየት ብለው ፈክተው የወጡ ልጆችን ማሳደግ እንችላለን።

አንድ ነገር ይህንን ውጤት በትልቁ ይወስነዋል። የልጆቻችንን ሥነ ምግባርና አእምሮ ለመቅረጽ ትልቅ አስተዋጽኦ ባለን በልጅነታቸው





ጊዜ፣ ልጆቻችንን ለምን ዐይነት ነገር እያጋለጥናቸው ነው? የሚለው የእነሱን የወደፊት አቅጣጫ ይወስናል። ሰው ማንነቱ እንደ ወፍ ዘራሽ ተክል፣ በአውላላ ሜዳ ላይ ዝም ብሎ አይበቅልም። የሰው ማንነቱ የሚቀረጸው፣ በሚያየው፣ በሚሰማውና በሚቀርብለት ነገር ነው። ምንስ ዐይነት ትልቅ ነገር በልጅ ውስጥ ቢኖር፣ ያለው ዕምቅ ኀይል፣ በትክክለኛ አቅጣጫ ካልተመራና ካልተገራ ወደ ታሰበለት ዐላማ ሊደርስ አይችልም።

እስቲ ራሳችንን እንጠይቅ፤ የምንፈልገው ነገር ምንድነው? ምን ዐይነት ትውልድ ነው ማፍራት የምንፈልገው? አዲስ ልብስ ለብሰው ፎቶ ተነስተው "አሜሪካ ኖርሁ" ብለው አርጅተው የሚሞቱ ልጆችን ነው ማሳደግ የምንፈልገው፣ ወይስ ከዚህ የላቀ ዐላማ አለን? ወይስ እንደ ከዋክብት ደምቀው የሚኖሩ፣ ምጡቅ አእምሮ ያላቸው ልጆች ማሳደግ እንፈልጋለን? በሰው አገር እንዲህ ከለፋን አይቀር፣ ፈክቶ ለሚያብብ፣ ፍንትው ብሎ ለሚበራ ነገር እንልፋ። ያለንን ሁሉ ከሰጠን አይቀር፣ ትክክለኛ ፍሬ የሚያፈሩ ልጆች በመቅረጽ ሂደት ላይ እንሰማራ። በቤታችን ያለው ያ ልጅ፣ትውልድን የሚመራ ልጅ ሊሆን ይችላል። ዛሬ ጎንበስ ብለን ወደ ታች የምናያት ያቺ ትንሿ ልጃችን፣ እስካሁን መድኀኒት ያልተገኘለትን በሽታ መድኀኒት ለማግኘት፣ በውስጧ ራእይ የተሰነቀባት ልጅ ትሆናለች፤ የነገን ትልቅ ሰው በቤታችን እያሳደግን መሆኑን ልብ ልንለው ይገባል።

ዋናውና ትልቁ ነጥብ፣ የልጆቻችንን አእምሮ መጠበቅ አለብን። በጠበበ ነገር ተከቦ ካደገ፣ በውስጡ ያለው ዘር የሚያስፈልገውን ውሀና ምግብ ካላገኘ፣ ያ ዘር ፍሬ መሆን ይሳነዋል፤ ተወሽቆ ወደ ውስጥ ሰምጦ ይቀራል። ምንም ያህል ለትልቅ ነገር የታሰበ ቢሆን፣ እንዳልነበር ይሆናል። ልጆቼ ምን አይነት ሰዎች እንዲሆኑ እፈልጋለሁ ብለን፣ ቆም ብለን እናስብ። ለእነርሱ የምንመኘውን ማንነት በጥራት ካየን በኋላ፣ እንደዚያ አይነት ሰዎች እንዲሆኑ የሚረዳቸውን ዘር በትጋት በውስጣቸው መትከሉ ላይ እንትጋ።

በዚህ ሂደት ውስጥ አንድ ነጥብ ልብ እንበል:: በሌላ አገር ባህል ውስጥ ስንኖር፣ ያ ባህል የሚሰጠውን ነገር በሙሉ ሳንመርጥ እንዲሁ ለልጆቻችን ከመስጠት እንቆጠብ:: "ትምህርት ቤት ያሉት ጓደኞቻቸው ይህን ያደርጋሉ፤ የዚህ ባህል ልጆችም እንዲህ ያደርጋሉ" ብለን አስበን ብቻ፣ ለልጆቻችንም ሁሉን አንፍቀድ:: ሳንለይ ሁሉን አቅርበንላቸው ካሳደግናቸው፣ ውጤቱ የሚሆነው አንድ ነው:: ለየት አድርገው ማሰብን ያልተማሩ የባህሉን ውላጆች እናተርፋለን:: የተለያዩ አስተማሪዎች፣ በልጅ አስተዳደግ ላይ ጥናት ያደረጉ ሰዎች፣ አንድ ደጋግመው የሚያነሱት ነጥብ አለ:: ያም ነጥብ፣ በዚህ ባህል ውስጥ ለልጆች ተስማሚ ያልሆነ፣ ልጆችን የሚጎዳ ብዙ ዘር እንዳለ ነው :: "የአሜሪካ ልጆች ናቸው፤ እንደ አሜሪካ ልጆች መኖር አለባቸው" ብለን፣ ሁሉን በገፍ በማቅረብ ፈንታ "ይህ ነገር ለልጆቼ ልምላሜን ያበረክታል ወይስ ያጠወልጋቸዋል? ብለን አርቀን እንመርምር:: ይህ የባህል ክፍል ልጆቼን አጥብቦ ያስቀራቸዋል? ወይስ ወደ ሰፋ ነገር ይወስዳቸዋል" ብለን ቆም ብለን እናስብ::

## *1) <u>የቴሌቪዥን ተጽእኖ</u>*

> "ልጆች ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጨርሰው እስኪመረቁ፤ በትምህርት ቤት ውስጥ የሚያጠፉት ጊዜ፣ በአማካይ 11 ሺህ ሰአታት ይሆናል። በእነዚህ ጊዜያት ውስጥ ቴሌቭዥን በማየት የሚያጠፉበት ጊዜ ደግሞ 15 ሺህ ሰአታት ይሆናል። ቴሌቭዥን ልጆችን በማስተማር ደረጃ ከአስተማሪም የበለጠ ትልቅ ተጽእኖ አለው ማለት ይችላል።"[11]

ቴሌቪዥን የልጆቻችንን አእምሮ ለመቅረጽ ትልቅ ኀይል ያለው ነገር ነው:: ብዙ ጊዜ ደግሞ በመጥፎ መንገድ ለመምራትም የሚጫወተው ሚና በቀላሉ የሚገመት አይደለም::

[11] Murray J.P (1997) <u>Media violence and youth</u>; children in a violent society J. Osofsky (Ed),New York , Guilfor Press





> "ልጆች ብዙውን ሰአታቸውን ቴሌቪዥን በማየት ሲያጠፉ፣ ለወደፊት ማህበራዊ ህይወት እድገታቸው ጎጅ የሆኑ፣ጥል /ድብድብ/ በብዛት ከማየት ባሻገር፣ ገንዘባቸውን ያለአግባብ እንዲያወጡ የሚገፏቸው የቴሌቭዥን ማስታወቂያዎችንም በብዛት የማየት እድል አላቸው።"[12]

ልጆቻችንን በቴሌቪዥን ፊት ለፊት ለረጅም ጊዜ የምንተዋቸው ከሆነ፣ ጠባብነትንና በአንድ መንገድ ብቻ ማሰብን እንኩ እያልናቸው መሆኑን እንገንዘብ:: ይህ ብዙ ስለ ልጅ አስተዳደግ የሚያስተምሩ አስተማሪዎች ደጋግመው ለወላጆች የሚያስተምሩት ሐቅ ነው:: ብዙ ጊዜ ቴሌቪዥን፣ የገሐዱ ዓለም እውነት የማይንጸባረቅበት የራሱን አለም ያቀርባል:: የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች፣ ሰውን መመሰጥና እዛው ጎልቶ ማስቀመጥ ዓላማቸው ስለሆነ፣ ጊዜና ስሜትን የሚሰልቡ፣ ከእውነት የራቁ ህልማዊ ድራማዎችን በየጊዜው ያቀርባሉ:: ከዚያ በተጨማሪ፣ በየደቂቃው የሚጮኸው የቴሌቪዥን ማስተዋወቂያ፣ የሕይወት ዋና ትርጉም ዕቃ፣ ልብስ፣ እንሥት... ወዘተ እንደ ሆነ የሚገልጽ መልእክት ያስተላልፋል:: በተለይ ልጆቻችን ዐደግ እያሉ ሲመጡ፣ አንዳችም እርባና የሌላቸው መልእክቶችን በየቀኑ ከቴሌቪዥን ይሰማሉ::

የልጆቻችንን ሥነ ምግባርና አእምሮ የሚቀርጹት የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ከሆኑ፣ በአደጋ ላይ መሆናችንን ልብ ልናደርገው ይገባል:: ልጆቻችንን በሥነምግባርና በአእምሮ የሚያሳድጉልን የቴሌቪዥን ተዋናይ ከሆኑ፣ የጠባብነት መንገድን እንዲወስዱ መንገዱ እየተመቻቸላቸው እንደሆነ፣ ልናስታውስ ይገባል:: መሪ፣ መሪ ነው:: ያ መሪ የቴሌቪዥን ሳጥን ቢሆንም እንኳ፣ በቤታችን መሪ እንዲሆን ተፈቅዶለታልና፤ ልጆቻችንን እየመራልን ይመጣል:: የሕይወት ዋነኛ አላማ፣ ያቺ ተዋናይ ለምሳ ምን እንደበላች ማጣራት መሆኑን እየመሰጣቸው ይመጣል:: ለየት ላለ ዐላማ

[12] Smith A Charles (1999) <u>The encyclopedia of parenting theory and research</u>

ተፈጥሮ የነበረው የልጆቻችን አእምሮ፣ ቀስ በቀስ እየተለወጠና በጠባብ ነገር እየተሞላ ይመጣል::

ልጆች ከቴሌቪዥን ጋር ተፋጠው መዋላቸው፣ አንድ ለአንድ ከሰው ጋር ያላቸውን ትስስርና ንግግር እንዳያዳብሩ ያደርጋቸዋል:: እንግዳ ሲመጣ ቁጭ ብለው ከእርሱ/ እርሷ ጋ መጫወት ይጠላሉ:: እነርሱ አፍጥጠው ማየት የሚፈልጉት ያቺን የለመዷትን የቴሌቪዥን ፕሮግራም ነው፤ሱስ ሆናባቸዋለችና:: በሰው ውስጥ ሕይወት የሚኖረው ከሌላ ጋር ሲተሳሰር፣ ፍቅርንና ትዝታን ከሚያጣጥሙ ሕያዋን ከሆኑ ሰዎች ጋር ሲጫወትና ሲያወራ ነው፤ ይህ የተፈጥሮ ሕግ ነው:: ሰው ሕያዋን ከሆኑ ሰዎች ጋር መጫወት ትቶ፣ ሕይወት የሌለበትን ሳጥን ዘወትር መመልከቱ፣ ያፈዘዋል፤በብዙ መልክ የሰውን ልጅ የሚያዳብሩ ንግግሮችና ትዝታዎች፣ እንዳይኖሩት ያደርጋል::

የቴሌቪዥን ፕሮግራም ሁሉ መጥፎ አይደለም:: የሚያዝናኑና የሚያስተምሩ ጥሩ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች መኖራቸው እሙን ነው:: ነገር ግን ቀን ተሌት፣ ቴሌቪዥን የልጃችን ጓደኛ እንዲሆን መፍቀድ፣ ከትርፉ ኪሳራው ይበረታል፤ ከማዝናናት አልፎ ጉዳትንም ያስከትላል። የልጆቻችንን የቴሌቭዥን አጠቃቀም፣ በጤነኛ መልኩ እንዲሆን ምን ማድረግ እንችላለን?

1. ልጅ ለዕድሜው ተስማሚ የሆነ ፕሮግራም ያስፈልገዋል:: ቴሌቪዥኑ ሲከፈት፣ልጆቻችን የሚያዩትን ፕሮግራም ምን ይዘት እንዳለው በአንክሮ እንከታተል:: ፍትወት፣ተቀነባብሮ የቀረበ የእርስ በርስ ድብድብ፣ መገዳደል...ወዘተ በቴሌቪዥን ፕሮግራም ውስጥ በብዛት የሚቀርቡት ናቸው:: እኛ ራሳችን ለማየት ብለን፣ ልጅ ሊያየው የማይገባውን ፊልም መክፈት፣ ለልጅ ብልግናን እንካ እንደ ማለት ነው፤ የልጅ አእምሮው ነገሮችን ሳያገናዝብ ሁሉን ነገር ለመቅለብ የተዘጋጀ ነውና::





> "በህጻናት፣ትምህርት ቤት እድሜ ባሉ ልጆች፣ እና ኮሌጅ ተማሪዎች ላይ የተደረጉ የምርምር ጥናቶች እንደሚያመለከቱት በቴሌቭዥን ጥል ድብድብን ደጋግሞ ማየት፣ ልጆችን ቁጡና ለጥል የተጋለጡ የማድረግ ትልቅ እድል አለው። የወደፊቱንም ሕይወታቸውን ሊቀርጽ አመለካከትና አስተያየታቸውን ሊለውጥ ትልቅ ሀይል አለው::"[13]

ልጆቻችን የሚያዩዋቸውን የካርቱን ፊልሞች ይዘት፣ ምን እንደሆነ እናጣራ:: እኛ ካላወቅን ስለ ፕሮግራሙ ይዘት ሌላ ሰውን እንጠይቅ:: ድሮ በቴሌቪዥን የሚቀርቡ የካርቱን ፊልሞች፣ ለልጆች ብቻ የሚዘጋጁ ነበሩ:: አሁን ግን፣ ልጅ ሊሰማው የማይገባው የዐመጽና ፍትወት ነገር ያለባቸው፣ ነገር ግን "አስቂኝ" ተብለው የሚጠሩ ብዙ ካርቱን ፊልሞች አሉ:: በቴሌቪዥንም ሆነ ተከራይተው ሊያዩት የሚገባውን ፊልም የመምረጡ፣ እና ያንን ህግ የማስጠበቁ ስራ፣ የልጆቻችን ሳይሆን የእኛ ስራ እንደሆነ ልብ ልንል ይገባል:: <u>የቴሌቭዥን ሾው፣ ፊልም፣ መጻህፍና ቪዲዮ ጌምን በተመለከተ፣ ለልጆች ተገቢ ስለሆኑ እና ስላልሆኑት ጥሩ ግንዛቤ ለማግኘት ከስር ያለውን ድረገጽ (ዌብ ሳይት) ይመልከቱ</u>[14]

[13] Huston, A. C., Donnerstein, E., Fairchild, H., Fashbach, N. D., Katz, P. A., Murray, J. P., Rubinstein, E. A., Wilcox, B. L., Zuckerman, D., (1992). <u>Big world, small screen; The role of television in American Society.</u> Lincoln, NE: University of Nebraska.

[14] Commonsensemedia.org ወላጆች ሊያዩት የሚገባ በጣም ጥሩ ዌብ ሳይት ነው Reviews and advice የሚለውን ብንጫን ስለተለያዩ በቴሌቭዥን ስለሚታዩ (shows), ፊልሞች, ቪዲዮ ጌም፣ መጻህፎች ለልጆቻችን (እንደየእድሜያቸው) ተገቢ ይሁኑ አይሁኑ በግልጽ ያሳየናል::

2. "ግልግል ነው" በሚል፣ ልጆቻችንን ለረጅም ጊዜ፣ በቴሌቪዥን ፊት መተውን እናቁም። እንደ ፕሮግራሙ ይዘት ሁሉ፣ የሰአቱ እርዝመትም፣ ተጽእኖ እንዳለው ተረድተን፣ እርምጃ እንውሰድ። ቴሌቪዥን ለተወሰነ ጊዜ የሚከፈት መዝናኛና መማርያ እንጂ ቋሚ ጓደኛ እንዳይደለ ለልጆቻችን ነግረን፣ ያለ አንዳች ማቅማማት ቴሌቪዥኑን እናጥፋ።

3. በፋንታው፤ልጆቻችን ሊያደርጉዋቸው የሚችሉዋቸው ሌሎች ነገሮች እናቅርብላቸው እርስ በርስ እንዲጫወቱ እናበረታ። ልጆቻችን መጽሐፍ እንዲያነቡ እናበረታታ። አብረን የቤተሰብ ጊዜ እናሳልፍ። የፈጠራ ችሎታቸው እንዲያድግ፣ በተፈጥሮዋቸው የሚመጥቁበት፣ ስዕል፣ ጽሕፈት፣ ፒያኖ፣ መገጣጠም ስፖርት ላይ እንዲያተኩሩ እናበረታታ። አገር ቤት ላሉ ወዳጅ ዘመዶች ደብዳቤ እናጽፋቸው። መነቃቂያ የሚሆናቸው ነገር አዘጋጅተን ቤት ውስጥ እንዲያግዙን እናድርግ።ደጋግመን በህጋችን ከቆምን ልጆች ይለምዳሉ። "ቴሌቪዥን ካልተከፈተ ሞቼ እገኛለሁ" ብለው መቁነጥነጥ ያቆማሉ፤በቤት ውስጥ በፈልጉ ጊዜ ሁሉ የማይከፈትመሆኑን ስለሚያውቁ፣ የራሳቸውን፣ የሚያደርጉት ነገር ይፈጥራሉ።

የቴሌቪዥን አጠቃቀምን መቀየስ ብቻ ሳይሆን፣ ልጆቻችን ውስን አስተሳሰብ፣ ጠማማ አካሄድ እንዳይኖራቸው ይረዳል ብለን የምናስበውን ነገር አብረናቸው እንወያይ። ሥራዬ ብለን ስለተለያዩ ጉዳዮች እየተወያየን የምናሳልፈው ጊዜ፣ ለየት ባለ መንገድ እንዲያስቡ ይረዳቸዋልና። ለምሳሌ "ይህች ተዋናዪት የምትከበረው ለምን ይመስልሻል? እንደ እነርሱ ያልሆነ ሰው ከእነርሱ የሚያንስ ይመስልሻል ወይ?" ብለን እንጠይቃቸው። እንዲያስቡም ቦታ እንክፈት፤ "ኅበዝ ወይ ጀግና ማለት ቴሌቭዥን ላይ ወጥቶ የሚሰራ ሰው ነወይ" ብለን እንጠይቃቸው፤ እንዲያስቡበት ቦታ እንስጥ፤እንወያይ። ባጠቃላይ፣ ከጠበበው ስእል ወጣ አድርጎ የሚያሳያቸውን የተለያየ ሀሳብ እናቅርብላቸው። ስለ አገር ቤት፣





አስተዳደጋችን፣ ስለ ኅብረተሰቡ አኗኗር እናውራቸው። ዓለም ውስጥ ስላሉ የተለያዩ ጉዳዮች እንሥተን እንወያይ። ሰዎች የሚከራከሩባቸውን የተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች እንንገራቸው። "ስለዚህ ነገር ምን ታስባላችሁ?" ብለን እንዲያስቡበት ዕድል እንስጣቸው። ስለተለያዩ ነገሮች ማወቃቸውና ስለ እነዚህ ነገሮች መነጋገራቸው፣ በአንድ ጎን ያዘመመና የተሳሳተ አካሄድ እንዳይኖራቸው ይረዳል።

## *የኮምፒዩተር አጠቃቀም*

ሌላው ልጆችን ወደ መጥፎ መንገድ የመሳብ ሀይል ያለው መሳርያ፣ ኮምፒዩተር ነው። ኮምፒዩተር ልጆችን የሚጠቅም ብዙ ነገር ያበረክታል። ልጆች ስለ አዲስ ነገር ለመማር እንዲችሉ፣ የሚፈልጉትን ለመጻፍ፣ ከሌሎች ጋ ለመገናኘት እንዲችሉ ይረዳቸዋል። ኮምፒዩተር ብዙ ጥቅም አለው፤ ግን በዛውም መጠን ጉዳት ሊኖረው ይችላል። ልጆች የፈለጉትን ይዩ ብለን ኮምፒዩተር ፊት የምንለቃቸው ከሆነ፣ ለእድሜያቸው ተስማሚ ያልሆኑ፣ጭራሽ ሊያዩ የማይገባቸው ምስሎችን ያቀርብላቸዋል። እነዚህ ምስሎች የልጆቻችንን አእምሮ ለመቅረጽ፣ ልጆቻችንን ወደ መጥፎ አቅጣጫ ለመሳብ ትልቅ ሀይል አላቸው፤ ለአደጋም የተጋለጡ ያደርጋቸዋል።

> "ካለወሰን ኢንተርኔት ውስጥ እንዲገባ የተፈቀደለት ልጅ፣ ፍትወትን በግልጽ የሚያሳዩ ሳይቶችን በቀላሉ የማግኘት እድሉ በጣም ከፍተኛ ነው።"[15]
> "በዚህ ጉዳይ ላይ በተደረገ ጥናት፣ 70 % የሚሆኑ ልጆች፣ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ፣ ፖርኖግራፊ (ፍትወት) ያለበት ሳይትን ተመልክተዋል።"[16]
> "ልጆች ሊያዩ የማይገባቸውን ሳይት የሚመለከቱት፣ ብዙውን ጊዜ (79% ያህል ጊዜ) ከቤታቸው ነው።"[17]

[15] (Internet safety 101.org)

[16] Victoria Rideout, Donald F. Roberts. Ulla G. Foehr. March 2005. The Henry J. Kaiser Family Foundation. 17 November 2006 (Generation M: Media in the Lives of 8-18 Year-Olds. http://www.kff.org/entmedia/up...f-8-18-Year-olds-Report.pdf

[17] http://www.unh.edu/ccrc/pdf/CV138.pdf).

ልጆቻችንን ወደ መጥፎ አቅጣጫ ሊስብ የሚፈልገው የጊዜው ቆሻሻ ወደ እነሱ አካባቢ እንዳይደርስ ከፈለግን፣ ኮምፒዩተር አጠቃቀማቸውን በብልሀት እናድርግ (ልጆቻችንን፣ ሊያዩዋቸው ከማይገቡ ከአስቀያሚ ሳይቶች ለመከላከል፣ ወላጅ ምን እርምጃ መውሰድ እንደሚችል፣ አለፍ ብለን ከስር እንመለከታለን::)

## የቍሳቍስ ተጽእኖ

ሌላው፣ የልጆቻችንን የአእምሮ ስፋትና ጥበት የሚወስነው፣ ሽቀጥን የሚያዩበት ዕይታ ነው:: ሽቀጥ እንደ ገፍ ባለበት፣ በውጩ አገር እንኖራለን:: በብዙ ዕቃ ተከበው ግን፣ መሳቅን እንኳ የረሱ፣ ብዙ ሰዎች እንዳሉ በአካለ ሥጋም ሆነ በቴሌቪዥን እናያለን::

ልጆቻችንን፣ ከሚያስፈልጋቸው በላይ በዕቃ አናፍናቸው:: "ሕይወታቸውን በደስታ ይሞላዋል፣ ስለ ራሳቸው ያላቸውን አስተሳሰብ በጥሩ ይለውጠዋል" ብለን አስበን፣ ጥሩ ወላጅ የመሆን ምልክት መስሎን፣ በማያስፈልግ ዕቃ አንክበባቸው:: እንዲህ አላደረኩላቸውም" የሚል፣ የጸጸት ስሜት በሽቀጥ ለማካካስ፣ አንሞክር፤ ያ ልጆቻችንን ይጎዳቸዋልና:: ስለ ቁሳቁስ ተጽእኖ የሚከተሉትን እውነታዎች እናስተውል፤

- ☞ ልጆቻችን ቁሳቁስ ላይ ከሚያስፈልገው በላይ ሲጣበቁ፣ ሰፋ አድርገው እንዳያስቡ ይገድባቸዋል፤
- ☞ ሽቀጥ በሕይወታቸው ትልቅ ስፍራ እንዲኖረው ቦታ ስለሚከፍት፣ ለሕይወት ዋነኛ ነገሮች ጊዜ እንዳይኖራቸው ያደርጋል:: ሕይወት በእነርሱ አዲሷ ዲቪዲ ጌም ዙርያ ብቻ እንደ ተወሰነች ማመን ይጀምራሉ፤
- ☞ ከእነርሱ ውጭ ሕይወት እንዳለ፣ በዓለማችን የሚበሉት እንኳ የሌላቸው ልጆች እንዳሉ ይረሳሉ፤
- ☞ ስላላቸው ጥሩ ነገር እንኳ በቅጡ አይረዱም:: ያ ነገር ለእነርሱ በግድ መደረግ እንዳለበት የሚያምኑ፣ ሽቀጡም





  እንዲያው ያለ አንዳች ድካም ዝም ብሎ የተገኘ ነገር እንደሆነ የሚያስቡ ይሆናሉ::
- ☞ ይህ ሁሉ ሆኖም ግን ደስተኛ አይሆኑም:: በውፌው ሁሉ ነገር ያላቸው ቢሆንም፣ ውስጣዊ ደስታ ስለማያገኙበት፣ የበለጠ ነገር የሚፈልጉና ለበለጠ ሽቀጥ የሚራቡ የሚጠሙ ይሆናሉ::
- ☞ ሁሉ ለእኔ ለእኔ የሚሉ ለራሳቸው ብቻ የሚያስቡ ስግብግቦች እንዲሆኑ በር ይከፍታል::
- ☞ ፍቅራችንን በምንገዛው ሽቀጥ ብዛት ልናሳያቸው ስንሞክር፣ ሽቀጥን የፍቅር መግለጫ ብቸኛ መንገድ አድርገው ይረዳሉ:: ሰው እንደወደዳቸው የሚያስቡት ዕቃ ሲገዛላቸው ብቻ ይሆናል:: ሲያድጉም ፍቅርን ለመግለጽ የሚሞክሩት፣ የትዳርን ፋይዳ የሚመዝኑት በሽቀጥ ብቻ ይሆናል::

በማደግ ላይ ባሉ ሐገሮች የተወለዱ ህጻናት፣ እጅግ ትንሽ ነገር ሲገዛላቸው፣ እንዴት ደስ ተሰኝተው፣ መጫወቻውን ወደው እንደሚንከባከቡት ግልጽ ነው:: እንደ አሜሪካ፣ ካናዳና አውሮፓ ባሉ ቦታዎች አብዛኞዎች ልጆች ብዙ ቢደረግላቸውም፣ እምብዛም እንደማይደንቃቸው እናያለን አይደለምን? አስገራሚ ቢሆንም፣ ሐቁ ይኸው ነው:: የሰው ልጅ ከሚገባው በላይ በውጫዊ ነገር ሲከበብ፣ ሽቀጡ ከማስደሰት ይልቅ አፋኝ ይሆንበታል::

- ልጆቻችን ሁሌ ይህ ዕቃ ይገዛልኝ የሚሉ ከሆነ፤
- ሁልጊዜ፣ ራሳቸውን ከሌላ ልጆች ጋር እያስተያዩ፣ "እገሊት ይሄ አላት፣ እገሌ ያ አለው እና እነርሱ ያላቸው ከሌለኝ" የሚሉ ከሆነ፤
- አንድ ስጦታ ሲሰጣቸው ሳያመሰግኑ የሚወስዱ ከሆነ፤
- መኝታ ቤታቸው በብዙ ነገር የተጣበበ ከሆነ፤

ምናልባትም ለልጆቻችን ሸቀጥ ከሚገባው በላይ በዝቶባቸዋል:: በሕይወት ውስጥ ከዕቃ የበለጠ ትላልቅ ዋጋ ያላቸው ነገሮች እንዳሉ የተረዱ፣ ደስታቸው ባላቸው ሸቀጥ ወይም በሌላቸው ነዋይ ላይ ያልተመሠረተ፣ ከዚያ ዐርነት የወጡ ልጆች ማሳደግ ከፈለግን፣ ካላግባቡ በሸቀጥ ፍቅር እንዳይነደፉ እንጠብቃቸው::

የፍቅር መግለጫ ሸቀጥ እንዳልሆነ እናሳያቸው:: ደስተኛ ለመሆን፣ ነጋዴ ሊሸጥ የፈለገውን እቃ ሁሉ መግዛት እንደሌለባቸው እናስተምራቸው:: እንዲያውም ይህ አጋጣሚ የሸቀጥን ጠባብነት ለማስተማር እንደ ምክር እንጠቀምበት:: "የሰውን ልጅ ዋጋ የሚሰጠው ምን ይመስልሀል? "አንድ ሰው ብዙ እቃ ስላለው፣ ጥሩ ስለ ለበሰ፣ ያን ሰው ዋጋውን የሚጨምር ይመስልሻል ወይ?" ብለን እንዲያስቡበት እንፍቀድላቸው:: በመገናኛ ብዙኀን ማስታወቂያ የሚሰሩ የተለያዩ አካላት፣ እቃቸውን ለመሸጥ ስለሚጠቀሙበት ስለተለያየ ዘዴ እንንገራቸው::

ጓደኛዬ አላት/አለው ያሉትን ዕቃ ሁሉ አንግዛላቸው:: "ጓደኛሽ አላት ማለት አንቺ ሊኖርሽ ይገባል ማለት ነው ወይ?" የሚለውን ቁልፍ ጥያቄ መልሰን መላልሰን እንጠይቃቸው:: በርግጥ በዚች ዓለም የሚኖሩ ሰዎች ናቸው፤ እንደ ጓደኞቻቸው መሆን፣ መልበስ ያምራቸዋል:: ልጆቻችንን ፍጹም ከሰው የተለዩ ሰዎች አድርገን እናሳድጋቸው እያልን አይደለም:: ነገር ግን ሸቀጥ በሕይወታቸው ውስጥ ትክክለኛውን ቦታ እንዲይዝ፣ ሸቀጥ አምላካቸው እንዳይሆን አድርገን እናሳድጋቸው ለማለት ነው::

መጫወቻ ልንገዛላቸው ያሰብነውን ገንዘብ ቤተሰብ አብረን ተሰብስበን ራት እንመገብበት፤ያ ለሕይወታቸው እጥፍ ድምቀት ያመጣል፤ ብዙ ገንዘብ የማያስወጣ ቦታ ቤተሰቡ ሁሉ አብረን እንሂድ፤በእቃ ላይ የሚወጣውን ሀይልና ጊዜ እንደዚህ አብሮ ማሳለፍ ላይ ስናወጣው የልጆቻችንንም የእኛንም ሕይወት በጣም እንጠቅማለን፤ ልጆቻችንም ከጠበበ አስተሳሰብ እንዲወጡ እናበረክታለን::





## *ልጆቻችን የለመለመ አስተሳሰብና ግንዛቤ እንዲኖራቸው ምን ማድረግ እንችላለን::*

- ***የበጎ ፍቃድ አገልግሎት***

ሌላን ሰው በመርዳት፣ ሌላን ሰው በፍቅር በመንካት ውስጥ እንዲሳተፉ፣ ከልጅነታቸው ጀምሮ ሁኔታዎችን ማመቻቸታችን፣ ለልጆቻችን ውስጣዊ ደስታ፣ ውስጣዊ ጤንነት፣ አርቆ ማየትና ማሰብ ያበረክታል። ልጆቻችን ከራሳቸው ያለፈ፣ ሌላ ሰውን የሚረዳ፣ የሚያገለግል ሕይወት ውስጥ እንዲገቡ መርዳታችን፣ ሕይወታቸውን በብዙ መንገድ ይለውጠዋል።

- ☞ ሌሎችን በመርዳት የሚገኘውን እውነተኛ ደስታ በትክክል እንዲያጣጥሙ ያደርጋቸዋል:: የሌላን ሰው ሕይወት በመንካት የሚገኘው ደስታ በሸቀጥ ከሚገኘው ደስታ ይልቅ፣ ጠንካራና ዘለቄታ ያለው እንደ ሆነ ይረዳሉ::
- ☞ ሰውን መውደድ ማለት ምን ማለት እንደሆነ፣ ከሰው ጋር የሚኖር ማኅበራዊ ግንኙነት ምን እንደሆነ በቅጡ ይረዳሉ:: እውነተኛ ፍቅር፣ እውነተኛ ሰላምና ከሰዎች ጋር ኅብረት ማድረግ ወደ ልጆቻችን ሕይወት ይገባሉ::
- ☞ አስተሳሰባቸውን ይለውጠዋል:: ሌላውን በመርዳታቸው፣ ዓለም በእነርሱ ችግር ዙርያ ብቻ የምታጠነጥን እንዳልሆነች ይረዳሉ:: ከዓለም ችግር ጋር ሲነጻጸር የእነርሱ ችግር እዚህ ግባ የሚባል ነገር እንዳልሆነ ይገነዘባሉ:: ባላቸው ነገር ተመስገን ማለትን እንዲማሩም ያደርጋቸዋል::
- ☞ የከበባቸው ዓለማዊ ነገር ሊሰጣቸው ያልቻለውን፣ ትርጉም ያለውን ሕይወትን ይሰጣቸዋል። ሰውን ጧት ከዐልጋው አዘልሎ የሚያስነሣው፣ ውስጡ አንቀሳቃሽ ሞተር የሚሆን፣ ከዕለት ጉርሱ ያለፈ ዐላማና ትርጉም ሲኖረው ነው:: ሌላውን በመርዳታቸው ሂደት ውስጥ፣ የችግሩ ሳይሆን የመፍትሔው አካል እንደሆኑ እንዲያውቁ

ያደርጋቸዋል፣ ይህም የወደፊት አቅጣጫ አሳዩ፣ መሪ ይሆናቸዋል። የነገዎቹ ዶክተሮች፣ መሀንዲስ፣ ጸሐፊ፣ የነገ አስተማሪ፣ አዲስ ነገር ፈጣሪ፣ ልጆችን ሰብስቦ አሳዳጊ፣ የነገ ስለ ሰው መብት ተከራካሪ ይሆናሉ። ባጭሩ በተሰጣቸው ችሎታና ስጦታ፣ የሰብአውያን ሕይወት አብሪ ክዋክብትና ጸሐይ ይሆናሉ። በዚህ በውስጣቸው በተዘረጋው አቅጣጫን የሚቀይስላቸው ኀይልም ፣ ከማንም በላይ እነሱ በርተውበት ይኖራሉ።

☞ ቤተሰብ አብረን ሌላን ሰው በመርዳት ነገር ውስጥ ስንሳተፍ፣ ያስተሳስረናል። በቤተሰብ መኻል ፍቅርን፣ጥሩ ትዝታን ይፈጥራል። ቅዱስ ለሆነ አላማ ተባብረን እየሰራን ነውና፣ ይህ ለትስስራችን ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

ዋናው ሰውን በመርዳት ነገር ውስጥ መሳተፋቸው ነው እንጂ፣ ለምናደርገው ነገር አንድ አይነት ቀመር መኖር የለበትም፤የተለያዩ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሥራዎች ላይ ቤተሰብ አብረን ልንሳተፍ እንችላለን። አንዳንድ ምሳሌዎችን እንይ፤

- ቤተሰብ ሁሉ፣ ወላጅ የሌለው ልጅን በመርዳት ላይ እንዲሳተፍ ልናደርግ እንችላለን። "እናንተም በዚህ ትሳተፉላችሁ ብለን ለልጆቻችን ነግረን፣ ለዚህ ልጅ ወይም ለእነዚህ ልጆች በየሁለት ሳምንቱ ወይም በየወሩ ደብዳቤ እንዲጽፉ፣ የሚያበረታታቸው መልእክት እንዲልኩላቸው ልጆቻችንን ማበረታታት።
- በኛው አካባቢ የሚኖር የሆነ እርዳታ የሚያስፈልገው ሰው ካለ ለምሳሌ፣ "ዛሬ እኔና ልጆቼ ቤትህ መጥተን በዚህ ነገር እንረዳሀለን" ብለን ነግረን ልጆቻችንን ይዘን ሄደን በዚያው ውስጥ ማሳተፍ።
- ለታመመ ሰው ምግብ እንስራ ብለን እነርሱም በቻሉት ምግቡን መስራት ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ።
- መኖርያ የሌላቸው ሰዎች የሚኖሩበት ቦታ በምሳና ራት ሠዓት ሄደን፣ ምግብ ሲቀርብ መርዳት።





- አጠገባችን ያለ አሮጊት ሽማግሌዎች የሚኖሩበት ነርሲንግ ሆም ሄደን፣ ሰዎቹን ቁጭ ብሎ ማውራት ፣ ከእነሱ ጋር አብሮ ጊዜ ማሳለፍ ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ።
- አገር ቤት ስንሄድ፣ ልጆቻችን እንደ ቱሪስት ጎብኝተው ብቻ እንዲመጡ በማድረግ ፈንታ፣ ለትንሽ ቀንም ቢሆን ሌላን በመርዳት በበጎ አድራጎት ስራ ውስጥ ተሳትፈው እንዲመጡ ማድረግ፤
- የገና በአል ሲመጣ ለራሳቸው ስጦታ ብቻ ማሰብ ሳይሆን፣ ለሌላ የሚሰጡበትንም መንገድ እንዲያስቡ፣ ጊዜ ኀይላቸውን እንዲሰጡ፤ ከምንሰጣቸው የኪስ ገንዘብ ትንሽ አውጥተው ሌላን እንዲረዱ ማበረታታት ወዘተ።

እኛም ጊዜ ወስደን ለልጆቻችን፣ የሕይወት ትርጉም ለራስ ብቻ መኖር እንዳልሆነ ሌላን መርዳት፣ ሌላን መደገፍ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ እንነገራቸው። "እኔ ታምሜ ፣ተቸግሬ ሌላ ሰው መጥቶ ቢረዳኝ ደስ ይላችኋል አይደለምን? ለሌላም ለተቸገረ ለታመመ መርዳት እንዲሁ ያንን ቤተሰብ ደግሞ ደስ ያሰኛል፤ ይባርካል" እያልን፣ እነርሱን በሚገባ መንገድ እናስረዳቸው።

ልጆቻችን በውጭ ብቻ ሳይሆን በቤት ውስጥም፣ ከእኔነት የራቀ ተግባር እንዲማሩ ተግተን እንስራ። የሚፈልጉት ሁሉ እየተደረገላቸው፣ ግን መስጠት ሳይጠበቅባቸው አድገው እኔነትን ወርሰው የሚያድጉ፣ ለስጋ ወንድም እህታቸው እንኳ ከቦታቸው ወጥተው ማድረግን የማይፈልጉ ብዙ ልጆች አሉ። ልጆች በኋላ ሲያድጉ ከወንድም እህታቸው ጋር በፍቅር ከሚያስተሳስራቸው ዋና ነገር፣ በልጅነት የተማሩት እርስ በእርስ የመረዳዳት፣ የመካፈል እና የመተጋገዝ ጸባይ ነው። በወንድምና እህት መሀል ያ ጸባይ እንዲኖር እንጣር። ልጆች ቤት ውስጥ እህታቸውን መርዳት፣ ወንድማቸውን ማገዝ፣ እናት አባታቸውን ማገልገል እንዲማሩ አድርገን እናሳድግ። በቤተሰብ ውስጥ መቀበል ብቻ ሳይሆን መስጠት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ እናስተምር። ልጆቻችንን በምን አይነት የበጎ ስራዎች ልናሳትፍ እንደምንችልና፣

ባጠቃላይ በዚህ ጉዳይ ላይ የተለያዩ ጥሩ ሀሳቦችን የሚሰጠን ድረገጽን ከስር ይመልከቱ:: [18]

- ***<u>በጎ ሥነ ምግባርን ማስተማር</u>***

ውስጡ ተንኮል፣ ቂም፣ ያለበት፣ ስለሌላው መጥፎ የሚያስብ ሰው፣ ከማንም በላይ ራሱ በስቃይ ውስጥ ይኖራል:: በሚኖርበት ህብረተሰብ ውስጥም የልብ ጓደኛ አይኖረውም:: በውስጡም ሰላም አጥቶ ይኖራል፤ ከስጋ ያለፈ ትርጉም ያለው ሕይወትንም ሳያውቅ ያልፋል:: ልጆቻችንን፣ ቅንና ጥሩ ሰዎች እንዲሆኑ አድርገን ስናሳድጋቸው፣ ከማንም በላይ የራሳቸው ሕይወት እንዲለመልም እያበረከትን ነው:: ደስተኛ ይሆናሉ፤ በሰው ዘንድ በጣም የተወደዱ ይሆናሉ:: ለራሳቸውም ለሌላውም ሕይወት በትልቁ የሚያበረክቱ ሰዎች ይሆናሉ:: ልጆቻችን ውስጥ ይህን ዋነኛ ሀብት ማበልጸግ ከፈለግን፣ ከልጅነታቸው ጀምሮ እናስተምር፤ ሰውን ከልብ እንዲወዱ፣ እንዲያከብሩ እናስተምር። ስለ መጥፎና ጥሩ ምግባር ግንዛቤን እንስጥ:: ውሸት፣ ስለ ሌላ ሰው ቁጭ ብሎ ማውራት፣ሌላን ዝቅ ማድረግና ተንኮል፣ እንዴት መጥፎ እንደሆነ እንንገር:: አንድ ነገር አደርጋለሁ ብለው ቃል ከገቡ፣ ቃልን መጠበቅ ምን ያህል አስፈላጊ ምግባር እንደሆነ ከልጅነታቸው እናስተምር::

[18] (ልጆቻችን የበጎ አድራጎት ስራ (volunteer) ሊያደርጉባቸው ስለሚችሉ ስለተለያዩ ቦታዎች ጥሩ ግንዛቤ የሚሰጥ ዌብ ሳይት dosomething.org
ከዛ በተረፈ ኢንተርኔት ጉግል ውስጥ ገብተን ያለንበትን ስቴት፣ ካውንቲ ጽፈን (volunteer opportunity) ብለን ብንጽፍ ልጆቻችን በበጎ አድራጎት ስራ ሊሳተፉባቸው ስለሚችሉ የተለያዩ ቦታዎች ምሪት እናገኛለን።)





ልጆቻችን ሌላን የሚጎዳ ነገር ሲያደርጉ ስናይ፣ "አይ ልጅ ናቸው" ብለን ወይንም፣ "ለልጄ አግዛለሁ" ብለን፣ ዝም አንበላቸው፤ እንደዚያ ስናደርግ የኛኑ ልጆች እንጎዳለንና፤ ውስጣቸውን የሚበላ መጥፎ ትምህርት እንዲነግስ መንገድ እንከፍታለንና:: መጥተው ስለ ሌላ ሰው ሊያሙልን ከፈለጉ፣ በቶሎ ብለን ያንን ምግባር እንቃወም:: "ስለ ሌላ ሰው ማውራት አያስፈልግም፤ የምትነግሩት ነገር ካለ ለዛው ሰው ተናገሩ" ብለን፣ ትምህርት እናስተምራቸው:: እኛ በምናስተምራቸው ትምህርት ምክንያት፣ ወሬን እየጠሉ ይመጣሉ:: እርስ በእርስ ወይ ከሌላ ልጅ ጋር ሲጫወቱ፣ ሌላውን የሚጎዳ ወይ የሚጫን ነገር ሲያደርጉ ወይ ሲናገሩ ካየን፣ በስግብግብነት የሌላን እቃ ሲቀሙ ለኔ ለኔ ሲሉ ከተመለከትን፣ በቶሎ ብለን እናርማቸው፤ የወደፊት ማንነታቸው የሚቀረጸው፣ ዛሬ በሚማሩት ትምህርት ነውና:: ባጠቃላይ፣ ለሌላው ጥሩ እንዲያስቡ፣ እንዲያደርጉ እናስተምር::

እኛ ከምንነግራቸውም በላይም፣ ስናደርግ የሚያዩን ዋነኛ ትምህርት እንደሚሆናቸው እናስታውስ::

- ☞ የቱንም ያህል ሰውን አትሙ ብንላቸው፣ እኛ ቁጭ ብለን ስለ ሌላው ስናወራ እያዩ ካደጉ ወሬን ተምረው ያድጋሉ፤ እነሱም ሲያድጉ ሀሜተኛ እንዲሆኑ በትልቁ ያበረክታል እኛ ምንለውን በልባቸው ቋጥረው አድገው፣ ሰውን ሁሉ ተጠራጣሪ ይሆናሉ::
- ☞ በምሬት ስለሰው ሁሌ ስናወራ ካዩ ምሬተኛ፣ ልባቸውን የዘጉ ሰዎች እንዲሆኑ ያበረክታል::
- ☞ አንድ ነገር አደርጋለሁ ብለን ቃል ገብተንላቸው፣ ምንም ሳይመስለን ቃላችንን የምናጥፍ ከሆነ እነሱም በቃላቸው ጽኑ ያልሆኑ እንደፈለጉት የሚለዋወጡ ይሆናሉ:: በሌላ በኩል፣ አቅቶን ባናደርግ እንኳ፣ "ይቅርታ ተሳስቻለሁ" ብለን ሁኔታውን ካስረዳናቸው፣ ቃልን መጠበቅ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ የተረዱ፣ የነገ ትላልቅ ሰዎች ይሆናሉ::

ባጠቃላይ፣ ወላጅ የሚያሳየው ምሳሌነት የልጅን ምግባር በዋነኝነት እንደሚቀርጽ ተረድተን፣ የእኛንም፣ አረማመዳችንን እንመርምር። ልጆቻችንን እንዲህ በምክርም በተግባርም ስናንጻቸው፣ በፍቅር ያበቡ የደመቁ፣ ቅን የሚያስቡ፣ በሌላውም ዘንድ የተከበሩ፣ የተወደዱ ሰዎች ይሆናሉ።

- ***ልምላሜ በመንፈሳዊ ሕይወት***

ልጆቻቸው በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያብቡ፣ ከእግዚአብሔር ጋር እውነተኛ ትስስር ኖሮዋቸው እንዲያድጉ፣ የሚፈልጉ ብዙ ወላጆች አሉ። በእነዚህ ወላጆች ስር አድገው፣ ከእግዚያብሔር ጋር ትስስራቸው ጠብቆ ለምልሞ የሚኖሩ ልጆች አሉ፤ ከቤት ሲወጡ የእግዚአብሔርን ነገር አታንሱብኝ የሚሉም ልጆች ይኖራሉ።

በዚህ ጉዳይ ላይ ዋነኛ ተጽእኖ ያለው፣ በወላጅ ሕይወት ውስጥ ተፈናጥቆ የሚያዩት ምሳሌነት ነው። እመኑ የምንላቸው እግዚያብሄር፣ በኛ ሕይወት ውስጥ መታየት አለበት። እኛ እግዚአብሔር እግዚአብሔር እያልን እየዋልን፣ ከኛ ውስጥ ግን ዘወትር ሾልኮ የሚወጣው፣ እግዚአብሔር ከሚጠብቅብን ማንነት የተለየ ከሆነ፣ እውነቱን ሳይረዱ ይቀራሉ፤ እውነተኛው የእግዚአብሔር ነገር በእኛ ውስጥ ተፈናጥቆ አይታያቸውምና። ከእግዚአብሔር ጋር እውነተኛ ትስስርን ለማዳበር እየጣርን፣ ስህተታችንን ለማረም እርምጃ እየወሰደን፣ ከእውነት በመነጨ ቅንነት፣ ሌላን ይቅር ማለት፣ ውስጣዊ ሰላምና ፍቅር የምንኖር ከሆነ ግን፣ ያ ሀይል ተፈናጥቆ ለልጆቻችን ትልቅ ምስክርነት ይሆናቸዋል፤ የኛኑ መንገድ መከተልም ይፈልጋሉ።

ከእነርሱ ጋር ባለን አንድ በአንድ ግንኙነትም፣ እንደዛው ነው። ቀን ለሊት ሀይማኖታዊ ልምምድ ስናደርግ ቢያዩ እንኳ፣ ዘወትር ከእኛ ውስጥ የሚወጣው ምሬት እነርሱን መዳኘት፣ መስደብ፣ዝቅ ማድረግ ከሆነ፣ እንዲያውም ጭራሽ እግዚአብሔር ጋር የተያያዘ ነገርን መፍራት ይጀምራሉ። ከእኛ የያዙትን እልህ ከእግዚአብሔር





ጋር አያይዘው፣ "የእነርሱ እግዚአብሔር ጫፌም እንዳይደርስ" ብለው፣ ጭራሽ ጀርባቸውን ይሰጣሉ። ወደ ፊትም ስለ እግዚያብሄር ሲያስቡ ቶሎ ብሎ የሚታያቸው፣ ከእኛ ተፈናጥቆ ያዩት መጥፎ ምሳሌ ይሆናል። ዘወትር ፍቅርን ስናሳያቸው፣ ለማንነታቸው ስናቅፋቸው፣ ስናከብራቸው፣ ደግነትን ደጋግመን ስናሳያቸው፤ ስለ እግዚአብሔር ስንነግራቸውም ልባቸውን ከፍተው ያዳምጣሉ፤ ውስጣቸውን ከፍተው እንዲያዳምጡን የሚያበረታታ ምግባር ከእኛ ውስጥ ተፈናጥቆ ያያሉና።
ሌላው ወላጅ ልብ ማለት ያለበት ነጥብ ይህ ነው። እግዚአብሔርን ከልባቸው እንዲያውቁት፣ የእግዚአብሔር ማንነት ከልብ እንዲገባቸው መንገድ መጠረብ እንጂ፣ በሀይላችን ውስጣቸው ልንወሽቅባቸው አንሞክር። እውነተኛ ማንነቱ እንዲገባቸው፣ ወደፊት አድገው ከቤት ሲወጡም የሚቆይላቸው እምነት በውስጣቸው እንዲሰራ እንጂ፣ እኛን ፈርተው ብቻ እንዲታዘዙ ማድረግ እናቁም። ልጅ ልቡን ከፍቶ እግዚአብሔርን የሚወደው እና የሚቀበለው ውስጡ ሲመሰጥ እንጂ፣ በግድ ካልተከተልክ ሲባል አይደለም። የምንወደውን ምግብ እንኳ "በግድ ብሉ" እያሉ ቢገርፉን፣ ያ ምግብ ሊያስጠላን ይመጣል። እግዚአብሔርን ከልብ እንዲያውቁት ሁኔታዎችን በማመቻቸትና መንገዱን በመክፈት፣ ልጆቻችንን በመርዳት ፈንታ በግድ ጠምዝዘን ከእግዚአብሔር ጋር ተሳሰሩ ብንል፣ ግዴታው አስጨንቋቸው ጭራሽ ይርቃሉ። ሲያድጉም ትዝ የሚላቸው በልጅነታቸው ልናስገድዳቸው የሞከርነው ነውና፣ ጭራሽኑም ዝር ማለት አይፈልጉም።

ልጆች፣ የእግዚአብሔር ማንነቱን፣ በእውነተኛ ሕይወታቸው ውስጥ ሊገባቸው በሚችል መንገድ እንዲረዱት እንዴት መንገድ እንከፍታለን? ቤተሰብ በሳምንት አንድ ቀን ወስነን፣ አብረን ተሰብስበን እግዚያብሄርን እናምልክ፣ ያ ለልጆች የማይረሱትን ትምህርትን ይሰጣቸዋል።ከልጅነታቸው ጀምሮ ስለእግዚአብሔር ስናስተምር፣ እውነቱ እንዳለ ሆኖ፣ ትምህርቱን ለእነርሱ በሚስባቸውና በሚገባቸው፣ መልክ እናቅርበው፤ ለምሳሌ ልናስተምራቸው የምንፈልገውን እውነት ከታሪክ ጋር እያያዝን

ብናቀርበው፣ ሊያዳምጡን የበለጠ እድል ይኖራቸዋል። ልጆች መዝሙር በጣም ይወዳሉና አብረን እግዚያብሄርን እናምልክ።

ከሕይወታቸው ጋር እያያዝን ትምህርትን እናስተምራቸው፤ ሩቅ ያለ፣ እንዲሁ ለአንዴ ጸሎት ብቻ የሚያስታውሱት አምላክ ሳይሆን፣ በየቀኑ ባለ ፈተናቸው፣ እርምጃቸው፣ ጥያቄያቸው እንዴት ሊረዳቸው እንደሚችል፣ ጊዜ ወስደን ለልጆቻችን እናስረዳ። ጊዜያችንን ወስደን ማስረዳት ብቻ ሳይሆን ጥያቄያቸውን እንመልስ። ማንም ሊረዳቸው በማይችልባቸው ሁኔታዎች እግዚያብሄር ግን ሁልጊዜ አብሯቸው እንደሚሆን እንንገር። እሱ እንደሰው ውጫቸውን አይቶ እንደማይዳኛቸው፣ በተፈጥሮ ማንነታቸው ከልብ እንደሚወዳቸው፣ ለልጆቻችን እናስተምር። ሕይወታቸው ትርጉም ያላት፣ ያበበች እንድትሆን፣እግዚአብሔር እንደሚረዳቸው ደግመን ደጋግመን እንንገራቸው። ልጆቻችን ስላላቸው ህልምና ፍላጎት እንጠይቅ፤ አብበው ፈክተው እንዲወጡ ከራሳቸውም አልፈው ለሌላም የሚሆን ትልቅ ፍሬ እንዲያፈሩ እግዚአብሔር እንደሚረዳቸው እናስተምር። ከልጅነታቸው አንሥቶ በችሎታ በእውቀታቸው፣ በጊዜያቸው ሌላን ማገልገል እንዲማሩ እናድርግ፤ ከስጋ ያለፈው የእግዚአብሔር ትልቁ አላማ እንዲገባቸው መንገድ ይከፍታልና።

ስለ እግዚአብሔር ትምህርት የሚያገኙበት ቦታም፣ ለልጆች በሚስማማ ሊያዳምጡት በሚችሉት መንገድ ትምህርቱ እንዲተላለፍላቸው፣ ሀሳብን እናቅርብ፤ እኛም ሀሳብን መስጠት ብቻ ሳይሆን የእውቀትና የጊዜን እርዳታን እንለግስ፤ ከሌሎች ወላጆችም ጋር እጅ ለእጅ እንያያዝ።ልጆቻችን እግዚአብሔርን ከልብ እንዲያውቁት መንገዱ ሲመቻችላቸው፣ ሰው ለቅርብ ወዳጅ ልቡን እንደሚከፍተው፣እግዚአብሔርን ከልብ መቅረብ ይጀምራሉ፤ ወላጅ በሌለበትም፣ በራሳቸው ባዳበሩት ትስስር ጠንክረው ጉዞዋቸውን ከእግዚአብሔር ጋር ይቀጥላሉ።





- ***በራስ መተማመን***

ልጆቻችን ሌላን በደበና የሚከተሉ የሌላ ግልባጭ በመሆን ፋንታ፣ በማንነታቸው የሚቆሙ፣ ራሳቸውን መሆን የማይፈሩ ሰዎች መሆናቸው፣ ሌላው በጣም አስፈላጊ ምጥቀት ነው። ይህ በውስጣቸው የተሰራው ማንነት፣በሕይወታቸው ለሚገጥሟቸው ለተለያዩ ግፊቶች መከላከያ ከመሆኑም በላይ፣ ለየት ወዳለ ቦታ እንዲመጥቁ ትልቅ እርዳታ ይሰጣቸዋል።

ብዙ ልጆች፣ የተፈጥሮ እውነተኛ ማንነታቸው ከስር ተወሽቆ፣ የሌላ ግልባጭ፣ ተከታይ ሆነው ያድጋሉ። ይህ በተለይ በእኛ ባህል ውስጥ ለሚያድጉ ልጆች ዋነኛ ፈተና ሊሆን ይችላል፤ ልክ ሌላን መምሰል እንዳለብንና ሌላው እንዳደረገው ማድረግ እንዳለብን የሚጠብቅብን የማህበረሰብ ግፊት አለና። አንዳንዴም ወላጆች ሳናስበው፣ የራሳችንን ፍርሀት በቀላሉ ወደ ልጆቻችን ልናስተላልፍ፣ እንችላለን። ሁሌ ከሌላ ሰው ልጅ ጋር ካስተያየናቸው፣ "የነእገሌ እገሊት ልጆች እንደዚህ እንደዛ ናቸው እናንተ እንደዚህ አይደላችሁም" ብለን የምንደጋግምባቸው ከሆነ፣ "የሌላው ቤተሰብ እንዲህ ሞልቶለት የኛ ይህ ጎደለው" ብለን ስናወራ እየሰሙ ካደጉ፣ በውጥረትና ፍርሀት ሌላ ሰውን ሲመለከቱ የሚኖሩ፣ ሌላውን ለመገልበጥ ሲሯሯጡ የሚኖሩ ሰዎች ይሆናሉ። ይህ ጸባይ አብሮዋቸው ካደገም በኋላ፣ ዋነኛ የሕይወት ግባቸው፣ ሌላን መመሰጥ፣ለሰው አስመሳይ ስእል መሳል ብቻ ሆኖ ይቀራል።

ልጆቻችን የራሳቸው በሆነው እውነተኛ ማንነታቸው ውስጥ እንዲኖሩ አድርገን እናሳድግ። በራሳቸው ማንነት ይደጉ ማለት፣ "ለሰው መጨነቅ ካቆምን ቆይተናል"፣ የሚል መልእክትን ሊልክ የሚሞክር፣ የውጭ ሀይለኝነትና አላስፈላጊ ድፍረት፣ ማለት አይደለም፤ እውነተኛ ነጻነት ማለት በማንነት ሳያፍሩ፣ "ሌላ ምን አለኝ" ብለው ቀን ሌሊት ሳይወጠሩ፣ በውስጣዊ ሰላምና

እረፍት መኖር ማለት ነው። ልጆቻችን ከውስጣዊ እስራትና ፍርሀት፣ ነጻ የሆኑ ሰዎች እንዲሆኑ አድርገን እናሳድግ።

- ☞ ሌላን በጎን ሲመለከቱ መኖር እስራት እንደሆነ እንንገር።
- ☞ ሌላ ሰው ስላደረገው ብቻ አንድ ነገር ትክክል ነው ማለት አይደለም፤ ጠንክራችሁ ከሰራችሁ በራሳችሁ መንገድ ማበብ ትችላላችሁ፤ እንበላቸው።
- ☞ ከሌላ በመማር መሀልና ሌላን በመገልበጥ መሀል ትልቅ ልዩነት እንዳለ፣ ሌላን ሊመስጡ እየሞከሩ መኖር እስራት እንደሆነ እናሳውቃቸው።
- ☞ በሕይወት ውስጥ ለየት ላለ ነገር የተነሱ፣ አዲስ ነገር የሰሩ የፈጠሩ ሰዎች፤ ራሳቸውን መሆን ያልፈሩ፣ ሌላን ለመገልበጥ የማይጥሩ ሰዎች እንደሆኑ እንንገር፤ በምሳሌነታችንም ጠቃሚውን ትምህርት ወደእነሱ እናስተላልፍ።

ልጆቻችን ለየት ብለው መቆምን እንዳይፈሩ ስንፈልግ፣ ከጅምላ አስተሳሰብ ለመውጣት የማይፈሩ፣የራሳቸው ህልም ራእይ ያላቸው ሰዎች ጋር እናገናኛቸው፤ ከእነዚህ ዐይነት ሰዎች ጋር ቁጭ ብለው እንዲያወሩ እናድርግ። እነዚህ ሰዎች አንድ ለአንድ የማናውቃቸው ከሆኑ፤ንግግር የሚያደርጉበት ቦታ ልጆቻችንን ይዘን እንሂድ፤ እነሱ የጻፉትን መጽሀፍ፣ የቀረጹትን ቪዲዮ፣ እናሳይ፤ እነዚህ ሰዎች ለልጆቻችን ምሳሌ ሊሆኗቸው፣ ራስን ችሎ ማሰብ ምን ማለት እንደሆነ በተግባር ሊያስተምሯቸው ይችላሉና።





## የሕይወት ተሞክሮ



### ሐና ጎዲፋ

ሐና ለየት ብለው ከተነሱና፣ በአላማ፣ ህልማቸው ከመጠቁ ልጆች መሐል አንዷ ናት፡ በትንሽ እድሜዋ፣ ብዙዎችን ያስገረመ አስተዋጽኦ ለህዝቧ አበርክታለች። ከሐና ጋር የተደረገው ቃለ መጠይቅ እነሆ።

- ➢ እስቲ ስለራስሽ ትንሽ ንገሪን?

ሀና ጎዲፋ እባላለሁ፤ እድሜዬ 14 ነው። ተወልጄ ያደግኩት ካናዳ ውስጥ ነው። የምኖረው ከአባቴ፣ ከእናቴና ከታናሽ ወንድሜ ጋር ነው።

- ➢ ህልምሽ በውስጥሽ እንዴት እንደተጠነሰሰ፣ እስቲ ከመጀመሪያው ንገሪን?

ኢትዮጵያ መጀመርያ ስሄድ የዘጠኝ አመት ልጅ ነበርኩ:: አገር ቤት ሄጄ፣ ባህሌንና ዘመዶቼን ሳይ በጣም ደስታ ተሰማኝ:: ወላጆቼ ዘመድ ጥየቃ ገጠር ይዘውኝ ሄዱ:: እዛ አንዲት ጓደኛ አግኝቼ ደስ አለኝ፤ ከሷ ጋራም በጣም ተቀራረብን:: ወደ አሜሪካ መመለሻችን ሲደርስ፣ ዘመዶቼንና ጓደኛዬን ልለይ ስለሆነ፣ በጣም ቅር አለኝ፤ ለአባቴ፣ "ከሷ ጋር በደብዳቤ መጻጻፍ (pen pal) መሆን እችላለሁ ወይ" ብዬ ጠየቅኩት:: አባቴም፣ እዛ አካባቢ ያሉ ልጆች በጣም በድህነት እንዳሉ፣ መጻፍያ እርሳስም እንደማያገኙ ነገረኝ፤ ይህን ስሰማ በጣም ሀዘን ተሰማኝ:: ጓደኛዬንም ሆነ እንደሷ ያሉትን ሌሎቹንም ልጆች ለመርዳት ውስጤ ተነሳሳ:: ካናዳ መጥቼ፣ ትምህርት ቤትም ሆነ ከሌላ ቦታዎችም የእርሳሶችን እርዳታ ለማግኘት ጥረት ማድረግ ጀመርኩ::

➢ እነዚህን እርሳሶች ለመሰብሰብ በምትሞክሪበት ሰአት፣ ያጋጠመሽ ሁናቴ ምን ይመሥል ነበር?

እንዳሰብኩት ቀላል አልነበረም፤ ከብዙ ቦታዎች የእንቢታ መልስን አገኝ ነበር፤ ግን ተስፋ ሳልቆርጥ በየቦታው እየሄድኩ፣ ሀሳቤን አቀርብ ነበር፤ ብዙ ልጆች መማር፣ መጻፍ እየፈለጉ ግን በእርሳስ እጦት ምክንያት መጻፍን ሳይማሩ እንደሚቀሩም፣ ለእነዚህ ልጆች መጻፊያ እርሳስ መላኩ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ፣ ሀሳቤን እገልጥ ነበር

➢ በዛ ጊዜ የሥንት አመት ልጅ ነበርሽ? እቅድሽ ምን ያህል እርሳስ ለመሰብሰብ ነበር?

ዘጠኝ አመቴ ነበር:: እቅዴ፣ 20 ሺ እርሳሶችን ለመሰብሰብ ነበር:: ከብዙ ጥረትና የቤተሰብ እርዳታ በኋላ ግን፣ 25 ሺህ እርሳሶችን መሰብሰብ ቻልኩኝ ያንንም ይዤ ወደ አገር ቤት ሄድኩ::





➢ እዛ ስትደርሽ ምን ተሰማሽ?

ያንን የሰበሰብኩትን 25 ሺህ እርሳስ ይዤ፣ አገር ቤት ስሄድ፣ በውስጤ የተሰማኝን የደስታና የእርካታ ስሜት በቃላት መግለጽ ያቅተኛል፤ ልጆቹ እርሳሶቹን ሲያዩ፣ ምን ያህል እንደተደሰቱ ሳይ፣ እኔም የእነሱ ደስታ ተጋባብኝ:: የብዙ ሰዎችን ድጋፍና ማበረታቻም ቃላት ማግኘቴ ተጨማሪ ሀይል ነበር:: እርሳሱንም አስረክቤ ወደ ካናዳ ተመለስኩ::

➢ የሚቀጥለው የሕይወትሽ ምእራፍ ምን ይመስል ነበር?

ከተመለስኩ በኋላ፣ የረዳኋቸውን ልጆች ጨምሬ ሌሎችንም ለመርዳት የነበረኝ ፍላጎት የበለጠ ጨመረ:: በዚህ በሁለተኛው ጊዜ 200 ሺህ እርሳስ ለመሰብሰብም ዕቅድን አወጣሁ:: የተለያዩ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ የህብረተሰብ ማእከሎች፣ ኮምፓኒዎች፣ ቤተክርስትያኖች እየሄድኩ፣ ስለአላማዬ እናገር፣ ነበር፤ በተለያየ መንገድ እርዳታንም ለማግኘት መጣር ቀጠልሁ:: ከብዙ ጥረት በኋላ ህልሜ ተሳካ:: ቀድሞ ካቀድኩት 200 ሺህ ይበልጥ 400 ሺህ እርሳሶችን መሰብሰብ ቻልኩ:: እነዚህን 400 ሺህ እርሳሶች እንዴት እልካለሁ የሚለው ሌላው ጥያቄ ነበር::የኢትዮጵያን ኤርላይንስ በማጓጓዙ ወጪ እንዲረዱን ጠየቅን፤ ከብዙ ሙከራ በኋላ፣ የኢትዮጵያን ኤርላይንስን ድጋፍ ለማግኘት ቻልኩ:: (2000 ኪሎ ግራም) የሚመዝኑ 50 ትላልቅ ሳጥኖች በነጻ ሊያጓጉዙልኝ ተስማሙ፤ ለሰጡኝ ድጋፍም ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነበር:: እኔም በ 13 አመቴ፣ ተመልሼ ወደ ኢትዮጵያ ሄድኩ:: አገር ቤትም ሚድያው ተባበረኝ፤ የትምህርት ሚኒስትር እርሳሶቼን በማሰረጫጨት ረዳኝ::

➢ የተሰማሽ ደስታ ወሰን የሌለው እንደነበር መገመት አያቅትም::

አዎ፣ ለኔ ትልቁ ስጦታ፣ የልጆቹን ደስታና የመነቃቃት ስሜት ማየቱ ነበር:: ልጆቹ የመማርና ትልቅ ቦታ የመድረስ ፍላጎት እንዳላቸውም ይነግሩኝ ነበር:: "ወደ ፊት ስናድግ እኛም፣ ዶክተር፣ ጠበቃ እንሆናለን፣" ብለው ስለ ህልማቸውም ይነግሩኝ ነበር:: ልጆቹ ያላቸውን መነቃቃትና ህልም ሳይ፣ እነዚህን እርሳሶች ሲያዩ የተሰማቸውን ደስታም ስመለከት፣ ልፋቴ ሁሉ ዋጋ እንደነበረው ተሰማኝ

> ➢ ባሁኑ ሰአት ስለወደፊቱ ስታስቢ፣ ምን ይሰማሻል?

በዚህ ሰአት፣ በውስጤ የበለጠ መነቃቃት እና በአገሬ ባህሌ ኩራት ይሰማኛል:: ኢትዩጵያ የወደፊት ተስፋዋ የበራ ነው:: እግዚያብሄር፣ በኢትዮጵያ ላይ ትልቅ አላማ እንዳለውም ይሰማኛል፤ ላገሬና ለህዝቤ በቻልኩት ለማበርከት ውስጣዊ አላማ አለኝ:: ልጆችንና ትምህርታቸውን በተመለከተ፣ ብዙ ማበርከት እፈልጋለሁ:: በተለይ፣ ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ጋ በተያያዘ፣ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችንና ዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን የሚረዳ ነገር ማበረከት እፈልጋለሁ::

> ➢ በትንሽነት እድሜሽ፣ እንዲህ ለህዝብሽ እንድታበረክቺ ተጽእኖ ያደረገብሽ ምንድነው?

ከውስጤ፣ እንድገፋ የሚያበረታታኝ በዋነኘነት የእግዚያብሄር ድጋፍና ምሪት ነው:: ቤተሰቦቼም፣ ሩቅ ቦታ እንዳልም፣ ለህዝቤ እንዳበረክት በትልቁ አስተዋጽኦ አድርገዋል:: ለሌላው ማድረግ፣ ሌላን በቻልኩት መርዳት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ፣ ከልጅነቴ ጀምሮ ይነግሩኝ ነበር:: ህዝቤን እንድወድና ትልቅ ቦታ እንዳስብም ያበረታቱኝ ነበር:: ሳድግ፣ ቤታችን ሁሌ ፍቅር ነበር፤ አባትና እናቴ ያሳዩኝ ፍቅር፣ ለኔ ትልቅ ድጋፍ ሆኖልኛል:: አባቴ ከኛ ጋ ጊዜ ለማሳለፍ ብሎ፣ (እናቴ ትሰራ ስለነበር) ስራውን ሰአት ቀንሶ ፣ ጊዜውን ለኛ ይሰጥ ነበር:: ባጠቃላይ፣ እናትና አባቴ ምንም እንከን የማይወጣላቸው ጥሩ ወላጆች ናቸው ብል ውሸት አይሆንም::



ልጅን እንዴት ላሳድግ? በምዕራብ አገሮች

ሐና ለበጎ ስራዋና ድርጊቷ፣ ከተቀበለቻቸው ብዙ ሽልማቶች መካከል፤ Vaughan Volunteer Award; 2009, Recognition from members of parliament of Don Valley, Young diplomats for humanitarian, Awards for Regional council of Vaughan, Nominated for International peace price for children; 2012, Nominated for June callwood outstanding Award for Volunteerism 20011; Humanitarian of the year, Ethiopia 2007, ይገኙበታል፤

## ከሐና አባት፣ አቶ ጎዲፍ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ

- አቶ ጎዲፉ፣ ልጅን ጥሩ አድርጎ ማሳደግን በተመለከተ፣ ለሌሎች ወላጆች የሚሰጡት ምክር አለ ወይ?
  ከሁሉ በፊት እግዚያብሄርን ማስቀደም፣ ለቤተሰብ ሰላምና ደስታ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል ብዬ አምናለሁ:: ሐና ሳትጸልይ ትምህርት ቤት ሄዳ አታውቅም፤ ሐና ጠዋት ጠዋት ሳትጸልይ ወጥታ አታውቅም፤ ይህ፣ በውስጧ ትልቅ እምነትንና ጥንካሬን ፈጥሮላታል ብዬ አምናለሁ:: ሩቅ ቦታ እንድታስብ፣ ለሌሎች ወጣቶችም መካሪ እንድትሆን፣ የህይወት ዋነኛ ዋጋዋ ውጫዊ ሀብት እንዳይደለ እንድታውቅ ረድቷቷል:: ደጋግሜም የምመክራት እግዚያብሔርን በሁሉ ነገር እንድታስቀድም ነው
- አባትና እናት ግልጽ የሆነ የንግግር ልውውጥ፣ ከልጃቸው ጋር መኖራቸው በጣም አስፈላጊ ነው ብዬ አምናለሁ:: እንደዛ ከሆነ፣ ልጅም ግልጽ መሆንን ይማራል፤ ከናትና ካባቱ የሚደብቀው ነገር አይኖርም

- ለልጅ ፍቅርን ማሳየት በጣም አስፈላጊ ነው። ልጆችን በፍቅር ስናሳድጋቸው፣ ፍቅራችንን በግልጽ ስናሳያቸው፣ ከወላጅ ጋር ትስስር ይኖራቸዋል።ምክር ሲያስፈልጋቸው ወላጅ ጋር ይመጣሉ፤ወደውጭ አይሄዱም። ከዚህ ጋር ተያይዞ፣ ከልጅ ጋር አብሮ ማሳለፍ በጣም ይጠቅማል።
- ልጆች የወላጆቻቸው ነጸብራቅ ይሆናሉ። አባት እናት በልጆቻቸው ፊት መከባበር፣ ባል ሚስቱን ማክበር፣ ሚስት ባሏን ማክበር በጣም አስፈላጊ ነው። ሀናን፣ "ከናትና ካባትሽ ማንን ትወጃለሽ" ብትያት፣ ሁለቱንም ነው የምትልሽ፣ ሁለታችንንም እንድታከብር እንድትወድ እንጂ፣ አንዳችንን ካንዳችን እንድትመርጥ አድርገን አላሳደግናትም። ወላጆች ቤት ውስጥ ስምምነት ካጡ፣ ልጆች ውጭ ይወጣሉ፤ ወደ መጥፎ ነገርም ይሄዳሉ።
- ሰውን መውደድ እንዳለብን ሁሉ ሰው የእግዚያብሄር ልጅ ስለሆነ፣ ሌላን ማክበር እንዳለብን፣ ለልጆቻችን ልናስተምር ይገባናል። ሌላን ሰው ስለማገልገል፣ ወላጅ በምሳሌነት ማስተማር አለበት። ሁሌ ለራሴ ምን ላድርግ በማለት ፋንታ፣ ለሌላስ ምን ላድርግ እንዲሉ አድርገን ማሳደግ አለብን። እኔ እራሴ፣ ለብዙ አመታት፣ በየሳምንቱ ቅዳሜና እሁድ፣ በነጻ አገልግሎት ስራ ተሰማርቻለሁ፤ የእርዳታ ኮምፓኒዪ፣ በነጻ የሚሰጠውን ዳቦ እየወሰድኩ፣ ለኢትዩጵያኖች ስደተኞች አድላለሁ። ሐና፣ ከህጻንነቷ ጀምሮ፣ ከኔ ጋ አብራ እየመጣች ያንን ታይ ነበር እሷም አብራኝ ታገለግል ነበር። ይህ በልጅነቷ ያየችው ሌላን የማገልገል ልምድ፣ በውስጧ መሰረት እንደሰራ አምናለሁ። አሁንም ቢሆን፣ አባት እናት የሌላቸው ልጆች ጋ ሄዳ፣ በነጻ ታገለግላለች፤ እሁድ





እሁድም ቤተክርስትያን የልጆች ትምህርት ማስተማር ውስጥ ትሳተፋለች።

- ልጆች፣ መጸሀፍ የማንበብ ልምድ እንዲኖራቸው መጣሩ በጣም አስፈላጊ ነው ብዬ አምናለሁ። ሐና መጸሀፍ በጣም ታነባለች፤የሌላ አገር ሰዎች፣ ልጆቻቸው የማንበብ ልምድ እንዲኖራቸው የተቻላቸውን ይጥራሉ። ለምሳሌ ስሪላንካዎች፣ ቋንቋ እንኳን ባይለምዱ ልጆቻቸውን ላይብረሪ ሁሌ እየወሰዱ ያስነብባሉ እኛ ቋንቋውን ብዙ ባንችል እንኳ፣ እዛ ያሉ ላይብረሪ የሚሰሩ ልጆቻችንን በማንበብ ሊረዱልን የሚችሉ ሰዎች ካሉ መጠየቅ አስፈላጊ ነው።
- ልጆቻችን ሌላን በጭፍን ተከታይ እንዳይሆኑ፣ የራሳቸውን አይምሮ እንዲከተሉ አድርጎ ማሳደግ ተገቢ ነው። ሥራ ስናስቀጥራቸው ማክዶናልድ፣ በርገር ቤት ብቻ ማድረጉን ትተን፣ ሆስፒታል አካባቢ ላይብረሪ፣ በነጻ እንኳ እንዲሰሩ ብናደርግ፣ ትላልቅ ህልም እንዲቀረጽባቸው ያበረክታል።

# ልጆቻችን ከህብረተሰብ ጋር ያላቸው ግንኙነት

የልጆቻችን ትልቅ ቦታ ማሰብና፣ ወደ ትልቅ ቦታ ማነጣጠር ላይ ተጽእኖ የሚያደርገው፣ በቤት ውስጥ ከእኛ ጋር ያላቸው ግንኙነት ብቻ አይደለም። ከውጭ ከህብረተሰብ የሚመጣውን ግፊት የሚቋቋሙበት መንገድ፣ ለእነርሱ ማበብ ወይ መጠውለግ ትልቅ ድርሻ ያበረክታል። ሴትና ወንዶች ልጆቻችን አንድ አይነትም፣ የተለያየም ጫና አለባቸው። የሚመጣላቸውን መልእክት፣ የሚደርስባቸውን ጫና ተረድተን፣ በእዛ ላይ የምንሰጣቸው ድጋፍ፣ትምህርትና ንቃት፣ ለእነሱ ምጥቀትና ልምላሜ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

## *ሴት ልጆችን በተመለከተ ሊሰጥ የሚገባው ምክር*

ሴቶች ልጆቻችን በተለይ እያደጉ ሲመጡ፣ የሚገጥማቸው ዋነኛ ፈተና አለ። በሴትነታቸው ሊወስናቸው የሚሞክር፣ ምን መሆን እንዴት ማሰብ እንዳለባቸው በየቀኑ የሚያስታውሳቸው መልእክት አለ።

> "በቅርቡ የወጡ ምርምሮች በቋሚነት የሚያሳዩት አንድ እውነት አለ። በምዕራቡ አለም ውስጥ ያሉ በውጩ ሲታዩ ሁሉ የተሟላላቸው የሚመስሉ ብዙ ሴቶች ነጻነታቸውን የሚሰልብ ውስጣዊ እስር አለባቸው። ይህ ውስጣዊ እስራት ፤ ሁሉን ነገር በመልክ ዙርያ ማየት፣ ራስን መጥላት፣ እርጅናን እንደ ጦር መፍራት እና መጨረሻዬ ምን ይሆናል በሚል ፍርሀት ውስጥ መኖር ነው።"[19]

እርግጥ ነው፤ ሴቶችን ለማንቃት፣ ወደፊት እንዲራመዱ ለመርዳት የሚያስችል ብዙ ስራ በዚ ሕብረተሰብ ውስጥ ተሰርቷል። አዎ፤ አሁን ሴቶች ልጆቻችንን በቀጥታ አስገድዶ

[19] Wolf Liz (1992) The beauty myth; How images of beauty are used against women publisher--Anchor





"በሴትነታችሁ እዚ ቦታ ተወስናችሁ ትቀራላችሁ" የሚላቸው ሀይል ላይኖር ይችላል። በዚያው መጠን ግን፣ ሴቶች ልጆቻችንን ዝቅ ሊያደርግ፣ ሊወስን የሚሞክር፣ ከውጭ የሚመጣ ሀይለኛ የአእምሮ ጫና አለ። ያም ጫና፣ መልክና ቅርጻቸው በሕይወታቸው ውስጥ ዋነኝነት ቦታ እንደያዘ፣ የሚያስታውሳቸው መልእክት ነው። የመገናኛ ብዙነን፣ መጽሄቱ ዝቅ የሚያደርግ መልእክቱን በየቀኑ ወደ ጆሮዋቸው ይልከዋል። በሴትነታቸው ዋጋ የሚኖራቸው፣ እንዲህ ሲለብሱ፣ ይህን ያህል ሲቀጥኑ እና እንዲህ አይነት መልክ ሲኖራቸው ብቻ እንደሆነ ይወተውታቸዋል። በእድገታቸውና በምጥቀታቸው ላይ አእምሮዋቸው ምንም ቦታ እንደሌለው፣ አሻንጉሊት መስለው መቆማቸው ከሁሉ እንደሚበልጥና ትልቅ ቦታ የሚያደርሳቸውም፣ ያ እንደሆነ፣ አድርጎ ሊመስጣቸው ይሞክራል።

በአሜሪካና በብዙ ምእራባውያን አገሮች፣ የመገናኛ ብዙነን ትልቅ ሀይል አለው። የሰውን አእምሮ በራሱ ፍላጎት ለመቅረጽም የሚረዳው የገንዘብም ሆነ የሰው ኀይል አለው። ለገበያ የሚወጡት እቃዎች፣ ጌጣጌጦችና ልብሶችን ለመሸጥ ብዙውን ጊዜ ሴት ልጆች ዋነኛ መጠቀሚያዎች ናቸው።

> "የልጆችን ገበያ ለማግኘት/ልጆችን ለመሳብ የሚሰሩት እነዚህ ማስታወቂያዎች (አድቨርታይዝመንት) መልእክታቸውን ለማስተላለፍ፣ በአመት 15 ቢሊዮን ብር በላይ ያወጣሉ ። አንድ ልጅ በአማካይ፣ በአመት ከ 40 ሺ በላይ የ ቴሌቪዥን ማስታወቂያዎችን ያያል ተብሎ ይገመታል።"[20]

በሌላ አነጋገር፣ የሴት ልጃችን የወገቧ ቅርጽ፣ ባቷ፣ አጠቃላይ ሰውነቷና ውበቷ፣ ለገበያ ማሻሻጫ ይውላል። በዚህም ቀን ከቀን በሚላክ የሚዲያ እና የህብረተሰብ መልእክት ምክንያት፣ የሴት ልጃችን አላማዋ፣ ህልሟ፣ አስተሳሰቧና አመለካከቷ ውስን ሆኖ

[20] Rigby Jill (2008) Raising unselfish children in a self absorbed world, Howard books.

ሊቀር ይችላል:: በሚጎርፍላት አሳሳች መልእክት ተመስጣ፣ "የኔ ማንነቴን ገላጩ ጸጉሬ ነው"፣ ብላ ተወስና ልታስብ ትችላለች:: በቴሌቭዥንና በመጽሔት ላይ በየቀኑ የምታየውን የውሸት ምስሎች እያጤነች፣ "እኔ እንደዚህ አልሆንኩም" ብላ መጨነቅ ትጀምራለች:: ለስንት ቁም ነገር ሊደርሱ የተጠሩ፣ ለሌላውም ብርሀን ሊሆኑ የሚችሉት ሴቶች ልጆቻችን ሳያስቡት፣ ቀን ከሌት የወገብ አጥንትን መለካት፣ ራስን ከሌላ ሴት ጋር ሲያወዳድሩ መዋል፣ የሕይወት ግባቸው ሆኖ ይቀራል:: በዚህ የአእምሮ ጫና ምክንያት ልጃችን በውስጧ የተቀመጠው እውቀቷ፣ ህልሟና ማንነቷ እየተሸረሸረ ይሄዳል::

ማንነቴ መልኬ ብቻ አይደለም ብላ የምታስብ፣ ውስጧ የታደሰ ሴት ልጅ ማሳደግ የምንፈልግ ከሆነ፣ ከመልክና ቅርጽ ህልም አልፋ የምታስብ፣ የነገ መሀንዲስ፣ ሳይንቲስት፣ ደራሲ፣ አስተማሪ፣ ነርስ፤ በተለያየ መልክ ህዝብን ደራሽ ለመሆን የምታነጣጥር ልጅን ማሳደግ የምንፈልግ ከሆነ፣ ከምንም በፊት የዚህን አሉታዊ ግፊት ጎታችነት እንረዳ:: አእምሮ ላይ የሚደረግ ጫና ትልቅ ሀይል እንዳለው እንረዳ፤ ለሴት ልጃችን አስፈላጊውን እርዳታና ድጋፍ ልንሰጣት የምንችለው ያለባትን ግፊት ጥልቀት ስንረዳ ነውና::

ልጃችንን ለመርዳት ምን ማድረግ እንችላለን? ከመልኳ በላይ እንድታስብ አድርገን እናሳድጋት:: እኛ ሴት ነች ብለን ሳንለያት ከልጅነቷ ጀምሮ፣ ከወንድሞቿ እኩል ትልቅ ቦታ እንደምትደርስ አድርገን እናስባት፤ እናውራትም:: "በሕይወትሽ ምን ደረጃ መድረስ ትፈልጊያለሽ"? እያልን እንጠይቃት፤እሆናለሁ ብላ ለምታምንበት ነገር ቦታ እንዳለም እናሳያት:: አስተሳሰቧ በሕይወቷ ላይ ትልቅ ቦታ እንዳለው እናስተምራት::

የሴት ልጅ ዋጋዋ መልኳ ነው በሚል መልእክቱ ሊመስጣት የሚሞክረውን የሚድያ ድምጽ እንዳታምን እናስተምር:: የመገናኛ ብዙኀን የእውነት ስእልን እንደማይወክሉ ከልጅነቷ ጀምሮ እንንገራት:: በቴሌቭዥን ተዘውትረው የሚታዩት፣ እንከን የለሽ መስለው የሚቀርቡት ሴቶች እውነተኛውን የሴቶች ስእል





እንደማይወክሉ ለልጃችን ግንዛቤን እንስጥ:: ለካሜራ ብቁ እንዲሆኑ፣ ብዙ ጥረትና ጊዜ ተፈጅቶባቸው እንደሚቀርቡ፣ ይህ በእውነተኛ ሴቶችን የሚወክል ስእል እንዳልሆነ እንንገር። ለትልቅ ቁም ነገር የበቁ ፣ አለምን ለመለወጥ የሚሰሩ፣ ሴቶች መልካቸውና ልብሳቸውን ማስዋብ ላይ ብቻ እንደማይጠመዱ እናስታውሳት:: በዘመናችን በተለያየ ቅርንጫፍ ውስጥ አብበው የወጡ፣ ታሪክን የለወጡ የሴቶች ምሳሌዎች፣ ታሪካቸውን እንንገራት:: ያለሙት ትልቅ ቦታ ስለደረሱ ሴቶች የሚተርክ መጽሀፍ ገዝተን ለሴት ልጃችን እናበርክት:: ይህ ትምህርት፣ የመገናኛው ብዙኀን ከሚያቀርብላት ህልማዊ ትረካ አልፋ፣ አርቃ እንድታይ ይረዳታል:: ምሳሌ አስተማሪዋ ሊሆኑ ከሚችሉ ሴቶች ጋር እናስተዋውቃት፤ "እኔም እንደ እነርሱ ልሆን እችላለሁ" ብላ ነገሮችን በአዲስ መልክ እንድትመለከት አስተዋጽኦ ያደርጋልና::

እኛም፣ የሴት ልጃችን መልኳን ዋነኛ ቦታ ከመስጠት እንቆጠብ:: "ቆንጆ" ነች የምትባል ልጅ ካለችን፣ "ልጄ ቆንጆ ነሽ" ከማለት አልፈን፣ የመልኳን ጉዳይ የንግግር ርዕስ አናድርገው:: ውበቷ ላይ ብዙ ካተኮርን፣ እሷም "ዋና ሀብቴ መልኬ ነው" ብላ ተመስጣ፣ ሌላው ማንነቷን፣ ቁም ነገሯን፣ ወደ ጎን ልታደርግ ትችላለችና፤ አእምሮዋቸውንና ውስጣዊ ማንነታቸውን የሚያስቀድሙት እኩዮቿ ነገ መጥቀው ሲነሱ፣ እሷ ከመልክ ፍቅር ጋር ብቻ እንዳትቀር ካሁኑ መጠንቀቅ በጄ ነው::

ልጃችን ሙገሳ ደጋግማ እንደምትሰማ ካስተዋልን፣ እኛም እናነጋግራት:: መልኳ ዋነኛ የማንነቷ ገላጭ እንዳልሆነ፣ ከመልኳ በላይ እንደሆነች እናስታውሳት:: "መልክሽን መውደድ ጥሩ ነው ግን ዋነኛ ማንነትሽ፣ መግለጫሽ መሆን የለበትም" ብለን እናናግራት:: ባንድ ወቅት በቁንጅናቸው ተጋነው የቀርቡ የቆንጆ የሴት ተዋናይ፣ ዘፋኞች የልጅነት እድሜያቸው ሲያልፍ፣ መልካቸው ሲለወጥ፣ ያ ሁሉ የተጋነነ ሙገሳና ክብር አብሮ እንደሚጠፋ እንንገራት:: "አብሮሽ በሚቆየው ውስጣዊ ማንነትሽ ላይ ማተኮርሽ ለወደፊቱም ይጠቅምሻል" ብለን፣ ለልጃችን እናስተምራት:: እዚህ

ጋር፣ እኛ አናሞግሳት ለማለት አይደለም:: በተገቢው መልክ ልጃችንን ማሞገስ ጥሩ ነው:: ብዙ ሴት ልጆች በተፈጥሮዋቸው ራሳቸውን ማሳመር ማስዋብ ይወዳሉ፤ ያም በራሱ ጥፋት የለውም:: ማንነቷን ገላጩ መልኳ ነው ብላ እንዳታስብ የሚረዳትን ግንዛቤ መስጠቱ፣ያ ነው ዋናው ነገር:: ከዚህ ጋር ተያይዞ፣ የሴት ልጅን መልክና ቅርጽ ላይ ብቻ የሚያተኩሩ፣ እንደዋነኝነት አድርገው የሚያወጡ መጽሄቶችን፣ ከቤታችን እናስወግድ:: እነዚህ ስእሎች ለልጃችን እውነታዊ ያልሆነ ጎጂ መልእክት ይልኩላታልና::

በሌላ መልኩ፣ ልጃችንን የሚጎዳ ነገር ከመናገር እንቆጠብ:: ልጅ ነች፣ አይሰማትም፣ አይጎዳትም ብለን "አይይ እሷ ከእህቷ ስትተያይ ፉንጋ ነች፣ አንቺ መልክሽ ይህ ይቀረዋል" እያልን፣ ቀራት ስለምንለው ነገር እየደጋገምን፣ ሴት ልጃችንን አናሳድግ:: መላልሰን እንዳነሳነው፣ ልጅ ወላጅ የሚነግረውን ያምናል፣ በውስጡም ይቀብራል:: እንደዚህ ጆሮዋ ላይ እየደጋገምን ካሳደግናት፣ ሴት ልጃችን ስለራሷ ያላት አመለካከት በጣም ዝቅ ያለ እንዲሆን ያበረክታል:: "ከሌሎች ሴቶች ያነስኩ ነኝ፤ ማንም የማይፈልገኝ የማስጠላ ነኝ" ብላ ትመሰጣለች፤ የአእምሮ ጭንቀት፣ በጉድለት ዙርያ መዟዟር፣ አንገትን መድፋትና ራስን መኮነን፣ ውርሷ ሊሆኑ ትልቅ እድል ይኖራቸዋል::

የውፍረት ነገር በተለይ፣ ልብ ልንለው የሚገባው በጣም አስፈላጊ ነጥብ ነው:: በዚህ ህብረተሰብ ውስጥ የሚያድጉ ብዙ ሴት ልጆች ውፍረትን በተመለከተ፣ ብዙ ውጥረት ውስጥ ያልፋሉ:: ሚዲያው በየቀኑ የሚልከው የሚያዋርድ መልእክት፣ ከህብረተሰብ ጫና ጋር ተጨምሮ የዚህ የውፍረት ፍርሀት የብዙ ሴት ልጆችን አእምሮ ለመበጥበጥና ለማስጨነቅ እድል አለው:: ልጃችን ጤነኛ ባልሆነ መንገድ ሰውነቷ እየወፈረ ካለ፣ በዛው እንዳትቀጥልና ክብደቷ እንዲቀንስ እንፈልግ ይሆናል፤ ያ ጥሩ ተገቢም ነገር ነው:: ነገር ግን፣ የአቀራረብ ዘዴውን ማወቅ አለብን:: "አይይ ወፈርሽ፣ አስጠላሽ፣ ምን ትመስያለሽ፣ የሚያይ ሰው ምን ይልሻል፣" እና የመሳሰሉትን ዝቅ አድራጊ ቃላት መጠቀም እናቁም:: እንደዚህ በሚመስል ሁኔታ ስንናገራት፣ ለመሻሻል በመነቃቃት ፈንታ ራሷን እንድትጠላ፣ ተስፋ እንድትቆርጥ፣ ያበረክታልና:: ውፍረትን ለማስተካከል ልጃችን ምግብ መለወጥ ካስፈለጋትም ሆነ የስፖርት ባህል ውስጥ መግባት፣ ለራሷ ብላ እንድታደርገው በሚመስጣት መንገድ እናናግራት:: ጤነኛ ምግብ መብላት፣ ስፖርት መስራት ለህይወት ጤናዋ፣ጥንካሬ መነቃቃትዋ፤ እንዴት እንደሚጠቅማት እንንገር:: አብረን ስፖርት ለመስራት ወይ ጤነኛ ምግብ ለመብላት እቅድ እናውጣ::

እናት ሁሌ ስለ ሰውነቷ ስትጨነቅ፣ ስታወራ ልጅ የምትሰማ ከሆነ እሷም በዛው የውጥረት፣ ጭንቀት አቅጣጫ ለመሄድ ትልቅ እድሉ እንደሚኖራት ልብ እንበል:: ባጠቃላይ ሰውነት ክፍላችን ላይ በጣም ባተኮረ መልክ ንግግርን እናቁም፤ የውፍረት ጉዳይን ቀን ከሌት፣ ከማውራት እንቆጠብ፤ ልጅም በዛ ዙርያ መዟዟር ይማራልና:: ለልጃችንም ሆነ ለራሳችን ስንል አላስፈላጊ፣ ዝቅ አድራጊ ቃላትን እናቁም:: "አስጠላሁ፤ መቼም አልከሳም፤ ይሄ የሰውነቴ ክፍል አያምርም"...ወዘተ የሚሉ ቃላቶችን እናስወግድ::

ከውፍረት አኳያ ችግር ያለባት ልጅ ካለችን፣ ምናልባትም የበለጠ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋት ተረድተን፣ ስራዬ ብለን ገንቢ መልእክት እንላክላት:: ስላሏት ጥሩ ነገሮች ደጋግመን እናስታውሳት፤ ልትደርስበት ስለምትችለው ትልቅ ቦታ እንንገራት:: ይህ ድጋፋችን፣ውፍረቷን እንደ መላ ማንነቷ አርጋ ይዛ እንዳትቆዝም፣ ውስጧ እንዲታደስ ያበረክታል::

ከዚህ ጋ ተያይዞ፣ ልጆቻችን ጤነኛ ምግብ መብላትን እንዲማሩ ከልጅነታቸው ጀምሮ እናበረታታ:: እፈልጋለሁ ባሉን ቁጥር ወይ ለኔ ቀለለኝ ብለን ጤነኛ ያልሆነ መክሰስ እየሰጠን፣ እንደማክዶናል ወይም በርገር ቤት ዓይነት ምግብ ቦታዎች ሁልጊዜ እየወሰድንና እየገዛን ካሳደግን፣ ልጆችም እንደዚያ አይነት ምግብ መብላት ለምዶባቸው ያድጋሉ፤ሲያድጉም በዚያው በለመዱት

ይቀጥላሉ። ጤነኛ የሆነ ምግብ በሚጣፍጥ መልክ እየሰራን ካቀረብንላቸው ግን፣ ያ እንደ ልምድ ሆኖ በትልቅ እድሜያቸውም እንዲቀጥሉበት መንገድን ይከፍታል።

## ***ለወንድ ልጃችን የሚሰጥ ምክር***

ወንዶች ልጆቻችን ዋናው የሚያጋጥማቸው ፈተና፣ በተለይ ከቀለማቸው ጋር የተያያዘ ነው። ልጆቻችን እንደ አሜሪካ ያለ ህብረተሰብ ውስጥ ሲኖሩ፣ ዋነኛ መለያቸው ጥቁርነታቸው ነው። "ልጄ ኢትዮጵያዊ ነው፤ ልጄ አበሻ ነው" እንል ይሆናል። አዎ፤ ለእኛ ቀድሞ የሚታየን ያ ማንነቱ ነው። ልክ እንደኛው፣ አንድ ከታይላንድ የመጣ ሰው፣ "ልጄ ዋናው ማንነቱ ታይላንዳዊ መሆኑ ነው" ብሎ ሊያስብ፣ ሊከራከር ይችላል። ያ ልጅ ግን ሲወጣ፣ መጀመሪያ የሚታወቀው፣ "ከታይላንድ" ተብሎ ሳይሆን "እስያዊ ልጅ" ተብሎ ነው። እኛም የልጃችን ኢትዮጵያዊነቱ ቀድሞ ቢታየንም፣ በውጭ ሲወጣ ተገልጦ ለህዝብ የሚታየው፣ ጥቁር ወንድነቱ ወይም ምናልባት አፍሪካዊነቱ ነው።"ታዲያ ያ ለልጄ ምን አይነት ተጽእኖ ያመጣበታል"? እንል ይሆናል። ከህብረተሰብ፣ ከመገናኛ ብዙኀን የሚመጣበት ግፊት አለ። ከዚያም ደግሞ ከሚመስሉት፣ ከራሱ ዝርያ፣ ከጥቁሮች የሚመጣበት ተጽእኖ አለ። ከህብረተሰብ እና ከመገናኛ ብዙኀን በጥቁሩ ወንድ ልጃችን ላይ ሊመጣ የሚችለውን ጫና እንመልከት።

እንደ አሜሪካ ባሉ አገሮች ውስጥ፣ ስለ ጥቁር የተሳለ ስእል አለ። በተለይ ደግሞ ስለ ጥቁር ወንድ የሚነገር፣ ልጃችን ደጋግሞ የሚሰማው መልእክት አለ። ይኸውም

- ጥቁር ወንድ ሰነፍ ነው።
- ጥቁር ወንድ ትልቅ ቦታ አይደርስም።
- ጥቁር ወንድ ሴትን ማሳደድ ይወዳል።
- ጥቁር ወንድ ሀላፊነት መውሰድን አያውቅም።
- ጥቁር ወንድ እስር ቤት ይገባል።





እነዚህን የመሳሰሉ፣ ነጮችና እስያዊ ወንዶች ልጆች ስለ ራሳቸው የማይሰሟቸው፣ ለጥቁር ወንዶች ብቻ የተጻፉ መለያዎች አሉ። ይህንንም ቴሌቭዥን፣ ፊልሙ፣ ጋዜጣው፣ በተለያየ መልክ ያስተጋባዋል። ይህ ልጃችን ደጋግሞ የሚያየውና የሚሰማው መልእክት፣ በእኛ ብርታት መስመር ካልያዘ፣ አስተዳደጉ ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል። ስለ ራሱ ዝቅ ያለ አስተሳሰብ እንዲኖረው ሊያደርግ፣ "ትልቅ ቦታ እኔ ልደርስ አልችልም" ብሎ የመደምደም ችግር ሊያመጣበት ይችላል። በውስጥ የሚሰማውን ብቁ ያለመሆን ስሜትን ለማካካስ፣ በተለያየ መንገድ ወንድነቱን ለሚሟላት፣ ብዙ ውጥረትና የሕይወት ውዝግብ ውስጥ ሊገባ ይችላል።

በዚህ ህብረተሰብ ውስጥ ያላደጉ ወላጆች፣ የዚህን ግፊት ክብደት ላይረዱ ይችላሉ። "ይህ ከልጄ ጋር ምን አገናኘው? እሱ እንደዚያ እንዳልሆነ ተረድቶ አይቀጥልም እንዴ? ጠንክሮ ከሰራ ትልቅ ቦታ እንደሚደርስ ገብቶት፣ በራሱ ቀና መንገድ አይሄድም እንዴ?" እንል ይሆናል። እንደ አሜሪካ ባሉ አገሮች ውስጥ፣ በልጅነት ማደግ እንዴት እንደሆነ አናውቅምና የልጃችን የውጥረት ምንጭ አይገባን ይሆናል።

ደጋግመን እንዳነሳነው፣ አእምሮ ላይ የሚደረግ ጫና በጣም የከበደ ነው። በአገራችን በኢትዮጵያ ወንድ ልጅ ሲያድግ፣ "የወንድ ሁለተኛ ነህ፤ ያንተ ቢጤ መጨረሻው በስተኋላ ሆኖ መቅረት ነው" የሚል የጎን መልእክትን ሲሰማ አያድግም። የሚያየው ባገሩ አንደኛ ወንድ እንደሆነ ነው። ያ ምን ማለት ነው? ስናድግ ያየነው፣ የእኛው ቢጤ አስተማሪ፣ ነጋዴ፣ኢንጂነር፣ አገር ገዢ ሲሆን ነው። ደሀ ሆነን ብንኖር እንኳ፣ ሲሳካለት፣ ላይ ሲወጣ የምናየው ሀብታሙ፣ የኛው ቢጤ፣ የኛው ከለር ነው። ስልጣን ላይ የወጣን ሰው ባንወደው እንኳ እኛኑ የሚመስል፣ የኛው አገር ሰው ነው። ቴሌቭዥን በከፈትን ቁጥር፣ ከኛ የተለየው ዘር (ነጩ) ከፍ ያለ ቦታ ላይ ተቀምጦ፣ እኛኑ የሚመስለው ደግሞ ዘላለም በወንጀል

ሲታወቅ፣ እያየን አላደግንም፡፡ ስለ አገራችንም የሚያኮራን ታሪክ እየሰማን አድገናል፡፡

ይህ አእምሮ ላይ ትልቅ ተጽእኖ አለው፡፡ "እኔም ከማን አንሼ፣ እኔም ትልቅ ቦታ እደርሳለሁ" የሚል ውስጣዊ ጥንካሬ፣ እምነት፣ ሀይልና መነቃቃትን ይሰጣል፡፡ የታወቀው ጥቁር አሜሪካዊው ተዋናይ ቢል ኮዝቢ (Bill Cosby) ከማን አንሼ የሚል የአእምሮ ነጻነት ስላለው ትልቅ ሀይል ሲናገር፤ እንዲህ ብሎ ነበር፤ "ኢትዮጵያዊው እዚህ መጥቶ ዝቅተኛ ስራ መስራቱ አይገደውም ምክንያቱም ነገ የዛ ቦታ አለቃ (ማኔጀር) እንደሚሆን በልቡ ያቃታልና" ብሎ ገልጾ ነበር፡፡ ከማንም አላንስ በሚል እምነት ታጥቀው የመጡት ብዙ ወገኖቻችን በሰው አገር መጥተው ህልማቸውን እውን ያደርጋሉ፡፡

በአንጻሩ፣ እንደ አሜሪካ ባለ አገር የሚያድጉት ወንድ ልጆቻችን፣ ብዙ ጊዜ የሚያዩትና የሚሰሙት፣ የእነሱ ቢጤ የጥቁር ወንድ መጨረሻው ጥሩ እንዳልሆነ ነው፡፡ ወንጀል፣ እስር ቤት፣ ሱስ፣ ግዴለሽነት፣የብጤያቸው እጣ እንደሆነ የሚያስታውሳቸው ድምጽ፣ በየቀኑ ይደውልባቸዋል፡፡ ውሸት ተደጋግሞ ሲነገር እውነት ይመስላል እንደሚባለው ይህንን ድምጽ ሁሌ ሲሰሙ፣ ወደራሳቸው ሊያዞሩት ይችላሉ፡፡ ስለ ማንነታቸው ያላቸው አስተሳሰብ እንዲቀንስ፣ ችሎታቸውን እንዲጠራጠሩ ሊገፋቸው ትልቅ ኃይል አለው፡፡ ኢትዮጵያዊ ወላጅ ቤት ቢኖርም እንኳ፣ እነርሱ እንደ ጥቁር ወንድነታቸው ያንን ጫና ተሸክመው ይኖራሉ፡፡

ጥቁሩ የአሜሪካ ፕሬዚደንት ኦባማ ስለ ሕይወት ታሪካቸው በጻፉት "የአባቴ ሕልም" በሚለው መጸሀፋቸው ላይ፣ ስለዚህ ውጥረት ያወሳሉ፡፡ያሳደጓቸው፣ ቤት ሲሄዱ የሚያይዋቸው፣ ነጭ እናታቸው እና ነጮቹ አያቶቻቸው ቢሆኑም፣ በውጭ ግን በጥቁርነታቸው፣ በማንነታቸው ይሰማቸው ስለ ነበረው ግራ መጋባት ደጋግመው ጠቅሰዋል፡፡ ከልጅነታቸው ጀምሮ፣ በተለያየ መልክ ከውጪ የሚያዩትና፣ የሚሰሙት ጥቁርን ዝቅ አድራጊ መልእክት፣





በውስጣቸው የውጥረት ስሜት እንዳመጣባቸው፤ይህ ራስን ለማወቅ፣ ለማግኘት የፍትጊያ ጊዜ፣ እንዴት ከባድ ጊዜ እንደነበር ያነሳሉ፡፡ ሙሉ ጥቁር አለመሆናቸው፣ በነጭ እናትና አያቶች ተከበው ማደጋቸው የእኚህን ሰው ፈተና አላሳነሰውም፤ ጥቁርነታቸውንም አልደበቀውም፡፡ እንደ ማንኛውም፣ በዚህ ህብረተሰብ ውስጥ እንደሚያድግ ጥቁር ልጅ፣ ስለራሳቸው ብዙ የተዘበራረቀ ነገር ሰምተዋል፡፡ ራስን ለማግኘት፣ ምቹ ነው የሚሉት ስፍራ ለመድረስ፣ ብዙ ውጥረት ውስጥ አልፈዋል፡፡ ልጆቻችንም በዚህ ህብረተሰብ ውስጥ ሲያድጉ፣ በጥቁርነታቸው ይህን አይነት ውጥረትን መጋፈጣቸው አይቀሬ ነው፡፡

ልጆቻችን አንገት የሚያስደፋ መልእክት እየሰሙ የሚያድጉት፣ እዚህ አገር ስላለው ጥቁር ህዝብ ብቻ አይደለም፡፡ "ቤተሰቦቼ መጡበት ምንጩ ነው" ስለሚሉት፣ አገራቸው አህጉራቸው ስላለው ጥቁር ህዝብም፣ አጉል ነገር ይሰማሉ፡፡ የመገናኛ ብዙኀን አፉን ከፍቶ በቀጥታ ባይናገረውም፣ ሊያስተላልፈው የሚጥረው መልእክት ይህን ይመስላል፤ "የአፍሪካ ህዝብ ሁሌ ተርቦ የሚለምን ህዝብ ነው፤ የአፍሪካ ህዝብ ከጦርነት እና እርስ በእርሱ ከመገዳደል በስተቀር ሌላ ምንም አያውቅም፡፡ የአፍሪካ ህዝብ ስልጣኔ፣ ሆነ ታሪክ የለውም" ወዘተ--. ይህም መልእክት በተዘዋዋሪ መንገድ፣ አንዳንዴም በፊት ለፊትም ይቀርባል፡፡ እውቀት፣ ስልጣኔ፣ ጉብዝና ጨዋነት ከዚያች አገር፣ ከዚያች አህጉር ጋር የተያያዙ እንዳልሆኑ መልእክቱን ያስተጋባል፡፡

ሌላው ወንድ ልጆቻችን የሚያጋጥማቸው አሉታዊ ተጽእኖ፣ ከመሰሎቻቸው፣ ከጓደኞቻቸው፣ ከጥቁር ቡድናቸው፣ ከዘፈኑና ከፊልሙ፣ የሚመጣው መጓተት ነው፡፡ ራስን ዝቅ አድርጎ የማየት ዝንባሌ አለ፡፡ ከዚያም በተጨማሪ፣የጉድለት ስሜትን ለማጣጣት፣ ጎጂ አቅጣጫን መውሰድ፣ በብዙ ጥቁር ወጣት አካባቢ አለ፡፡ ያ ምን ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ " ወንድነቴን የማስረጋግጠው ብዛት ያላቸውን ሴቶች ሳወጣ ነው፣ ክብርን የማገኘው ከሌላ ጋር ስደባደብና ሀይለኝነቴን ሳሳይ ነው፤ ከፍ ተደርጌ የምታየው እንደዚህ አይነት

ልብስ ለብሼ ቋንቋዬን በዚህ መልክ አድርጌ ስራመድ ነው" የሚል እምነት በብዙ ጥቁር ወጣቶች ዘንድ ዘልቆ ገብቷል። ከዚህ በተጨማሪ፣ ስለ ራስ መጥፎ የማውራት፣ ራስን ዝቅ አድርጎ የመገመት ዝንባሌ አለ።

ለጥቁሮች የተዘጋጁ ዘፈኖች፣ ፊልሞችና "አስቂኝ ቲያትሮች" በብዛት ራስን አቅልሎ የሚያቀርብ፣ መጨረሻን አሉታዊ አድርጎ የሚያሳይ መልእክትን በድግግም ያስተላልፋሉ። ከዚህ አምልጠው ታሪካቸውንና ባህላቸውን ለማክበር የሚሞክሩ፣ የጥቁር ህዝብን ማንነት አዎንታዊ ታሪኩን ለማስተላለፍ የሚጥሩ ብዙ ጥቁር ወንድሞችና እህቶቻችን እንዳሉ ሁሉ፣ አሁንም በዚህ አደንዛዥ እውነታ ስር ሆነው ራሳቸውን ዝቅ በሚያደርግ ሁኔታ የሚራመዱና ለሕይወታቸው የሚወስኑ ብዙዎች አሉ።

ልጆቻችን ቴሌቭዥን ሲከፍቱ ይህንን በብዛት ያያሉ። ውጭ ሲወጡ፣ ትምህርት ቤት ሲሄዱ የሚያገኟቸው ጓደኞቻቸውም በዚህ አደንዛዥ ባህል ታስረው ሊሆን ይችላል።"ራስህን ለማስከበር፣ ወንድነትህን ለማሳወቅ ይህን ያህል ሴቶች ጋር አብረህ መታየት አለብህ፤ የወንድነትህ መለኪያው ቁመትና ሰውነትህ ነው፤ ያለበለዚያ ሴታሴት ትባላለህ" የሚሉና የመሳሰሉ መልእክቶችን ከተለያየ አቅጣጫ ይሰማሉ።

## ***<u>ወንዶች ልጆቻችንን ለመርዳት ምን ማድረግ እንችላለን?</u>***

ከምንም በላይ፤ ልጆቻችን ላይ ያለውን ግፊት፣ ሀያልነት እንገንዘብ ራስን፣ ማንነትን ባለማወቅ መኖር ውስጣዊ ጉዳትና የጉድለት ስሜት እንደሚያመጣ፣ አንድ ሰው ስለ ራሱ በቂ እውቀት ሳይኖረው ሲቀር ጓደኛ ወይም አካባቢው በሚያሳየው ስእል ውስጥ ሊጠቃለል እንደሚሞክር እንገንዘብ።

ወንድ ልጅ ስለ ማንነቱ እና ስለምንጩ ጤነኛ አመለካከት መኖሩ በጣም አስፈላጊ እርምጃ መሆኑን መረዳት አለብን። ጥቁር





አሜሪካኖችን እንደምሳሌብንወስድ፣ ከቀድሞ ታሪካቸውና ባሕላቸው በግድ ተላቀው በባርነት ሲኖሩ፣ ከምንም በላይ የጎዳቸውና ዋናው ተነጥቆ የተወሰደባቸው፣ የማንነታቸው ሕልውና ነው። የራሳቸው ባህል እንዳላቸው እንዲረሱ ተደርገዋል። ራሳቸውን ችለው መቆምና መኖር እንደሚችሉ፣ እንዲረሱ ተበይኖባቸዋል። ማንነታቸው ተወስዶ "ባርያ ወይ የነጭ በታች" በሚለው ስር እንደሚጠቃለሉ ተደጋግሞ ተነግሯቸዋል። ሰው ምንጭህ፣ ማንነትህ ዋጋ ቢስ ነው ተብሎ ሲነገረው ወደ አንድ ድምዳሜ ይደርሳል። ፍሬ ቢስ፣ የበታች ነኝ ወደሚለው ድምዳሜ ይገባል። ውጫዊ ባርነቱ ቢያቆም እንኳ ውሸቱ እንደ እውነት ሆኖ በአእምሮው ተቀምጦ ፣ ይህ ሀይለኛ የአእምሮ እስራት አካሄዱን እና መጨረሻውን ይመራዋል፤ "አልችልም፣ አልደርስም፣ አልወጣም፤ አላሸንፍም" በሚለው እምነት ይታሰራል። ይህ ጎጂ እምነት ከወላጅ ወደ ልጅ እየተላለፈ ትውልድን ይበክላል።

ወንድ ልጆች፣ ከዚያ እስራት ነጻ እንዲሆን፣ ወደ ላይ እንዲነሳ፣ መሰረት ያስፈልገዋል፤ጥቁሩ የአሜሪካ ፕሬዚደንት ኦባማ፣ እናታቸው መሰረት የመኖር ጥቅሙን ተረድተው፣ ማንነታቸውን እንዲያውቁ፣ በጥቁርነታቸው እንዲኮሩ ሊገነቧቸው እንዴት ይጥሩ እንደነበር በመጽሀፋቸው ላይ ደጋግመው ጠቅሰዋል። ህብረተሰብ ስለ ጥቁርነታቸው የተዘበራረቀ አዋራጅ መልእክቱን ሲልክላቸው፣ በሌላ ጎኑ ደግሞ እናታቸው የዳበረ፣ ጤነኛ አመለካከት እንዲኖራቸው፣ ምንጫቸውን እንዲያውቁ፣ በቻሉት ይጥሩ ነበር። "ጥቁሮች ጎበዞች ናቸው፤ ጥቁሮች ጀግኖች ናቸው። አንተ የመጣኸው ከጥሩ ህዝብ ነው" እያሉ የልጃቸውን አእምሮ ያድሱ ነበር። እናታቸው እሳቸውን መሰረት ለማስያዝ የነበራቸውን ጥረት ሲጠቅሱ፣ እንዲህ ብለው ጽፈዋል፦

> "እናቴ ሁሉን ጥቁር ህዝብን በሙሉ ያካተተ መልእክት ታስተላልፍልኝ ነበር። ስለ ሲቪል መብት እንቅስቃሴ የተጻፉ

> መጻህፍትን፣ የማህሊያ ጃክሰን ሙዚቃዎችን፣ የዶ/ር ኪንግን ንግግሮች ቤት ይዛልኝ ትመጣ ነበር።"[21]

የእናታቸውን ጥረት ሲያወሱ፣ በሌላ ቦታ፣ እንዲህ ሲሉ ይጠቅሳሉ፡- "በራስ የማፈር ጉዳቱን ትረዳ ነበርና የሀፍረት፣ የዝቅተኝነት ስሜት እንዳይሰማኝ በአንጻሩ በምንጩ እንድኮራ የቻለችውን ታደርግ ነበር" ብለው ያወሳሉ:: አስከትለው ሲናገሩ እንዲህ ብለዋል፤

> "ስለ ኢንዶኔዢያዊ ጓደኞቼና ስላደረጉት የሚገርም ትዕይንት መጥቼ ስነግራት፣ እሷ ደግሞ ስለሌላ ትእይንት ትነግረኝ ነበር። ከኔ በእድሜ ዩማያንሱ ግን ለመብታቸው ቆመው ስለተሰለፉ ጥቁር ልጆች ታሪክ ትገልጽልኝ ነበር። ጥቁርነት ትልቅ ሀብት፣ ውርስ፣ ለጠንካራ ብቻ የሚሰጥ ቅርስ እንደሆነም ልታሳየኝ ትጥር ነበር" ብለው ያነሳሉ።[22]

እኚህን ሰው በማንቃት ስራ ላይ የተሳተፉት እናት ብቻ አልነበሩም:: ነጮቹ አያቶቻቸውም ምንጭን የማወቅ ጥቅሙ ገብቷቸው፣ ስራዬ ብለው እንዲሁ ማንነታቸውን እንዲያከብሩ ያስተምሯቸው ነበር:: ስለ ኬንያዊ አባታቸው ምንጭ ትንትን አድርገው ይነግሯቸው ነበር:: ብሩህ ጭንቅላት የነበረው፣ በራሱ የሚተማመን ሰው እንደነበረም፣ ይነግሯቸው ነበር:: እናትም፣ "አብሮኝ አይደል፤ ምን አገባኝ" በሚል አስተሳሰብ፣ የኦባማን አባት ማንነት በመደበቅ ወይም በማዋረድ ፈንታ፣ለልጃቸው ሲሉ፣ ስለ ድሮ ባላቸው ገንቢ ነገር ይናገሩ ነበር:: "ኬንያዊው አባትህ ደሀ ሆኖ ቢያድግም ከጥሩ ህብረተሰብ የመጣ ሰው ነው" እያሉ ልጃቸውን ያስተምሩ ነበር::

እኚህ ጎበዝ እናት አርቀው አዩ:: "እኔ ነጭ ነኝ ፤ እርሱም ልጄ ነው ምን ይሆናል" ሳይሉ፣ ስራዬ ብለው ልጃቸውን መሰረት

[21] Obama, Barack. (2004) Dreams From My Father, Three Rivers Press, New York City

[22] Obama, Barack. (2004) Dreams From My Father, Three Rivers Press, New York City





አስያዙ፤ራሳቸውን እንዲወዱ እንዲያከብሩ አድርገው አሳደጉ:: ሀሳባቸው ተሳካ፤ ህብረተሰብና የመገናኛ ብዙኀን ስለ ጥቁር የሚያስተጋባው አሉታዊ መልእክት ጥቁሩን ልጃቸውን ለጊዜው ቢያጉላላም አላሸነፋቸውም፤ ታሪክ ሰሪን አፈሩ:: በአንድ ወቅት ጥቁር ብቸኛ ታሪኩ ባርነት በነበረባት አገር፣ የመጀመሪያውን ጥቁር ፕሬዚደንት ለበትረ ስልጣን አበቁ::

እኛስ ለልጆቻችን መሰረት እናስይዛቸዋለን ወይ? እኛስ ልጆቻችን ማንነታቸውን እንዲያውቁ አድርገን እናሳድጋቸዋለን ወይ? እኛስ ልጆቻችን ታሪካቸውን፣ ባህላቸውን እንዲወዱ እንዲያከብሩ አድርገን እናንጻቸዋለን ወይ? ወይስ "እኔ የማውቀውን አውቃለሁ እነሱም ልጆቼ ስለሆኑ ምንም አይሆኑም" ብለን እንተወዋለን? ትውልድ ማንነቱን በነሲብ ከየትም እንዲያገኘው ትተንለት ልናልፍ ነወይ? ልጆቻችን ስለ ወንድነታቸው ብቸኛ መልእክት ነጋሪያቸው የአሜሪካ ዜና እንዲሆን አንፍቀድ:: አይሁዳውያን ልጆቻቸውን እንደዚያ አያሳድጉም፤ እስያውያን ልጆቻቸውን እንደዚህ አያሳድጉም፤ ልጆቻቸው መሰረታቸውን እንዲያውቁ እንዲያከብሩ አድርገው ያሳድጋሉ::

ለልጆቻችን ማስተላለፍ ያለብንን ቋሚ ቅርስ አንርሳ:: ራሳቸውን እንዳይጠሉ፣ ማንነታቸውን ምንጫቸውን እንዲያከብሩ አድርገን እናሳድግ:: እኛ ኢትዮጵያውያን ባህል ታሪካችን ከኛ አልፎ፣ ሌላው ጥቁር ህዝብን የሚያኮራ ነው:: የጥቁር መሰረቱ ሁሌ ተሸናፊ፣ ሀይማኖተ ቢስ እና ታሪከ ቢስ ነው የሚለውን የልጆቻችንን አንገት ሊያስደፋ የሚሞክረውን የዛሬውን ውሸት የሚሰርዝ፣ ከእኛ አልፎ የብዙ ጥቁሮችን አንገት ቀና የሚያስደርግ ባህል እና ታሪክ አለን:: "እኔ ታሪኬን አውቃለሁ ያ በቂ ነው" ማለቱን ትተን፣ ልጆቻችንን ስለ ባህል ታሪካቸው እናስተምር:: ምንጫቸውን ማወቃቸው በማንነታቸው መኩራት መቻላቸው የወደፊት ህይወታቸውን አንቀሳቃሽ፣ ሞተር እንደሚሆናቸው ተረድተን፣ ያለንን ጥሩ ባህልና ታሪክ ሁሉ እንንገራቸው::

ከኛም አልፈን፣ ባጠቃላይ ስለ ጥቁር ታሪክ ሠሪዎች፣ ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑ ሰዎች፣ የተጻፉ መጸሀፎችን ለልጆቻችን ገዝተን እንስጥ:: በዚህ ጉዳይ ላይ የተሰሩ ፊልሞች እናሳይ:: ችግርን ፈተናን አልፈው ህልማቸውን ስላሳኩ ስለተለያዩ ጥቁሮች ታሪክ እንንገር:: ከዚህ ጋር ተያይዞ ጥቁር አሜሪካኖችን ወይም ሌላው ጥቁር ህዝብን ባጠቃላይ እየተሳደብን፣ ልጆቻችንን ከመበረዝ መጥፎ ልምምድ እንቆጠብ:: "አይይ ጥቁር" እያልን ስንሰድብ እኛ ሌሎችን ያዋረድን ቢመስለንም የኛው ልጆች በጥቁርነታቸው እንዲያፍሩ፣ እኔም እንደዛው ነኝ ብለው ዝብርቅርቅ ህይወት ውስጥ እንዲገቡ የሚዳርግ ጎጂ ልምምድ ነው::

ራሳችንን ህዝባችንን ልጆቻችን ፊት ከመሳደብ እንቆጠብ:: "የአበሻ ነገር፣ የኛ ህዝብ አያልፍለት፣" ወዘተ እያልን ልጅ ፊት ማውራቱ፣ ትልቅ ጉዳት እንዳለው እናስታውስ:: የአበሻ ነገር ብለን ስንሳደብ ልጆቻችን መሰረታቸውን እየተሳደብን ነው:: ህዝባቸውን ከዚያም አልፈው ማንነታቸውንና ራሳቸውን እንዲጠሉ እየመራናቸው ነው:: በውስጣቸው ያለው የተስፋ ብርሀን እንዲጨልም እየዳረግን ነው:: ራስን፣ ምንጭን፣ ዝቅ አድርጎ መሳደብ፣ ልጅን ዝቅ ማድረግ እንደሆነ ተረድተን ከዚህ ጎጂ ልምድ እንቆጠብ:: ልጆቻችን ለየት አድርገው እንዲያስቡ፣ በአዲስ መልክ እንዲመለከቱ፣ የሚረዷቸውን እውነቶች በየአጋጣሚው አብረናቸው እንወያይ::

- ☞ ዋጋ ቢስ ታሪክ እንዳላቸው ሲነግራቸው የሚሞክረውን የመገናኛ ብዙሀን መልክትን የሚሰርዝ ትምህርት እናስተምራቸው:: "አብዛኛውን ጊዜ፣ታሪክ የሚጻፈው ሚድያውን በሚቆጣጠረው ክፍል ነው፤ ያ ማለት ግን የተጻፈ ነገር ሁሉ ትክክል ነው ማለት አይደለም፤ የጥቁርነት ትርጉም፣ መገናኛ ብዙኀን ሲያሳይ ከሚሞክረው በጣም የላቀ ነው" ብለን፣ ለልጆቻችን እንንገር::
- ☞ "ስልጣኔ ማለት መኪና መስራት ወይ ፎቅ መስራት ብቻ አይደለም፤ ፖሊስ ወይ ህግ ሳይኖር ህብረተሰብ ተዋዶ፣





ተከባብሮ ተቃቅፎ ለረጅም ጊዜ አብሮ መኖር ጥልቀት ያለው ስልጣኔ ነው" ብለን ለልጆቻችን እናስተምር:: ከመሰሎቻቸው ሊመጣባቸው የሚችለውን ግፊት ከወዲሁ አይተን ራሳቸውን ችለው እንዲያስቡ የሚረዳቸውን ነገር ለልጆቻችን እናስተምር::
- ☞ ወንድነት ድምጽ ጎርነን አድርጎ ማውራት ወይ ከብዙ ሴት ጋር መታየት አይደለም፣ ወንድነት መለኪያው የሰውነት ትልቅነት አይደለም፤ ወንድነት ውስጣዊ መልክ ነው ፤ ወንድነት ማለት ላመኑበት መጣር፣ ከማንም አላንስም ብሎ ማመን፣ ስህተትን ተቀብሎ ማረም፣ ራስ ችሎ መቆም-- ነው ብለን፣ ከልጅነት ጀምረን አስተሳሰባቸውን የሚያድስ ግንዛቤን እናቀርብላቸው::
- ☞ የአእምሮ እስራት ህዝብ ላይ ስለሚያመጣው ጉዳት እንንገራቸው:: "ነጭ እራሱን ዝቅ እያደረገ አይዘፍንም፣ ቻይና ራሱን እየሰደበ አይዘፍንም፣ እኛስ ጥቁሮች ለምን እንደዛ እናደርጋለን?" ብለን እንዲያስቡበት መንገድ እንክፈትላቸው::
- ☞ ማንነትን ንቆ ሌላን የመገልበጥ አደገኛነትን ለልጆቻችን እናስተምር:: "ሌላን ለመምሰል ስትሞክር ሁሌ ሁለተኛ ሆነህ ትቀራለህ:: ራስህን ከናቅህ ሌላም ይንቅሀል፤ ያንተ ወደሆነው ትልቅ ቦታ መድረስ የምትችለው ራስህን መሆን ሳትፈራ ስትቀር፣ ያንተ የሆነውን ስታቅፍ ነው" ብለን ለልጆቻችን እናስተምር::
- ☞ ከዚ ጋር አያይዘን፣ ባህላቸውን፣ ታሪካቸውን አክብረው እንዲይዙ ለልጆቻችን እናስተምራቸው "ታሪክ ባህላቸው የተወሰደባቸው ህዝቦች ምንጫቸውን ለመረዳት በቻሉት በሚሞክሩበት በዚህ ዘመን አንተ ያለህን ታላቅ የታሪክና የባህል ቅርስ አውጥተህ አትጣል" ብለን አዳሽ ግንዛቤን እንስጣቸው::
- ☞ አገር ቤት ስንወስዳቸው፣ ለቱሪስት በተዘጋጁ ዘመናዊ ቦታዎች ብቻ ወስነናቸው በመጣት ፋንታ እውነተኛ ባህላቸውን ሊያዩ የሚችሉበት ቦታ እንውሰዳቸው፤

እንደዚህ ልጆቻችንን ከገነባን፣ ራሳቸውን እንዲያከብሩ፣ ስለ ማንነታቸው ጤናማ እምነት እንዲኖራቸው አድርገን ካሳደግን፣ ሀፍረት በራስ ማፈርና ሌላን ለመምሰል ሙከራ ከአካባቢያቸው የራቁ ይሆናሉ:: "ከማንም አላንስም፣ እኔም ትልቅ ቦታ እደርሳለሁ" በሚል ውስጣዊ መነቃቃት እየተመሩ፣ ያሰቡት ቦታ ይደርሳሉ::

## ማጠቃለያ

አባት ወይ እናት በተናጥል ልጆቻችንን የምናሳድግ ከሆነ፣ ይህንን ነጥብ ልብ እንበል፤ ለልጆቻች አዎንታዊ ምሳሌዎች የሆኑ የጾታቸው አባል ሰዎች በሕይወታቸው ውስጥ መኖራቸው ትልቅ ጥቅም ሊኖረው ይችላል:: እናት ከሆንን፣ ለወንድ ልጃችን ጥሩ ምሳሌ አስተማሪ ሊሆን የሚችል ወንድ ዘመድ፣ የምናምነው ጓደኛ ጋር ልጃችን ቅርበት ኖሮት እንዲያድግ ጥረት እናድርግ:: አባት ሆነን ሴት ልጅ ካለችን፣ ብንችል ልጃችንን የምትቀርብ፣ በአንዳንድ ጉዳይ ላይ ልታነጋግራት የምትችል፣ ሴት ዘመድ ወይ ጓደኛ ከልጃችን ጋር ጥሩ ቅርበት እንዲኖራት ጥረት እናድርግ::

ልጃቻችን ተመሳሳይ ጾታ ካላቸው፣ ምሳሌ ሊሆኗቸው ከሚችሉ ሰዎች ጋር ጊዜ ማሳለፋቸው፣ በተለያየ ጉዳይ ይጠቅማቸዋልና:: ለምሳሌ እናት ምንስ ወንድ ልጇን ብትወድ፣ እንደ አባት ሆና አባት ሊያሳድርበት የሚችለው ተጽእኖ በልጁ ላይ ማሳደር ያዳግታት ይሆናል:: ወንድ ዘመድ ወዳጆች በአካባቢው ካሉ ግን፣ ለወንድነቱ ጠቃሚ የሆነ ምሳሌነትና ምሪትን ሊሰጡት ይችላሉ:: ልጆች የራሳቸው ጾታ የሆኑ ምሳሌዎች ሲኖሩዋቸው፣ በራስ የመተማመን ብቁነት ስሜት እንዲሰማቸው ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል፤ የብቸኝነት ገለልተኝነት ስሜት ከሕይወታቸው እንዲጠፉም፣ በትልቁ ሊያበረክት ይችላል:: ወንዶችም ሆነ ሴቶች እንደየጾታቸው፣ እንዲያብቡ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው ተረድተን፣ ይህ አስፈላጊ ተጽእኖ በሕይወታቸው እንዲኖር እንጣር::





# የሕይወት ተሞክሮ



## ለልጆቻችሁ የእናት ቋንቋችሁን ማውረስ የማንነታቸው ማረጋገጫ ነው

ከኢትዮጵያዊያን ወላጆች አብራክ የተገኘሁ የመጀመሪያው ትውልድ አሜሪካዊ፣ (First Generation American) ነኝ:: በአሜሪካ ለሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ገንቢ ምክር አለኝ:: የእናት ልሳን የሆነውን ቋንቋችሁን፣ ለልጆቻችሁ አሳውቁ፣ አስተምሩ፣ አስልተላልፉ:: የፈለገው ዓይነት ከኢትዮጵያ የበቀለ ቋንቋ ሊሆን ይችላል፤ አማርኛ፣ አፋን ኦሮሞ፤ ትግርኛ፣ ጉራጊኛ፣ አፋርኛ፣ ሲዳማ፣ ወላይታኛ፣ ሱማሊኛ ወ.ዘ.ተ...

ይህንን ገንቢ ያልኩትን ምክሬን ስለግስ፣ በማያውቁትና ባለመዱት አገር ልጅን ለማሳደግ ሊያጋጥሙ የሚችሉ የተወሳሰቡ ፈተናዎችንና ችግሮችን ሳላጤን ቀርቼ አይደለም። ወላጆች ለልጆቻቸው ይጠቅማል የሚሉትን መልካም ነገር ሁሉ እንደሚሰጡ ሁላችንም እንስማማለን፤ እኔም በቤተሰቦቼ ተመልክቼዋለሁና። እንዲያውም ይህንን መልእክት የምጽፈው እኔን መሰል ልጆች እንዴት እንደሚያስቡ ስለማውቅ ነው። ልጆቻችሁ ሃላፊነት ያላቸው ሰዎች ሆነው እንዲያድጉ፣ በሚያገኙት ትምህርትና አካባቢያዊ ተሞክሮ ተጨማሪ፣ የናት ልሳን የሆነውን ቋንቋችሁን ማስተማርና ማስጨበጥ፤ በማሳደግ ሂደት ውስጥ ከሚያጋጥሙ ችግሮች አብዛኛውን ይቀርፋል ብዬ ከልብ ስለማምን ነው።

ብዙ ልጆች በትምህርት ቤት እያሉ፣ ከአሜሪካዊያን ጓደኞቻቸው ተለይተው መታየትን ስለማይሹ የቤተሰቦቻቸውን ቋንቋ መማር አይፈልጉም።“ቋንቋው ለኛ አያስፈልገንም፣ የኔ ቋንቋ አይደለም፤ ስለዚህ ለምን እማራለሁ?” እያሉ ሰምተው እንዳልሰሙ በእንግሊዝኛ ቢመልሱ፤ተስፋ ሳትቆርጡ አስተምሯቸው። እንደኔ ነፍስ አውቀው አእምሯቸው በስሎ የህይወትን ጣዕም በሚገባ በተገነዘቡ ጊዜ የእናት ልሳን የሆነውን ቋንቋችሁን በመማራቸው ያለውን ጥቅም ሲረዱ ያኔ አብዝተው ከልብ ያመሰግኗችኋል።

ልጆቻችሁ በእናት ቋንቋ የተባ ወይም የተቀላጠፈ ልሳን ካላቸው፣ ከባህላቸው የሚያስተዋውቃቸውን እውነተኛ መሳሪያ መጨበጣቸውን ታረጋግጣላችሁ። ከባህላቸው ጋር መተሳሰርና እንዲዋሃዳቸውም ማድረግ ህሊናቸውን ለማዳበር አንዱ ቁልፍ የሆነ መሣሪያ ነው። ልጆቻችሁ ባህላቸውን፣ ታሪካቸውንና ማንነታቸውን ሊያውቁ የሚችሉት ደግሞ የእናት ቋንቋቸውን አውቀው ከማህበረሰባቸው አባላት ጋር በራሳቸው ቋንቋ መነጋገር ሲችሉ ነው። ከኢትዮጵያዊያን የአገር ልጆችና አረጋዊያን ጋር ሃሳብ መጋራት መቻል ከትውልድ ትውልድ የግንኙነት መስመርን የሚያጠናክር ነው። የራሱን ቋንቋ





የማይናገር የኢትዮጵያዊ ዝርያ ያለው አሜሪካዊ፣ ይህ ዕድል ሊኖረው አይችልም። ልጆች ያለፈውን ታሪካቸውንና ባህላቸውን በሚገባ ካልተረዱና አጥንተው ካልተገነዘቡ የራሳቸውን ዓለም የሚረዱበት በራስ መተማመንና ጠንካራ መንፈስ ሳይዙ ያድጋሉ።

በእርግጥም የእናት ልሳን የሆነው ቋንቋ ስላወቁ ብቻ ወይንም ስለተናገሩ፣ልጆቻችሁ ሙሉ ደስተኛ የሆነ ህይወት ይኖራቸዋል ማለት አይደለም። ያም ሆኖ፣ ቋንቋ የመጡበትን ለመረዳት፣ ስር መሰረታቸውን ለመጨበጥ ዋነኛው ቁልፍ መሆኑ ሊካድ አይገባም። ለምሳሌ ከኢትዮጵያዊያን አብራክ የተገኘ አንድ ትውልደ አሜሪካዊን እንውሰድ፤ በትምህርት እጅግ አመርቂ ውጤቶችን የሚያገኝ ብሩህ አእምሮ አለው። በትላልቆቹ የአይቪ ሊግ ኮሌጆች እውቀት ቀስሟል። አሁን የደለበ ደመወዝ ያገኛል፤ የሀብት ችግር የለበትም። የናት ቋንቋ ችግር ግን አለበት። አስር የሚሆኑ ቃላት እንኳን በእናቱ ልሳን መናገር አይችልም። አስቡት፣ከሩቅ አገሮች የሼክስፒርን ስነ-ጽሁፍ አንብቦ፣ ከግሪኮች ፍልስፍና አክሎበት፣ የአሜሪካዊያንን የዴሞክራሲና የሃያልነት ታሪክ አብጠርጥሮ ሲያውቅ፣ ለሱ ቅርብ የሆነውን፣ በየለቱ በቤት ውስጥ የሚነገረውን የእናት አባቱ ልሳንና ባህል ባዳ ሆኖበታል።

ይሄንን ሁኔታ ማስታረቅ ሲያቅተው ከቤተሰቡ ይለያል፣ ይርቃል። የሚበዙት ባልንጀሮቹ አሜሪካዊያን ናቸው። በባህልም ባስተሳሰብም አሜሪካዊ ይሆናል። ያም ሆኖ ግን የፈለገውን ያህል አሜሪካዊ ቢሆን ከማንነቱ ከትውልድ ስር-መሰረቱ ስለተራራቀ ብዙውን ጊዜ ባዶነት ይሰማዋል፤ ቅርም ይለዋል። ከትውልድ ስር-መሰረት ጋር አለመተዋወቅና መራራቅ ደግሞ በራስ አለመተማመንን ያመጣል። ለራሱ ባህል ባእድ መሆን እንዲያም ሲል ከራስ ቤተሰብና ከወላጆችም ጭምር መራቅን ያስከትላል። ይሄ ሁኔታ ከልጅ ልጅ ሲዋረድ ደግሞ በወደፊቱ

ትውልድ ላይ የሚያስከትለውን የረጂም ጊዜ የባህልና ማንነት መሸርሸር አስቡበት።

በሌላ በኩል ደግሞ፣ኢትዮጵያዊያን ወላጆች ለማየት የሚሳናቸው አንድ ሌላ ቁምነገር አለ። በአሜሪካ አገር ተወልደው ያደጉት ልጆቻቸው መጀመሪያ አሜሪካዊያን ናቸው፤ ቀጥሎ ደግሞ አፍሪካዊ አሜሪካዊያንም ናቸው። አፍሪካዊ አሜሪካዊነታቸውን መካድ አይችሉም። ብዙ ኢትዮጵያዊያን ወላጆች አፍሪካዊ መሆናችንን ይቀበላሉ፤ አሜሪካዊነታችንንም እንዲሁ፤ ሆኖም አፍሪካ-አሜሪካዊነታችንን ለመቀበል ሲከብዳቸው እናያለን። ምን እንድንሆን ነው የሚፈልጉት? "ነጭ አሜሪካዊያን?" አንድ የማይካድ አቢይ ቁምነገር አለ። ልጆቻቸው አፍሪካ አሜሪካዊ እንዳልሆኑ ገና በለጋ የልጅነት አእምሯቸው የሚነግሩ ወላጆች ህጻናቱን፣ ቆይተው ደግሞ ሲያድጉ ግራ የገባቸውና በአስተሳሰብ የተመሰቃቀሉ ሰዎች እንዲሆኑ ማዘጋጀት ነው። ይሄ ደግሞ በህይወታቸው ላይ አጉል የሆነ አሉታዊ አንድምታን ያጠላል። ይሄ ብቻ አይደለም፤ ለሰው ልጅ መብትና እኩልነት ታግለው፣ በህይወታቸው ጭምር መስዋእትነት ከፍለው ዛሬ የተሳካ ህይወት ይዘን የምንኖርባት አሜሪካን ትተውልን ያለፉትን አፍሪካዊ አሜሪካዊያን ውለታቸውን መንፈግ ይሆናል።

አንድ እውነት አለ፤ ኢትዮጵያዊያን ወላጆች ስጋቶች አሏቸው። አንዳንድ ጥቁር አሜሪካዊያን ወንድሞቻችንና እህቶቻችንን የተጠናወተ አጉል የሆነ ጥራዝ-ነጠቅ ባህል ልጆቻቸውን እንዳያበላሽ ይፈራሉ። የወንጀል ህይወትን ማዳነቅ፣ ለትምህርት ዋጋ አለመስጠት፣ በስራ ታታሪ አለመሆን፣ አባት በሌለባቸው ቤቶች ህጻናት ማደጋቸው እና የመሳሰሉት አጉል ባህርያት በልጆቻቸው እንዲደርሱ ኢትዮጵያዊያን ወላጆች ፈጽሞ አይፈልጉም። ይህንን ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው። ያም ሆኖ ግን እንደ ጥቁር ማህበረሰብነታችን ደግሞ ከጥቁር አሜሪካዊያንም አልፎ በዓለም ዙሪያ ካሉ ጥቁር ህዝቦችም የሚያስተሳስረን ገመድ አለ።





ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ከሌላው ዓለም የተለየ ለዘመናት የቆዩ ባህሎችና የነጻነት ታሪክ ቢኖራትም፤ የምንመሳሰለውን ከፍተኛውን የጥቁር ህዝቦች ቤተሰብ ልንዘነጋውና ልናርቀው አንችልም። ስለሆነም ልጆቻችሁ ጠንካራና ሰው አፍቃሪ የሆነ የታላቅ ጥቁር ዘር አካል መሆናቸውን አስገንዝቧቸው፣ አረጋግጡላቸው።

በዚህ ላይ የራሳቸው የሆነውን ልዩ ቋንቋና ባህል አስጨብጧቸው። ይህንን ካደረጋችሁ ልጆቻችሁ በራሳቸው የሚተማመኑ፣ የሚያኮሩና የነቁ፣ በሳል ህሊና ያላቸው ኢትዮጵያዊያን ይሆናሉ። እናንተም ከወላጆቻችሁ ለዘመናት ሲተላለፍ የቆየውን የቤተሰብ ባህልና እውቀት ለልጆቻችሁ ታወርሳላችሁ፤ በዚህም የኮራችሁና ሃላፊነታችሁን በሚገባ ያከናወናችሁ ወላጆች መሆናችሁን ታረጋግጣላችሁ።

ይሄ ካልሆነ ልክ እንደዚህ መልእክት፤ ደብዳቤውን ልጃችሁ በእንግሊዝኛ ይጽፍና ወዳማርኛ ተተርጉሞ ታነቡታላችሁ። እኔ ዛሬ የቋንቋና ባህል ክፍተቴን ለመሙላት፤ አስቀድሜ ልናገረው ያልፈለኩትን አማርኛ ልማር ወደ አዲስ አበባ ሄጄ አንድ ወር ሙሉ የቋንቋ አስተማሪ ቀጥሬ ንባብና ጽህፈቴን እያሻሻልኩ ነው። ብዙ ለመማር አቅጃለሁ፤ ሆኖም ማን እንደልጅ አእምሮ፤ ቶሎ ለቀም ማድረግ የምችልበት ጊዜ አልፏል፤ ቢሆንም ትግሌን አላቆምም። እናንተም ከልጆቻችሁ ጋር ዛሬ ትግላችሁን አታቁሙ፤ ቋንቋ ዛሬ እንጂ ነገ አይማሩምና።
ከተስፋዬ ንጉሴ-- በእንግሊዝኛ ተጽፎ፤ ወደ አማርኛ
የተተረጎመ

# ምዕራፍ አምስት

## ተግዳሮቶችን የሚቋቋሙ ልጆችን ማፍራት

ልጆቻችንን፣ በሕይወት ጎዳናቸው ውስጥ፣ ከአደጋ ልንከልላቸው እንሞክር ይሆናል:: "ልጆቼ ችግር እንዳያዩብኝ፣ በሕይወታቸው ውስጥ ፈተና እንዳያጋጥምብኝ" ብለን በተቻለን እንጣጣር ይሆናል:: ልጆቻችንን ከችግር ልንከልላቸው መሞከራችን ጥሩም ተገቢም ነው:: ነገር ግን፣ አንድ በጣም አስፈላጊ የሆነና ከዚህ ጋር ተያይዞ መሄድ ያለበት ነገር አለ:: ይኸውም፣ ፈተና ቢመጣ ሊጋፈጡ የሚችሉበትን ዐቅም በልጆች ሕይወት ማጎልበት በጣም አስፈላጊ ነው ::

ብዙ ጊዜ፣ ወደ ልጆቻችን ሕይወት ሊመጣ ስለሚችል ፈተና ማሰብ አንፈልግም:: "ችግርን መጥራት አያስፈልግም" በሚል፣ ችላ እንለዋለን:: ነገር ግን፣ አንድ ማስታወስ ያለብን ትልቅ ነጥብ አለ:: በመጀመርያ፣ የምንኖረው በዚች ዓለም ውስጥ መሆኑን መዘንጋት የለብንም:: በዚች ዓለም ውስጥ ደግሞ፣ ወደድንም ጠላንም ፈተና አለ:: ቤት ውስጥ ሁሉን ልናሟላላቸው ብንጥር እንኳ እኛ በሌለንበት በውጭ፣ ችግር ያጋጥማቸዋል:: በተለይ እያደጉ ሲመጡ በትምህርት ቤት፣ በጓደኛ ዘንድ የተለያየ ግፊት፣ ፈተናና ችግር ማጋጠሙ አይቀሬ ነው::

በቤት ውስጥም፣ ያላሰብነው ችግር ሊመጣ ይችላል፤ አለመግባባት፣ ጥል፣ ህመም፣የገንዘብ ችግር፣ በቤተሰብ መካከል ሊከሰት ይችላል:: በዚህ ሰዓት፣ ቤተሰቦቻቸው አርቀው አይተው ችግርን እንዲጋፈጡ ያዘጋጇቸውና ያስታጠቋቸው ልጆች ችግሩንና ፈተናውን በጥንካሬ መወጣት ሲችሉ፣ ሳይታጠቁ፣ ስለ ችግር





ፈተና ምንም ሳይዘጋጁ ባዶዋቸውን የሚጋፈጡ ልጆች ደግሞ፣ በጣም ይጎዳሉ:: ካሁኑ አርቀን አይተን፣ ጤነኛ የሆኑ ችግርን መጋፈጫ ዘዴዎች ለልጆቻችን ካስተማርናቸው ግን፣ ንፋሱ ቢመጣ እንኳ መከላከያ መንገዱን እንዲያውቁ ወይም በሁሉ መሀል ጠንክረው እንዲቆሙ እናዘጋጃቸዋለን::

በሁለተኛ ደረጃ፣ ልጆቻችንን ከልጅነታቸው ጀምሮ ስራዬ ብለን ስናስታጥቃቸው፣ ለልጅነት ጊዜያቸው ብቻ እየጠቀምናቸው አይደለም፤ ለሕይወታቸው የሚቆይላቸው፣ ነገ በእድሜ ትልቅ ሲሆኑ የሚረዳቸው ነገር እያስተማርናቸው ነው:: ሰው ራሱን ችሎ በሚኖርበት በትልቅ እድሜው፣ ችግሩን የሚጋፈጥበት ዘዴ፣ በአብዛኛው በልጅነቱ የተማረውን መርሆን የተከተለ ነው:: ዛሬ ያስተማርናቸው ትምህርት፣ ነገ በትልቅ እድሜያቸው፣ ችግርን በጤነኛ መልክ እንዲቋቋሙት፣ ትልቅ ድጋፍ ይሆናቸዋል::

ወላጅ እንደ መሆናችን መጠን፣ ዋነኛ ግባችን ሊሆን የሚገባው፣ ልጆቻችን እንዲጠነክሩ፣ ለሚያጋጥማቸው የሕይወት ንፋስ እንዲዘጋጁ እንጂ፣ እኛ ልንከልላቸው በሌለንበት እንዲፍረከረኩ አይደለም:: ሁልጊዜ አብረናቸው እንደማንኖር አስታውሰን፣ ለልጅነታቸው ጊዜም ሆነ ለትልቅ እድሜያቸው ለሚጠቅማቸው ነገር እንሥራ:: "ልጆቻችንን ለማስታጠቅ ምን ማድረግ እንችላለን" የሚለውን ጥያቄ፣ ለመመለስ እንዲረዳን የሚከተሉትን እውነታዎች እንመልከት፤

### <u>ጠንካራ ተግባቦት መፍጠር</u>

ልጆቻችንን ልንገነባቸው፣ ልናጠነክራቸው የምንችልበት ዋነኛ መንገድ፣ ከልጆቻችን ጋር የንግግር ባሕልን በማዳበር ነው:: ያ ምን ማለት ነው? ግልጽነት የሞላው የንግግር ሂደት በእኛ እና በልጆቻችን መሐል መኖሩ ነው፤ ልጆቻችን የተለያዩ ነገሮችን አንስተው፣ እኛን በግልጽ ማውራት መቻላቸው፣ ስለተለያዩ የሕይወት ገጠመኞች፣ (እንደየዕድሜያቸው መጠን) ከልጆቻችን

ጋር በግልጽ ልንወያይ መቻላችን፣ አንድ ነገር ቢነግሩን፣ እኛ ሳንስቅባቸው ወይም በቶሎ ሳንቆጣቸው ልባችንን ከፍተን እንደምናዳምጣቸው ማወቃቸው፣ በሁሉ ነገር ትክክል ነኝ ሳንል የልጆቻችንንም ሐሳብ መስማት መቻላችን፣ ማለት ነው:: መልካም የሆነ የንግግር ባሕልን ከልጆቻችን ጋር ብናጎለብት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፤

- ልጆቻችን እንዲህ አይነት የንግግር ትስስር ከእኛ ጋር ኖሮዋቸው ሲያድጉ፣ ለሕይወታቸው የሚጠቅማቸው ነገር በውስጣቸው እየተሰራ ይመጣል:: በግልጽ ስሜትን ማውራት፣ ችግርን ውስጥ በመቅበር ፈንታ መጋፈጥ፣ በማይጠቅም ሁኔታ ራስን በመኮነን ፈንታ መላ ላይ ማተኮር የመሳሰሉ፣ ጤነኛ የሆኑ ችግርን መጋፈጫ ዘዴዎች፣ የሕይወታቸው ክፍል ይሆናሉ::
- እንዲህ አይነት የንግግር ትስስር ከእኛ ጋር ኖሮዋቸው ሲያድጉ፣ ልጆቻችን ያምኑናል:: ወደ ፊት የሆነ ችግር ውስጥ ቢገቡ፣ ቢፈተኑ፣ ከእኛ ጋር ጤነኛ በሆነ መንገድ መነጋገር ተምረዋልና፣ ሳይፈሩና ሳይሳቀቁ ያማክሩናል፤እኛም በግልጽ መጥተው ሲያማክሩን ልንረዳቸው፣ ልንመክራቸው፣ ልናግዛቸው እድል እናገኛለን::
- ከእኛ ጋር ጥሩ የሆነ የንግግር ትስስር ሲኖራቸው ልጆቻችን ያከብሩናል:: በኂላ ስንመክራቸው፣ ከልብ አዳምጠው ሊቀበሉን ትልቅ እድል ይኖራል::

- በአንጻሩ ከኛ ጋር ግልጽ የሆነ የንግግር ትስስር ሳይኖራቸው ካደጉ፣ ፈተና ሲመጣባቸው እንኳን ሊነግሩን፣ ጭራሽ ይርቁናል፤ ወይም ስሜታቸውን ይደብቁናል::
- ስለ ነገሮች ከእነሱ ጋር በመወያየት ፋንታ፣ "እኔ ያልኩትን ብቻ ስሙ" እያልን፣ እኛ ብቻ እያወራን ካሳደግናቸው፣ በኂላ እድሜያቸው ሲሄድ፣ ሲተልቅ





"ምክራችሁን አልፈልግም፣ የራሳችሁ ጉዳይ"፣ ብለው በራሳቸው መንገድ ይሄዳሉ::

- ከልጅነታቸው፣ ጤነኛ የሆነ ስሜትን መግለጫ መንገድ ካልተማሩ ኂላ፣ ራስን መጉዳት፣ ችግርን ለመሸፈን ሱስ ውስጥ መግባት፣ የመሳሰሉት ጎጂ ነገሮች ውስጥ ሊጠመዱ ይችላሉ::

ብዙ ጊዜ በባህላችን ውስጥ፣ ወላጅ ከልጅ ጋር በግልጽ ነገሮችን አይወያይም:: ከወላጅ ጋር ባለው የንግግር ልውውጥ፣ የልጅ ግልጽነትን እናጣጥላለን፤ እንዲያውም የልጅን ግልጽነት አንፈልግም:: "ወላጅህን አዳምጥ፤ የተነገረህን አድርግ፤ ከዚያም ዝም በል"፤ ነው የምንለው::

ባህላችን፣ አብዛኛውን ጊዜ፣ ስሜትን ገልጾ መናገርን አያበረታታም:: ልጅ የተሰማውን ነገር ቢሆን መዋጡ፣ እንደተገቢ ነገር ይታያል:: ቤተሰብ ፊት መጥፎ ነገር ያልተናገረ፣ ክፉ የማይወጣው ልጅ፣ ችግር እንደሌለው ተደርጎ ይታያል:: በግልጽ የተሰማውን የሚናገር ደግሞ፣ "ባለጌ፤ ዝም አትልም! አንተ ወላጅን አታከብርም" ተብሎ ይመታል:: ልጅ እኛ ፊት ዝም አለ ማለት፣ በችግር ውስጥ እያለፈ አይደለም ማለት አይደለም፤ እኛ ፊት ዝም ብሎ፣ ሁሉን ጥሩ አስመስሎ እያሳየን፣ በውስጡ ግን ኀይለኛ ጭንቀትና ውጥረት ውስጥ ሊያልፍ ይችላል:: ልጅ ወላጅ ፊት የጨዋነት ፊት አሳየ ማለት፣ ከጥፋት ርቋል ማለት አይደለም:: ልጆች ወላጅ ፊት ድምጻቸውን አጥፍተው፣ ወይም እኛን የሚያስደስት የሚመስላቸውን ነገር እያደረጉ፣ ግን በትምህርት ቤት ሲሆኑ፣ ከጓደኞቻቸው ጋር ሲሆኑ፣ ፍጹም የተለየና የማናምነው ነገር ሊያደርጉ ይችላሉ::

24 ሠዓት ከልጆቻችን ጋር አይደለንም:: በተለይ ልጆቻችን እያደጉ ሲመጡ፣ ከእኛ ተለይተው የሚያሳልፉት ጊዜ እየሰፋ ይመጣል:: አገራችንን ጥለን ባለንበት፣ ለእነርሱ ያለናቸው እኛ ብቻ በሆንበት በዚህ ቦታ፣ ፈተና ሲያፈጥባቸው ልጆቻችን በግልጽ መጥተው እንዲነግሩን እንጂ፣ ሁሉን ጉዳይ ደብቀውን በራሳቸው መንገድ

እንዲጋፈጡት የምንፈልግ ብዙ የለንም:: ያብራካችን ክፋዮች ግልጽ እንዲሆኑልን ከፈለግን፣ ይህንን ልብ እንበል፤ በግድ ግልጽ ልናደርጋቸው አንችልም!! ወላጆች ስራዬ ብለን፣ በቀን በቀን ምሳሌ ስናስተምራቸው፣ ያኔ ነው ያ ጸባይ የሚዋሀዳቸው:: በልጆቻችን ዘንድ ግልጽነትን እንዴት እናበረታታለን?

- ከምንም በፊት፣ ግልጽነት ጨዋ መስሎ ዝም ከማለት፣ በብዙ ዕጥፍ እንደሚሻል እንረዳ::

ልጃችን ሁሉን ጥሩ አስመስሎ፣ ግን በሚጎዳው ነገር ውስጥ ከሚያልፍ፣ ስላጋጠመው ነገር በግልጽ ቢነግረን ይሻላል:: እዚህ ጋ ግልጽነት ስንል፣ ለወላጅ ክብርን የነሣ ንግግር ወይም በልቡ ያሰበውን ሁሉ ወላጅን በማያከብር ሁኔታ የሚናገር ልጅ ማለት አይደለም:: ግልጽነት ማለት፣ የተሰማውን ገልጾ የሚናገር፣ ሲያዝን፣ ሲናደድ ወይም በአስቸጋሪ ነገር ውስጥ ሲያልፍ፣ ለወላጁ መጥቶ የሚናገር፣ ፊቱን አሳምሮ፣ ሁሉ ጥሩ እንደ ሆነ ለመግለጽ የማይሞክር ልጅ ማለት ነው:: እንዲህ ዐይነቱ ግልጽነት በእጅጉ ጠቃሚ ነው::

- እውነት መናገር በቤታችን ትልቅ ዋጋ ሊኖረው ይገባል::

ልጅ ሁልጊዜ፣ "እውነት ልናገር" ብሎ መጥቶ ከነገረን፣ ያንን እንደ ዋጋ በመቁጠር ልናመሰግናቸው እንዲሁም ቅጣቱን ልናቀልላቸው ይገባል:: "እንዲህ አይነት ስህተት ሰራሁ" ብለው የልባቸውን ገልጸው ሲነግሩን፣ እውነቱን መጥተው መናገራቸው ምንም ዋጋ ሳይኖረው፣ ወዲያው ከጮኽንባቸው ወይም ከተገረፉ፣ "እውነት መናገሬ ነው ይህን ያደረሰብኝ" ብለው ያስባሉ፤ ወደፊት ተመሳሳይ ነገር ሲመጣ፣ ለእኛ መጥተው ማናቸውንም ነገር አይነግሩንም:: ያታለለ ልጅ ሳይገረፍ ሲታለፍ፣ እውነትን መናገር ግን ቅጣትን እንኳ እንደማያቀል ስለሚረዱ፣ እውነተኛ ለመሆን አይበረታቱም፤ በፈንታው፣ እኛ ፊት ተዋናይ ሆነው መቅረብን ይማራሉ::

ትልቁ ቁም ነገር፣ እውነት መናገራቸው እንደሆነ ከሕጻንነታቸው ጀምሮ እናስተምራቸው:: "እውነቱን እንነጋገር፤ ለሚያጋጥሙን





ነገሮች አብረን መላ እንፈልጋለን" የሚለው ባህል፣ በቤተሰባችን ውስጥ መሰረት እንዲጥል እናድርግ:: እንዲህ አድርገን ስናስተምራቸው፣ እውነትን እየወደዷት፣ ፍሬዋ ጥሩ እንደ ሆነ እየተገነዘቡ ይመጣሉ::"እኔ ቤተሰቦቼ ፊት ሳልፈራ ግልጹን መናገር እችላለሁ" ብለው ያምናሉ:: ኋላ አድገው፣ ከበድ ያለ ችግር ሲገጥማቸው፣ ያቺ የተለማመዷትን እውነት ይዘው እኛ ዘንድ ይመጣሉ፤ መላ ላይ ለማተኮርም እድሉ ይከፈታል:: በልጅነት ብቻ ሳይሆን በትልቅነት እድሜያቸውም፣ እውነትን ተጋፍጦ መላ ላይ የማተኮር ትልቅ ጥቅሙ ስለሚገባቸው በዚያው ልምምድ ይቀጥላሉ::

- ልጆቻችን ስለሆነ ነገር ሲነግሩን፣ እኛ ስለምናሳየው የፊት ገጽታ እንጠንቀቅ::

አንድ ነገር በነገሩን ቁጥር፣ በቶሎ ብለን የደነበረ ፊት አናሳይ:: ይህ በተለይ፣ የሚያልፉበትን ውስጣቸውን የሚጎዳ ነገር፣ ወይም ያጋጠማቸውን ገልጸው ለመንገር ትልቅ ተጽእኖ አለው:: በቶሎ የምንደነግጥ ከሆነ፣ ልጆች ለየት ያለ ነገር እኛ ፊት መጥተው መናገርን በጣም ይፈራሉ:: ለምሳሌ የ11 ዓመት ልጃችን መጥታ፣ "ጓደኛዬ ክፍል ውስጥ የሆነ ልጅ ወዳለች" ብትለን፣ ፊታችንን ቅጭም አድርገን፣ "በስመአብ ወልድ ሂጅ ከዚህ" ብንላት፣ በሚቀጥለው አስደንጋጭ ነገር ለመንገር ትፈራለች:: የእኛ ምላሽ ስላስደነበራት፣ በልቧ ትይዘዋለች::

ልጆቻችን "ተጨንቄያለሁ፤ በመጥፎ ነገሮች ውስጥ እያለፍኩ ነው" ብለው የልባቸውን ገልጸው ሲያወሩን፣ ከእነርሱ በላይ ተሰባብረን ቁጭ አንበል:: ወላጅ እንደዚያ ተወጥሮ ሲያዩ፣ የሚያልፉበት ነገር መፍትሄ የለሽ እንደሆነ ይሰማቸዋልና፤ ወደፊትም ውስጣዊ ስሜታቸውን አውጥተው ለሰው መናገር እየፈሩ ይመጣሉ:: እዚ ላይ፣ እኛ ውስጣችን አይደነግጥም ወይም አይጨነቅም እያልን አይደለም:: እውነትም የሚያስደነግጠን፣ የሚያስጨንቀን ነገር ልንሰማ እንችላለን፤ ኋላ በራሳችን መንገድ ነገሩን መጋፈጡም ጠቃሚ ነው:: ልጅን በምናዳምጥበት ጊዜ ግን፣

ተረጋግተን፣ ስሜታችንን ተቆጣጥረን፣ ሁሉን ለመስማት ዝግጁ እንደሆንን የሚያሳይ ገጽታ ይዘን እንቀመጥ፤ ሲያወሩን፣ ንግግራችንን ብቻ ሳይሆን ፊታችንንም ያያሉና።

- ልጆቻችን ላይ ከባድ ሸክም እንዳንጭን እንጠንቀቅ።

“የእኔ ልጅማ መቼም ስሕተት አያደርግም” የሚል ጫና ካበዛንባቸው፣ ወይም እንዲህ ዐይነት አመለካከት እንዳለን ከተረዱ፣ ካሰብናቸው ቦታ ጎድለው መታየት አይፈልጉምና ያልሆኑትን ሆነው ለመቅረብ ሙከራ ሊያደርጉ ይችላሉ። ዐቅማቸውንና ችሎታቸውን ያላገናዘበ መስፈርት ካለን፣ ልጆቻችን መስፈርቱን ባላሟሉ ጊዜ ትልቅ የበደለኝነት ስሜት ስለሚሰማቸው፣ የሚያልፉበትን ነገርም ሊያጋሩን አይደፍሩም። አላስፈላጊ በሆነ በጸጸት ስሜት እንዳይዋጡ፣ ልጆቻችን ከእኛም መደበቅ እንዳይማሩ ሚዛናችንን እናስተካክል።

ልጆች ባጠቃላይ፣ አንድ ነገር አውጥተው ቢነግሩን፣ ወዲያው ወደ ቁጣ፣ ጭንቀት፣ ድንጋጤና ውጥረት እንደማንዞር፣ መሰረት ያለን ጠንካራ መሆናችንን ካወቁ ፣ የሚያጋጥማቸውን መጥተው በግልጽ ለእኛ መንገር ይበረታታሉ፤ “ወላጆቼ፣ ይህን ያን አምጥቼ ልነግራቸው የምችላቸው ዓይነት ናቸው፤ ስለዚህም ምርኩዜ ናቸው” ብለው ማሰብም ይጀምራሉ። እኛም እውነቱን ካወቅን፣ ለማበረታታት፣ ለመምከር፣ ወደ መጥፎ መንገድ እንዳይሄዱ አንድ ነገር ለማድረግ፣ ዕድሉን እናገኛለን።





## ***ልጆቻችንን በእውቀት ማስታጠቅ***

ከላይ እንደተመለከትነው፣ ግልጽነት የሞላው የንግግር ትስስር፣ በጣም ልናተኩርበት የሚገባ፣ አስፈላጊ እርምጃ ነው። ሌላኛውና ልጆቻችንን የምናዘጋጅበት ዋነኛ መንገድ፣ በሕይወት ጉዞዋቸው ውስጥ ሊያጋጥሟቸው የሚችሉትን የቀን ከቀን ፈተናዎች ከወዲሁ መዝነን፣ ስለነዚህ ጉዳዮች ከእነሱ ጋር በግልጽ መወያየት ነው። በትምህርት ቤት ሆነ በጓደኛ ግፊት፣ በቤት ሆነ በውጭ፣ ልጆቻችንን ሊያጋጥሟቸው የሚችሉትን አቀባዎች ከወዲሁ አርቀን አይተን፣ ለልጆቻችን በዛ ነገር ላይ ግንዛቤን መስጠት በጣም አስፈላጊ ነው።

አብዛኛውን ጊዜ፣ ስለእነዚህ ጉዳዮች መወያየት የምንጀምረው፣ ችግሩ ከመጣና በልጆቻችን ላይ ከደረሰ በኋላ ነው። ያ የተሳሳተ እርምጃ ነው፤ ምንም ሳያውቁና ሳይታጠቁ ብቻቸውን ሆነው ችግሩን የተጋፈጡት ልጆቻችንም ይጎዳሉ። ካሁኑ ስለ እነዚህ ጉዳዮች ጥሩ ግንዛቤ ካልሰጠናቸው፣ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚማሩት ከጓደኛ አፍ ወይ ከአሳሳች መልእክተኛ እንደሆነ ተረድተን፣ ስለተለያዩ ጉዳዮች በግልጽ እናውራቸው፤*ልጆቻችንን በእውቀት ልናስታጥቅ የሚገባን በምን በምን ጉዳይ ላይ ነው?*

### ***1.አደንዛዥ ዕጽ መጠጥ የተቃራኒ ጾታ ጎዳይ***

> “ሁሉም ምሁራን የሚስማሙበት አንድ ነጥብ አለ፤ ያም ከወዲሁ ልጅን ማስታጠቅ ድራግን መከላከያ ዋነኛው መንገድ መሆኑን ነው።”[23]

አደንዛዥ እጽ፣ መጠጥን በተመለከተ፣ ስራዬ ብለን ለልጆቻችን አስፈላጊ እውቀትና ግንዛቤ መስጠት አለብን፤ “የኔ ልጆች በዚህ ነገር ውስጥ አያልፉም” ብለን፣ ነገሩን ችላ

[23] Steinberg Laurence (2011) <u>you and your adolescent</u>, Simon and Schuster

ከማለት እንቆጠብ:: እውነቱ ሌላ ነውና፤ ልጆች በየቀኑ ለእነዚህ ነገር ይጋለጣሉና::

> "ከ15 እስከ 20 አመት እድሜ ያሉ ፣መኪና አደጋ ውስጥ የገቡ ልጆችን በተመለከተ፤ ወደ 29% የሚጠጉት ልጆች አደጋ የደረሰባቸው፣ ጠጥተው በማሽከርከራቸው ምክንያት ነው።"[24]
>
> "ከአራት (ልጆች) አንዱ ወይም ከዚያ በላይ /28.7% በት/ቤት እያሉ ህገወጥ ዕጽ (ድራግ) እንዲሸጡ ወይም ለራሳቸው እንዲጠቀሙ ተሰጥቶዋቸዋል"[25]
>
> "ልጆችን በተመለከተ፤ ከአራቱ አንዱ ወይም ከዚያ በላይ፣ /28.3%፤ በአሁኑ ወቅት ከመጠን በላይ ይጠጣሉ።"[26]
>
> "ወደ ግማሽ የሚጠጉት (46.7%) ልጆች 2ተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ከማጠናቀቃቸው በፊት ድንግልናቸውን አጥተዋል። ከ15 እስከ 24 አመት ባሉ ወጣቶች፣ በየአመቱ 9.1 የግብረስጋ ግንኙነት ኢንፌክሽን ይከሰታል"[27]

*ዋናው ነጥቡ፤ እነዚህን ስታቲስቲኮች ተመልከቶ ወላጅ ውጥረት ውስጥ እንዲገባ አይደለም፤ ከስር የተጻፈውን ሀያል እውነት እንዲመለከቱ እንጂ፡*

> "ወላጆች በልጆቻቸው ላይ፣ ከጓደኛ፣ ከሙዚቃ፣ ከቴሌቭዥን፣ ከኢንተርኔትና ከታወቁ ሰዎች የበለጠ ተጽእኖ አላቸው። ስለ አደገኛ እጾችና መጠጥ ከወላጆቻቸው የሚማሩ ልጆች፣ በሱስ የመጠመድ እድላቸው፣ ይህንን እውቀት ከወላጆቻቸው ካላገኙ ልጆች ሲነጻጸር፣ በ50% ያነሰ ነው።"[28]

**ከላይ እንደምንመለከተው፣ ስለእነዚህ ጉዳዮች ከልጆቻችን ጋር በግልጽ የመወያየት ልምድ ማዳበሩ በጣም አስፈላጊ ነው፤ እነዚህ ነገሮች ሊኖራቸው ስለሚችለው ጉዳት፣ በሕይወታቸው ውስጥ ሊያመጡ ስለሚችሉት ክስረት ለልጆቻችን እንንገር::**

---

[24] Cline and Jim Fay_(2006) Parenting teens with love and logic, Nava Press Publishing

[25] )ከላይ ያለውን ይመልከቱ
[26] )ከላይ ያለውን ይመልከቱ
[27] )ከላይ ያለውን ይመልከቱ
[28] Drug free.org





*ለልጆቻችን ግንዛቤን ስንሰጥ፤ አነጋገራችንና አቀራረባችን ትልቅ ኀይል አለው::*

☞ ሁሌ ምክር ልምከራችሁ እያልን፣ ቁጭ አድርገን መምከር ላይ ካተኮርን፣ በቶሎ ሊሰለቻቸው፣ጆሮ ዳባ ልበስ ሊሉን ይችላሉ፤ አጋጣሚዎችን ተጠቅመን የምናስተላልፈው መልእክት ትልቅ ተጽእኖ ሊያደርግ ይችላል:: ለምሳሌ፣ የሚወዱት የፊልም ተዋናይ "አደንዛዥ ዕፅ ወሠደ" የሚል ዜና ከመጣ፣ ስለዚያ ነገር ከእነርሱ ጋር ለመነጋገሪያ ጥሩ አጋጣሚ ነው። ቴሌቭዥን አብረን ስንመለከት፣ እነርሱ ሊረዱት የሚገባ እውነት ካየን፣ በዚያው አጋጣሚ ተጠቅመን ግንዛቤ ማስተላለፍ እንችላለን።

☞ ለልጆቻችን ስለነዚህ ነገሮች መጥፎነት ስናስረዳ፣ ለእነርሱ በሚመስጥ መልክ እናድርገው:: ምሳሌ ብንወስድ፣ "ሲጋራ ማጨስ ካንሰር ያመጣል" ብለን፣ ለ12 አመት ልጃችን ብንነግር፣ ያ አእምሮዋ ውስጥ ላይገባ ይችላል:: "ልብስሽን፣ ጸጉርሽን ያሸተዋል፤ ጥርስሽን ቢጫ ያደርገዋል" ብለን ለልጃችን ብንነግር ግን፣ የበለጠ ልቧን ከፍታ ታዳምጠናለች:: "አደንዛዥ ዕጽ ውስጥ ብትገባ፣ ሕይወትህን ያበላሸዋል" ብለን በደፈናው ለልጃችን ብንነግር፣ ጭራሽ ላይገነዘበው ይችላል፤ በፋንታው፣ ለምሳሌ ስፖርት የሚወድ ልጅ ከሆነ፣ አደንዛዥ ዕጽ በስፖርት እንዳትመጥቅ ያደርግሀል፤ ሰውነትህን አድክሞ ያስቀራል ብንለው የበለጠ ልቡን ከፍቶ ያዳምጠናል::

☞ከእነርሱ ቦታ ሆነን፣ የሚመጣባቸውን ግፊትና ሊሰሙት የሚችሉትን መሳጭ የውሸት መልእክቶች መገምገሙ አስፈላጊ ነው፤ በእነሱ ላይ የሚደርሰውን ግፊት ከተረዳን፣ እነሱን በሚመስጣቸው መልክ ምክራችንን ልናስተላልፍ፣ እነሱም ሊያዳምጡን፣ እድል ይኖራልና:: ምሳሌ ብንወስድ፣ ልጆች መጠጥ ሰውን ደፋር ያደርጋል የሚለውን መልእክት ደጋግመው ይሰማሉ:: ያንን መልእክት የሚቃረን እውነት እንስጣቸው:: "መጠጥ ለጊዜው ያደነዝዛል እንጂ ደፋር አያደርግም፤ አንድ

ሰው ለጊዜው፣ በመጠጥ ሀይል ደፋር የሆነ ቢመስለው እንኳ፣ በነጋታው የበለጠ ፍርሀት፣ ሀፍረት ይውጠዋል"፤ ብለን እናስረዳቸው:: "ዝግጅት፣ (ፓርቲ) ሲኖር፣ መጠጣት ደስተኛ ያደርጋል" የሚለው፣ ሌላው ልጆች የሚሰሙት ውሸት ነው:: ለመደሰት መጠጥ መጠጣት የለብህም፤ መጠጥ የጠጡ ልጆች፣ በነጋታው ያደረጉትም ጭራሽ ስለሚጠፋባቸው፣ ጥሩ ትዝታም አይኖራቸው፣ ብለን እንንገር:: ለሴት ልጃችን፣ "ወንድ አብሮሽ ሆነ ማለት ወደደሽ ማለት አይደለም፤ ምንም የፍቅር ስሜት በውስጣቸው ሳይኖር፣ የወደዱ መስለው፣ ከሴት ጋር አብረው ጊዜ የሚያሳልፉ፣ ብዙ ወንዶች አሉ::" ብለን እንንገር:: "ወንድ መልክሽን ወደደው ማለት፣ አንቺን ከልቡ ወዶሻል ማለት አይደለም፤" እንበል:: በዚህ መልክ፣ ከጓደኞቻቸው፣ ሚድያ የሚሰሙት መልእክት እየገመገምን፣ ተቃራኒውን ግንዛቤ ስናቀርብላቸው፣ ሊያዳምጡን እድል ይኖረዋል::

☞ምክራችን በትስስር ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፤ ጆሮዋቸውን ከፍተው የሚያዳምጡን በቁጣና ማስፈራራት መልክ ስናቀርበው ሳይሆን፣ ፍቅራዊ ትስስር ሲኖረን ነውና

☞እኛ ራሳችን የምንጠጣ ወይ የምናጨስ ከሆነ፣ ለልጆቻችን ምሳሌነት ትልቅ ዋጋ እንዳለው ተረድተን፣ ለራሳችን ጤንነትና ደህንነትም ስንል፣ ለማቆም የተቻለንን እንሞክር:: በሙከራ ሂደት ውስጥ እያለንም፣ ልጆቻችንን በአዎንታዊ መንገድ የመቅረጹ ሀይል አለን:: ችግሩን ለመደባበቅ ወይ ለመሸፈን ሳንሞክር፣ ግልጽ ሆነን፣ ከልጆቻችን ጋር እንወያይ:: "እንደምታየው አጨሳለሁ ግን ሲጋራ ለማቆም በጣም እፈልጋለሁ፤ እየሞከርኩም ነው:: አንተ እኔ ባለፍኩበት ጎዳና ላይ እንድትራመድ አልፈልግም" ብለን፣ በግልጽ የሚያዩትን እውነት እናብራራላቸው:: ባጠቃላይ፣ እንደ ልጆቻችን እድሜና የተፈጥሮ ጸባይ፣ አቀራረባችንና ግንዛቤ መስጫ መንገዳችን የተለያየ ሊሆን ይገባዋል::





(ልጆቻችንን እንደየእድሜያቸው ስለተለያዩ ጉዳዮች እንዴት ልናወራቸው እንደምንችል፣ ጥሩ ምሪት የሚሰጠን ድረ ገጽ ስም ለማየት ከስር ይመልከቱ።)[29]

## የጓደኛ ግፊት

ልጆቻችንን፣ ከድራግ መጠጥና ሌላ ግብረወጥ ድርጊት መከላከል ስንፈልግ፣ አንድ እውነት ልብ ልንል ይገባል፤ በእነርሱ ዕድሜ ያሉ እኩዮቻቸውና ጓደኞቻቸው፣ በልጆቻችን በአስተሳሰብ እና እርምጃቸው ላይ ትልቅ ተጽእኖ ሊኖራቸው ይችላል።

> "ልጆች አደንዛዥ እጽን የሚሞከሩበት ምክንያት ምንድነው በሚለው ላይ የተደረጉ ጥናቶች ተመሳሳይ ምላሽ አግኝተዋል፤ ያም ከጓደኛ ላለመለየት ነው። ከጓደኞቻቸው የሚመጣው ግፊት፣ ልጆችን ወደ መጠጥ ሲጋራ ድራግ ሊመራ፣ ማድረግ የማይፈልጉትንና የሚጎዳቸውን ነገር ሊያስደርግ፣ ትልቅ ሀይል አለው።[30]

ልጅ ጓደኛን መምሰል ይፈልጋልና፣ ከእነርሱ ላለመለየት፣ በእነርሱ ዘንድ፣ "ሞኝ የማይገባው" ላለመባል፣ ተቀባይነት ለማግኘት ሲል፣ ሌሎች ልጆች ያደረጉትን ለማድረግ ሊነሳሳ ይችላል። ከጓደኛ የሚመጣ ግፊትን አልፈው፣ጠንክረው እንዲቆሙ የሚያስችል ኀይል በልጆቻችን ውስጥ እንዲሰራ፣ ወላጅ ጥረት ማድረጉ በጣም አስፈላጊ ነው፤ ግፊትን የሚቋቋም ሀይል በውስጣቸው ካለ፣ በወጀቡ ውስጥ አልፈው መውጣትን ይችላሉና።

ልጅ ጓደኛን እንዳይከተል በዋነኝነት የሚያበረክተው፣ የወላጅ ቁጣ አይደለም፤ በውስጡ እንዲመሰረት ያበረታታነው፣ ግንዛቤ፣ ራስን

[29] parentdrugfree.org ልጆቻችንን ስለተለያዩ ሱሶች፣ ጎጂ ልምምዶች ለመጠበቅ፣ ለማዳን፣ በየእድሜ ክልላቸው፣ እንዴት ልናወራቸው ልንመክራቸው እንደሚገባ በጣም ጥሩ ምክር ይሰጣል

[30] Steinberg Laurence (2011) you and your adolescent, Simon and Schuster

ችሎ የማሰብ፣ ለራስ የመወሰን ችሎታ እንጂ። ብዙ ጊዜ፣ የጓደኛ ግፊትን አሸንፈው የሚያልፉ ልጆች፣ የራሳቸው የሆነ ጥሩ ነገር እንዳላቸው የሚረዱ፣ የሰው አድናቆት ጭብጨባን የማይጠሙ፣ ላመኑበት ትክክል ነው ለሚሉት፣ ጸንተው መቆም የሚችሉ፣ ልጆች ናቸው። እንዲህ አይነት ጠንካራ መሰረት በውስጣቸው እንዲሰራ፣ የጓደኛ ግፊትን ልጆች እንዲቋቋሙ፣ ወላጅ ምን ማድረግ ይችላል?

☞ ቀደም ብለን በምእራፍ አራት እንዳነሳነው፣ ለልጆቻችን፣ ራሳቸውን መሆንን ስላለመፍራት፣ ላመኑበት ስለመቆም፣ ከልጅነታቸው እናስተምር፤ በንግግር ብቻ ሳይሆን በምሳሌነትም እናስተምር። ትክክለኛ ለሆነና ላመኑበት ጸንቶ የመቆም ምግባር ስናይባቸውም፣እናበረታታቸው።ለምሳሌ፣ በህጻንነት እድሜያቸው እኛ ጋ መጥተው፣"ዛሬ ትምህርት ቤት ልጆች አስተማሪ እንረብሽ ሲሉኝ፣ እኔ ግን እንቢ ብዬ ያንን መረጥኩ" ብለው ሲነግሩን፣ "ጎበዝ ልጄ" ብለን፣ በምርጫቸው እንዴት እንደተደሰትን እናሳያቸው፤ ሌላው ያደረገውን ሁሉ መከተል እንደሌለባቸውም እንንገራቸው። እዚህ ጋር ነጥቡ፣ልጆቻችን፣ የውስጣዊ ትዕቢት ወይ "ሁሉን እኔ አውቃለሁ" የሚል ጸባይ ይያዙ፣ ማለት አይደለም፤በአንጻሩ ለሚያምኑበት፣ትክክል ነው ለሚሉት ጸንተው መቆም እንዳይፈሩ ከልጅነታቸው እናበረታታ።

☞ በተለይ በልጅነታቸው ጊዜ፣ ልጆቻችን፣ "ራሳቸውን ችለው፣ ላመኑበት ጸንቶ የመቆም" ጸባይ፣ በውስጣቸው እንዲመሰረት፣ ሊረዷቸው የሚችሉ ጨዋታዎችን አብረናቸው ልንጫወት እንችላለን።ከልጆቻችን ጋር የምናደርገውን፣ የዚህ "አስተማሪ ንግግር" ልውውጥ፣ ምሳሌ እንስጥ፤ ለምሳሌ፣ "ዛሬ፣ ጠይቁን እንመልሳለን የሚለውን፣ የምወደውን ጨዋታ እንጫወታለን" ብለን፣ እንደ መዝናኛ ጊዜ አድርገን፣ ጥያቄዎችን አዘጋጅተን፣ እናቅርብ። "ትምህርት ቤት አንድ ልጅ፣ ጥሩ ያልሆነ ጎጂ ነገር፣ እንካ ብሎ ይሰጣችኋል፤ በዚህ ጊዜ ምን ታደርጋላችሁ? " 1.እኔ ይህን አልወስድም ብላችሁ ለልጁ ትሰጡታላችሁ? 2.ልጁ





እንዳይታዘባችሁ እሺ ብላችሁ ወስዳችሁ ከዚያ በሁዋላ ትጥሉታላችሁ? 3.ወስዳችሁ ትጠቀሙበታላችሁ? የቱን ትመርጣላችሁ?" ብለን እንጠይቅ፤ ልጆቻችን እንዲያስቡበትም ዕድል እንስጣቸው። ልጅ፣ "እኔ ይህን አልወስድም እለዋለሁ" ብሎ ሲመልስ፣ ወላጅም የእርካታ ፊት አሳይተን፣ ጎበዝ፤ ለምን እንዲህ አልክ እስቲ አብራራልን ብለን፣ ልጅ እንዲያብራራ ቦታ እንስጥ፤ ልጅም ለተጠየቀው ጥያቄ ሲመልስ፣ ለራሱም እያሰበበት፣ ያ እውቀት ውስጡ እየሰረጸ፣ ይመጣል። ሌሎችም፣ የሚመለከቱ ወንድምና እህቶች፣ ወላጅ በመልሱ እንዴት ደስ እንደተሰኘ ሲያዩ፣ ትልቅ ትምህርትን እየተማሩ ይመጣሉ። ከጠበቅነው የተለየ ምላሽ ብናገኝ እንኳ፣ "ልጄ፣ እኔ የማልፈልገውን መለሰ" ብለን፣ ንዴት ብስጭት አናሳይ፤ "እሺ ለምን ይህን መረጥክ" ብለን በመጠየቅ፣ ከዚያ ቀስ ብለን የሚረዳው ምክር መምከር፤ ደግመን በሌላ ጊዜ፣ ያንን ጨዋታ አብረን መጫወት፣ ለልጆቻችን ትልቅ እውቀት ሊሰጣቸው ይችላል።

☞ ከጓደኛ ዘንድ ጥያቄና ግፊት ሲመጣባቸው፣ ሊመልሷቸው የሚችሏቸውን፣ የብልሀት መልሶች፣ አብረናቸው መለማመድ፣ ልጆቻችንን በትልቁ ሊረዳ ይችላል። የእኩዮቻቸው ማሾፍያ መሆንን ባለመፈለግ፣ ብዙ ልጆች ማድረግ የማይፈልጉትን እንኳ፣ እሺ ብለው ያደርጋሉ፤ ለጓደኞቻቸው ፌዝ በማያጋልጣቸው መልክ፣ እንዴት ጥሩ መልስ ሊመልሱ እንደሚችሉ በመወያየት ልጆቻችንን ልናስታጥቅ እንችላለን።

☞ እኛ እንዲማሩ የምንፈልገውን ትምህርት፣ እንደተረት አድርገን በታሪክ ውስጥ በማስገባት፣ (በተለይ በህጻንነት እድሜያቸው)፣ ልጆችን በትልቁ ልናስተምር እንችላለን።

☞ ልጆች አደግ እያሉ ሲመጡ፣ "እስቲ የውይይት ጊዜ ይኑረን" ብለን፣ ልጆቻችንን ሰብስበን፣ "ጓደኛን በተመለከተ ከሁሉ የሚያስቸግረው ምንድነው? ውሳኔን በተመለከተ፣ ከሁሉ ከባድ ምንድነው?" ብለን እንጠይቅ፤ ሁሉም ልጅ የየራሱን እንዲያበረክት

ቦታ እንስጥ:: የበላይ ተመልካች አይነት ሆነን ሳይሆን፣ እኛም የጥያቄው ተካፋይ ሆነን ያለንን እናበርክት:: የማልፈልገውን ሰማሁ ብለን ሳንቆጣ፣ ከልጆቻችን ጋር ከልብ እንወያይ፤ አንዱ ለሌላው ጠቃሚ ምክር እንዲሰጥ፣ መድረክ እንስጥ፤ ይህ ወንድምና እህትን ያቀራርባል፤ ልጆች ስለሚያልፉበት፣ ለወላጅ በግልጽ እንዲናገሩም ያበረታታል፤ እኛም፣ እነሱ ስላለባቸው ግፊት፣ በጥልቀት እንድናውቅ ይረዳናል::

☞ ይህን ትምህርታዊ ጊዜ፣ ልጆችን በሚስብ መልኩ አድርገን ማዘጋጀቱ ትልቅ ጥቅም እንዳለው እንረዳ፤ ደረቅ፣ ልጆችን የማይስብ ከሆነ፣ ልጆች ደስ ብሏቸው አይሳተፉምና:: ዘዴን ተጠቅመን፣ ልጆቻችን ውስጥ የምንመሰርተው ይህ እውቀት ለሕይወታቸው በትልቁ ያበረክታል:: የጓደኛ ግፊትና የተጽእኖ ወጀብ ሲመጣ፣ በውስጣቸው የተመሰረተው ጥንካሬ አሻጋሪ ድልድይ ይሆናቸዋል::

ልጆቻችን ስላለባቸው ግፊት፣ እንደየእድሜያቸው እንዴት ልናነጋግራቸው፣ልንረዳቸው እንደምንችል፣በጥልቀት የሚያሳውቁን፣ ለወላጅ ተብለው የተዘጋጁ፣ ረጂ የእውቀት ምንጮች (ዌብ ሳይቶች) አሉ:: (በግርጌ ማስታወሻው ላይ ያሉትን ድረገጾች (ዌብ ሳይት) ቢመለከቱ፣ በጣም ጠቃሚ የሆኑ ግንዛቤዎች ሊያገኙ ይችላሉ። [31]

## 2 በውጪ ስላለው ወጀብ፤ በእውቀት ማስታጠቅ

ልጆቻችንን ፍቅር በሞላበት፣ ሁሉ ጥሩ በሆነበት ቤት ውስጥ እያሳደግን፣ "በውጪም ሁሉ ጥሩ ነው" በሚለው አስተሳሰብ ስር

[31] www.theantidrug.com የሚለው ዌብ ሳይት ልጆቻችን ስላለባቸው የተለያዩ ግፊቶች ጥሩ ግንዛቤ ይሰጠናል። እንዴት ልንረዳቸው እንደምንችል ከእነሱ ጋር ባለን የንግግር ልውውጥ (communication) ወደ ድል እንዲሸጋገሩ ረጂ መንገድ ምን ጥሩ ገለጻን ያደርግልናል።



ልጅን እንዴት ላሳድግ? በምዕራብ አገሮች

እንዳያድጉ፣ መጠንቀቅ አለብን:: አንዳንድ ጊዜ፣ ቤታቸው ውስጥ በፍቅር እና በሰላም የሚኖሩ ልጆች፣ "ሰው ሁሉ ጥሩና የሚታመን ነው" ብለው ሊያስቡም ይችላሉ፤ ልጆቻችን "ሁሉ ሰው በጎና፣ ሊታመን የሚችል ነው"፣ የሚል እምነት ካደረባቸው፣ በውጭ ያለው ስሕተት ቶሎ ሊያጠቃቸው ይችላል:: ያንን ተገንዝበን፣ ውጪ፣ ሁሉ በጎ የሆነበት እንዳልሆነ፣ ለልጆቻችን ማስተማር፣ ሊመጣ ስለሚችል ጥቃትም ማስገንዘብ አለብን::

ይህ ማለት፣ ልጆቻችን ሰውን ሁሉ እንዲጠራጠሩ ወይም ሰውን ፈርተው እንዲያድጉ እናስለጥናለን ማለት አይደለም፤ ሰውን ሁሉ በጎን እንዲያይ ተደርጎ ያደገ ልጅ፣ ከማንም በላይ ራሱ ይጎዳል፤ ሌላውን ሰው እንዲወዱና እንዲያከብሩ አድርጎ ልጅን ማሳደግ በጣም አስፈላጊ ነው:: በአንጻሩ ግን፣ በውጭ ያለው ሁሉ በጎ እንዳልሆነ፣ ሌላን ለመጉዳት የሚሞክሩ ሰዎች እንዳሉ፣ ልጆቻችን ከእኛ መረዳት አለባቸው:: ከዚህ በተጨማሪ፣ እነዚህ ሰዎች ቢያጋጥሟቸው፣ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል::

## *ሀ.* በልጆች ላይ እኩይ ተግባር የሚፈጽሙ ሰዎች መከላከል

በተለያዩ አገሮች የሚኖሩትን ቤተሰቦችና ልጆች አጠንክረን የምንገልጸው፣ልጆችን ለራሳቸው አስቀያሚ የፍትወት ፍላጎት ለመጠቀም፣ የሚፈልጉ ብዙ ሰዎች መኖራቸውን ነው:: በዚህ ጉዳይ ላይ የተደረገ ጥናት እንደሚያሳየው፣ በአሜሪካ አገር፣

> "በአሁኑ ወቅት/ ከ644,865 በላይ የሆኑ፣ በህገወጥ ወሲብ ድርጊት ተሳትፈው የሚያውቁ ህግ የሚያውቃቸው (ሴክስ ኦፌንደር) ሰዎች በውጪ አሉ። በ10,000 የሚገመቱት ከአሰራሩ ውስጥ ጠፍተዋል። (በድብቅ ላይ አሉ፤ የት እንዳሉ አይታወቅም)"[32]

[32] (National Center for Missing and Exploited Children, 2008).

እኩይ ተግባራቸው ህግ ፊት ያልቀረበ ደግሞ ሌሎች ብዙዎች አሉ:: እነዚህ ሰዎች የሚቀርቧቸውን ልጆች ተጠቅመው፣ ለራሳቸው የፍትወት ፍላጎት ማሚያ ሊጠቀሙባቸው ይሞክራሉ:: ለዚህ መከላከያ መድኀኒቱ፣ ይህ ችግር እንዳለ ተረድተን፣ ለልጆቻችንም በግልጽ ማስረዳት ነው::

ብዙ ልጆች ለጥቃት ምቹ የሚሆኑት፣ ጥቃቱ ሲጀምር ለቤተሰብ ሄደው ለመንገር ስለሚፈሩ እንደሆነ፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ያጠኑ ሰዎች ይናገራሉ:: ሌላው ምክንያት፣ የሰዎቹ ሸር ልጅን ሊያታልል ስለሚችል ነው:: እነዚህ እኩይ ተግባር የሚፈጽሙ ሰዎች፣ ልጆችን ለመጠቀሚያነት የሚያመቻቹት፣ ብዙዎቻችን እንደምናስበው፣ አስፈራርተው ወይ አስጨንቀው አይደለም:: ልጅን የሚቀርቡት፣ ቀስ ብለው፣ አባብለው አታለው፣ ጓደኛ መስለው ነው፤ በዚህም ምክንያት፣ ልጅ የእነሱን እኩይ ተግባር እንደ ፍቅር መግለጫ ተርጉሞ፣ በልቡ ይዞ ጸጥ ሊል ይችላል::

ከሕጻንነታቸው ጊዜ ጀምሮ፣ ከልጆቻችን ጋር ስለዚህ ጉዳይ በግልጽ መወያየት አስፈላጊ ነው:: "ትምህርት ቤት ሆነ፣ ሰው ጥየቃ በሄድንበት ቦታ፣ ጓደኛ ቤት ሆነ ጎረቤት፣ ስለ እንደዚህ አይነት ነገር ሊያወራሽ የሞከረ ሰው ካለ፣ ያለ አግባቡ ሊያቅፍሽ/ሊያቅፍህ የሞከረ ሰው ካለ፣ እዚህ ቦታ ሊነካካሽ/ሊነካካህ የሞከረ ሰው ቢኖር፣ በቶሎ ብላችሁ ለእኔ ንገሩኝ" ብለን በግልጽ ማስተማር አለብን:: ልጆቻችን መጥተው የሚነግሩን ምንም ይሁን ምን፣ ሳናጣጥል እናዳምጣቸው:: የእውነት ተጎድተው ዝም ከሚሉን፣ በስሕተት እንኳ መጥተው ቢነግሩን ይሻላልና፣ የሚነግሩንን ከልብ እናዳምጥ::

ሌላው ልናውቅ የሚገባን፣ ይህን ነጥብ ነው፤ ከልጆቻችን ጋር ብቻውን እንዲሆን የምንተወው ሰው፣ ጠንቅቀን የምናውቀው ሰው ሊሆን ይገባል:: አዎ፣ ውጭ ሲወጡ የማያውቁትን ሰው እንዲጠነቀቁ ማስተማር ብቻ ሳይሆን፣ ልጆቻችን የከበቧቸውን "የቅርብ" ሰዎችንም፣ እነማን እንደሆኑ መለየት አለብን:: አገር





ቤት እንደለመድነው፣ ልጃችንን ከሁሉ ሰው ጋር አንመን:: ጎረቤት ይሁን የስራ ባልደረባ፣ ጥሩ ስለመሰለ ወይ ስለሣቀ ብቻ፣ "ለልጆቼ ጥሩ ይሆናል" ብለን አንደምድም:: በልጅነታቸው የወሲብ ጥቃት የደረሰባቸው በርካታ ሰዎች የሚመሰክሩት፣ ያ ጥቃት ቤተሰብ በሚያውቀው "በታመነ" ሰው እንደ መጣ ነው:: እዚ ጋር ነጥቡ፣ ከመጠን በላይ ተጠራጣሪ ሆነን ሁሉን ሰው የጎን እንመልከት ለማለት አይደለም፤ ጥሩ፣ ደግ፣ አዛኝና ልጆቻችንን በብዙ ሊረዱልን የሚችሉ ብዙ ቅን አሳቢዎች አሉ:: ጥሩ ሰዎች እንዳሉ ሁሉ፣ ክፉ አሳቢም ሊኖር እንደሚችል መረዳቱ ግን፣ ተገቢ ነው፤ ልጆቻችንን ሆነ ራሳችንን በሚገባው ግንዛቤ ካስታጠቅን፣ ክፉን ልንከላከል እንችላለንና::

ከዚህ ጋር ተያይዞ፣ ልጆችን ለእኩይ ተግባራቸው መጠቀሚያነት የሚፈልጉ ሰዎች፣ ባሁኑ ጊዜ በብዛት የሚጠቀሙበት ዋና መሳሪያ፣ ኮምፒዩተር (ኢንተርኔት) ነው:: ብዛት ያላቸው ልጆች፣ ባለማሰብ ራሳቸውን ላደጋ ያጋልጣሉ:: በዚህ ጉዳይ ላይ፣ በአሜርካ አገር የተደረገ ጥናት እንደሚያሳየው፣

> "71 ፐርሰንት የሚሆኑት በአስራዎቹ የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ልጆች፣ በቀጥታ ከማያውቋቸው ሠዎች የግል መልዕክቶችን በተከታታይ ይቀበላሉ፡ ይህንንም የሚያደርጉት ለወላጅ (ዘመድ) ሳይናገሩ፣ በድብቅ ነው::"[33]
>
> "30%ቱ ልጆች፣ እነዚህን በኢንተርኔት የተገናኟቸውን እንግዳ ሰዎች፣ "በፊት ለፊትም ላግኝ" የሚለው ሀሳብን አስተናግደዋል::"[34]
>
> "14% እነዚሁኑ ሰዎች በአካል አግኝተዋቸዋል::"[35]

[33] Gregory S. Smith; (August 30, 2007) How to Protect Your Children on the Internet: A Road Map for Parents and Teachers, Praeger publisher; Resource from the national center of missing and exploited children

[34] ከላይ ያለውን ይመልከቱ

[35] ከላይ ያለውን ይመልከቱ

**ብዙ ጊዜ፣ እነዚህ ሰዎች አቅደው፣ የልጆች እድሜ እኩያ መስለው፣ ልጅን የሚስብ ታሪክ ፈጥረው፣ ልጆችን በአካል ለመገናኘት ሁኔታን ያመቻቻሉ:: ቀደም ብለን እንዳነሳነው፣ ያላግባብ የተተወ ኮምፒዩተር፣ ብዙ አደጋ አለው፤ አስቀያሚ የሆኑ፣ ልጅ ሊያያቸው የማይገባቸውን ምስሎች ከማሳየት በተጨማሪም፣ ልጆችን ለአደገኛ ሰዎችም አጋልጦ ይሰጣል:: በኮምፒዩተር ሊከሰት ከሚችል አደጋ ልጆችን ለመጠበቅ፣ ወላጅ ምን ማድረግ ይችላል? በዚህ ጉዳይ ላይ፣ ለወላጆች ምክር የሚሰጡ ብዙ፣ ጥናት አድራጊዎች የሚደጋግሙት፣ ይህንን ነጥብ ነው፤**

- ኮምፒተርዎን የጋራ በሆነ፣ ማንም ቤተሰብ አባል ሊያየው የሚችልበት ግልጽ ቦታ ያስቀምጡ
- ልጆች ኢንተርኔት ውስጥ ሲገቡ፣ ሊጎበኙት የሚችሉትን የመገናኛ መረብ (ኦን ላይ ሳይትን) በተመለከተ፣ ገደብ ያብጁ፤ ያንንም ለልጆችዎ በግልጽ ይንገሩ
- ልጆች ኮምፒዩተር የሚጠቀሙበትን ጊዜውንና ሰአቱን የተወሰነ ያድርጉ
- በቀጥታ የንግግር መስመር (ቻት ላይን) ላይ፣ ህጻናት ልጆች እንዲጠቀሙ አይፍቀዱ፤ እንዲሁም በእድሜ ተለቅ ያሉ ልጆች፣ በቀጥታ ንግግር መስመር (ቻት ላይን) ላይ፣ ከማን ጋር እየተገናኙ (እያወሩ) እንደሆነ፣ ያጣሩ፤ አንድ በአንድ ይወቁ
- ከማያውቁት ሰው ጋር በቀጥታ መነጋገር አደጋ እንዳለው ለልጆችዎ ደጋግመው ይንገሩ።
- ትናንሽ ልጆች ፌስ ቡክ እንዲገቡ መፍቀድ ትክክለኛ እርምጃ እንዳልሆነ ባለሞያዎች ይናገራሉ። ወላጅ እሺ ብሎ ቢፈቅድ እንኳ፣ ልጆች ፌስ ቡክ ውስጥ የሚሰሩትንና፣ ያሏቸውን ጓደኞች፣ ማየት የሚችልበትን መንገድ ማመቻቸት፣ በጣም አስፈላጊ ነው።
- ልጆች ላደጋ የሚጋለጡት ቤት ውስጥ ባለ ኮምፒዩተር ላይ ብቻ አይደለም፡ ኢንተርኔት ሊያገኙ የሚችሉበት የሞባይል/ተንቀሳቃሽ/ የመጫወቻ መሳሪያዎችንና ላፕቶፖችን መቆጣጠርዎን እርግጠኛ ይሁኑ፤ (ያለ ወላጅ ክትትል የተተወ ላፕቶፕ፣ ልጅን ለአደጋ ሊያጋልጥ ይችላልና) ባጠቃላይ፣ ልጆች በኮምፒዩተር ላይ የሚያዩትን መከታተል አስፈላጊ ነው፤





**ከዚህ በተጨማሪ፣ ትምህርት ሰጪ ብዙ ባለሞያዎች፣ ለወላጆች በጥብቅ የሚሰጡት ምክር፤ <u>ኮምፒዩተር ሳይት የሚያጠራ ሶፍትዌር (ፊልተር ሶፍትዌር) ማስገባት በጣሙን አስፈላጊ እንደሆነ ነው::</u>**

ልጆችን ከአደጋ ለመጠበቅ፣ የሚያጠራ ሶፍትዌር መግዛት ለምን ያስፈልጋል?

- አላስፈላጊ የሆኑ ሳይቶች በኮምፒዩተርዎ መስመር እንዳይመጣ ያደርጋሉ፤
- ልጆችም፣ አውቀው ሆነ ባለማወቅ፣ የማይሆን ሳይት ውስጥ ከመግባት ያግዳቸዋል።
- በተጨማሪም፣ እነዚህ ሶፍትዌሮች፣ ወላጆች የልጆቻቸውን ቀጥታ ኢንተረኔት እንቅስቃሴ ለመከታተል (ለመሰለል) እንዲችሉ ይረዷቸዋል። የእነዚህ ሶፍትዌሮች ዋጋ፣ በአማካይ ከ60 ዶላር በአመት የማይበልጥ ነው። ውጤታማነቱን እና ዋጋውን መዝነን ትልቅ የእርዳታ ምንጭ ቤታችን ልናስገባ እንችላለን።
- በሚሰጡት አገልግሎት ጥሩ የተባሉ የተወሡኑ የማጣሪያ ሶፍትዌር ለምሳሌ ያህል እነሆ፤ ኔት ናኒ፣ሳይበር ፓትሮል፣ሴፍ አይ ፣ሳይበር ሲተር፣ ፒሲ ተትልቴል ወዘተ፤ (ዋናው ነጥብ፤ የሚገዙት ማጣርያ ሶፍትዌር ልጆችን በደንቡ ሊከላከል የሚችል መሆኑን አይቶ መምረጡ ነው።
- እንደ ጉግል፣ አልዞ ዌብ የመሳሰሉት የኛ የራሳችን መረጃ አገልግሎቶች ማለትም፣ (ኢንተርኔት ሰርቪሶች) አላስፈላጊ ሳይቶችን በማገድ ሊያግዙ ቢችሉም፣ አብዛኛውን ጊዜ ያ ብቻውን በፈለግነው መልክ ውጤታማ አይደለም (በግዢ የምናስገባው ማጣርያ ሶፍትዌር ጥቅሙ ይመረጣል)

**እንዲህ አይነት፣ አስፈላጊ እርምጃዎችን ወስደን፣ በቅድሚያ በመጠንቀቅ፣ ልጆቻችንን ከአደጋ ልንከላከል እንችላለን::**

"ልጅን ከኮምፒዩተር አደጋ መጠበቅ" ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ፣ ተጨማሪ ግንዛቤ፣ ማብራሪያ ከፈለጉ፣ በግርጌ ማስታወሻው ላይ የሰፈሩትን ጠቃሚ ድረገጾች ይመልከቱ።[36]

## ልጆችን ለመጥለፍ የሚሞክሩ ሰዎች

ልጆችን አታለው ለመጥለፍ (kidnap ማድረግ) የሚሞክሩ ሰዎች፣ እንዳሉ ተረድተን፣ ልጆቻችንን በግንዛቤ ማስታጠቅ፣ ሌላው ልንወስድ የሚገባው እርምጃ ነው:: በውጩ የሚያገኙትን ሁሉ ሰው እንዳያምኑ፣ ለእኛ ሳይነግሩ ማንንም ተከትለው እንዳይሄዱ፣ በማንም መኪና ውስጥ እንዳይገቡ፣ ለልጆቻችን ጠንቅቀን እንምከር:: አንድ ሰው አስገድዶ ሌላ ቦታ ሊወስዳቸው ቢሞክር፣ በተቻለ መጠን፣ እዛው ባሉበት ቦታ፣ እንዲንፈራገጡና እንዲጮሁ እንምከር፤ ይህም ምክንያት አለው:: አደጋን ስለመከላከል የሚያስተምሩ ሰዎች፣ ለህጻንም ሆነ ለትልቅ ሰው ጠቃሚ ምክር ብለው የሚናገሩት ነጥብ አለ፤ አጥቂው ብዙ ጊዜ ኀይሉን ለማስረገጥ እድል የሚያገኘው፣ ተጎጂውን ከሰው ራቅ አድርጎ (ጭር ያለ ቦታ) መውሰድ ከቻለ በኋላ እንደሆነ ያስተምራሉ:: በቻልነው አቅም፣ እዛው ያለንበት ለመቆየት መጣር፣መጮህና ለእርዳታ መጣራት፣ ከክፉ ሊያድነን እንደሚችል ያስተምራሉ፤ ለልጆቻችንም ያንኑ ግንዛቤ እናስተላልፍ::

[36] ስለዚህ ጉዳይ የበለጠ ለማወቅ ቢፈልጉ ጥሩ ግንዛቤ ለማግኘት Internetsafety101.org ገብተው safety የሚለውን ቢጫኑ ጥሩ ምሪት ያገኛሉ

ሌላ ጥሩ ገለጻ ሰጪ ሳይቶች getnetwise .org—ገብተው kids safety የሚለውን ይመልከቱ

enough.org

Wiredsafety.org





## ለ. በትምህርት ቤት ልጆችን የሚጎዱ ተማሪዎች

ልጆቻችን ሊጎዱበት የሚችሉበት አንድ ሌላ ዋና ቦታ፣ ትምህርት ቤታቸው ነው:: "ልጆች በትምህርት ቤት ውስጥ ምንም ጉዳት አይደርስባቸውም" የሚለው እምነት፣ ብዙ ሰዎች አለን:: እውነቱ ግን ሌላ ነው:: በትምህርት ቤት ውስጥ፣ ሌሎች ልጆችን የሚያሰቃዩ ልጆች ከፍተኛ ችግር እያመጡ ነው:: በቴሌቭዥን፣ ጋዜጣና የተለያዩ ዜና ምንጮች እንደምናየው፣ ብዙ ልጆች በሚደርስባቸው ግፊያ ምክንያት፣ ጉዳት እየደረሰባቸው ነው:: ተንኳሾችና በኀይል አስፈራሪዎች፣ በሌሎቸ ልጆች ላይ የሚያስከተሉት ጫና እና አደጋ፣ ተጠቂዎቹ ላይ የአእምሮ ጭንቀት፣ ብቸኝነት፣ ፍርሀት፣ ራስን መጥላት፣ እና ሌላም ብዙ ጉዳት ሊያመጣ ይችላል:: ከዛም አልፎ፣ በሚሰነዘርባቸው ስድብ፣ ፌዝ፣ እና ጥላቻ ምክንያት ራሳቸውን እስከ ማጥፋት የደረሱ ብዙ ልጆች አሉ::

ትምህርት ቤት ውስጥ ልጆች ላይ የሚደርስን ጥቃት በተመለከተ፣ በአሜሪካን አገር በቅርብ በተደረገ ጥናት

- 77% ተማሪዎች ጥቃት ደርሶባቸው እንደሚያውቅ መዝግበዋል።
- ከነዚህ ተማሪዎች ውስጥ፣ 14% የሚሆኑት በጥቃቱ ምክንያት ሀይለኛ ጉዳት እንደደረሰባቸው መዝግበዋል።
- 46% ያህል ወንዶች እና 26% ሴቶች በድብድብ ውስጥ ተሳትፈው እንደነበር ተናግረዋል።
- 23% የሚሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች በወር ውስጥ ከአንድ እስከ ሶስት ያህል ጊዜ ጥቃት እንደሚደርስባቸው ጥናቱ መዝግቧል[37]

[37] Howtostopbullying.com

- በየቀኑ፣ 160000 የሚሆኑ ተማሪዎች፣ በትምህርት ቤት ውስጥ የሚደርስባቸውን ነውጥ ፈርተው ቤት ይቀራሉ።[38]
- ልጆች ከሌላ ልጆች በሚደርስባቸው ጥቃት የተነሳ ራስን እስከመግደል፣ ሌላን እስከመጉዳት እንደሚደርሱ ተመዝግቧል። በኮሎምቢያ 2ተኛ ደርጃ ትምህርት ቤት እና በሌሎችም የአሜሪካ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የደረሱት የተኩስ አደጋዎችን አስመልክቶ በተደረጉ ጥናቶች፤ ለእነዚህ ክስተቶች በዋነኝነት ያበረከተው ልጆች እርስ በእርስ ላይ የሚያደርሱት ጥቃት (bullying) እንደሆነ ተመዝግቧል።[39]

እነዚህ አጥቂዎች ልጆችን የሚጎዳ ስድብ ይናገራሉ:: ከሌሎች ልጆች ጋር አድመው ተጠቂውን ይደበድባሉ ወይም ተጠቂዋ ላይ ሲያፌዙ ይውላሉ:: በፊት ለፊት ብቻ ሳይሆን እንደ ፌስ ቡክ ባሉ፣ የኮምፒዩተር መገናኛዎች ተጠቂዋን የሚያዋርድ ስድብ ሲሰድቡ ይውላሉ::

ብዙ ጊዜ አጥቂዎቹ የሚያነጣጥሩት፣ የእነሱው ጾታ የሆነ ተማሪ ላይ ነው:: ልጅን ለማሰቃያ ከሚጠቀሙበት ስድብ ምሳሌ ብንወስድ፣ ለወንድ ልጅ፤ "ሴታ ሴት ነህ፣ ከወንድ ያነስህ ነህ፣ ወንድ ሳትወድም አትቀር" ብለው ሊያዋርዱት ይሞክሩ ይሆናል:: አጥቂ የሆኑት ሴቶች ደግሞ ተጠቂያቸው ለሆነችዋ ሴት ልጅ፣ "በማንም ዘንድ ውዴታ የለሽም፣ የተናቅሽ የተዋረድሽ ነሽ፣ የሌላው ማሾፊያ ነሽ" እና የመሳሰሉትን፣ ውስጥ ድረስ የሚጎዱ ስድቦች ለልጆች ይናገራሉ::

ልጆች፣ ብዙ ጊዜ፣ ስለራሳቸው የተነገራቸውን፣ በድፍን ያምናሉ:: ስድቡ ውስጣቸው ዘልቆ ሊያማቸው ሊጠዘጥዛቸው ይጀምራል:: በዚ በሚደርስባቸው ጥቃት፣ ብቻቸውን እንዳሉ ተሰምቷቸው፣ ብዙ ጊዜ ስሜታቸውን ደብቀው ይይዛሉ፤ ወላጅ ፊትም ሁሉን ደህና አስመስለው ሊቀርቡ ይችላሉ::

[38] Howtostopbullying.com
[39] Howtostopbullying.com





ልጆቻችን በትምህርት ቤት፣ የሌላ ተጠቂዎች እንዳልሆኑ በቻልነው መንገድ ሁሉ እናረጋግጥ:: አብዛኛውን ጊዜ፣ የሚገፉ የሚጠቁ ልጆች፤ መልሰው የማይናገሩ፣ ዝም የሚሉና አይናፋር ልጆች ናቸው:: በቁመት አጠር ሰውነታቸው አነስ ያሉ ልጆችም ለጥቃት የተጋለጡ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ያ ማለት ግን ሁሉን አያጠቃልልም፤ በሰውነት አነስ ያሉ፣ ትምህርት ቤት ውስጥ ምንም ችግር ሳያጋጥማቸውየሚያድጉ ብዙ ልጆች አሉ፤ በአንጻሩ ደግሞ በቁመት ረጅም የሆኑ፣ ብዙ ጥቃት የሚደርስባቸው ልጆችም አሉ:: ከወላጅ ጋር በግልጽ የማይወያዩ ልጆች፣ ለጥቃት የበለጠ የተጋለጡ ሊሆኑ ይችላሉ::[40] ልጄ ተጠቂ ወይም አጥቂ ነው ወይ ብሎ የመመርመር ተግባር፣ የወላጅ መሆን አለበት::

ልጆቻችን በግልጽ እንዲነግሩን ከፈለግን፣ አጠያየቃችንን በብልኀት እናድርግ:: ለምሳሌ፤ በፊት ለፊት መጥተን፣ "ልጆች ያሾፉብሀል እንዴ?" ብለን ለልጃችን ብንጠይቀው፣ ግልጽ ሆኖ ሊነግረን ያፍር፣ ይፈራ ይሆናል:: በሌላ በኩል፤ "ትምህርት ቤት ውስጥ ሌሎችን ስለሚጫኑ ልጆች (bullies) ምን ታስባለህ/ታስቢያለሽ"፣ ብለን መልሳቸውን ልንሰማና በዛም ምክንያት እየተጠቁ እንደሆነ ወይስ እንዳልሆነ ልንረዳ እንችላለን::

ከግልጽ መልሳቸው ይልቅ በሚያሳዩን ፍንጮች፣ ተጠቂዎች እንደሆኑና እንዳልሆኑ ልንገመግም እንችላለን:: ልናያቸው የሚገቡ ፍንጮች፤ ትምህርት ቤት አስጠላኝ ብለው ደጋግመው የሚያወሩ ከሆነ፣ ጓደኛ የለኝም፣ ልጆች አይወዱኝም ሲሉ ከሰማናቸው፣ የትምህርት ቤት ስብስብ፣ በዓል ላይ መገኘትን የሚፈሩ ወይ የሚጠሉ ከሆነ፣ አለባበሳቸውን ባንዴ መለወጥ ከጀመሩ፣ ፊታቸው ላይ ጭረት፣ እብጠት ካየን፣ ክፍል ውስጥ የነበራቸው ውጤት በጣም መቀነስ ከጀመረ፣ ቤት ሲመጡ ብዙ ጊዜ ርቧቸው የሚመጡ ከሆነ፣ ትምህርት ቤት ውስጥ ጓደኛ የማፍራት ችግር ካለባቸው፣ ሌሎች ልጆች ሲያዩ የመደንገጥ የመፍራት ሁኔታ ካየንባቸው፣

[40] Sheras Peter, (2002) Your Child: Bully or Victim? Understanding Fireside; Sumon and Schuster.

ድሮ ያልነበራቸው ውጥረት ጭንቀት፣ እነሱ ላይ መታየት ከጀመረ፤ እነዚህና የመሳሰሉት ፍንጮች፣ ልጆቻችን በሌሎች ልጆች እየተጠቁ እንደሆነ ሊገልጹልን ይችላሉ::[41]
ልጆቻችን በትምህርት ቤት፣ ጓደኛ አካባቢ ተጠቂዎች እንደሆኑ ካረጋገጥን፣ በቶሎ፣ ይህን ነገር ለማስቆም፣ እርምጃ እንውሰድ:: ልጆቻችንን ለመርዳት ምን ማድረግ እንችላለን?
ይህ ነገር በልጆች ላይ ሊከሰት እንደሚችል ተረድተን፣ ከመጀመሪያውኑ ልጆቻችንን በግልጽ ማስተማሩ፣ ትልቅ ጉዳትን ሊከላከል ይችላል:: ጥሩነት ሰላማዊነት፣ ዝም ብሎ ከመጠቃት የተለየ እንደሆነ እናስረዳቸው:: ጥሩነት ማለት፣ ሲጠቁ ዝም ማለት እንዳልሆነ፣ሰላማዊነት ማለት፣ሌላው ሲያሾፍባቸው አንገታቸውን ደፍተው መሄድ ማለት እንዳልሆነ፣ እንንገር:: ቀና ብለው፣ ሰውን አይን አይኑን እያዩ እንዲያወሩ እናበረታታ:: ተገቢ በሆነ መልኩ፣ ራሳቸውን መከላከል፣ ለመብታቸው መቆምን እንዳይፈሩ፣ እናስተምር::

ልጆቻችን ለእኛ መጥተው በግልጽ እንዳይናገሩ፣ ሊያደርጓቸው የሚችሉ ነገሮችን እናስወግድ:: ለምሳሌ፣ ስለዚ ጉዳይ ከነሱ ጋር በምንወያይበት ሰአት፣ ስሜታዊ ከመሆን እንቆጠብ:: ስንናደድ ወይ በውጥረት ስንሞላ ካዩ፣ እነሱም የበለጠ ይበጠበጣሉ፤ በሚቀጥለው መጥተው ስሜታቸውን ገልጸው ለኛ መንገርን፣ ሊፈሩ ይችላሉ፤የኛ መረጋጋት ግን ለእነሱም ጥንካሬ ይሆናቸዋል:: ለልጃችን "ምንም አትሆኝም ዝም ብለሽ ትምህርትሽ ላይ አተኩሪ" የመሳሰሉ ንግግሮችን አንናገር:: "አንቺ አንድ ነገር ስላደረግሽ ይሆናል፣ ያንተ ጥፋት ይሆናል" ብለን፣ ልጃችን ላይ በቶሎ ከመጠቆም እንቆጠብ:: እንዲህ አይነት መልሶች ከኛ ከሰሙ፣ ብቻቸውን እንዳሉ ተሰምቷቸው ይቆያሉ፤

[41] Sheras Peter, (2002) Your Child: Bully or Victim? Understanding Fireside; Sumon and Schuster.





ልጆቻችን ጥቃት ላይ እንዳሉ ከተረዳን፤ ሌላ ዋና ልንወስድ የሚገባን እርምጃ ይህ ነው:: ትምህርት ቤት ሄደን፣ ይህንን ጉዳይ ከአስተማሪ፣ ትምህርት ቤት ዳይሬክተር ጋር መወያየት፣ በጣም አስፈላጊ ነው:: የዚህን ጥቃት አደገኝነት እየታየ በመሆኑ፣ የሕግ ድጋፍ እንዲያገኝ እየተደረገ ነው:: ትምህርት ቤቱ ለችግሩ መላ የማይፈልግ ከሆነ፣ የሕግን አማራጭ እንደምንከተል፣ ለሚመለከተውአካል ሁሉ እንግለጽ:: የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተርና አስተማሪዎች፣ እነዚን ጉዳት ፈጣሪዎች በቅጣት ሊያስቆሙልን ይችላሉና፣ ችላ ሳንል ጉዳዩን እንከታተል:: ሌላው ያለን ምርጫ የአጥቂውን ወላጅ አግኝተን ስለጉዳዩ መወያየት ነው:: የልጁን ጥፋት አምኖ የማይቀበል የማይተባበረን ወላጅ ሊገጥመን እንደሚችል መጠበቅ አለብን:: በሌላ በኩል፣ ልጃቸው አጥቂ እንደነበር ያላወቁ ፣ይህንን ጉዳይ ከኛ ሲረዱ፣ ልጃቸውን ለማስቆም እርምጃ የሚወስዱ ቤተሰቦችም አሉ::

ልጆቻችን ውስጣቸው እንዲታደስ፣ በተቻለን እናበርክት:: ልጆች ደጋግመው ዝቅ አድራጊ ስድብን ሲሰሙ፣ የአነስተኛነት ስሜት ሊወራቸው፣ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ሊመለከቱ ይችላሉ:: ያንን ለመከላከል፣ ልጆቻችንን እንገንባ፤ ስላላቸው ጥሩ ችሎታ፣ የተፈጥሮ ስጦታ፣ ደጋግመን እንንገራቸው:: ከሌሎች በጣም የተለየ አለባበስ፣ አጥቂዎቹን ሊስብ ይችላልና፣ ከሌላው ተማሪ በጣም ተነጥለው እንዲታዩ በሚያደርግ ሁኔታ ልጆቻችንን አናልብስ:: አስተሳሰባቸውን በጥሩ መንገድ ሊለውጡ፣ የድጋፍ ምንጭ ሊሆኗቸው፣ከሚችሉ ሌሎች ልጆች፣ ወጣቶችም ሆኑ ትላልቅ ሰዎች ጋር እናገናኛቸው፤ የሚያበረታታ፣የሚያድስ መጸሀፍ እንዲያነቡ እናበረታታ:: የልጅ ጸባይ አንዱ ካንዱ የተለየ ነው፡ ልጆቻችን እንደየጸባያቸው እንዲነቃቁ፣ እንዴት ልንረዳቸው እንደምንችል ምክርን ሊሰጡን የሚችሉ አስተማሪዎችና ካውንስለሮች መጠየቅ፣ ጥቅም ይኖረዋል።፡

በአንጻሩ፣ የእኛ ልጆች የሌሎችን ሰዎች ልጆች፣ በዚህ መልክ እንዳይጎዱ ከፍተኛ ጥንቃቄ እናድርግ፣ እናስተምራቸውም:: ልክ

የእኛ ልጆች እንዳይጎዱብን እንደምንፈልገው ሁሉ፣ ሌላ ልጅም መጠቃቱ መገፋቱ ትክክል እንዳልሆነ መረዳት አለብን:: ከዛም በላይ፤ ሌላ ልጅን ለመግፋትና ለመጉዳት እየሞከሩ ያደጉ ልጆች፣ ለራሳቸው ሰላም የሌላቸው፣ ሰው የሚርቃቸው ሰዎች እየሆኑ ይመጣሉ:: ሌላ ልጅን መጉዳት፣ የጠንካራነት ምልክት ሳይሆን፣ የፈሪነት ምልክት እንደ ሆነ በመግለጽ፣ ከድንበራቸው ዐልፈው ሌላ ልጅን ለማሠቃየት እንዳይሞክሩ፣ ለልጆቻችን እናስተምር::

በማጠቃለያ፣ ይህን ጉዳይ በተመለከተ "ልጄ እየተጠቃ አይደለም" ወይ "ገና ህጻን ነው" ብለን፣ስለዚህ ጉዳይ ከመማር ችላ አንበል:: ልጆች ጥቃት የሚደርስባቸው ከአንደኛ ሁለተኛ ክፍል ጀምሮ ነው:: በተጨማሪ፣ በዚ ጉዳይ ላይ እውቀት ካዳበርን፣ ልጃችን ራሷን መከላከል እንድትማር ከወዲሁ ምን ማድረግ እንደምንችል፣ በቂ ግንዛቤ ይኖረናል:: ልጆቻችን ተጎጂ መሆናቸውን እንዴት ፍንጭ ልናገኝ እንደምንችል፣ ልጆቻችንን እንዴት መርዳት እንደምንችል ጥሩ ግንዛቤ የሚሰጡን፣ ይህን ጉዳይ ባጠኑ ሰዎች የተጻፉ፣ ጠቃሚ ዌብሳይቶች አሉ:: ስለእነዚ ድረገጾች ከስር ይመልከቱ[42]

## *3. ለቤት ውስጥ ወጀብ፤ በእውቀት ማስታጠቅ*

ከቤተሰባቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት በተመለከተ፤ ልጆቻችንን ሊመጣ ለሚችል ፈተና እናዘጋጅ:: በሌላ አነጋገር፣ ወላጆች በሁሉ አዳኝ ደራሻቸው በሁሉ ነገር ፍጹም እንደሆንን፣ የሚመስጥ ስእል ለልጆቻችን አንቀባ:: ያ ጉዳቱ ምንድነው? ልጆቻችን እውነተኛ ባልሆነ፣ ህልማዊ አለም ውስጥ እንዲኖሩ፣ አላስፈላጊ ለሆነ ጉዳት እንዲጋለጡ ያበረክታል::

[42] Stopbullying.gov
www.jodeeblanco.com
"The Bully, the Bullied and The bystander; How parents and teachers can help break the cycle of violence;"
"Odd Girl out; The hidden culture of aggression in girls;" Rachel Simmons





ሕይወት ፍጹም አይደለችም:: ምንስ ለልጆቻችን ቀና የምንመኝ ወላጆች ብንሆን፣ እኛም ፍጹሞች አይደለንም:: በቤተሰብ መሀል አለመግባባት ሊመጣ ይችላል፤ በቤት ውስጥ ፣ ከወላጅ ቁጥጥር ውጭ የሆነ ፈተና ሊመጣ ይችላል፣ ህመም ሊመጣ ይችላል፤ ይደክመናል፣ እንቸገራለን:: "ሕይወቴ ፍጹም ትሆናለች፣ እናቴና አባቴ በሁሉ ጠንካራ ናቸው" በሚለው እምነት ስር ተጠቅልለው ያደጉ ልጆች፣ በዚ ሰአት፣ ለጉዳት ይጋለጣሉ:: "እናቴ እስካለች፣ ምንም ችግር አይደርስብንም"፣ ብለው ተመስጠው ቆይተው፣ በኋላ፣እናት ልትፈታው የማትችለው ችግር ሲመጣ፣ ራቁታቸውን እንደሆኑ ያህል ይሰማቸዋል:: "አባቴ ፍጹም ነው፣ አንድም ስህተት አይሰራም"፣ ብለው አምነው አድገው፣ በኋላ አባት ሲሳሳት፣ ወይ ከእናት ጋር ሲጨቃጨቅ ቢያዩ እውነታቸው ይዘበራረቅባቸዋል::

ለልጆቻችን የማይሆን የፍጹማዊነት ስእል እየቀባን ስንኖር፣ እኛም ራሳችንን ሆነን ልጆቻችንን ለመቅረብ ነጻነቱን እናጣለን፤ ያንን ለልጆቻችን የሳልነውን ህልማዊ የሆነ፣ የፍጹምነት ስእል እንዳለ ለመጠበቅ፣ዘላለም፣አላስፈላጊ በሆነ ውጥረት ውስጥ እንኖራለን፤ ሁሌ ፍጹም ሆኖ መቅረቡ ላይ ስናተኩር፣ እውነታዊ ያልሆነ አርቴፊሺያል ግንኙነት ከልጆቻችን ጋር እንዲኖረንም ያበረክታል::

የጥሩ ወላጅ ትርጉሙ፣ ሁሉን ያስተካከለ፣ በሁሉ የተስተካከለ፣ ከስህተት ሁሉ የራቀ አይደለም፤ ልጆቹን ከልብ የሚወድ የቻለውን የሚጥር እንጂ:: ልጆች፣ ወላጅ በሁሉ ፍጹም እንዳይደለ ማወቃቸው አይደለም የሚጎዳቸው፤ ከእውነታው ውጭ የሆነ አመለካከት (ግምት) ኖሯቸው፣ ይህ እውነት ሲለወጥባቸው እንጂ፤ በህልም አለም ኖረው፣ ኋላ ችግርን ሲጋፈጡ እንጂ:: ስለሕይወት፣ እውነታዊ ያልሆነ ፍጹማዊ የሆነ ስእልን አቅፈው ማደጋቸው፣ በወደፊት ሕይወታቸው ውስጥም ጉዳትን ያመጣል፤ ስለአለም እውነት እንዳይረዱ፣ መጋረጃ ሆኖ ከልሎ፤ ላልጠበቁት ጥቃት ያጋልጣቸዋል::

ልጆችን በደኅናው ጊዜ እውነቱን እንንገራቸው:: " እናት አባታችሁ እንደ መሆናችን እንወዳችኂለን፤ ቤተሰባችን ጥሩ ሕይወት እንዲኖረንም የተቻለንን እናደርጋለን፤ ያ ማለት ግን እናት አባት ፍጹም ነው ማለት አይደለም:: እኛም እንደማንም ሰው እናጠፋለን፣ እንሳሳታለን" ብለን፣ ከልጅነታቸው እንንገር:: "ቤት ውስጥ ያላሰብነው ፈተና፣ ችግር፣ መጥቶ ልናይ እንችላለን፤ ሌላው ቀርቶ ህመም እንኳ ሊመጣ ይችላል ፤ ይህ የሕይወት ክፍል ነው፤ በዛ ሰአት አትደናገጡ፤ ቤተሰብ አብረን ተባብረን ችግሩን ለመፍታት የተቻለንን ሁሉ እናደርጋለን" ብለን፣ ልጆቻችንን በእውቀት እናስታጥቅ:: እንዲህ ልጆቻችንን በእውነት ከከበብናቸው፣በኂላ የሕይወት ፈተና መጥቶ ሲያዩ፣ አይብረከረኩም፤በደህናው ጊዜ ከኛ ከሚያምኑን ወላጆቻቸው ሰምተዋልና፣ በጤነኛ መንገድ እንዲጋፈጡት፣ በትልቁ ያበረክታል፤ ራሳቸውን ችለው መቆምን የተለማመዱ፣ የተረጋጉ እንዲሆኑም ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል::

## *4) ችግርን መቋቋሚያ መንገድ ማስተማር*

ሕይወት ፍጹም እንደማትሆን መንገር ብቻ ሳይሆን፣ ችግርን በጤነኛ መንገድ መጋፈጫ ስልትን እናስተምር፤ ልጆቻችን፣ ችግርን በጤነኛ መንገድ መጋፈጥን ካልተማሩ ፣ ወደ ጎጂ አቅጣጫ ሊያዘነብሉ ይችላሉ፤ የሚያልፉበትን ችግርና ፈተና ለመርሳት በተለያየ ጎጂ ነገር ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ:: ይህ የምናስተላልፍላቸው ጠቃሚ ትምህርት፣ ከልጅነት ዘመን አልፎ ለሕይወት ዘመናቸው ሁሉ መመሪያ እንደሚሆናቸው ተረድተን፤ በማስተማሩ ላይ እንትጋ::

- ☞ ያለፈ ጥፋትን እያሰቡ ያላግባብ ራስን መደብደብ ጭራሽ ወደ ኂላ እንደሚያስቀር አድክሞ አድቅቆ እንደሚተው፣ ለልጆቻችን ጠቃሚ ትምህርት እናስተላልፍ ዋናው ከጥፋት መማርና ወደ ፊት መመልከት እንደሆነ፣ ግንዛቤን እንስጥ::
- ☞ ውድቀትና ስህተት አንድ ሰውን ሊወስነው እንደማይችል፣ለልጆቻችን ግንዛቤን እናስተላልፍ፤





ሰው ከወደቀበት ከተነሳ፣ ተስፋ ሳይቆርጥ ከጣረ፣ ውድቀቱ ሳይወስነው፣ ያለመበት እንደሚደርስ፣ ጠቃሚ ትምህርትን እናስተምር::

- ☞ ቂም መጥፎ እንደሆነ፣ ለልጆቻችን እናስተምር:: በሌላው የተጎዳውን እያሰላሰለ፣ ሰው ምሬትን በልቡ ቋጥሮ ሲይዝ፣ ያ ጉዳት ሁልጊዜ እንደ አዲስ ሆኖ፣ ሀይል ኖሮት በውስጡ እንዲቆይ፣ እንደሚያበረክት፣ከማንም በላይ፣ ለራሳቸው ሰላም ነጻነት ሲሉ፣ ምሬትን መልቀቅ፣ ይቅር ማለት፣ መተውን እንዲለማመዱ፣ እናስተምር::

ሰዎች፣ በተለያየ ጊዜ፣ አእምሮዋችን ውስጥ፣ የሚያስጨንቀን፣ የሚያሳዝነን፣ የሚያሳቅቀን፣ የሚያሳፍረን፣ የሚያስደነግጠን ሀሳብ መምጣቱ አይቀሬ ነው። ልጆቻችንም እንደማንኛውም ሰው፣ በሚጎዳቸው፣ በሚጸጽታቸው፣ በሚያሳፍራቸው፣ በሚያስጨንቃቸው ነገር ውስጥ ያልፋሉ:: ከዚህም በተጨማሪ፣ በቴሌቭዥን በሚያዩት ዝብርቅርቅ፣ እና በእድሜ ተጽእኖ ምክንያት፣ ጭራሽ ያልጠበቁት ሀሳብ ሊመጣባቸው ይችላል። ባጠቃላይ፣ በውስጣቸው የሚሰማቸው ነገርን፣ ወደውስጥ በመቅበር ፋንታ፣ መጋፈጥን እንዲለምዱ፣ የሚረዷቸውን እውነቶች እናስተላልፍላቸው።

- ☞ ሰው እንደመሆናችን መጠን፣ ሁላችንም፤"ይሄ ይቀረኛል ስሜት፣ የብቸኝነት፣ የዝቅተኝነት ስሜት፣ የቅናት ፣ ሀፍረት ስሜት፣ ወዘተ ልናልፍ እንደምንችል በግልጽ እንንገራቸው::ሁሉም ሰው በውስጣዊ ጉዳት የስብራት ስሜት ውስጥ እንደሚያልፍ መልእክት እናስተላልፍ::
- ☞ አንዳንዴ በዐስራዎቹ የእድሜ ክልሎች (ቲኔጀር እድሜ) አካባቢ አስበው የማያውቁት እንግዳ ኀሳብ ሊመጣባቸው እንደሚችልም እንንገር::
- ☞ የማንፈልገው ስሜት ተሰማን ፤ ወይ ያልጠበቅነው ሀሳብ ወደአእምሮዋችን መጣ፣ ማለት መጥፎ ነን

ወይ መጥፎ አደረግን ማለት እንዳልሆነ፣ ለልጆቻችን እናስተምር። ከሚሰማን ስሜት የተለየ ምርጫ ለማድረግ፣ ሁልጊዜ ሀይሉ እንዳለንም እንንገር።

- ☞ "የማንፈልገው ስሜት ኀይል የሚያገኘው ስንቀብረው፣ ከውስጥ ደብቀን ስናኝከው፣ ወይም ደግሞ ተሳቀን በሌላ ነገር ጸጥ ልናደርገው ስንሞክር እንደሆነ፣ እናስተምር።
- ☞ ለሚያምኑት ሰው ማማከር፣ በውስጥ ያለ ሸክምን እንደሚያቀል ለልጆቻችን መልእክት እናስተላልፍ።
- ☞ ቃላት ሀይል እንዳላቸው፤ ደጋግሞ፣ አዳሽ ቃላትን መናገርና ለራስ መደጋገም፣ ውስጥን እንደሚያንጽ ለልጆቻችን እናስተምር
- ☞ አማኞች ከሆንን፤ ለልጆቻችን፣ ጸሎት ስላለው ሀይል እናስተምር። እግዚያብሄር ልብን እንደሚያይ፣ በምንም አይነት ችግር ውስጥ ቢያልፉ፣ ልባቸውን ከፍተው ካነጋገሩት፣ ችግሩ በእነሱ ላይ እንዳይነግስ፣ እርዳታ እንደሚለግሳቸው፣ነግረን፣ በግልጽ ወደ አምላካቸው እንዲጸልዩ እናበረታታቸው።

ባጠቃላይ፣ እኛ የልጆቻችንን ጠባይ/ደካማ ጎን እናውቃለን፤ ማን ቶሎ ራሱን ወደመውቀስ እንደሚዞር፤ ማን በውስጡ የመያዝ ጠባይ እንዳለው እንረዳለን። ማድረግ ያለባቸውን እና የሌለባቸውን፣ እንደየጠባያቸው እንምከር፣ እናስረዳቸውም። እንዲ ከልጅነታቸው ጊዜ ጀምሮ ብናስተምር፣ ነገ በቤት እንኳ ባይሆን በትምህርት ቤት በሚገጥማቸው ችግር አይንበረከኩም። ከእኛ ከሚያምኑንና ሚወዱን ወላጆቻቸው፣ ፍርሀት ጭንቀት ሀፍረት ሊያስቆማቸው እንደማይችል፣ ሰምተዋልና ቢመጣ ሳይፈሩ ይጋፈጡታል። ነገሩ ቁስል ሆኖ እንዳይቀር ወደ ብርሃን ያወጡታል። ለወደፊት ሕይወታቸውም በጣም ረጂ የሆነ ችግርን መቋቋሚያ መሳሪያ በውስጣቸው ይቀመጣል።





# *የሕይወት ተሞክሮ*

## የትምህርት ቤቱ ፈተናዬ

በትምህርት ቤት በነበርኩበት በአብዛኛዎቹ አመታት፣ ከሌሎች ተማሪዎች ዘንድ በብዛት ጥቃት ይደርስብኝ ነበር። ከአመታት አመታት የሚደርስብኝ ጥቃት መጠኑ እየበዛ ስቃዬም እየጨመረ መጣ። እናቴ አባቴ ሁሌ የሚነግሩኝ ለሁሉም ሰው ደግነትን እንዳሳይ፣ ጥሩ ልጅ እንድሆን ነበር። ትምህርቱ ጥሩ ቢሆንም በትምህርት ቤት ለሚደርስብኝ ጥቃት ግን መላ ሊሆንልኝ አልቻለም። ራሴን ለመከላከል ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም ነበር። መጀመሪያ፣ ጥቃቱ ሲደርስብኝ፣ ለእናቴ መጥቼ መናገር ጀመርኩ። የልጅ ነገር ነው ብላ አስባ ከልብ አላዳመጠችኝም። ባንድ ወቅት እንዲያውም "አንቺ ምንም ሳታጠፊ እንዴት ዝም ብለው ሊያጠቁሽ ይችላሉ ጥፋቱ ያንቺ እንዳይሆን" ትለኝ ነበር።

እነዚህን ልጆች ምንም መጥፎ ነገር አላደረኩባቸውም ነበር። እንዲሁ ከእነሱ የተለየች አድርገው አይተው ይጠሉኝ ነበር። አሜሪካ አገር ተወልጄ ባድግም፣ እንደ ውጭ አገር ሰው አይተው፣ "አገርሽ ተመልሰሽ ሂጂ፣ አንቺ ግንባራም ኢትዮጵያዊ እና ሌላም ውስጤን የሚጎዳ ነገር ይናገሩኝ ነበር። እቤት እየመጣሁ በብዛት አለቅስ ነበር። እናቴም ቀስ በቀስ የጉዳቴ ጥልቀት እየገባት መጣ። ሳለቅስ አብራኝ ታለቅስ ነበር፤ ምን ማድረግ እንደምትችል ግራ ገብቷትም በጣም ትጨነቅ ነበር።

ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስገባ ከሌሎች ልጆች የሚደርስብኝ ጥቃት መጠኑ እየጨመረ መጣ። ከእኔ በእድሜ የተለቁ ሴቶች ልጆች እየመጡ ይሰድቡኝ ያመናጭቁኝ ነበር።

ሳልጠቃ፣ ሳልሰደብ ያለፈ ሳምንት ትዝ አይለኝም:: በዚህ ሂደት ውስጥ ስሜቴ በጣም ተጎድቶ አእምሮዬ በጣም ተበጥብጦ ነበር:: አንዳንዴ ከእንቅልፌ መንቃት፣ ካልጋዬ መነሳት በጣም ያስጠላኝ ነበር:: ቀን የሚጠብቀኝን አውቀው ነበርና ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ይሞላኝ ነበር:: ያማረ ልብስ ስለብስ የልጆቹ ስድብ ይብስ ነበርና ልጆቹ ቢተውኝ እያልኩ የቤት ልብስ እየለበስኩ ሁሉ እሄድ ነበር::

በዚህ ሁሉ የስቃይ ዘመን ሳልረታ እንድወጣ የረዳኝ አንድ ዋና ነገር፤ እናቴ ለኔ የሰጠችኝ ድጋፍ እና ተስፋ ሳትቆርጥ እኔን ለመርዳት ያደረገችው ጥረት ነው:: እናቴ የጉዳቱ ጥልቀት ከገባት በኋላ ልትረዳኝ የተቻላትን ትጥር ነበር:: ያጋጠመኝን ነገር ስነግራት የልጅ ነገር ሳትል ልቧን ከፍታ ታዳምጠኝ ነበር:: ተስፋ ሳትቆርጥ ትምህርት ቤት እየሄደች አስተማሪዎቹን ታነጋግር ነበር:: ያ አልሆንም ሲላት ደግሞ ከትምህርት ቤቱ አስወጥታ ሌላ ትምህርት ቤት አስገባችኝ:: አዲሱ ትምህርት ቤት ከገባሁ ጀምሮ አንድም ጥቃት ግፊያ ሳይደርስብኝ በሰላም ቆየሁ፤ ለመጀመሪያ ጊዜም፣ ትምህርት ቤት ስሄድ፣ ደስታ ይሰማኝ ጀመር፤ ትምህርት ቤቴን ጨርሼ ተመረቅኩኝ:: እንዲህ አይነት እናት ሳላለችኝ በጣም እድለኛ ነኝ:: አበረታቼ፣ ደጋፊዬ፣ የሆነች ተስፋ ሳልቆርጥ እንድራመድ የረዳችኝ ነች::





# ምዕራፍ ስድስት

## ልጆቻችንን በሥነ ሥርዐት አስታጥቆ ማሳደግ

ልጅ ስለ ወላጅ የቤቱ መሪነት፣ ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል:: ልጆች በቤታችን ውስጥ፣ በወላጅነታችን እንዲያከብሩን ማስተማር አለብን:: አንዳንዴ፣ ወይም ጥሩ ባህል መስሎን፣ ወይም፣ "ባሁኑ ዘመን ልጅ እንዲህ ነው የሚያድገው" ብለን አስበን፣ ልጅን ከልጅነት ቦታ አውጥተን እንደ ጓደኛ ልናደርግ የምንሞክር ሰዎች አለን:: በልጅነታችን የደረሰብንን፣መጠኑ የበዛ ቅጣትና አሉታዊ ሕይወት፣ በልጃችን ልናካክስ የምንሞክርም ወላጆች እንኖራለን፤

ልጃችን ቤት ውስጥ አዛዥ እንዲሆን መፍቀድ ካለ እኛ ተጽእኖ በራሱ ሁሉን እንዲያደርግ ቦታ መስጠት፣ ያ ፍቅር አይደለም:: የፈለገ የሥነ ልቦና ዐዋቂ ይናገረን ወይም አዲስ መጤ መጽሐፍ ያስተምረን፣ ልጅን ከልጅነቱ ዐልፎ እንደ ጓደኛ እንዲያየን አድርገን አናሳድግ፤ ያ ልጃችንን መጉዳት ነውና::

ልጅ ገና ብዙ ጓደኞች ያፈራል፤ ወላጆቹ ግን አንድ ወይም ሁለት ብቻ ናቸው:: አንድ ህጻን፣ መሪ ያስፈልገዋል:: ለዓለም አዲስ የሆነው ይህ ፍጡር፣ የሚመራው፣ ክፉና ደጉን የሚነግረው፣ ለጥሩ እና ለመጥፎ ሥራው ምላሽ የሚሰጠው፣ ወላጅ ያስፈልገዋል:: ልጄን ነጻነት ሰጠሁት ብለን፣ እንደልቡ ከለቀቅን፣ ክፉና ደጉን የማይለይ ፣ በራሱ የሚጋልብ ይሆናል:: ልንመራው በሚገባን ሰአት ከላይ ሆነን አልመራነውምና፤ ቀናውን መንገድ የሚያሳየው የወላጅ ተጽእኖ ሳይኖረው ያድጋል:: እኛንም ክብር ይነሳናል:: "አባት እናቴ፣ ልጅ እያለሁ እንደ ወላጅ አልሆኑልኝም" ብሎም ይማረርብናል:: ልጅ የሚያስፈልገውን ነጻነት መስጠት፣ እንዳይፈራና እንዳይሳቀቅ አድርጎ ማሳደግ ተገቢ

ቢሆንም፣ በዚያው መጠን ግን ወላጅ የቤቱ ዋና አዛዥ እንደሆነ፣ ማወቅ አለበት::

ልጆቻችንን ቀና አካሄድ ልናስተምራቸው ስንፈልግ፣ ሁለት ዋና ነጥቦችን እናስታውስ፤

1. እኛ ፊት መታዘዛቸው ላይና፣ አሳምሮ ማድረጋቸው ላይ ብቻ አናተኩር፤ ክፉና ደጉን በጥልቀት እንዲረዱ እንትጋ:: ደጋግመን እንዳነሳነው፣ ልጅ ከልብ ያልተማረው ትምህርት ነገ ከውስጡ ውልቅ ብሎ ይጠፋል:: አዎ፤ አሁን ሰባት ወይም ስምንት ዓመት ሆኖዋቸው ሳለ፣ ለጊዜው እኛ ፊት፣ የፈለግነውን ሲያደርጉልን፣ ጥሩ ያሰለጠንናቸው ይመስለን ይሆናል፤ ያ ብቻውን ግን በቂ አይደለም፤ ያስተማርናቸው ትምህርት ከልብ ካልገባቸው፣ ውስጣቸውን የሠረጸ፣ ጥሩውንና መጥፎውን፣ ክፉና ደጉን የሚለይ፣ የተተከለ ዕውቀት ከሌለ፣ የእኛ አይን የሌለበት ቦታ ሲሆኑ፣ "አሁን ነጻ ሆንሁ፤ ያሻኝን ማድረግ እችላለሁ" ብለው፣ የፈለጉትን ሁሉ ማድረግ ይጀምራሉ::

2. ሌላኛው ማስታወስ ያለብን፣ ይህን ነጥብ ነው:: ልጆቻችን አንድ ነገር እንዲያደርጉ ስንፈልግ፣ በኀይላችን መጠቀም ላይ ብቻ አናተኩር፤ እንዲያከብሩን፣ እንዲያዳምጡን፣ የሚያበረታታቸው ምግባር ይኑረን:: ዛሬ ባለን ኀይላችን እና ጩኸታችን አንተማመን:: በኋላ ሲያድጉ፣ ዛሬ እነርሱ ላይ ያለን ኀይል አይኖረንም:: በግንኙነታችን መሐል አብሮ የተሰራ የመከባበር እና የመደማመጥ ነገር ከሌለ፣ በኋላ በእድሜ ከፍ ሲሉ፣ እኛንም ክብር ይነሱናል፤ "ድሮ እኔ ላይ የነበራችሁ ኀይል አሁን የላችሁም" ይሉናል:: እንኳን ሊያዳምጡን ቀርቶ፣ አጠገባችንም መድረስ ያቆማሉ::

> "ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ከልጅ ጋር ያለን ፍቅራዊ ትስስር፣ በልጅ ላይ የቀጥታ ብቻ ሳይሆን ተዘዋዋሪ ተጽእኖ አለው። (በሀይሉ ብቻ በመጠቀም ፋንታ) ትስስርን ያዳበረ





> ወላጅ በልጁ የመከበር፣ታዛዥነትንና አዎንታዊ ምላሽን የማግኘት ትልቅ እድል አለው (ከልጁ ጋር ትስስርን ካላዳበረ ወላጅ ጋር ሲነጻጸር)"[43]

እስከ ወዲያኛው የሚዘልቅ መከባበርና መስማማት በእኛና በልጆቻችን መሐል እንዲኖር የሚረዳን ብቸኛ ገመድ፣ በልጅነታቸው ጊዜ የተመሰረተው ለእኛ ያላቸው አክብሮት መሆኑን አስታውሰን፣ እንዲያከብሩንና እንዲያዳምጡን የሚያበረታታቸው ምግባር ይኑረን:: ወረድ ብለን ስርአት ማስተማርያ ዘዴዎችን ስንመለከት ከላይ ያነሳናቸውን ሁለት ነጥቦች እያስታወስን "ልጆቼን ሥነ ሥርዐት የማስተምርበት ዘዴዬ እነዚን ሁለት ነገሮች ያበረታታል ወይ?" ብለን ራሳችንን እየጠየቅን ይሁን::

ለልጆቻችን በጎ ምግባርን የምናስተምረው በተለያየ መንገድ ነው:: ምክር፣ ልጅን ማስተማርያ አንደኛው መንገድ ነው:: የጥፋቱን ዋጋ ማሳየት (ቅጣት) ልጅን መቅረጺያ ሌላኛው መንገድ ነው:: ቀና ሥራውን ማበረታታት ልጅን ለማስተማር አስፈላጊ መንገድ ነው:: በምሳሌነታችን ማስተማር፣ ሌላው ልጅን ማስተማርያ ዋነኛ ዘዴ ነው:: በእነዚህ ሥርዐት ማስተማርያ ዘዴዎች ተጠቅመን፣ እንዴት ልጆቻችን ውስጥ የሚቆይ እውቀትን ለመትከል እንችላለን?

## *1. <u>ምክር</u>*

ከምንም በፊት፣ ልጆቻችንን ልናስተምር የምንፈልገውን ዋና ዋና ነገሮችን እንምረጥ:: "ልጆቼ በጥልቅ እንዲማሩት የምፈልገው ይህን ይህን ነገር ነው፤ እንዲከተሉት የምፈልገው ምግባር፣ ይህን ነው፤ እንዲርቁት የምፈልገው ያንን ነው ብለን ዋና ዋና የምንላቸውን ነገሮች እንምረጥ:: ከዚያ አትኩሮታችን እነዚህን

---

[43] Smith A Charles (1999) <u>The encyclopedia of parenting theory and research</u>

ነገሮች በጥልቀት ማስተማር ላይ እናድርገው። ለምሳሌ፣ ልጆቼ እንዲርቁት የምፈልገው ዋናው ነገር ውሸት፣ ስርቆት፣ ወላጅን አለማክበር፣ ቃልን ማጠፍ ወዘተ ብለን፣ ዋና እና አስፈላጊ የምንላቸውን ጥቂት ነገሮች እንመርጥይሆናል። ከዚያ ወዲያ፣ ከልጅነታቸው ጀምሮ፣ በማይለዋወጥ ሁኔታ ያን ትምህርት ልናስተምራቸው መጣር አለብን።

"እኔን ስለሚያናድደኝ፣ ስለሚያስቆጣኝ፣" ወይም "እንዳትገረፍ ይህንን፣ ያንን አታድርግ" በማለት ፈንታ፣ የጉዳዩን መጥፎነት በቅጡ እናስረዳቸው። "እኔ ስላልሁ ብቻ" ወይም "ስለሚያናድደኝ ነገሮችን አታድርግ/አታድርጊ" እያልን፣ በደፈናው እየተናገርን ብናሳድጋቸው፣ ያ ነገር ለእነርሱ ሕይወት ያለውን ጉዳት ሳይገነዘቡት ይቀራሉ። ግንዛቤው ስለሌላቸው፣ ወይ ተደብቀው ያደርጋሉ፣ ወይም እኛ ፊት ለማስመሰል ይሞክራሉ። ቢያቆሙ እንኳ ያንን መጥፎ ድርጊት ያቆሙት፣ በግንዛቤ የጠነከረ መረዳት ኖሯቸው ሳይሆን፣ እኛን ፈርተው ለጊዜው ነው።

ሁኔታውን፣ ችግሩን ለእነርሱ በሚገባቸው መልክ ሳናስረዳ እንዲሁ በደፈናው "የእኔ ህግ ስለሆነ፣ አድርግ፣ ወይ አታድርግ" እያልን ስንጮህባቸው፣ ለእኛ ያላቸው ክብር እየጠፋ ይመጣል። "አባቴ እኔን አያዳምጥም ፤ እርሱ ግድ የሚለው የእርሱ ፍላጎት መሳካቱ ላይ ብቻ ነው" ብለው ይደመድማሉ። በመደማመጥ ላይ የተመሰረተ ግንኙነት የለንምና ሲያድጉና እነርሱ ላይ ያለን ኃይል እንደድሮው ሳይኖረን ሲቀር፣ "የራሳችሁ ጉዳይ" ብለውን ይሄዳሉ።

## 2. *ቅጣት*

ቅጣትን በተመለከተ፣ አንድ ዋና ነጥብን ልብ እንበል። ቅጣት፣ ለልጅ ተብሎ የሚደረግ ነው። "ልጁ እንዲስተካከል፣ በሕይወቱ ውስጥ የሚጎዱትን እና የሚጠቅሙትን ነገሮች እንዲማር፣ በጥሩ መንገድ እንዲሄድ ምን ይረዳዋል"፣ የሚለውን አርቀን አስበን እንጂ፣ ስለ ተናደድን፣ ወይ የተነካውን ስሜታችንን ለማብረድ





ብለን አናድርገው። በዋና ዋና ነገሮች ላይ ማተኮር ትተን፣ ዋናውን ከትንሹ ጋር እያደበላለቅን ልጆቻችንን የምንጮህባቸው ከሆነ፣ ዋና የሆነውን ከዋና ካልሆነው መለያየት ያቅታቸዋል። ልጅ ብርጭቆ ተሳስቶ ሲሰብር፣ በስሜት ተመርተን፣ ትናንት ውሸት ሲዋሽ የቀጣነውን ያህል ብንቀጣው፣ ሁሉ ነገር ድብልቅልቅ ይልበታል፤ ለእኛ ዋና ነገር ስኒ መስበር ይሁን ውሸት፣ ማወቅ መለየት ያቅተዋል። ከዚያም፣ እኛ በትንሹ ትልቁ ከተቆጣን፣ የእኛን በየደቂቃው መጮኽና መናደድን ይለምዱትና፣ ለምንነግራቸው ቁም ነገር አትኩሮት መስጠት ያቆማሉ። "እናቴ ጯሂ ነች፤ አባቴ የሚያውቀው ቁጣ ብቻ ነው" ብለው ይደመድማሉ። በኋላ አንድ ቁም ነገር ልንነግራቸው ብንሞክር እንኳ፣ ማዳመጥ አይፈልጉም፤ "እንግዲህ ጀመራቸው" ብለው ጆሮዋቸውን መዝጋት ይለምዳሉ።

እዚህ ጋ ልብ እንበል፤ ዋናው ቁም ነገር፣ ለልጆቻችን በሕይወት የሚረዷቸውን፣ ዋና ዋና ነገሮች መማራቸው ነው። ልጅ አዳልጦት ብርጭቆ ስለሰበረ፣ ነገ ሕይወቱ አይጎዳም፤ የሚዋሽ ልጅ ግን ይጎዳል፤ እናት አባቱን ማክበርን ያልተማረ ልጅ ግን፣ ይጎዳል። ኃይላችንን ካወጣን አይቀር፣ ልጆቻችን ገንዘባቸው እንዲያደርጉት በምንፈልገው ሥነ ምግባራዊ ፋይዳ ላይ እንትጋ። ዛሬ ሁሉን በሚሰሙበት ጊዜ የሚማሩት፣ ለረጅም ጊዜ መሪያቸው እንደሚሆን አስታውሰን፣ ዋና የምንላቸው ነገሮች ላይ እናተኩር። "እናቴ በእውነት የምትጠላው ይህንን ነው"፣"አባቴን የሚያስቆጣው ይህ ነው" ብለው ከልብ እንዲረዱ፣ በተመረጡ ዋና ነገሮች ላይ እናተኩር።

ልጅን ስንቀጣ እኛ ብቻ በመጮኽ ፈንታ፣ የድርጊቱን መጥፎነት እንዲያስብበት እያደረግን ብንቀጣው፣ ያጠፋው ጥፋት ጥልቀቱ ምን ያህል እንደሆነ፣ እንዲገባው ያበረክታል። ያ ምን ማለት ነው? ለምሳሌ፣ ልጅ ዋሽቶ ስናገኘው፣ ወዲያው ከመምታት ወይም ከመጮህ ፈንታ፣ እያነጋገርነው ስላደረገው ነገር እንዲያስብበት እናድርግ። "ስለ ውሸት የነገርኩህን አስታውስ፤ ያስተማርኩህ ምንድነው? ይህ ድርጊት በምን ይጎዳሀል ብዬህ ነበር?"፤ ልጅ

መልስ ይመልሳል:: "ውሸት ስትዋሽ ምን ዐይነት ፍሬ ይኖረዋል ብዬህለሁ? እሺ፣ ለዚህ ነገር ቅጣቱ ምን ይሆናል ብዬ ነበር?" ልጅ መልስ ይመልሳል:: በዚህ የጥያቄና መልስ ሂደት ውስጥ፣ ያስተማርነውን ነገር ሁሉ እያስታወሰ ነው:: የሠራው ሥራ የተሳሳተ እንደ ሆነ፣ እያስታወሰ ነው:: በዚህ መልክ እያወያየን፣ ስለሠሩት ሥራ በጥልቅ እንዲያስቡበት እናድርግ:: እንዲሁ ዝም ብለን መጮሁ ላይ ካተኮርን ግን፣ ስለኛ ጩኸት ብቻ እንጂ፣ ስለሠሩት ሥራ ለማሰብ እድል አያገኙም::

ከዚህ ጋር ተያይዞ፣ የምንቀጣቸው ቅጣት፣ ለደቂቃ አሳምሞ ወይም አስፈራርቶዋቸው የሚረሱት ሳይሆን፣ ስለሠሩት ጥፋት ቀስ ብለው እንዲያስቡበት የሚረዳቸው ዐይነት ቅጣት ይሁን፤ ውስጣቸው የገባ ግንዛቤ የሚኖረው፣ ቀስ ብለው ሲያስቡበት ነውና:: ለምሳሌ ለልጅ፣ "ማታለል ጥፋት ነው" ብለን ነግረነው ነበር እንበል:: ልጅ እኛን አታሎ የሆነ ነገር አደረገ እንበል:: በዛ ሰአት፣ እዚያው ጮኸን፣ ገርፈን ነገሩ ካለቀ፣ የጥፋቱን ውጤት እንዲያስብበት ረዘም ያለ ጊዜ አይኖረውም:: ከደቂቃ ዱላ ይልቅ፣ "ለአንድ ሳምንት ቴሌቪዥን ተከልክለሀል" ብንለው፣ የአንድ ሳምንቱ ጊዜ፣ ስለ ጥፋቱ ደግሞ ደጋግሞ ያስገነዝበዋል:: ዛሬ ባይገነዘበው፣ ነገ ያቺን የሚወዳትን የቴሌቪዥን ፕሮግራም ማየት ሳይችል ሲቀር፣ የሥራውን ውጤት እንዲያስብበት እድል ይሰጠዋል::

ልጅ ለሰራው ጥፋት፣ ሀላፊነት መውሰድን፣ ለማካካስ ተገቢ እርምጃ መውሰድን፣ እንዲማር እናድርግ። ያ ምን ማለት ነው? ለምሳሌ የሆነ ነገር ተናግሮ ወይም አድርጎ ሰውን ካስቀየመ፣ እኛ ለእሱ፣ይቅርታ አንጠይቅለት፤ በራሱ እንዲጋፈጠው እናድርግ፤ ራሱ ሄዶ ይቅርታ ሲል፣ ስለ ሰራው ስህተት እንዲያስብበት የበለጠ እድል ይሰጠዋልና፤ ከዚህም በተጨማሪ ለጥፋት ኀላፊነት መውሰድን ይማራል:: በግዴለሽነት ገንዘቡን አጠፋፍቶ ከሆነ፣ ጮኸን መልሰን ወዲያው አንስጠው:: ያን ገንዘብ አሁን ስላጠፋው፣ገንዘቡን መልሶ ለማግኘት ምን ማድረግ





እንዳለበት እንንገረው:: ልጅ ያበላሸው ነገር ካለም፣ ለዚያች ደቂቃ ጮኸን፣ ከዚያ ግን እኛው ሄደን ነገሩን ሁሉ በማስተካከል ፈንታ፣ "በል ተነሥተህ አጽዳ" ብለን እንዲያጸዳ ብናደርገው፣ የሠራውን ሥራ ውጤት ረዘም ያለ ጊዜ ወስዶ ለመገንዘብ፣ ከስህተቱም ለመማር፣ ዕድልን ይሰጠዋል::

"ይህ ነገር ያስቆጣኛል ወይም ያስቀጣል" ብለን ህግ ካወጣን፣ ሀሳባችንን ሳናወላውል ልክ እንዳልነው መቆየትና መቅጣት አለብን:: ለምሳሌ፣ ከቤተሰባችን የቅጣት ሕግ መኻል ማታለል እና ወላጅን አለማክበር ካሉበት፣ ልጆች መዋሸት እና ወላጅን ክብር መንሳት፣ ሁሌም ቅጣትን እንደሚያስከትሉ ማወቅ አለባቸው:: አንድ ቀን በጣም ተቆጥተንና በዚያም ነገር ቀጥተናቸው፣ በሚቀጥለው ያንን ነገር ችላ ብንለው፣ ቀጣይነት ያለው ትምህርት ለልጃችን ሳናስተምር እንቀራለን::

ልጅ ስሜታዊ በመሆን ሀሳባችንን ሊያስለውጠን ቢሞክር፣ እኛ ባልነው ነገር መጽናት አለብን:: ለምሳሌ እናቷን ክብር የሚነካ ንግግር ለተናገረች ልጅ፣ "በዚህ ባሳየሽው መጥፎ አመል ምክንያት ያ ሊገዛልሽ የነበረው ነገር ቀርቷል"፣ ብለን ነግረናታል እንበል:: ልጅ፣ " እኔን አትወዱኝም" ብላ ስታለቅስ "በቃ ተዪው ፤ሀሳቤን ስለለወጥኩ ይገዛልሻል" ብንል፣ ከቅጣት ነጻ በማድረጋችን፣ ልጃችንን በትልቁ የሚጎዳና መጥፎ ትምህርት የሚያስተምር ነገር ምሳሌነትን እያሳየን ነው:: እንደዚያ ስናደርግ፣ "ወላጆቼን እንደፈለግሁ መጠምዘዝ እችላለሁ" ብላ እንድታምን መንገድ እንከፍትላታለን:: "እናቴን መሳደቤ ትልቅ ጥፋት አይደለም"፣ ብላ እንድታምን እናደርጋታለን:: "በዚህ ቤት ውስጥ ሀይል ያለኝ እኔ ነኝ" ብላ እንድታምን እናበረታታታለን:: "ለማጠፋው ጥፋት ቅጣት አያገኘኝም" ብላ እንድትደመድምም መንገድ እንከፍታለን:: እኛ፣ ወላጅን በማክበር ጉዳይ ላይ፣ የማይነቃነቅ ሕግ እንዳለን ልጃችን ሳትረዳ ትቀራለች:: ልጃችን ትምህርቷን በጥልቀት እንድትማር ብቻ ሳይሆን፣ እኛንም ማክበር እንድትማር፣ በቃላችን እንጽና:: "እኔ ይህን ነገር እንዴት እንደምጠላ ታውቂያለሽ:: ይህ ነገር

እንዴት መጥፎ እንደሆነ ተናግሪያለሁ፤ አሁን ለጥፋትሽ ዋጋን መቀበል አለብሽ" ብለን፣ ሳንነቃነቅ መቆም አለብን።

ከዚህ ጋር ተያይዞ፣ ልጆች ፊት አባትና እናት በሥነ ሥርዐት ትምህርቱ ውስጥ አብረው መቆም አለባቸው። ወላጅ ቅጣት ካወጀ በኋላ፣ ልጅ ፊት፣ " ይህ ቅጣት መኖር የለበትም" የምንል ከሆነ፣ ቅጣት ያወጀውን ወላጅ በልጅ ፊት የሚከራከሩ ከሆነ፣ የራሳችንን ልጅ በኀይለኛ እየጎዳን እንዳለን፣ ልብ እንበል። ልጅ እናትና አባቱ በቅጣት ዐይነት፣ በሥነ ሥርዐት አያያዝ ዐይነት እንደማይስማሙ ሲያይ፣ አባትን እየተጠቀመ የእናት ቅጣትን ማፍረስ እንደሚችል፣ እናትን እየተጠቀመ የአባትን ትእዛዝ ማፍረስ እንደሚችል ይማራል። በሚቀጥለው ጊዜ፣ "ለዚህ ጥፋት ይህን ቅጣት ታገኛለህ" ብሎ አንደኛው ወላጅ ሲነግረው፣ "ሀሳባቸውን ይለውጣሉ፤ አባቴ እንዲህ ቢል እናቴ ታስጥለኛለች ፤ ቅጣቴንም አላገኝም" ብሎ ስለሚያስብ፣ ማስጠንቀቂያችን አያሳስበውም። ከጥፋት መማርን፣ ታላቅን ሰምቶ መታዘዝን፣ ሳይማር ያድጋል። የወላጅን ቃል የማያከብር፣ ሀሳቡን ይለውጣል ብሎ የሚያስበውን ወላጅ እየጠመዘዘ የፈለገውን ለማግኘት የሚሞክር፣ ይሆናል። በልጅ በአቀጣጥ ወይም በሥነ ሥርዐት አያያዝ ዘዴው ያልተስማማንበት ነገር ቢኖር እንኳ፣ ውይይቱ ልጅ በሌለበት መሆኑ አስፈላጊ ነው። ከዛ በተረፈ ግን፣ እናትና አባት እንደወላጅነታቸው፣ በሥነ ሥርዐት አስፈጻሚነት ሁሌ እጅ ለእጅ ተያይዘው እንደቆሙ፣ ለልጅ ማሳወቅም ማሳየትም አለባቸው፤ የጋራ ግባቸው ልጅ ስርዐት ተምሮ፣ ቤተሰቡን አክብሮ፣ ማደጉ ነውና። ልጅ እያለቀሰ ለእናት መጥቶ፣ "አባባ እንዲህ ትቀጣለህ አለኝ" ቢል፣ "አባትህ ነው፤ የእርሱን ውሳኔ ማክበር አለብህ" ብላ፣ እናት አቋሙዋን ማጽናት፣ ያስፈልጋታል፤ ቢበዛ፣ "የምትጠይቀው ነገር ካለ እርሱን አነጋግር፤ አባትህ ነው" ማለቱ፣ ትክክለኛው እርምጃ ነው። አባትም ይህንኑ ሊያስታውስ ይገባል፤ እናት አንዴ ወስና ለልጅ፣ "ይህን ማድረግ አትችልም" ካለች፣ ተዘናግቶ ልጅ የፈለገውን እንዲያገኝ መፍቀድ፣ የልጅን ሥነ





ሥርዐት እንደሚጎዳ ተረድቶ፣ በተወሰነው ነገር መቆም አስፈላጊ ነው።

ልጅን፣ በምንም አይነት፣ መጥፎና ዝቅ የሚያደርግ ስድብ እየሰደብን አንቅጣ። አንዳንዴ ስንናደድ፣ልጅን የማይሆን ስድብ እንሳደብ ይሆናል። "አንቺ መቼም አያልፍልሽም፤አንተ መቼም የማትረባ ነህ፤ ዘላለምህን እንዲህ ሆነህ የምትቀር ሰነፍ ነህ፤" እያልን የምንናገራቸው ነገሮች የልጆቻችንን አእምሮ ይጎዳሉ። በተጨማሪም ልጆቻችን "እንደዚያ ነኝ" ብለው እንዲያስቡ፣ያም በልባቸው እንዲቀረጽ ያደርጋል። ለጊዜው ተናደን መሳደባችንን አያዩም፤ እኛን ያምኑናልና፣ "ለካ እኔ እንዲህ ዐይነት ሰው ነኝ" ብለው ይደመድማሉ። አንድ ሰው ደግሞ " እኔ እንዲህ ነኝ" ብሎ ከደመደመ፤ ልክ እንደዛው ሆኖ ሊቀር ትልቅ እድል ይኖረዋል።

ልጅን የራሱን ጥፋት እያነሣን እንቅጣ እንጂ፣ በፍጹም ከወንድምና ከእህት ወይም ከሌላ ልጆች ጋር አናስተያይ። "እነርሱ የተባረኩ፣ አንተ ግን ባለጌ፣ እነርሱ ጨዋ አንቺ ሁሌ አጥፊ፣" ብለን እየተናገርን፣ ልጃችንን ለመቅጣት ከመሞከር እንቆጠብ፤ ከሌላ ጋር ማስተያየት ፣ ልጅ ስለ ራሱ ያለውን አመለካከት ሊያቆሽሽ፣ ትልቅ ሀይል አለውና።

ልጆቻችን ያጠፉት ጥፋት፣ ከእኛ ፍቅር እንደለያያቸው የሚናገር መልእክት አንላክ፤ ያ ልጅን በጣም ሊጎዳ ሀይል አለውና። "ባንተ ምክንያት ቤተሰብ እንዲህ ሆነ፤ ባንቺ ምክንያት ታመምኩ" ወዘተ፣ የሚሉ ንግግሮችን ልናቆም ይገባል፤ እንዲህ አይነት ጎጂ ቃሎች ልጅን በማስተማር ፈንታ የሚያደነዝዙ፣ ከዚያም በተጨማሪ ለእኛ ያለው ውስጣዊ አክብሮት እንዲጠፋ የሚያደርጉ ናቸውና።

ባጠቃላይ፣ ልጅን የማይለቅ ጸጸት ውስጥ የሚከቱ፣ ንግግሮች ከመናገር፣ ወይ ድርጊቶች ከማድረግ፣ እንቆጠብ። እውነት ነው፤ የራሳችን የኑሮ ጫና ምክንያት፣ ከልጃችንም ጥፋት ጋር ተደምሮ፣ አንዳንዴ ስሜታዊ ሊያደርገን ይችላል። ለምሳሌ፣ ቀን ደክሞን ውለን መጥተን፣ ልጅን ተው እያልነው ሲያጠፋ

ስናይ፣ የምንናገረውን ለመግታት ሊያዳግተን ይችላል:: በእንደዚህ አይነት ጊዜ፣ ንዴታችንን ልናበርድበት የምንችልበትን ሌላ መንገድ እንፈልግ:: በረድ እስኪልልን ክፍል ለቀን እንውጣ፤ ጓደኞችን ጋር ደውለን ስልክ እናውራ:: የማይሆን ቃል ከዱላ እጥፍ በሆነ ሁኔታ ልጅን ሊሰብር እንደሚችል አስታውሰን፣ ለእኛ ተስማሚ የሆነ እኛን የሚያበርደንን ዘዴ ስራዬ ብለን እንጠቀም፤ ኋላ ተመልሰን ስናየው፣ በውሳኔያችን ደስ እንሰኛለን::

ልጅ ጥፋት አጥፍቶ አንዴ ለጥፋቱ ቅጣትን ካገኘ በኋላ፣ መዝገቡን እንዝጋ:: ያ ማለት ምን ማለት ነው? የአንድ ጊዜ ጥፋታቸው፣ የዘላለም መወንጀያቸው አናድርገው:: በተናደድን ቁጥር፣ "ያን ጊዜ ይህን አጥፍተህ ያኔ ደግሞ እንዲህ አጥፍተሽ" ብለን ያለፈውን አናንሳ፤ ሊለወጡ የማይችሉ ነገሮች ላይ ሀይልን ማፍሰስ፣ ትርፉ እኛን ማናደድ፣ ልጆችም ወደፊት እንዳይራመዱ መዳረግ ነውና::

## 3. ጥሩ ምግባርን ማበረታታት

> "ብዙ ጥናቶች እንደሚያሳዩት፣ ጥሩ ምግባርን ማበረታታት፣ ከቅጣት የበለጠ አዎንታዊ ተጽእኖ በልጅ ላይ አለው::" [44]

ልጅን በጥልቀት ማስተማርያ ሌላኛው መንገድ፣ ከመጥፎ ስራው በተቃራኒ ጥሩ ነገርን ሲያደርግ፣ ከድሮው ሲሻሻል፣ ማሞገስ፣ ማበረታታትና መሸለም ነው:: ልጆች በጥሩ መንገድ ሲሄዱ ስናይ፣ እንዴት እንደተሻሻሉና እንዴት እንደ ኩራንባቸው መንገር አስፈላጊ ነው:: ከላይ እንዳየነው፣ ብዙ ጥናቶች ይህንን ይደጋግማሉ፤ የልጅን ጥሩ ምግባር ማበረታታት ልጅን ለማነጽ ዋነኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ይናገራሉ::

[44] Jing Zhou, M.S, BCBA Decreasing problem behaviors through good teaching www.brightfeats.com/articles





አብዛኛውን ጊዜ፣ ዋነኛ አትኩሮት የምንሰጠው ለሚያጠፋ ልጅ ነው:: ከሚያጠፋው ልጅ ጋር ስንጯጯህ፣ ጥሩ የሚሠራና ብዙ የማይረብሽ ልጅ ይረሳል፤ ጥሩ ሥራውም ሳይታይለት፣ ይቀራል:: ያ ትክክለኛ እርምጃ አይደለም። ብዙውን ጊዜ ብቻቸውን በሚያሳልፉበት፣ በተለይ በውጭ አገር፣ ልጆች የወላጅ አትኩሮትን በጣም ይጠማሉ:: ልጅ የወላጁን አትኩሮት የሚያገኘው፣ መጥፎ ሥራ ሲሠራ፣ ሲባልግ ብቻ መሆኑን ካየ፣ በዚያ መጥፎ ሥራ ይቀጥላል:: ጥሩ ልጆችም፣ ጥሩ ስራቸው ምንም አይነት ሙገሳና ደገፉ እንዳላመጣላቸው ሲያዩ፣ ሁሌ የእኛን አትኩሮት የሚያገኘው የሚያጠፋው ወንድማቸው፣ ጥፋት ውስጥ የምትገባው እህታቸው እንደሆኑ ሲረዱ፣ ሌላው ቢቀር የእኛን አትኩሮት ለማግኘት ሲሉ፣ መጥፎ ነገር ለማድረግ ይነሣሣሉ::

ይህንን እውነት ልብ እንበል፤ የልጅ ምርጫውና የእርምጃ አቅጣጫው፣ በወላጅ ምላሽ ይቀረጻል:: ውሸት አትዋሽ ብለን ደጋግመን መክረነው፣ ወዲያው ተግባራዊ አድርጎ እውነት ሲናገር፣ ሳናስተውል ቀርተን ችላ ብለነው ሲያይ፣ "ለጥሩ ሥራዬ ምንም ዋጋ የለውም" ብሎ ማመን ይጀምራል። ስለዚህም በዛ ጸባይ ለመቀጠል አይበረታታም። ይህ የማንም የሰው ልጅ ጸባይ ነው። በራሳችን እንኳ ብናየው፣ ስራ ሄደን፣ ወር ሙሉ ሰርተን፣ ከእንግዲህ ደሞዝ የለም ቢሉን፣ ለሚቀጥለው ወር ለመስራት አንነቃቃም፤ ልጅም እንደዛው ነው:: ራሱን አሻሽሎ፣ ጥሩ ሰርቶ፣ ለዛ ግን ከኛ ምንም አይነት አዎንታዊ ምላሽ ሳያስገኝለት ሲቀር፣ በዛው መንገድ ለመቀጠል ያለው መነቃቃት ይጠፋል:: ጥሩ ስራው ጥሩ ምላሽ ሲያስገኝለት፣ እኛ ጥሩ እንዳደረገ ስንነገረው፣ ስናሞግሰው፣ "በርታ ልጄ" ስንለው ግን፣ በጥሩ ሥራው እንዲቀጥል ይነቃቃል፤ ቀስ በቀስም ያ አዎንታዊ ተግባር፣ የጸባዩ ክፍል ይሆናል::

ልጅን ለጥሩ ሥራው መሸለምና በቃላት ደስታችንን መግለጥ ጠቀሜታው ለእርሱ ብቻ አይደለም:: ሌሎች ወንድምና እህትም፣

ከዚያ ሁኔታ እንዲማሩና እንዲሻሻሉ መንገድ ይከፍታል። ለምሳሌ አንድ ልጅ ውሸት ዋሽቶ፣ የሚወደውን የቴሌቪዥን ፕሮግራም፣ "ለሳምንት ማየት አትችልም" ተብሏል እንበል። እህቱ ደግሞ እውነት ተናግራ፣ ስትሸለም ወይ ስትሞገስ ያያል። ያኔ፣ "እውነት የመናገር" ጥቅሟን ይማራል። የእርሱ ጥፋት እንዴት እንደጎዳው ብቻ ሳይሆን፣ ትክክል መሥራት ደግሞ እንዴት ሊጠቅመው እንደሚችል ያስተውላል። ልጆችን በጥሩ ስራቸው ማሞገስና ማበረታታት፣ ጥልቅ ትምህርት ማስተማርያ መንገድ ብቻ ሳይሆን፣ ከእኛ ጋር ላላቸው ግንኙነት ማጠንከርያ መሰላል መሆኑን ተረድተን፣ በጥሩ መንገድ ሲሄዱ ስናይ፣ እንደግፋቸው።

ልጆቻችንን እንዴት መቅጣትና እንዴት ማበረታታት አለብን የሚለው ነገር የሚወሰነው፣ እንደ ዕድሜያቸውና ጠባያቸው ነው። ያ ምን ማለት ነው? ወንድም ከወንድም እህት ከእህት ይለያያሉ፤ ለአንዱ ልጅ ቀላል የሆነለት፣ ለሌላው ከባድ ነው። አንዳንድ ልጅ አንዳችም ችግር ውስጥ ሳይገባ ሶስት ዓመት ይቆያል፤ አንዳንድ ልጅ ደግሞ ትናንሽ ጥፋት ቶሎ ቶሎ ያጠፋ ይሆናል። ይህ የጸባይ (የተፈጥሮ) ጉዳይ ነው። ያንን ተረድተን፣ ልጃችንን በራሱ ሚዛን እንለካ፤ ብዙ ጥፋት ደጋግሞ የሚያጠፋ ልጅ፣ ትንሽ ጥሩ ነገር ሲሠራ፣ አጋጣሚው አያምልጠን፤ ለበጎ ስራው አዎንታዊ ምላሽን እንስጠው፤ "ልክ እንደ ወንድሙ እስኪሆን፣ እስኪሠምር ድረስ ድጋፌን አላሳየውም"፣ ከማለት እንቆጠብ፤ በጥረት የተራመደውን መንገድ ማየት ትተን ከሌላ እርምጃ ጋር ስናወዳድረው፣ ልጅ ጭራሽ ተስፋ ይቆርጣልና።

## 4. <u>ምሳሌነት</u>

ልጅ እንዲያከብረን፣ እንዲያዳምጠን እና ግንዛቤ እንዲያገኝ የሚረዳውን ዋነኛ መንገድ ማወቅ ከፈለግን፣ ይህንን ነጥብ ልብ እንበል። ዋናው መንገዱ፣ የእኛ ምሳሌነት ነው። "እንዲህ አታድርግ ልጄ" እያልን፣ እኛ የዚያን ተቃራኒ ስናደርግ ካየን፣ የሚከተለው ምክራችንን ሳይሆን ድርጊታችንን ይሆናል። ልጅ፣ አስተሳሰቡንና





አካሄዱን የሚመሰርተው፣ እኛን ተመልክቶ ነው። ቤት ውስጥ ወላጅ ሲሰዳደብና ሲጯጯህ እያየ ካደገ፣ እርሱም ልክ እንደዚያው መጯጯህን ይለምዳል። በወደፊት ሕይወቱም ሆነ በትዳር ግንኙነቱ፣ ያንን መንገድ ለመከተል ትልቅ እድል ይኖረዋል። ወላጅ "አንድ ነገር አደርግልሀለሁ" እያለ፣ ግን ቃሉን ሲያጥፍ እያየ ካደገ፣ ልጅም ቃሉን የሚያጥፍ፣ አደርጋለሁ የሚለውን የማያደርግ እንዲሆን ትልቅ እድል ይኖረዋል። አትዋሽ ልጄ ብለነው፣ እኛ "ስልክ ሲደወል አባባ የለም በል ልጄ" የምንለው ከሆነ፣ መዋሸት ጥሩ ነው ብሎ አምኖ ያድጋል። ለልጃችን ልናስተምረው የምንፈልገውን ደግ ነገር፣ በጥልቀት ማስተማርያ ዋነኛው መንገድ ምሳሌነት መሆኑን አስታውሰን፣ በሕይወቱ እንድያቅፍ የምንፈልገውን፣ በተግባር እናሳየው።

ምሳሌነታችን ትልቅ ዋጋ ያለው፣ሌላው ምክንያት፣ ከልጃችን ጋር ለሚኖረን የወደፊት ግንኙነት ነው። ለምሳሌ እኛ ጥፋት ስናጠፋ በማመን፣ "ልክ ነህ፤ ያ የኔ ጥፋት ነው" በማለት ፋንታ፤ "እኔ ወላጅ ነኝ፤ ሁሌ ትክክል ነኝ" እያልን ካሳደግነው፣ ልጅም በምሳሌነታችን ያንኑ ይማራል። በኋላ ሲያድግ፣ እኛንም እንደዚያው "እኔ ብቻ ነኝ ትክክል" ይለናል፤ ወይም ጭራሽኑ ይርቀናል። ስንሳሳት ስናምን፣ በእውነት መንገድ ስንቆም ሲያየን ግን፣ እሱም ያንኑ ጸባይ ለመከተል ትልቅ እድል ይኖረዋል። ልጆቻችን ከፍ አድርገው እንዲመለከቱን፣ እንዲያከብሩን ከፈለግን ምክራችንን ብቻ ሳይሆን ምግባራችንንም እንደሚመዝኑ ተረድተን፣ ሁኑ የምንላቸውን ነገር እኛ በምሳሌነታችን እናስተምራቸው።

# የሕይወት ተሞክሮ



## የወላጆቼ ምሳሌነት

የአሜሪካ ተወላጅ ላልሆነ ሰው፣ አሜሪካ አገር መጥቶ ኑሮን መስርቶ መኖር ቀላል ነገር አይደለም:: የለመድነውን ባህል፣ አኗኗርና ስራ ጥለን መምጣት ለማንም ከባድ የሆነ ለውጥ ነው:: እንደዛም ሆኖ ከሁሉም በላይ ውጭ አገር መጥቶ መኖር የሚከብደው የሚመስለኝ ለወላጆች ነው፤ምንም በማያውቁበት አገርና ባህል ውስጥ ልጆቻቸውን እያሳደጉ ነውና::

ቤተሰቦቼ ብዙውን ትምህርት ያስተማሩኝ በንግግር ሳይሆን በምሳሌነት ነበር:: ከጸባይ ጀምሮ፣ ከሰው ጋር እንዴት ልሆን እንደሚገባኝ፣ ሁሉን ነገር ሊያስተምሩን ይሞክሩ የነበረው በምሳሌነታቸው ነበር:: ለምሳሌ እውነተኛ የሴትነት ትርጉምን ያወኩት፣ እናቴ ላይ የማየውን ቀን ከቀን ጸባይ ተመልክቼ ነው:: ጠንካራነቷን፣ እምነቷን፣ ስራ ወዳድነቷን፣ ፍቅሯን እያየሁ አድጌያለሁ፤ ሳይለዋወጥ የሚታየው ምሳሌነቷ፣ እኔም በሴትነቴ ምን ማድረግ፣ እንዴት መሆን እንደሚገባኝ በጥልቁ አስተምሮኛል::





እውነተኛ ፍቅር ምን እንደሆነ የተማርኩት፣ እውነተኛ ፍቅር ምንም ቢሆን እንደማይወድቅ የተረዳሁት፣ አባቴና እናቴ ለእርስ በርስ የነበራቸውን ፍቅር፣ትእግስትና መከባበር እያየሁ በማደጌ ነው::ስለእምነት የተማርኩት ወላጆቼ በነገሩኝ አይደለም፤ በደጉ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በክፉም ጊዜ የነበራቸውን ጠንካራ እምነትና ከእግዚአብሄር ጋር መጣበቅ ትልቅ ትምህርት ሆኖልኛል:: እናቴ በህመም ውስጥ ስታልፍ፣ እግዚያብሄር ላይ የነበራት ቋሚ እምነት ለህይወቴ ትልቅ ትምህርት ሆኖልኛል::

አባቴ ቁጭ አድርጎ፣ እግዚአብሄርን የሚወድ ሰው እንዲህ አይነት ነው እንዲህ እያለ ብዙም አልመከረኝም፤እሱ ራሱ ግን በምሳሌነቱ የእግዚአብሄር ሰው ትርጉም ምን እንደሆነ አሳይቶኛል:: ከቤተሰቦቹ፣ ጓደኞቹ ጋር ባለው ግንኙነት እና በቀን በቀን ህይወቱ ውስጥ በሚወስናቸው ውሳኔዎች፣ ትላልቅ ምሳሌን ትቶልኛል:: አሁን በሀያዎቹ አመታቴ ውስጥ ሆኜ እያለሁ እውነተኛ ወንድ ማለት ምን ማለት እንደሆነ አውቃለሁ፤ ወንድ ልጅን ስተዋወቅም ጥሩነቱን፣ ማንነቱን ለመለካት ብዙ የሚከብደኝ አይመስለኝም፤አባቴ የዛ ትርጉም ማለት ምን እንደሆነ በተግባር አሳይቶኛልና::

ባጠቃላይ፣ የዛሬው ማንነቴ በዋነኛነት የተወሰነው በወላጆቼ ምክንያት ነው:: አላማዬ፣ ህልሜ የተቀረጸው የእነሱን የሕይወት ጎዳና እና ምርጫ በመመልከት ነው:: የእነሱ በኔ ሕይወት ላይ ያደረጉት ተጽእኖ፣ማንም ጓደኛ ሆነ ወዳጅ ሊወስደው የማይችለው ነው:: አንድ ቀን እኔም በተራዬ ለልጆቼ፣ ወላጆቼ የሰጡኝን ዋና ነገር መስጠት ብችል ዋነኛው ምኞቴ ነው::

# ምዕራፍ ሰባት

## በቤት ውስጥ ችግር ቢገጥም

በዚህ ርእስ ሥር የምንመለከተው፣ በሕይወታችን ችግር ሲከሰት፣ ችግሩ ልጆቻችንን እንዳይጎዳ፣ ምን ማድረግ እንደሚኖርብን ነው:: በዚህች ምድር ስንኖር፣ ያላሰብነውና ያልጠበቅነው ችግር ሊመጣ ይችላል:: በዚህ ሰዓት፣ ወላጅ የሚወስደው እርምጃ እና የሚመርጣቸው ምርጫዎች፣ ልጆች ጠንክረው ከተከሠተው ችግር በመውጣቸው ላይ፣ ትልቅ ተጽእኖ ያደርጋል::

> "ልጆች በሀዘን መዋጥ ብቻ ሳይሆን፣ ከብዙ አኳያ ሀዘናቸው ከአዋቂዎች የጠነከረና የባሰ ሊሆን እንደሚችል፣ ብዙ ጥናቶች መዝግበዋል።"[45]

ችግር ሲፈጠር፣ "ልጆች ናቸው አይገባቸውም" ብለን፣ ችላ አንበላቸው::ቤተሰብ ውስጥ ውዥንብር ሲፈጠር፣ ልጅ በጣም ያስተውላል፤ ሰው ቤት ውስጥ ሲታመምና የመሳሰሉት ፈተናዎች ሲከሠቱ፣ ልጆች ሁሉን ነገር በጭንቅላታቸው ይይዛሉ:: በህብረተሰባችን ውስጥ፣ ብዙውን ጊዜ፣ እንዲህ አይነት ነገር፣ ልጆች ልብ ያላሉ ብለን አናስብም፤ በዛ ፈታኝ ሰአት ምን ይሰማቸው ይሆን ብለንም፣ አንመረምርም:: አብዛኛዎቻችን፣ ስለመጣው ችግር ከመሰሎቻችን ጋር እንወያያለን እንጂ፣ ከልጆቻችን ጋር ጊዜ ወስደን አንነጋገርም::

አያት አጎት አክስት በሌለበት፣ ልጆቻችን ብቻቸውን በሆኑበት በተለይ በውጪ አገር፣ በፈተና ጊዜ ካገለልናቸው፣ ይጎዳሉ፤

[45] Fitzgerald Helen; (1992) The Grieving Child: A Parent's Guide , Touchstone publishing





በራሳቸው አእምሮ ነገሩን መተርጎም፣ ለችግሩ ትክክለኛ ያልሆነ ገጽታ መስጠት ይጀምራሉ:: ለምሳሌ በእናትና በአባት መሀል ጥል ቢፈጠር፣ ልጅ ያያል፤ ያስተውላል:: በዚያን ሠዓት ልጅ እንደሌለ አድርገን ችላ ብንለው፣ ምኑን እንደሚጨብጠው እንደሚለቀው ግራ ይገባዋል:: የልጅ አእምሮ እንደ ትልቅ ሰው የማመዛዘን ችሎታ የለውምና፣ በራሱ ጤነኛ ያልሆነ እምነት ላይ ይደርሳል:: "እናት አባቴን ለሁሌም ላጣ ነው" ብሎ ሊያስብ ይገደዳል:: "ይህ ሸክም ዘላለማዊ ነው ካሁን በኋላ ደስታ የለም" ብሎ ሊያስብም ይችላል::

> "ልጆች ከደረሰባቸው ጉዳት እንዲያገግሙ ስንፈልግ፣ ይህንን ነጥብ ልብ እንበል፤ በግልጽ ከማነጋገር የበለጠ ትልቅ መፍትሄ የለም። በግልጽ ስለጉዳዩ መወያየት፣ ልጆች የሚሰማቸውን ገልጸው እንዲናገሩ መንገድ ይከፍትላቸዋል። ልጆቻችንን ስለእነዚህ ነገሮች በግልጽ የማናነጋግር ከሆነ፣ በራሳቸው ያልሆነ ድምዳሜ ላይ ይደርሳሉ።"[46]

ከላይ ያለው ሀሳብ እንደሚያመለክተው፣ በቤት የደረሰው ከባድ ሸክም፣ ልጆችንም ከእኛ እኩል ወይም ከእኛ በበለጠ ሊበጠብጥ እንደሚችል ተረድተን፣ ለእነርሱ ቦታ እንስጥ:: በግልጽ ችግሩን እያዩት ከሆነ፣ ሚዛናዊ በሆነ መልክ እንዲታያቸው፣ ከእኛ ከወላጆቻቸው የሆነ ነገር መስማት እንዳለባቸው ተረድተን፣ ስለእውነቱ በሚገባቸው መልክ እናነጋግራቸው፤ "እንደምታዩት በቤተሰብ መሐል ትንሽ ችግር አለ፤ ይህ ከእናንተ ጋር ምንም የተያያዘ ጉዳይ አይደለም፤ በትልቅ ሰው መሐል አንዳንዴ አለመግባባት አለ:: ነገሮችን በውል ለመፍታት ደግሞ የቻልነውን እናደርጋለን" "ወንድምሽ ያው እንደምታዩው ትንሽ ህመም ደርሶበታል፤ግን ግዴለም አብረን እንወጣዋለን፤ እኛም የተቻለንን ሁሉ እያደረግን ነው፤" ብለን፣ በግልጽና ሊሰሙት በሚስማማ መልክ አድርገን፣ እናስረዳቸው:: እንዲህ ከእኛ መስማታቸው፣ በውስጣቸው የመዘገቡትን አሉታዊ አመለካከት ይሰርዝላቸዋል::

[46] Fitzgerald Helen; (1992) The Grieving Child: A Parent's Guide , Touchstone publishing

ከዚህ ጋር ተያይዞ፣ ልጆች የሚያውቁት ወይም የሚወዱት የቤተሰብ አባል በሞት ከተለየ፣ ስለዚያ ሰው በግልጽ ማውራት ልጆችን በጣም እንደሚጠቅም ብዙ አስተማሪዎች ይናገራሉ። ልጆቻችን ስሜታቸውን በግልጽ አውጥተው ከኛ ጋር እንዲያወሩ እናበረታታ፤ስለተሰማቸው ሀዘን፣ጭንቀትም በግልጽ እንዲናገሩ፣ ማልቀስ ከፈለጉ ሳይሳቀቁ እንዲያለቅሱ እናበረታታ ሀዘናቸውን ካልተጋፈጡት፣ ትርፉ የሚሆነው፣ በውስጣቸው መቅበርና መቆዘም ነውና።

በሕይወታችን ውስጥ ፈተና ሲመጣብን፣ ንዴታችንን፣ ምሬታችንን፣ ልጃችን ላይ አንወጣ። አዎ፤ የገጠመን ፈተና፣ ከባድ ሊሆን ይችላል፤ ጭንቀትና ብስጭት ከውስጣችን ገንፍሎ ለመውጣትም ይዳዳው ይሆናል። ይሁንና፣ ይህ ጊዜ ከባድነቱ ለእኛ ብቻ አይደለም፤ ለልጅም በጣም ከባድ ጊዜ ነው። ውዥንብሩ፣ የፈጠረባቸው ጭንቀት ሳያንስ፣ ወላጅ በተጨማሪ ሲለወጥባቸው፣ በጣም ግራ ይጋባሉ፤ ያዝናሉ። "ጥፋቱ የእኔ ነው" የሚለውን ጎጂ የሆነ አስተሳሰብ፣ በውስጣቸው ይቀብራሉ። ልጆችን በማመናጨቅ፣ በአፋችን እንደ መጣ በመናገር ፈንታ፣ በተለይ በዚህ ጊዜ የበለጠ አስፈላጊ መሆኑን ተረድተን፣ በሰላምና በፍቅር ልንቀርባቸው ይገባል።

በወላጆች መኻል ጥል ከተፈጠረ፤ልጅ ፊት በፍጹም አንጨቃጨቅ፤ ስለ ሕጻናት አስተዳደግ የሚያስተምሩ ብዙ ሰዎች ለወላጆች፣ "ልጅ ፊት አትጣሉ" እያሉ፣ይህን እውነት ይደጋግማሉ። ወላጆች በእነርሱ ደረጃ ሊነጋገሩባቸው የሚገቡ ነገሮችን፣ በልጅ ፊት ዘክዝኮ መጨቃጨቅ፣ ልጅ የልጅነት ጊዜውን ሊኖር በሚገባው መልክ እንዳይኖር ያደርገዋል፤ጣፋጩን የልጅነት ጊዜውን ወስዶበት፣ ያለጊዜው ትልቅ ሰው ባለበት አለም ውስጥ ገብቶ እንዲያስብ የሚያስገድደው ነገር ነው። ልጅ በእዚህ ዕድሜው፣ ለእንደዚህ ዐይነቱ ሁኔታ ዝግጁ አይደለም። በእድሜ ትልቅ የሆነ ሰው ጭቅጭቅ ቢያይ፣ ነገሩን ማየት፣ ማመዛዘን ይችላል። የልጅ አእምሮ ግን እንደዛ አይደለም። የሚወዳቸው ወላጆቹ ጭቅጭቅ





ውስጥ ገብተው ሲያይ፣ ሁሉ ነገር ዝብርቅርቅ ይልበታል፤ የሚያደርገውም ይጠፋዋል። እናቱና አባቱ እንዲህ የሚጣሉት፣ እርሱ ቀድም ብሎ ባጠፋው ጥፋት ምክንያት ይመስለዋል ራሱንም መውቀስ ይጀምራል። ሀዘንተኛ እንዲሆን፣ በራሱ እንዲቆዝም ያደርገዋል። የምንሰጠውና የምናደርግለት "አስደሳች" ነገር ሁሉ ሊያስደስተው ኀይል ያጣል፤ የሚያየው ጥል ይሸፍንበታልና። በወላጅ መሀል ያለ አሉታዊ የቃል ልውውጥ ልጅን በትልቁ ሊጎዳው እንደሚችል ተረድተን፣ የማንስማማበት ወይም የሚያጨቃጭቀን ነገር ቢመጣ፣ በተቻለ መጠን ልጅ በሌለበት ሌላ ክፍል ገብተን እንነጋገር።

ልጆቻችንን፣ በጠባችን መኻል አናስገባ። በባል ወይም በሚስት ተናደን ሳለን፣ ወደ ልጅ ዞረን፣ "አንተ ባደረከው ወይም አንቺ ባደረግሽው ምክንያት ነው ይህ የሆነው" ወይንም "አንተ የእናትህ ልጅ ነህ፤ አንቺ የአባትሽ ልጅ ነሽ" ከማለት እንቆጠብ፤ በልጅ ውስጥ ጻጸት እንዲፈጠር ያደርጋልና። በጥል ጊዜ፣ ልጅ ከአንዱ ወገን ይልቅ ለእኛ እንዲያግዝ ለማድረግ መሞከር ትልቅ ስሕተት ነው። ይህ የልጅን አእምሮ በጣም ይረብሻል። በሁለቱ በሚወዳቸው ሰዎች መኻል መምረጥ፣ አንዱን ለማግኘት ሌላውን ወላጁን ማጣት ያለበት ይመስለዋል፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ፣ስለ እናት ወይም አባት መጥፎ ነገር፣ ለልጅ ወይ፣ ልጅ ፊት፣ በፍጹም አናውራ፤"እናትህ ይህ ችግር አላት፤ አባትሽ መጥፎ ነው" ማለት ለልጅ፣ "ጭንቀትን ፣ ውጥረትንና እነሆ" እንደ ማለት ነው።

ቤት ውስጥ የመጣው ፈተና ምንም ይሁን ምን፣ ስለችግሩ ስናወራ ከአፋችን የሚወጣውን ቃል፣ መምረጥ አለብን። "ጉዳችን ፈላ፤ በቃ አለቀለን፤ የእኛ ነገር ከንግዲህ ወዲያ ተስፋ የለውም" እያልን፣ ልጅ ፊት ከማውራት እንቆጠብ። ደጋግመን እንዳነሳነው፤ ልጅ ወላጅን ያምናል። ልጅ የሰማውን ቃል ልክ እንደ ቃልነቱ ወደ ልቡ ይወስዳል እንጂ፣ "ወላጄ ለጊዜው ስለተረበሸ ይህን ተናገረ" ብሎ አያመዛዝንም። ለምሳሌ፣ እናት ምርር ብላ፣ "በቃ አለቀልን! ከእንግዲህ ሕይወት የለም" ብላ ስታወራ፣ ልጅ፣ "እናቴ ለጊዜው

ስሜታዊ ስለሆነች፣ ወይ ችግሩ ስለገዘፈባት ነው" ብሎ አያስተውልም። ለእርሱ አእምሮ "በቃ አለቀልን" ማለት ልክ በቁሙ "በቃ አለቀልን" ማለት ነው። በተለይ ሁሉን በውስጡ የሚመዘግብ ልጅ፣ በጣም ሊጎዳ እድል ይኖረዋል። ይህን ተረድተን፣ የምንናገረውን እንምረጥ። ለሰው መንገር በፈለግን ቁጥር፣ ማውራት ባሰኘን ቁጥር፣ ስለ ችግር መላልሶ ከማውራት ልምምድ እንቆጠብ፤ ተደጋግሞ የሚወራ ችግር፣ የልጅ አእምሮን የመረበሽና የመበጥበጥ ሀይል አለውና።

የማይለወጥ ወይም እነርሱ መስማት ያለባቸው ችግር ከሆነ፣ ደባብሰን በማለፍ ፋንታ ግልጹን እንንገራቸው። ለምሳሌ በባልና ሚስት መሐል ፍቺ መጥቶ፣ "አባባ ሌላ አገር ሄዷል"፤ እማማ ሌላ አገር ሄዳለች" ወዘተ እያልን፣ በህልም ዓለም ውስጥ አናኑራቸው። የተከሠተውን ችግር እንደሌለ ልናስመስል ከሞከርን፣ ወይም ቀለም ለመቀባባት ከሞከርን፣ ልጆች በራሳቸው ነገሮችን ገምግመውና አብላልተው፣ የማይሆን ድምዳሜ ላይ ይደርሳሉ፤ ይህ ነገር ግልጽ በሆነ መንገድ ተወርቶ፣ እንዲጋፈጡት እድል አልተሰጣቸውምና፤ የሚያም ቁስል ከውስጣቸው ይፈጠራል። በግልጽ ስናነጋግራቸው ግን፣ በጣም በተሻለ መንገድ ሊቀበሉት እድል ይኖራቸዋል።የምንነግራቸው ነገር ይዘቱና ጥልቀቱ፣ እውነትም እንደ እድሜያቸውና እንደ ሁኔታው ሊለያይ ይችላል። ለ4 ዓመት ልጃችን የምንነግረው፣ ለ16 ዓመት ልጃችን ከምንነግረው የተለየ ሊሆን ይችላል። ባጠቃላይ፣ ከእኛ ከወላጆቻቸው እውነትን መስማታቸው በጣም አስፈላጊ መሆኑን ተረድተን፣ ማወቅ ባለባቸው መጠን በግልጽ እናናግራቸው።

ከዚህ ጋር አያይዘን፣ ይህን ነጥብ ልብ እንበል። በዚህ በመጣው ፈተና ምክንያት፣ ሕይወት እንደማታቆም፣ነገሩ የሕይወት መጨረሻ እንዳልሆነ፣ ለእነርሱ መጠቆምም አንርሳ። ለምሳሌ፣ በባልና ሚስት መኻል ፍቺ ካለ "እኔና አባትሽ" ወይም "እኔና እናትሽ" አሁን ልንለያይ ነው፤ "በአንዳንድ ነገር ልንስማማ አልቻልንም፤ ግን ሁለታችንም እናንተን ከልብ እንወዳችኋለን።





ለእናንተ ያለን ፍቅር አይለወጥም፤ እኛ ግን ተለያይተን ነገሩን ማየት አለብን" ብለን ረጋ ብለን እንንገራቸው። ህመም ቢመጣ፣ ለልጆቻችን በሚስማማ መንገድ በግልጽ እንናገር። "እናትህ ትንሽ ታማለች፤ እኔ አባትህ እንደምታየው ታምሜአለሁ፤ እውነትም ስታየው ከበድ ያለ ሊመስል ይችላል፤ ነገር ግን ቤተሰብ በሙሉ ተጣምረን ይህን ችግር ለመጋፈጥ የቻልነውን እናደርጋለን" ብለን እንንገራቸው። እነሱም የሚሰማቸውን በግልጽ እንዲናገሩ እናበረታታቸው፤የሚነግሩንን፣ ከልብ ልናዳምጣቸው አብረን ልንወያይ፣ ሁሌም ዝግጁ እንደሆንን እናሳውቃቸው። ይህ ግልጽ የሆነ ንግግር ለእነርሱ ትልቅ እርዳታ ይኖረዋል። ከሚያምኑት ወላጅ አፍ ስለ ችግሩ ሰምተዋል፤ ቤተሰብ አብሮ የመጣውን ችግር እንደሚጋፈጥም ተነግሯቸዋል። ይህ በቤተሰብ የደረሰው ፈተና፣ የአለም መጨረሻ እንዳልሆነ ይረዳሉ፤ እነርሱም ተጋፍጠውት፣ወደ አዲስ ምእራፍ እንዲገቡ ይረዳቸዋል።

በችግር ውስጥ እያለፈ ያለ የቤተሰብ አባል ላይ ብቻ አተኩረን፣ ሌሎቹን ልጆቻችንን እንዳንረሳ እንጠንቀቅ። ይህ ብዙ ጊዜ ልንፈጥረው የምንችለው ስሕተት ነው። ለምሳሌ አንድ ልጅ የሆነ ችግር ቢያጋጥመው፣ ያ ልጅ ላይ ብቻ ሳናስበው ተጠምደን፣ ሌሎች ልጆቻችንን አትኩሮት ከነሳናቸው፣ በጣም ይጎዳሉ። የሚያዩት እና የሚያስተውሉት ውዥንብር ያስደነገጣቸው ሳያንስ፣ የእኛ እነሱን መርሳት፣ የበለጠ ብቸኝነት፣ ፍርሀት ውስጥ ይከታቸዋል፤ በእኛም ሆነ በሌሎቹ ልጆች ላይ ምሬት እንዲያድርባቸው ይሆናል። በዚህ የፈተና ሰአት፣ ኀይላችንን ልክ እንደድሮው ልናሰባስብ ይገባናል ለማለት አይደለም፤ እውነትም ድሮ በምናደርገው መጠን፣ ለእያንዳንዱ ልጅ አትኩሮ ለመስጠት ያዳግተን ይሆናል። ነጥቡ "እንደድሮው ጊዜና ሀይሉ ይኑረን" አይደለም፤ ጭራሽ ግን ችላ አንበላቸው። በግልጽ እንንገራቸው፤ "በዚህ ጊዜ የሚያሯሩጠኝ ነገር በዝቷል፤ ነገር ግን ለእናንተ ያለኝ ፍቅሬ እንዳለ ነው" ብለን እናስታውሳቸው።ጥቂት ደቂቃ እየወሳሰድን እናውራቸው፤ እነሱን ስናስባቸው እንደነበር እንንገራቸው፤ ያ ለሕይወታቸው ትልቅ ለውጥ ያመጣል። ።

በዚህ የፈተና ሰአት፣ የልጆቻችን የስጋ ምቾት መጠበቁ እንደዋነኛነት አያሳስበን:: በተለይ ቁሳቁስ በበዛባቸው አገሮች የሚኖሩ ልጆች፣ ዋነኛ ረሀብና ጥማቸው የስጋ ምቾት ማጣት አይደለም:: የኛ ፊት አይለወጥባቸው፣ ከኛ ጋ ያላቸው ትስስር እንደጠበቀ ይቆይ እንጂ፣ ምሳ ወይ እራት በየአይነቱ አለመሰራቱ አይጎዳቸውም:: በዚህ የሩጫ ሰአት፣ እነርሱም ሊረዱን በሚችሉ ነገር ውስጥ እናሳትፋቸው:: "ይህ እንደ ቤተሰብ አብረን የምንተጋገዘው፣ የምንወጣው ነገር ነው" ብለን፣ እናስረዳቸው፤ ያ ለእኛ እርዳታ ብቻ ሳይሆን በቤተሰብ መሐል ትስስርን ይፈጥራል::

ቤት ውስጥ አንድ ውዥንብር ሲደርስ፣ ልንወስደው የሚገባው ሌላው ጠቃሚ እርምጃ ይህ ነው። ልጆቻችንን ሊያጽናኗቸው፣ ሊያበረታቷቸው ከሚችሉ፣ ከምናምናቸው ወዳጅ፣ ዘመዶች፣ የሀይማኖት አስተማሪዎች ጋር፣ ስራዬ ብለን እናገናኛቸው:: እነዚህ ታማኝ ሰዎች ከልጆቻችን ጋር ጊዜ እንዲያሳልፉና እንዲያወሯቸው እናበረታታ፤ ከሰው ጋር የሚኖራቸው ይህ ማህበራዊ ሕይወት ልጆቻችን በቶሎ ከውጥረት እንዲያገግሙ በትልቁ ሊያበረክት ይችላል::

በችግር ጊዜ፣ አንዳንድ ልጆች፣ አእምሮዋቸው በጣም ሊታወክ፣ የህክምና እርዳታ ሊያስፈልጋቸው ይችላል። አንዳንዴ በኛ ባህል፣ "ልጅ ምንም አይሆንም፤ ያልፋል" የምንለው ነገር አለ:: በተለይ፣ ልጆች ለብዙ ነገር በተጋለጡባቸው በውጭ አገሮችና ባሁኑ ዘመን፤ እንደዚህ ማለት አይሰራም:: ከአእምሮ ጭንቀት ጋር የተያያዙ ነገሮች፣ ልጅን ወደ አደገኛ ቦታ ሊመሩ ይችላሉ:: ልጆቻችንን የአእምሮ ውስብስብ ያመጣባቸው የሕይወት ፈተና ይሁን የጤና ችግር፤ ሁኔታቸውን ሳናቋርጥ እንገምግም:: አንዳንድ ልጆች በግልጽ ስሜታቸውን ያሳያሉ፤ ሌሎች ደግሞ በውስጥ ይቀብራሉ:: ጸባያቸው ከድሮው በጣም ከተቀየረ፣ ብዙ ነገር በውስጣቸው መቅበር ከጀመሩ፣ የጭንቀት የውጥረት ነገር ደጋግመን ካየንባቸው፣ ውጫዊ እርዳታን በቶሎ እንፈልግ::





ህክምና ወይም ቴራፒ የሚያገኙበትን መንገድ እንይ:: ትምህርት ቤት አማካሪያቸውን፣በአካባቢያችን ያሉ ቴራፒስቶችን ምን ማድረግ እንደምንችል እንጠይቅ:: ከዚህ አርእስት ስር ከአእምሮ ጋር ለተያያዙ ችግሮች በአካባቢያችን የት መሄድ እንደምንችል የሚጠቁመን ስልክ ቁጥር እና ድረ ገጽ ስም ያገኛሉ::[47]

ወላጆች፣ ችግር በመጣ ጊዜ ችግሩን የምንጋፈጥበት መንገድ፣ ከእኛም በላይ ልጆቻችን ላይ ትልቅ ተጽእኖ አለው:: ባልጠበቅነው በኀይለኛ ችግር ውስጥ እያለፍን፣ ሁሉን ብቻችንን ከተጋፈጥነው ሳናስበው እንንሳቆላለን፤ እንዝላለን፤ ኀይላችን ይመነምናል፤ በሥነ ሥርዐት ማሰብ፣ መላን ማግኘት ሊያቅተንም ይችላል:: ድጋፍ ማግኘት ያጠነክረናል፤ ያበረታታናል፤ ተስፋን ያሳየናል፤ ልጆቻችንን በጥሩ ሁኔታ እንድናሳድግ ኀይልም ይሆንልናል:: ከእኛም በላይ ለልጆቻችን ስንል፣ በድጋፍና፣ አብሮ በማሳለፍ፣ ሊረዱን የሚችሉትን የዘመድና የወዳጅ እርዳታ እጃችንን ከፍተን እንቀበል፤አስፈላጊ ከሆነም፣ የህክምና እርዳታን ለማግኘት ወደኋላ አንበል::

[47] 1-800=662-4357 treatment referral (የአይምሮ ህክምናን በተመለከተ፣እኛ በምንኖርበት አካባቢ ስላሉ የህክምና (treatment) ቦታዎች ይነግሩናል። (ልጆቻችን እዛው ቆይተው እርዳታ የሚያገኙበት፡ ሆነ ከቤት እየተመላለሱ፤እነዚህ የእርዳታ ቦታዎች የት እንዳሉ፣ በመጠቆም ያገለግሉናል። ከዛም በተረፈ፣ በምንኖርበት ስቴት፣ ካውንቲ ውስጥ ዋጋ ቅናሽ፡ ከፍያ እርዳታን ለማግኘት የት እንደምንደውል ይጠቁሙናል።

ከስልኩ ሌላ በአካባቢያችን ስላሉ የእርዳታ ቦታዎች ሊጠቆመን የሚችለው findtreatment.samhsa.gov የተባለ ዌብ ሳይት ነው።

# የሕይወት ተሞክሮ



## የልጃችን የጤና ጉዳይ

ልጃችን አብራሀም ሲወለድ እንደማንኛውም ልጅ ጤነኛ ነበር። እስከ 18 ወሩ ድረስ እንደማንኛውም የእሱ እድሜ ልጆች፣ ያወራ፣ ይራመድ ነበር። በመጀመሪያው የዶክተር ምርመራው ውጤቱ ጥሩ ነበር። ከ18 ወር ክትባቱ በኂላ ግን፣ አንዳንድ ለውጥ ማየት ጀመርን። ብዙ ያለቅስ ነበር፣ ግራ የሚያጋባ የጣቶች መንቀሳቀስና ሌሎችን በትክክል ማየት አለመቻልን (compex finger movement & luck of eye contact) ማየት ጀመርን። ዶክተሩ በልጃችን ላይ የምናየው ለውጥ ብዙም አላሳሰበውም ነበር። ነርሷ ግን, ኤሞሪይ ዩኒቨርስቲ አውቲዝም ማዕከል ይዘነው እንድንሄድ መከረችን።

ልጃችን አውቲዝም (autism) እንዳለውና ምናልባትም መቼም ጊዜ ሙሉ ለሙሉ ላይድን እንደማይችል ስንረዳ ሀይለኛ ሀዘን ተሰማን። የጤና ችግር ያለው ልጅ ማሳደግ በጣም ከባድ ነው። ከህይወትም ብዙ ነገሮች መለወጥን ይጠይቃል፤ ከፍ ያለ መስዋዕትነትን ሊጠይቅም ይችላል። በዚህ ጊዜ ወደፊት





እንድንራመድ የሚያስችሉንን ነገሮች መረዳቱ በጣም ጠቃሚ ነው።

- የጤና ችግር ያላቸው ልጆቻችን የተለየ እንክብካቤ እና ድጋፍ ከእኛ ያስፈልጋቸዋል። እንዲህ በሆኑልኝ ኖሮ የሚለው ላይ ሀይልና ጊዜን አናጥፋ። በፋንታው፣ የተከሰተውን ሁኔታ አምነንና በሙሉ ልብ ተቀብለን፣ ህይወታቸውን በሚረዳቸው መልክ ማሳደጉ በጣም ይጠቅማል።
- የልጃችንን የጤና ችግር ከሌላው ለመደበቅ መሞከር፣ ሰው ምን ይላል ብሎ ማሰብ በጣም ጎጂ ነገር ነው። ሌሎች የቤተሰብ አባሎችን ሆነ የቅርብ ጓደኞቻችንን በግልጽ ማዋየት፣ ስለ ጤና ችግሩ እነሱም እንዲረዱ ትምህርት መስጠቱ በጣም ጠቃሚ ነው። ለእኛም ክብደታችን ያቀልልናል፤ ብቻችንን ከመጓዝ ይልቅ፣ ከቅርብ ጓደኛና ቤተሰብ ድጋፍ ማግኘቱ ጠንክረን እንድንራመድ ትልቅ አስተዋጽኦ አለውና። እነሱም ልጃችንን እንዴት እንደሚደግፉ፣ እንደሚረዱ ጥሩ ግንዛቤ ይኖራቸዋል።
- የልጃችንን ሆነ የራሳችንን የጤና ችግርን በተመለከተ፣ እነሱ ያውቃሉ ብለን ሁሉን ነገር ለዶክተሮቹ አንተው። በኛ ባህል በተለይ በሁሉ ነገር ዶክተሮችን ሙሉ ለሙሉ የማመን ሁኔታ አለ። እነሱ የሚሳሳቱት ወይም እነሱ የማያውቁት ብዙ ነገር ሊኖር ይችላል። አንድ ዶክተር ይህ ነው ችግሩ ስላለ ወይ ችግር የለውም ስላለ ብቻ በዛ ደምድመን አንቀመጥ ። ሁለት ሶስት ቦታ ወስዶ ሌሎች ዶክተሮች ምን እንደሚሉ ማወቁ ጠቃሚ ነው።
- እኛም ስለዛ የጤና ችግር ጥልቅ እውቀት እንዲኖረን እንጣር፤ ልጃችንን ልንረዳ የምንችለው ግንዛቤው ሲኖረን ነውና። ኢንተርኔት ውስጥ ብንገባ ስለዛ የጤና ችግር ብዙ ጠቃሚ ግንዛቤ ልናገኝ እንችላለን። ከዛም በተጨማሪ ያንን የጤና ችግር በተመለከተ የተለያየ

ጠቃሚ ጽሁፍ የሚያዘጋጅ በየወሩ የሚታተም መጽሄት ፈልጎ ማግኘቱ ጠቃሚ ነው::

- ከቤት ውጭ ልጃችን ሊያገኝ ስለሚችላቸው እርዳታዎች ጥልቅ እውቀት እንዲኖረን እንጣር፤ያ የልጃችንን ህይወት በጣም ሊረዳ ይችላልና:: ለምሳሌ በትምህርት ቤት ውስጥ ልጃችን ምን አይነት እርዳታን ማግኘት እንደሚችል በውጭ ስላሉ ቴራፒስትቶች ፣ ስለተለያዩ ጤና ጣብያዎች፣ መንግስት ምን አይነት እርዳታ እንደሚሰጥ፣ ያንን የጤና ችግር በተመለከተ ምን አይነት ህግ እንዳለ በደንብ ማወቁ ትልቅ ጥቅም አለው::
- በዚህ ከባድ ጊዜ የእናት አባት ወንድምና እህት መተባበርና አብሮ መስራት በጣም አስፈላጊ እና ጠቃሚ ነው:: አብረው ሲሸከሙት ይቀላልና:: ለዚህ የጋራ አላማ ስንል፣ ትናንሽ ልዩነቶችን ወደኋላ አድርገን አብረን መደጋገፉ ሁላችንንም ሊረዳን ይችላል::
- እኛን በጣም የረዳን አንድ ሌላ ነገር፣ በአካባቢያችን ያሉ እንደኛው፣ አውቲዝም የልጅ ጤና ችግር ውስጥ የሚያልፉ ቤተሰቦች ጋ አብረን በመወያየት የምናሳልፈው ( support group) ጊዜ ነው:: ከእነዚህ ቤተሰቦች ጋር እየተገናኘን መወያየታችን፣ድጋፍ እንዲኖረን፣ ብቻችንን እንዳልሆንን እንድንረዳ ከመጥቀሙም በላይ፣ የተለያየ አስፈላጊ እውቀትን እንድንለዋወጥ ረድቶናል:: በጤና ብቻ ሳይሆን፣ በምናልፍበት በተለያዩ ችግሮች ውስጥ ስፖርት ግሩፖች በጣም ጠቃሚ አስተዋጽኦ እንዳላቸው ተረድተን፣ ለዚህ ጠቃሚ የእርዳታ ምንጭ ልባችንን እንክፈት::





# ምዕራፍ ስምንት

## ልጆቻችን የባህሪ ለውጥ ሲያሳዩ

ልጆቻችን በዕድገት ዘመናቸው ውስጥ፣ በተለይም በአስራዎቹ የዕድሜ ክልሎች እያሉ፣ "የአስቸጋሪነት ጸባይ ሊያሳዩ ይችላሉ:: "ልጄ አስቸግሮኛል" ስንል ለተለያየን ሰዎች የተለያየ ትርጉም ሊኖረው ይችላል:: አንዳንዶቻችን ልጃችን ትምህርት ላይ እየደከመብን ተቸግረን ይሆናል ወይም ከማይሆኑ ጓደኞች ጋር ገጥሞብን ይሆናል ልጄ አስቸገረኝ ስንል ምናልባት እያመሸ መምጣቱን ይሆናል ወይም እናት እና አባቱ ሲያናግሩት ያልተገባ መልስ መስጠቱን ሊሆን ይችላል:: ልጃችን በመጠጥና በእጽ ሱስ ውስጥ ወድቆ ይሆናል:: ለአንዳንዶቻችን ደግሞ ልጄ አስቸገረኝ የምንለው አለባበሱ ስለተለወጠብን ወይም በስልክ ብዙ ስለሚያወራ ሊሆን ይችላል:: የልጆቻችን "አስቸጋሪነት ጸባይ" በተለያየ መልክ የሚገለጽ ነው፤ ለሁሉም ጥፋት፣ አንድ አይነት መፍትሄ የለውም:: ይህም ሆኖ በተለያዩ የባህሪ ለውጦች ውስጥ ማስታወስ ያሉብን የጋራ ነጥቦች አሉ::

ልጆቻችን የአመል ለውጥ ስናይባቸው፣"ልጄ ባልጓል፣ ልጄ ሰነፍ ሆናለች" ብለን በቶሎ ከመፍረድ እንቆጠብ፤ልጆቻችን ያለባቸውን ፈተናዎች ልንረዳቸው ይገባል:: "ጭራሽ አያጠፉም ወይም ጥፋቱ የእነሱ አይደለም" ለማለት አይደለም:: ብዙ ጊዜ ልጆች ከመስመር ውጭ ሲወጡ ከመበላሸታቸው በስተጀርባ የተደበቀ ምክንያት ሊኖራቸው ይችላል:: በተለይም በምእራቡ ዓለም ልጆች ከጓደኞች ከማህበረሱና ከመገናኛ ብዙኃን ብዙ ተጽእኖ አለባቸው:: ለምሳሌ ልጅ በጓደኞቹ ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት፣ አነጋገሩን አለባበሱንና ባህሪይውን መለወጥ እንዳለበት ተስምቶት የማንወደውን ነገር ሁሉ ሊያደርግ ይችላል:: ምንም

እንኳን ልጅ ለጥፋቱ ተገቢ የሥነምግባር እርማት ማግኘት ቢኖርበትም እሱም እንዲያ እንዲሆን ያስገደዱትን የተለያዩ ጫናዎች ወይም ግፊቶች እንዳሉበት ማወቅ ተገቢ ነው፤ ልጅ ምን ዓይነት ማኅበረሰባዊ ጫና እንዳለበት ከተረዳን ባጠቃላይ እንዴት አድርገን ሁኔታውን መቆጣጠር እንደምንችል ግንዛቤ ይኖረናል። ልጆቻችንንም ያለባቸውን ግፊት በጤነኛ መንገድ እንዲቋቋሙ ልናግዛቸው እንችላለን።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ማስታወስ ያለብን አንድ ነገር ሁለት ልጆች ፍጹም በተለያዩ ምክንያች አንድ አይነት ጥፋት ውስጥ ሊገቡ እንደሚችሉ ነው። አንዳንድ ልጅ ከጋጠወጥነት የተነሳ ባህሪዩ ፈጽሞ ሊበላሽ ይችላል።ሌላው ልጅ ደግሞ ውስጡ የሚሰማውን የስቃይ ስሜት ለመሸሽ ጥፋት ውስጥ ሊገባ ይችላል። አንዷ ልጅ በግዴለሽነት ማምሸት ልትጀምር ትችላለች፤ ሌላዋ ልጅ ደግሞ ቤት ውስጥ የምታየውንና፣ የምትሰማውን፣ በወላጅ መሀል ያለውን ጭቅጭቅ ለማምለጥ ብላ ውጭ ልታመሽ ትችላለች። ልጃችን መስመር ስትለቅቅ ችግሩን ብቻ ሳይሆን መንስኤውን ከመዘንን፣ ሙሉ ስእሉን ከግምት ካስገባን፣ ሊረዱ የሚገባቸው ቦታ ልንደርስላቸው እንችላለን።

የልጆቻችን ስነምግባር ሲበላሽ ወላጅ የሚወስደው አቋም ውጤቱን የመወሰን አቅም አለው፤ በሌላ አነጋገር፣ ወላጅ ለጉዳዩ የሚሰጠው ምላሽ ልጁን ለተሻለ ሕይወት ሊያበቃው ወይም ለከፋ ሕይወት ሊዳርገው ይችላል።

አንድ እውነት ልብ ልንል ይገባል። ወላጅ ለልጅ ያለው ፍቅርና ጥሩ ምኞት ብቻውን በቂ አይደለም። እኛ ልጆቻችንን ሊጠቅማቸው የሚችል ቁም ነገር መያዛችንም በራሱ በቂ አይደለም፤ በእኛ ዘንድ ያለውን ጥሩ ነገር፣ (ምክራችንን ድጋፋችንና እርዳታችንን) ለልጆቻችን የምናስተላፍበት መንገድ ወሳኝነት ይኖረዋል። በእኛ በኩል ያለውን መልካም ነገር ወደ ልጆቻችን የምናስተላልፍበት ድልድይ ከሌለን ጥሩ ምኞታችንን





እርዳታችንን ሁሉ ታስሮ ይቀራል። ይህንን ድልድይ ደግሞ የሚሰብረውም ሆነ የሚጠግነው፣ የወላጅ ጠባይ ነው።

ወላጅ ጠባይ ስንል ምን ማለታችን ነው? ስለ ልጃችን ባሕሪይ መሻሻል፣ ከችግሩ ነጻ መውጣት፣ ጠንክረን ልንሰራ እንችላለን፤ ወይም ችግሩ በእኛ ሰሜት ላይ የፈጠረውን ጉዳት በማጠንጠን ብቻ ልንወሰን፣ እንችላለን። ልጆቻችንን የሚያጋጥሟቸው ፈተናዎች ቢለያዩም፣ እውነቱ ግን አንድ ነው። ስሜታዊነት ከወረሰን፣ ለልጆቻችን ልንሰጣቸው የምንችለውን እርዳታ በተገቢ መልኩ ሳንሰጥ እንቀራለን።

> "እንደ መፍትሄ ብለን፤ በሀይለኛ ቁጣ፣ ወቀሳ እና ልጅን በማስፈራራት ሀይልን ለማስረገጥ፣ ህይወቱን ለመቆጣጠር መሞከር፤ ከልጁ አለመታዘዝና ቀጣይነት ካለው ግጭት ጋር ይያያዛሉ።"[48]

- የልጅ ስለምግባር ሲበላሽ ልጅን ለረጅም ጊዜ ማኩረፍ ችግሩን ያባብሰዋል። ልጅ የሚልፍበትን የሕይወት ውጣ ውረድ ለጓደኛ ብቻ እንዲናገር ወይም ከነጭራሹ ድብቅ እንዲሆንና እኛን የበለጠ እንዲርቀን ያደርገዋል።
- ልጆቻችን ሲበላሹ በንዴት ተሞልተን የምንሳደብ ከሆነ ልንነግራቸው የምንሞክረውን ምክራችንን በመስማት ፈንታ ያቺን የሰሟትን ስድብ እንዲያብሰለስሉ ያደርጋቸዋል። ስድባችንን ለጊዜው በንዴት የተወረወረ ቃል አድርገው ሳይሆን የሚያዩት እንደ ቋሚ የባህሪያቸው መገለጫ አድርገው ነው። ይህ ደግሞ በእኛ ላይ እንዲማረሩ፣ የበለጠ እልህ እንዲያያዙ፣ እነርሱ የሚያውቁት እኔን መሳደብ ብቻ ነው ብለው እንዲርቁን ያደርጋቸዋል።
- እኛ በሆነ ነገር ስነሳሳት ጥፋታችን በመቀበል ፈንታ እኔ የቤቱ መሪ ነኝ አንዲት ነገር እንኳ አልሳሳትም የሚል

[48] Crockenberg, S., & Litman, C. (1990) Autonomy as competence in two year olds; Maternal Correlates of child defiance, compliance and self-assertion.

አቋም የምንይዝ ከሆነ ልጆቻችን ስለ እኛ እውነተኛነት ያላቸው እምነት ይናጋል።

- ልጆቻችን የውስጣቸውን ስሜት ሲናገሩን በጥሞና አለማዳመጥ "ከነሱ ጋር ምን አነጋገረኝ" እንዲሉና ለእኛ እውነቱን መናገር እንዲያቆሙ፣ እንዲያውም አስመሳዮች እንዲሆኑ፤ ያደርጋቸዋል። ልጅ ሲያወራ አቋርጦ ራስን ሃሳብ ብቻ ማውራት "ከእኔ አስተያየትና ቁም ነገር ለእነርሱ ቦታ የለውም" ብሎ እንዲደመድም ይዳርገዋል። ለችግሩ መፍትሔ ከመፈለግ ይልቅ በጥፋት ውስጥ የበለጠ እንዲዘልቅ ይገፋፋዋል።
- የልጃችንን ማንነት የምንመዝነው አንድ ጊዜ ባጠፋው ጥፋት ብቻ ከሆነ ልጃችን በችግሩ ውስጥ ዘልቆ እንዲገባ ያደርገዋል። ሁሌ ስላጠፋው ጥፋት፣ ስለ ችግሩ የምናወራና የምናጉረመርም ከሆነ በውስጡ የዝቅተኝነት ስሜት እንዲሰማው፣ ጭራሽም ያለውን ጥሩ ነገር ሁሉ እንዲተው ያደርገዋል። እኛንም "ስለ እኔ አንዲት ጥሩ ነገር አያስቡም" ብሎ እንዲርቀን በትልቁ አስተዋጽኦ ያደርጋል።
- እልህን፣ ምሬትን፣ ንዴትን ወዘተ ሙጥኝ ብለን መያዝ ልጃችንን ለመርዳት ያለንን አቅም ያዳክማል።

ይህ ችግር ሲከሰት ትልቁን ግባችንን እናስታውስ። ይህ ጊዜ የራሳችንን ስሜት ብቻ የምናውጠነጥንበት ጊዜ ሳይሆን የተግባር ጊዜ ነው። እኛ የምንወዳቸውንና ሕይወታችንን እንኳን ሳይቀር የምንሰጣቸውን ልጆቻችንን፣ በቀናው መንገድ ተመላለሱ ስንላቸው፣ በተቃራኒው ደግሞ ያመረ መልክ እያሳየ "ኑ አይዟችሁ፤ እኔ ዘንድ ሁሌ ደስታና ፈንጠዝያ አለ" እያለ ሊስባቸው የሚሞክር የጨለማ ገመድ ያለበት ሠዓት ነው። የጓደኞቻቸው ምክር፣ የመገናኛ ብዙኃንና፣ ጊዜያዊ አስደሳች ነገሮች በየደቂቃው ኑ እያሏቸው ነው። በዚህ ጊዜ እኛ በሩቅ ቆመን "ልክ እኔ እንደምንፈልገው ካላወራኸኝ ልክህን ነው የማስገባህ" ብለን እጃችንን አጣጥፈን ጥግ ይዘን መቆማችን አያዋጣም፣ ያ ለጨለማው ኀይል ይሰጠዋል። "ቀድሞውንም ብዬህ ነበር፣ ወላጆችህ አያዋጡህም፤ አያዳምጡህም፣ የምበጅህ





እኔ ነኝ" ብሎ በአእምሮዋቸው የሐሰት መልእክቱን እንዲደውል ዕድሉን ይሰጠዋል፤ ልጆቻችንም በጨለማው መልእክት ተመስጠው በጥፋት ጎዳና ይበልጥ እንዲጓዙ ያደርጋቸዋል።

> "ልጅ ከእሱ የምንጠብቅበትን በግልጽ ማስቀመጥ ብቻ ሳይሆን በዛው መጠን ደግሞ የራሱን ማንነት እንደምናከብርለት ሲገነዘብ የበለጠ ታዛዥ እንዲሆን ይበርታታል።"[49]

ልጆቻችን ምንም ብንወዳቸውና እነሱን ለመርዳት ችሎታው ቢኖረንም ስሜታዊነት መሀል ከገባ ነገሮችን እንደሚያበላሽ ተረድተን ለልጆቻችን መጻኢ ዕድልና ለመልካም ግንኙነታችን ስንል እልህን፣ ቂምንና ስድብን አስወግደን በመፍትሔ ላይ ብቻ እናተኩር።

- የልጆቻችን ማንነት የተመሰረተው በዛሬ ጥፋታቸው ላይ እንዳልሆነ ተረድተን በፊት የነበረንን የእርስ በእርስ ግንኙነት በተቻለ መጠን እንቀጥል። ሕይወታቸውን የምንመዝነው አሁን በሚያሳዩት ባህሪይ እንዳልሆነና ፍቅራችንና ወላጅነታችን እንዳላቆመ ሲያዩ ከእኛ ጋር ያላቸው ትስስር ይጠነክራል፡ለመለወጥም ይበረታታሉ፡
- ልጅን ከመሳደብ ይልቅ ጥፋቱን እናመልከተው፤ መፍትሄው ምንድነው ወደሚለው እንዙር። ልጃችን በዚያ መልክ ስናወራው ለማዳመጥ ልቡን ይከፍታል።
- ሁል ጊዜ፣ የእኔ ብቻ ይደመጥ በማለት ፈንታ፣ ልጆቻችንንም እናዳምጥ፤ እነሱም እኛን ማዳመጥ የሚማሩት በምሳሌነታችን ነውና።
- ጥሩ ስራ የሚለመልመው፣ ሲታረም ብቻ ሳይሆን ለእድገት የሚያስፈልገው ምግብ ሲቀርብለት እንደሆነ ተረድተን ልጆቻችንን ሲያሻሽሉ ስናይ እናበረታታቸው ይህም ድካማቸውን ብቻ ሳይሆን ጥንካሬያቸውንም

---

[49] Crockenberg, S., & litman, C. (1990) Autonomy as competence in two year olds; Maternal Correlates of child defiance, compliance and self-assertion.

እንደምንመለከት ያሳያቸዋል፡፡ ስለ ራሳቸው ያላቸውን ግምት ጠንካራ አድርጎ ተስፋን ይዘራባቸዋል፡፡

- ዋናው ነገር ልጆቻችን ከወደቁበት ችግር መፍትሔ ማግኘታቸው እንጂ የእኛ ሰው ሰራሽ ሕግ የመጠበቁ ጉዳይ እንዳልሆነ አስታውሰን በአንዳንድ ነገሮች ላይ ከልጆቻችን ጋር እንስማማ፡፡ ልጃችንን እስካልጎዳ ድረስ፤"እሺ ግዴለም እፈቅድልሀለሁ" የምንላቸው ነገሮች ይኑሩን፡፡ ለልጃችን ፍላጎት ትኩረት ስንሰጥ በእኔ መንገድ ብቻ ሂድ የምንል ሰዎች እንዳልሆንን፣ የእነርሱንም ምርጫ የምናከብር መሆናችንን ልጆቻችን ይገነዘባሉ፡፡ "ወላጆቼ ሚዛናዊ ናቸው" ብለው እንዲያስቡና እኛንም እንዲያደምጡን፣ እንዲቀርቡንም ያበረታታቸዋል፡፡

ራሳችንን ተመልክተን፣ ማስተካከል እንዳለብን ሁሉ፣ ከልጆቻችንም የምንጠብቃቸው ዋና ዋና ነገሮች መኖር አለባቸው፡፡

ልጅ ወላጅን፣ በፈለገው መንገድ ለመጠምዘዝ ኀይል ሊኖረው አይገባም፡፡ልጅ ላጠፋው ጥፋት ይቅርታ መጠየቅ፣ አስፈላጊውን እርማት ማድረግ እንዳለበትና፣ በብልጠቱም ሊያመልጥ እንደማይችል ማወቅ አለበት፡፡ አንዳንድ ጊዜ ልጆች፣ ወላጅን በመለማመጥ ለመመሰጥ እንደሚችሉ ካወቁ፣ ጥፋታቸው የሚያስከትለውን ኀላፊነት ላለመውሰድ፣ ብለው የተለያየ ዘዴ ይጠቀማሉ፡፡ ጸጸት ተስምቶን ጥፋቱን እንድናልፍለት ለማድረግ መሞከር አንዱ ዘዴ ነው፡፡ የበፊቱን አንስቶ "እናንተ እንዲህ አላደርጋችሁልኝም፤ በዚያን ወቅት እንዲህ ጎዳችሁኝ"፤ ወይም "እኔ ይህ ስለሌለኝ ነው፤ ይህ ስለጎደለኝ ነው ጥፋት የማጠፋው" በማለት ሊያለሳልሰን ይችላል፡፡ እኛም ልጄ ብዙ ተጓድቷል ብለን በማሰብ ጥፋቱ እንዲሻርለት እናደርግ ይሆናል፡፡ ይህ ግን ጎጂ መንገድ ነው፡፡ ልጆች የሠሩት ነገር ጥፋት እንደ ሆነ በሚገባ ያውቃሉ፡፡ እኛ እንደ ወላጅነታችን በፊት የሰራነው





ስህተት ካለ አሁን ለማስተካከል የተቻለንን ልንጥር፣ ልጆች የተጎዱበት ነገር ካለ ልንረዳቸው ይገባል፡፡ ያ እንዳለ ሆኖ ግን ልጆች ለጥፋታቸው ኀላፊነት መቀበልን መማር አለባቸው፡፡ በብልጠት ንግግራቸው እኛን ማሸነፍ ከተማሩ ኀላፊነት መሸሽን፣ ቁጭ ብሎ ለራስ ማዘንንና ሰበብ መስጠትን እንደሚማሩ መረዳት አለብን፡፡

ልጅ አስፈላጊ ነው ብለን ያወጣነውን የቤታችንን ህግ በብልጠቱ ሊያስለውጠን ኀይል ማግኘት የለበትም፡፡ ለምሳሌ የፈለገውን ለማግኘት ሲል፣ "እዚህ አገር ጓደኞቼ ወላጆቻቸው እስከዚህ ሰዓት እንዲያመሹ ይፈቀድላቸዋል፤ በዚህ ባህል ይህ ይፈቀዳል፤ እናንተ ብቻ ናችሁ በዚህ ነገር ጥብቅ የምትሉት" ብሎ እኛንም እንደልቡ ሊመራን ይሞክር ይሆናል፡፡ "የፈለገ ወላጅ ይፍቀድ፤ እኛ የቤታችን ህግ ይሄ ነው" ብለን በተወሰኑ ህጎች ላይ የማያወላውል አቋም እንዳለን ለልጃችንም ማሳወቅ አለብን፡፡

## *በወጀቡ ውስጥ ጠንክሮ መቆም*

ልጅ በችግር ውስት በሚያልፍበት ጊዜ፣ የወላጅ መረጋጋት፣ ጠንክሮና መሰረት ይዞ መቆም በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ልጃችን በስነምግባር ችግር ውስጥ ሲያልፍ፣ የሚያልፍበት መንገድ ቀጥ ያለ አይሆንም፤ ዳገት ቁልቁለት ያለውና ጥምዝምዝ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ የፈተና ጊዜ ምን ያህል እንደሚቆይ ላንተምን እንችላለን፡፡ በእዚህ ውጣ ውረድ መሐል፣ እንደ ወላጅነታችን በአካልም ሆነ በአእምሮ ሳንዝል ተደላድለን ጠንክረን መቆማችን በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

- ስንረጋጋ ትእግስት ስለሚኖረንና አርቀን ስለምናይ በስሜታዊነት ነገሮችን አናበላሽም፣ ውስጣችን ሲረጋጋ፣ ልጃችንን ሊረዱልን የሚችሉ የተለያዩ

አማራጮችን፣ ለማየትና ለመመዘን፣ አስፈላጊ የሆነ እርዳታንም ከሌሎች ለማግኘት ኀይሉ፣ አቅሙና በልንቱ ይኖረናል።

- ልጃችን በተዘበራረቀ ነገር ወስጥ እያለፈ ቢሆን እንኳ በወላጆቹ ውስጥ ደጋግሞ የየሚያው ጽናትና የተረጋጋ መንፈስ ዋና ምሳሌውን አስተምሪው ይሆንለታል። ለምክር፣ ለብልሀት፣ የልቡን ለመንገር ወደ እኛ እንዲመጣም ይበረታታል። እኛም ልጃችን ሲቀርበንና
- የሚያልፍበትን ነገር ገልጾ ሲነግረን ለመምከርና እርዳታችንን ለመለገስ ትልቅ እድል እናገኛለን፡፡
- ጠንክረን ስንቆም፣ የልጃችን በፈተና ጎዳና የመራመጃ ጊዜው ቢረዝምም እንኳን፣ ወደ ፊት መጓዝ እንችላለልን። ለልጃችን ልንሰጥ የምንችለውን ጠቃሚ እረዳታ ያለምንም ችግር እናደርሳለን። ባጠቃላይ፣ የወላጅ ተረጋግቶ መቆም፤ ለልጃችን ችግር መፍትሄ ማግኘት ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

ካልተጠነቀቅን ግን ተቃራኒው እውን ሊሆን ይችላል። ልጃችንን የምንወድና፣ እሱን/እሷን ለመረዳት የሚያስችል ብዙ ነገር ልናበረክት የምንችል የነበርን ወላጆች ሳናስበው መንገዱ መሀል ዝለን ልንቀር እንችላለን፤ "እኔ በቃኝ መረረኝ" ብለን ከልጃችን ጋር ልንጣላ፣ ወይም ግራ በመጋባት ከጎዳናው ወጥተን ዳር ልንቆም እንችላለን።

በዚህ ቀውጢ ጊዜ፣ ልጃችን የእኛ ድጋፍ ከመቼውም ይልቅ ያስፈልገዋል፤ እኛም እንደ ወላጅነታችን አስፈላጊውን፣ ጠቃሚ እርዳታን ለማበርከት እንድንችል መጀመሪያ ጸንተን መቆም አለብን። የተሰበረ ወንበር ሰውን እንደማያስቀምጥ ሁሉ ውስጣችን ከዛለ እንኳን ልጆቻችንን ለመርዳት ለራሳችንም እርዳታ ፈላጊዎች ልንሆን እንደምንችል ተረድተን፣ አሰራራችንን እንገምግም። ጸንተን እንድንቆም የሚረዱንን ነገሮች እንወቅ፣ በአንጻሩ በቶሎ ተስፋ እንድንቆርጥ፣ እንድንዝል የሚያደርጉንን ሁኔታዎች ለይተን እንወቅ።





*ወላጅ በጉዞው ላይ በቶሎ እንዲደክም፣ እንዲዝል፣ የሚያደርጉት ዋና ዋና ምክንያቶች ምንድን ናቸው?*

1."ልጄን ጠምዝዤ እለውጠዋለሁ" ብሎ ማሰብ፣ ጉልበትን የሚጨርስ ልፋት ነው። ልጃችን የእኛ ሰውነት አካል እንደሆነ ያህል፣ "በራሴ የጊዜ ገደብ ውስጥና በራሴ መንገድ፣ ጠምዝዤ እመልሰዋለሁ" ብሎ መነሳት ኃይልን ይጨርሳል። አንዳንዴ ወላጆች ማመን ባንፈልግም እንኳ፣ ልጅ የራሱ አመለካከት፣ ምርጫና ውሳኔ አለው። ምንም ብንደክም፣ ልጅ እኛ ልክ እንደፈለግነው ላይሆንልን፣ በጠበቅነው መንገድም ላይሄድልን ይችላል። "በዚህ የጊዜ ገደብ ውስጥ፣ በዚህ መንገድ እለውጠዋለሁ" ብለን ወስነን፣ ሀይላችንን ሁሉ አሟጥጠን፣ ኋላ ልጃችን ልክ እንደፈለግነው ሳይሆን ሲቀር፣ እንዝላለን ልፋታችን ሁሉ ወድቆ ስለሚከሰከስ ቶሎ እንደክማለን። በዚያም ሰአት፣ ልጃችን ላይ ተማረን እንቀራለን፤ ተስፋም እንቆርጣለን። አቅመ ቢስ እንደሆንን፣ ከእንግዲህ ምንም ማድረግ እንደማንችል ያህል ይሰማንና ለልጃችን ትልቅ እርዳታ ሊሆን ይችል የነበረ ትከሻችን ይጠብባል።

ጸንተን ለመቆም ከወዲሁ ወስነን መጀመር አለብን፤ "ልጄ በፈለግኩት ጊዜ በፈለግኩት መንገድ ላይ ላይሄድልኝ ይችላል። የእኔ ተግባር በቻልኩት ድጋፍ መሆን እንጂ ልጄን በኃይል ለመለወጥ መሞከር አይደለም" ብለን መቆም ይኖርብናል። እንዲህ ብለን ከጀመርን ውስጣችን ጠንክሮ በትእግስትና በጽናት እንቆያለን፤ ከልጃችን ጋር ያለን ግንኙነትም ጠንክሮ ይቆያል። ልጃችንን ልንረዳው በምንችለው ቦታ ላይ በማተኮር እገዛችንን እንድንለግስ እድል እናገኛለን።

2.ልጆቻችን ለራሳቸው ሊያደርጉ የሚገባቸውን ሁሉ እኛ እየሸፈንንላቸው፣ እጅና እግራቸው ሆነን መቆየት፣ በመንገዳችን ላይ ቶሎ እንዲደክመን፣ አቅማችንን ሁሉ ጨርሰን እንድንዝል ያደርጋል። እንደዚህ ሁሉን ተረክበን ልንሰራላቸው ስንሞክር፣

ይደክመናል፡፡ ያለንን አቅም ሁሉ እነሱ ላይ አፍስሰን፣ መልሰው ሲያበላሹ ስናያቸውም በጣም እንናናደድባቸዋል፡፡ “ይህን ሁሉ ለፍቼ፣ አሁንም አልተመለሱ” ብለን አይናችሁ ላፈር ብለን ጥግ እንይዛለን፡፡ የእኛ ያላግባቡ መዛል ብቻ ሳይሆን፣ ልጃቻችንም ለጉዳት ይዳረጋሉ፡፡ “ወላጆቼ ሁል ጊዜ ይደርሱልኛል” ብለው እንደልባቸው መረን እንዲሆኑ እናደርጋቸዋለን፡፡ መላልሰው በማጥፋት፣ ሞልቃቃነት እንዲጠናወታቸው እናመቻችላቸዋለን፡፡

ልጆቻችን ጥፋታቸው ዋጋ እንደሚያስከፍላቸው፣ ወላጅ ሁልጊዜ ፈጥኖ ደራሽ ነጻ አውጫቸው እንዳልሆነ ማወቅ አለባቸው፡፡ በተለይ እያደጉ ሲመጡ፣ በሕይወታቸው ውስጥ እኛ ያለንን ቦታ እና ከእነርሱ የሚጠበቅባቸውን ቁም ነገር በዝርዝር እንግለጽላቸው፡፡ “አሁን ራስሽን ችለሽ የምታስቢ ትልቅ ሰው እየሆንሽ ነው፡፡ እኔ ሁሌ እወድሻለሁ፤ አብሬሽ እቆማለሁ፤ ነገር ግን በሁሉ ነገር አዳኝሽ አልሆንም፣ በሁሉ ነገር ፈጥኖ ደራሽ ከችግር አውጭሽ መሆን አልችልም፡፡ ውሳኔውም የምትወስኝም አንቺው እስከሆንሽ ድረስ፣ የውሳኔሽንም ውጤት መቀበል አለብሽ፤ ይህንን ካሁኑ እነግርሻለሁ” ብለን እናስረዳ፡፡ እንደዚህ ብለን ከተናገርን በኋላ ልጃችን ደግማ ያንኑ ጥፋት አጥፍታ፣ “ወላጆቼ በሁሉ ነገር ደርሰው ያወጡኛል” ብላ ብትጠብቀን “ያልኩሽን ብዬሻለሁ” ብለን በተናገርነው መጽናት አለብን፡፡ እኔ መርዳት የምችለው እስከዚህ ድረስ ነው ብለን ስንወስን ጤንነታችን፣ ኃይላችንና ሰላማችን ተጠብቆ ጸንተን እንቆማለን፡፡ ልጃችንን በተመለከተ አላስፈላጊ ምሬት ውስጥ እንዳንገባ ያስችለናል፡፡

3.ልጆቻችንን ልንረዳቸው በሚገባን መንገድ እንዳንረዳቸው እጃችንን የሚያስረን፣ ኀይላችንን የሚበላብንና፣ የሚያዝለን ሌላ ዋነኛ ነገር ዓይናችንን ሌላ ሰው ላይ ማድረግ ነው፡፡ ሰው ስለ ልጄና ስለ ቤተሰቤ ቢያውቅ ምን ይላል? ብሎ ማሰብ ዋነኛ የሚያዝለን እና ከትልቁ ግባችን የሚያስቀረን ጉዳይ ነው፡፡ አንዳንዴ ሳናስበው ነገሩን ከሌላ ሰው ጋር እናያይዘዋለን፡፡ ምን ማድረግ አለብኝ የሚለው ጉዳይ ላይ ከማተኮር ይልቅ “ልጄ





ችግር ውስጥ መሆኑን ማን ሰማ ወይም ማን አወቀ?” በሚለው ሃሳብ ሳናስበው እንጠመዳለን፡፡ እንደዚህ ማድረግ መፍትሔ የማግኘት ሂደቱን ያስተጓጉለዋል የእኛን አቅምም ያዳክመዋል፡፡

ይህ አላስፈላጊ ጭንቀት ኀይላችንን አሰባስበን ልጆቻችንን ከገቡበት ወጥመድ ነጥቀን እንዳናወጣቸው ጋሬጣ ይሆንብናል፡፡ “ሰው ምን አለ?” እያሉ አይንን ውጭ ላይ ማድረግ፣ ቤተሰብ መኻል ቅራኔ እና መለያየትን ያመጣል፡፡ ልጆቻችን እንኳን ያንን አይተው ያዝኑብናል፡፡ “እሷ የምትጨነቀው ስለኔ ችግር ሳይሆን ስለ ጓደኞቿ አስተሳሰብ ነው”፡፡ “እሱን ያሳሰበው የኔ ደህነነት ሳይሆን ስሙ ነው” ብለው ያስባሉ፡፡ ይህ የይሉኝታ አስተሳሰብ፣ እኛም የሚያስፈልገውን እርዳታ ሁሉ እንዳንሻ እና እርዳታ ሊሰጡን ከሚችሉ ሰዎች ጋር እንዳንገናኝ አንቆ ይይዘናል፡፡ ጉልበታችንን አሰባስበን መፍትሔ የማምጣት ዓቅማችን ተበታትኖ ይቀራል፡፡

ልብ እንበል! ይሄ ጊዜ “ሌላው ምን አለ?” እያሉ ቀን ከሌሊት በማሰብ የሚታወኩበት ጊዜ አይደለም፡፡ “ሰው ምንም እንዳይል ምን ላድርግ? ሰው ምን ይለኛል?” የሚለው ላይ ስናተኩርና ስንጨነቅ የልጆቻችን ጊዜ በርሮ ይሄዳል፡፡ መፍትሄ ሳንሻ ጊዜው ያልፋል፡፡ ቆሞ “ማን አየኝ? ማን አላየኝ?” እያሉ ማመንታት ሞኝነት፣ እጅን ራስ በራስ ማሰር፣ ችግሩን በሬን ወለል አድርጌ ከፍቼልሃለሁ ዘው ብለህ ግባ እንደ ማለት መሆኑን እናስታውስ፡፡ አዎ፤ አንዳንድ ጊዜ ከኛ ቦታ ሆነን ስናየው ሌላው ሰው ሕይወት ፍጹም፣ የእኛ ቤተሰብ ግን በእንደዚህ አይነት “ጉድ” እያለፈ ያለ ብቸኛ ቤተሰብ ሆኖ ሊታየን፣ ይችላል፡፡ በማህበረሰባችን ውስጥ፣ አንዳንዴ፣ ውጭውን አለባብሶ ፍጹም መስሎ የመቅረብ ልምድ አለ፡፡ ሁሉ ጥሩና የተስተካከለ እንደሆነላቸው አስመስለው ለማቅረብ የሚሞክሩ ቤተሰቦች ቢያጋጥሙን፣ የሚያሳዩት ስእል እውነት እንዳልሆነ እንረዳ፡፡ ልጆችን ወልዶ ለቁምነገር በማድረሱ ሂደት ውስጥ ችግር የማይገጥመው ቤተሰብ የለም፤ ዓይነቱና ደረጃው ይለያይ እንጂ መልካም ውጤት ላይ የሚያደርሱት ግን ይሉኝታን ወደ ጎን

አድርገው ችግሩን በመፍታት ላይ ብቻ ያነጣጠሩ ቤተሰቦች ናቸው።

4.በራሳችን መማረር፣ "ወደፊት ምን ይሆናል?" እያሉ በጭንቀት ውጥረት መቆዘም፣ ትርፉ ራሳችን በቶሎ ማድቀቅ ብቻ ነው። ይህ አይነት አሉታዊ አስተሳሰብ ብቸኛ ፍሬው፣ አእምሮአችንን ማዛልና ልጃችንን እንዳንረዳ እጃችንን ማሰር እንደሆነ አስተውለን፣ ራሳችንን ለማረጋጋት አስፈላጊውን እርምጃ እንውሰድ።

እውነት ነው፣ አንድ ሰው አይምሮዬን ላረጋጋ ስላለ ብቻ፣ በቀላሉ ከጭንቀት መራቅ፣ ያቅተው ይሆናል። ችግርን እግዚያብሄር ፊት መውሰድ፣ ጸሎት ትልቅ ሀይል አለው፤ ለጥንካሬ፣ ለጽናት፣ ለመፍትሄ እንጸልይ። ይረዱኛል፣ ያበረታቱኛል፣ ድጋፍ ይሆኑኛል ብለን ከምናስባቸው ሰዎች ጋር ልባችንን ከፈተን እንነጋገር። ከሰው ጋር መማከር፣ ውጥረታችንን ሊቀንስልንና መፍትሄ እንድናገኝም ሊረዳን ይችላል፤ ልባችንን አውጥተን ስናወራ በፊት ያልታየን መላ ሊታየንም ይችላል። ባጠቃላይ፣ ያብራካችን ክፋዮች ወደታለመላቸው የሕይወት ምዕራፍ መሸጋገራቸው ዋነኛው ዓላማችን ስለሆነ ባጠቃላይ፣ ትኩረታችን መፍትሔው ላይ ብቻ ይሁን።

### *ልጅን ለመርዳት፣ ወላጅ ምን ማድረግ ይችላል?*

ስለሚያልፉበት ችግራቸው፣ ጥልቅ እውቀት ሊኖረን ይገባል። የስነምግባራቸው መበላሸት ምክንያት ከአስተሳሰባቸው የተያያዘ ይሁን፣ ሱስ ይሁን፣ የጓደኛ ግፊት ይሁን... ወዘተ ስለ ጉዳዩ በጥልቀት ማወቅ አለብን፤

ልጆቻችንን ለመርዳት ምን እርምጃ ልንወስድ እንደሚገባን ማወቁም አስፈላጊ ምርጫ ነው። ከላይ እንዳየነው፣ ከእኛ ጋር





በሚኖረው የንግግር ልውውጥ ምን ተገቢ፣ ምን ጎጂም እንደሆነ ልንገመግም ይገባል።

ልጅን ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ ስለተለያዩ ችግሮች ምንነት ተንትነው የሚናገሩ፣ ልጅ በባህሪ ለውጥ ሲያልፍ፣ ወላጅ በምን መንገድ ሊረዳ እንደሚችል ጥሩ ግንዛቤ የሚሰጡ፣ በድረገጽ (ዌብ ሳይት) እና በመጽሐፍም የተጻፉ ጽሁፎች አሉ። እነዚ ጽሁፎች የተዘጋጁት፣ ችግሮቹ ላይ አተኩረው ለረጅም ጊዜ ባጠኑ ባለሙያዎች እንዲሁም ራሳቸው እና ልጆቻቸው በፈተና ውስጥ አልፈው ከልምድ ግንዛቤን ባገኙ ቤተሰቦች ነው። ጠቃሚ ምክር የሚሰጡንን አንዳንድ ድረገጾች ለማየት፣ ከስር ይመልከቱ።[50]

[50] Drugfree.org የተባለ ድረ ገጽ፣ የመጠጥ ችግር፣ የተለያዩ ሱሶች በተመለከተ፣ ልጆቻችን ድል አድርገው ነጻ እንደሚወጡና ወደፊት እንዳያልፉበት እንዴት ልንረዳቸው እንደመንችል የሚረዳ ተቃሚ መረጃዎችን ይለግሰናል። በተጨማሪም ልጆቻንን እንደ የእድሜያቸው ደረጃ እንዴት ብለን ልንመከራቸው እንደሚገባ እንዲሁም ችግር ውስጥ ከወደቁ ደግሞ ከማነጋገር ጀምሮ እርዳታ እስከ ማግኘት ድረስ ምን አይነት ደረጃዎችን መከተል እንዳለብን ጥሩ ምክር ይመከረናል። www.paretingteensonline.com በጣም ጠቃሚ ድረ ገጽ ነው። እዚህ ድረ ገጽ ውስጥ ገብተው resource የሚለውን ቢጫኑ ልጆችን ሊያገጥሟቸው የሚችሉ የተለያዩ ችግሮችን በተመለከተ ጠቃሚ መረጃን ከመስጠት በተጨማሪ፣ ከእነዚህ ችግሮች ለመወጣት ስለሚያስችሉን የተለያዩ የእርዳታ ምንጮች (resource) ይጠቁመናል። **ሌሎች ጠቃሚ ድረገጾችን ከመጽሐፉ በስተጀርባ ተጽፈዋል**

## *ውጫዊ እርዳታ*

በተለይ በብዙ ምእራብያውያን አገሮች ህብረተሰቡ፣ በአገራችን እንዳለው አይነት ማህበራዊ ኑሮ የለውም። ይሁን እንጂ በማህበረሰባቸው ያላቸው መልካም ነገር አለ፤ ያም ህዝቡን ለመርዳት የተመሰረቱ ብዙ ተቋማት መኖራቸው ነው። ወላጆች የልጆቻቸው ሥነምግባር ሲበላሽ እነርሱን ለመረዳት የሚጠቀሙበት ዋነኛ መሣሪያዎች እነኝህ ተቋማት ናቸው።

ከወላጅ አቅም ቁጥጥር ውጭ በሆኑ ጉዳዮች ላይ፣ እነዚህ ማህበራዊ ተቋማት፣ አስፈላጊውን እርዳታና ድጋፍ ሊሰጡ ይችላሉ። ልጆቻችን፣ ከችግራቸው ነፃ ለማውጣት ይህን ውጫዊ እርዳታ (ቴራፒ ህክምና) ማግኘታቸው አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። በምንኖርበት አካባቢ፣ ለልጆቻችን ምን ዓይት እርዳታ እንዳለ፣ ማወቁ በጣም ጠቃሚ ነው።

ልጆቻችን ህክምና/ቴራፒ ካስፈለጋቸው የት ልንወስዳቸው እንደሚገባ የሚጠቁሙን የእርዳታ ምንጮች አሉ። የህክምና ወጪውንም ለመሸፈን የሚረዳን የገንዘብ እርዳታ በምን መልክ ልናገኝ እንደምንችል ጠቃሚ ግንዛቤ የሚሰጡን የመረጃ ማዕከሎች አሉ። እነዚህን የመረጃ ምንጮች ለማየት ከስር ይመለከቱ።[51]

[51] 1-800=662-4357 treatment referral ሱስ ጋር የተያያዘ ችግር እርዳታን በተመለከተ፤እኛ በምንኖርበት አካባቢ ስላሉ የህክምና (treatment) ቦታዎች ይነግሩናል። (ልጆቻችን እዛው ቆይተው እርዳታ የሚያገኙበት፡ ሆነ ከቤት እየተመላለሱ፤እነዚህ የእርዳታ ቦታዎች የት እንዳሉ፣ በመጠቀም ያገለግሉናል። ከዛም በተረፈ፣ በምንኖርበት ስቴት፣ ካውንቲ ውስጥ ዋጋ ቅናሽ፣ ከፍያ እርዳታን ለማግኘት የት እንደምንደውል ይጠቁሙናል።

ከስልኩ ሌላ በአካባቢያችን ስላሉ የእርዳታ ቦታዎች ሊጠቆመን የሚችለው findtreatment.samhsa.gov የተባለ ዌብ ሳይት ነው።





በማጠቃለያ፣ ልጅ ችግር ውስጥ ሲያልፍ ቤተሰብ አብሮ መቆሙ በጣም አስፈላጊ ነው። የበለጠ መላ የሚገኘው ቤተሰብ እጅ ለእጅ ተያይዞ ሲቆም ነውና፣ ትናንሽ መለያየትን ወደኋላ አድርገን አብረን መቆማችን ለድላችን ያግዘናል። ኀላፊነትን በመወጣት አኳያ፣ መላ ቤተሰብ እንዲተባበር ማድረጉ አስፈላጊ ነው። ዋናው ቁም ነገር በጉዞው ላይ በርትቶ መቆምና ስሜታዊነት ሳያግድ ጸንቶ ከልጃችን ጎን መራመድ እንደሆነ፣ አስታውሰን፣ ራቅ አድርገን እንመልከት፤ የሚያዝሉንን ነገሮች እናስወግድ። ጥንካሬና ጽናት የሚሰጡን ነገሮች አቅፈን እንያዝ። እንዲህ ከሆነ ድል የእኛ ይሆናል።

# የሕይወት ተሞክሮ

## ልጅነቴና የሕይወት ወጀብ

ኢትዮጵያ እያለሁ ደስተኛ፣ ጥፋት ውስጥ የማልገባና ታዛዥ ልጅ ነበርኩ። ግማሽ የልጅነት ዘመኔን እንዳጠናቀኩኝ፣ ወደ አሜሪካ መጣሁ። እኔ በራሴ ጥቂት ወራት ኖሬ ሳየው ግን ሽክሙ እየከበደኝ መጣ። እዚህ አገር፣ ትምህርት በጀመርኩበት በመጀመሪያው አመት፣ ከትምህርት ቤት አራት ጊዜ ተባረርኩ። ጥፋቴም፣ አንዱ ባንዱ ላይ መደራረብ ጀመረ።

ወደ አሜሪካ ስመጣ የተሰማኝ ደስታ ጥልቅ ነበር። ከአውሮፕላን ጣብያ፣ እኛን ለማምጣት ብሎ በተከራየው በአዲሱ መኪና፣ አባቴ ከእህቴና ወንድሜ ጋር መጥቶ ተቀበለኝ። ቤተሰቦቼ የሚኖሩት ጥሩ አካባቢ በሚገኝ ባለ ሁለት ክፍል አፓርትመንት ውስጥ ነበር። በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ቀናት ውስጥ በደስታ ተሞልቼ ቆየሁ። የቦታው ንጽህና፣ አዲስ አገር መምጣቴ፣ አገር ቤት የማላገኛቸውን እቃዎች እዚህ በቀላሉ ማግኘት መቻሌ የደስታ ምንጭ ሆኑልኝ።

ገና እንደመጣሁ ሰሞን፣ ከኔ በፊት የመጣው ወንድሜን አየውና ጠባዩ ድሮ ከማውቀው መለወጡን ሳይ ይገርመኝ ነበር። አባቴ ወንድሜን ባለግህ ብሎ ሲገርፈው፣ ከመጥፎ ልጆች ጋር ዋልክ ብሎ ሲቆጣው አይ ነበር። ወንድሜ ለምን እንደሰነፈና ከማይሆኑ ጓደኞች መግጠም እንደጀመረ፣ ፍጹም አይገባኝም ነበር። ሁሉ የሞላበት አገር ሆኖ ለምን ራሱን መጥፎ ነገር ውስጥ ይከታል ብዬም አስብ ነበር። አሜሪካ ከመጣሁ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ግን፣ ደስታዬ እየጠፋ ውስጤ እያዘነ መምጣት ጀመረ።





ጥያት የመጣኋትን እናቴን እና ሌሎች ቤተሰቦቼን በጣም መናፈቅ ጀመርኩ። አባቴን አኗኗሩን ሳይ ደግሞ ሀዘን ይሰማኝ ነበር። አባቴ አገር ቤት ጥሩ ኑሮ ነበረው። እዚህ መጥቶ፣ ድሮ ከነበረው በጣም ዝቅ ያለ ስራ ሲሰራ ሳየው ውስጤ በጣም ይረበሽ ነበር። ይህም ሆኖ ግን ስሜቴን ገልጬ የማናግረው፣ የማማክረው ሰው አልነበረኝም። በቤታችን ውስጥ ሁሉም ሰው በየራሱ መንገድ ሲሯሯጥ ይውል ነበር። ቁጭ ብሎ ከኔ ጋ የማውራት ጊዜም የነበረው ሰው አልነበረም። ይህም፣ የሚሰማኝን የብቸኝነት መንፈስ እንዲጠነክር አደረገው።

ትምህርት ቤት ስንገባ ደግሞ በተማሪው ዘንድ እንደ ባይተዋር መታየት ጀመርኩ። የምሄድበት ትምህርት ቤት (ሀይ ስኩል ውስጥ) ክብርን የሚያገኙት ተማሪዎች አለባበሳቸው የተለየ፣ ለጥል ወደኋላ የማይሉት ተማሪዎች ነበሩ። እኔ አለባበሴ ከነሱ በጣም የተለየ ነበር። ከዛም በተጨማሪ፣ ዝም በማለቴና ቋንቋዬ ከእነሱ የተለየ ስለነበር ሊያስቸግሩኝ ጀመሩ። ይህ ሁሉ ባንድ ጊዜ ተደራረበብኝ።

ራሴን ለመከላከል ብቻ ሳይሆን፣ የሚሰማኝን ብቸኝነት፣ ውጥረትና ንዴት ለመሸሽ በድብድብ እወጣው ነበርና፣ በትምህርት ቤት ውስጥ ጥፋቴ በዛ። ከትምህርት ቤት መባረር የጀመርኩትም በዚያ ጊዜ ነበር። አባቴ በዛ ሰአት የማልፍበትን ብዙም አይረዳልኝም ነበር። እውነት ነው አባቴ ይወደኝ ነበር። አገሩን ጥሎ በዚህ ዋጋውን የሚከፍለውም ለኛ ብሎ ነበር። እንደዚያም ሆኖ ግን፣ የማልፍበትን ውስጣዊ ስቃይ አይረዳልኝም ነበር። ለሱ የሚታየው ጥፋቴ፣ ችግር ውስጥ መግባቴ ብቻ ነበር። ያንን ሊያስተካክል የሚፈልገውም በግርፊያና ዱላ ብቻ ነበር።

አሁን መለስ ብዬ ያንን የልጅነት ግዜዬን ሳየው ግን እንዴት ከባድ እንደነበር ይታየኛል። ያኔ በዛ ጊዜ ምን ትመኝ ነበር ብዬ ብጠየቅ መልሴ ይህ ይሆናል።

- ቤተሰቦቼ ሁሌ በመሯሯጥ ፋንታ አብረን ጊዜ የማሳለፊያ ጊዜ ቢኖረን ብዬ እመኝ ነበር።
- ቤተሰብ ተሰባስበን ስለምናልፍበት ነገር በግልጽ ብንወያይ ብዬ እመኝ ነበር።
- አባቴ ሁሌ በመጮህ ፋንታ ቢያዳምጠኝ ብዬ እመኝ ነበር። ይህን አደረክ ያንን እያለ ብቻ በመቆጣት ፋንታ ያን እንዳረግ የሚገፋፋኝን የውስጤን ጭንቀት እና ከውጭ ያለብኝን ግፊት ቢረዳልኝ እኔንም በጣም ይረዳኝ ነበር። ከሱ በመደበቅ ፋንታ በግልጽ መጥቼ ሁሉን እንድነግረው ያበረታታኝ ነበር።
- ሁሌ ጥፋቴን ብቻ በማየት ፋንታ፣ ጥሩ ስሰራም ቢያይልኝ፣ ቢያሞግሰኝ እጠቀም ነበር።

ለአዲስ ወላጆች ያለኝ ምክር ይህ ነው። ከዛም በተጨማሪ በምሳሌነት ልጆችን ማሳደግ እና በሁሉ በመናደድ ፋንታ ዋና ዋና ላይ ማተኮር ትልቅ ጥቅም ያለው ይመስለኛል።





# ምዕራፍ ዘጠኝ

## የወላጅን የግል ሕይወት በተመለከተ

የግል ሕይወታችንን በተመለከተ፣ ለለውጥ የተከፈተ ልብ ሊኖረን ያስፈልጋል። ሁሉም ሰው ስህተት ይሰራል፤ ወደ መፍትሄ የሚሻገሩት ግን፣ ራሳቸውን በጠራ መስታወት የሚያዩ ብቻ ናቸው። ራሳችንን ለመገምገምና ምክርን ለማዳመጥ ፈቃደኞች ብንሆን፣ ለኛም ሆነ ለቤተሰባችን ሕይወት መሻሻል፣ በትልቁ ልናግዝ እንችላለን። 'ከልጆቼ ጋር ባለኝ ግንኙነት መለወጥ የሚገባኝ ምንድነው?' ብለን፣ እንመርምር። 'እየታየብኝ ያለ ምናልባት ልምድ ሆኖ አብሮኝ ያለ፣ እኔና ቤተሰቦቼን እየጎዳ ያለ ፀባዬ ምንድነው?' ብለን ራሳችንን እንጠይቅ፤ የእውነት መንገድን ከወሰድን፣ ደረጃ በደረጃ፣ ለውጥን በማምጣት፣ ድል ልናገኝ እንችላለን።

ሕይወታችንን፣ እንመዝን፤ ነገር ግን የኛን ከሌላ ሰው ሕይወት ጋ ከማስተያየት ልምምድ እንራቅ፤ከጥቅሙ ጉዳቱ ይበልጣልና። የሌላ ሰውን አኗኗር እየመዘንን የእኛን በእዚያ ስንለካ፣ አብዛኛውን ጊዜ የሚታየን የሌላው ጥሩ፣ የእኛ መጥፎ ሆኖ ነው፤ በዚያም ምክንያት፣ ሐዘንና ስብራት ይደርስብናል፤ ምሬትም የሕይወታችን ክፍል ሊሆን ይችላል። የሌላ ሰው ሕይወት ላይ አይናችንን ስናደርግ፣ በትክክል እኛ የምናምንበትን መንገድ ትተን፣ አሉታዊ አካሄድንና ተገቢ ያልሆነ ምርጫን ልንመርጥ እንችላለን። ልብ እንበል፤ ፍጹም የሰመረ ሕይወት ያላቸው እየመሰሉ በባዶነት የሚኖሩ ብዙ ሰዎች አሉ። ለውጭ ዓይን ያማረ የሚመስል፣ ውስጡ ግን በሀዘንና ጭንቀት የተሞላ ሕይወትን እየመሩ ያሉ ብዙ ቤተሰቦች አሉ። የጥሩ ሕይወትን መስፈርት ለማወቅ፣ የሌላን ሕይወት መመልከት አቁመን፣

በኛው ሕይወት ማስቀደም ስለምንፈልገው ጉዳይ፣ አብክሮ ማሰብን መመሪያችን እናድርግ።

ስለራሳችን መብልና መጠጥ ከመጨነቅ ባለፈ መልኩ፣ ለሌሎች የምንደርስበት ሕይወት እንዲኖረን መጣር፣ የኑሮዋችን አቋም ሊሆን ይገባል።ከራስ አልፎ ለሌሎች ማድረግ፣ ለሕይወት እውነተኛ ትርጉም የሚሰጥ፣ በእውነተኛ ሰላምም እንድንኖር የሚያበረታ አብይ ነገር ነው። እኔነት የወረሰውን ሕይወት የምንመራ ከሆነ ግን፣ በውጭው ምንም ያህል ቢሞላልን፣ በውስጣችን ግን የባዶነት ስሜት ይወርሰናል፤ ሕይወታችን ትርጉመ ቢስ እንደሆነች እንኖራለን። በአንጻሩ ደግሞ ከራሳችን አልፈን፣ ለሌሎች ሕይወታችንን ስናካፍል፣ ለልጆቻችንም ጥልቅ ትምህርትን እናስተላልፋለን።

ትዳራችንን በተመለከተ ይህንን ልብ እንበል። በዚህ ዘመን ለብዙዎች እየተላለፈ ያለ አንድ የስህተት ትምህርት አለ። ይህም “እኔና መብቴ” የሚለው ትምህርት ነው። በትዳር ውስጥ ግን እንደዚህ ያለ ነገር ሊኖር አይገባም፤ ጉዳዩ የጋራ ነውና። የእኔ መብት፣ የእኔ ፍላጎት የሚለው ላይ የምናተኩር ከሆነ፣ ልጆቻችንና ትዳራችንን እንጎዳለን። ለዋናው ግባችን ስንል አርቀን እንይ። እኔ የፈለግሁት ሁሉ ይሁን እያልን፣ ትዳራችን አናበላሸው። ክርክር አሸነፍሁ ብለን የልጆቻችንን ሕይወት ለውድቀት አንዳርግ። ማወቅ ማለት አርቆ ማየት እንደሆነ፣ ብልጥነት ማለት እስከወዲያኛው የሚበጀንን ነገር ማከናወን እንደሆነ ልብ ተረድተን፣ የቤተሰብ ሰላምን ፍቅርንና አብሮ መሥራትን እናስቀድም።

ለራስ ጊዜ መስጠትንና፣ ማረፍን አንርሳ። አንዳንዴ፣ ራስን መጠበቅን፣ ከእኔነትና ከስግብግብነት ጋር እናምታታዋለን። ብዙ ጊዜ፣ ጥሩ ወላጅ መሆን ማለት “ሁልጊዜ ራስን ወደኋላ ማድረግ” ይመስለናል። ይህ እምነት፣ በተለይ ብዙ እናቶች





አእምሮ ውስጥ ዘልቆ ገብቷል፤ ሆኖም ፍጹም የተሳሳተ አመለካከት ነው።

የእኛ ራስን መጠበቅና መንከባከብ፣ ከማንም በላይ ጥቅሙ ለልጆቻችን ነው። እኛ የምንወደው ሰው ተጎሳቁሎ፣ ራሱን ጥሎ ብናይ ደስ እንደማንሰኝ፣ ለልጆቻችንም እንደዛው ነው። ወላጆች ተጎሳቁለው ሲያዩ፣ ልጆቻችን ውስጣዊ ደስታቸው ይቀንሳል። ብዙ ነገር ብናደርግላቸውም፣ ራሳችንን ጥለን፣ ሰላም አጥተን እያዩ ነውና፣ ውስጣቸው ያዝናል። በአንጻሩ፣ ልጆቻችን የወላጆቻቸውን ደህንነት ሲያዩ፣ ውስጣዊ ደስታ፣ የመነቃቃት ስሜትና እረፍት ይሰማቸዋል።

ሁሌ በድካም ውስጥ ከሆንን፣ ሳናስበው ልጆቻችን ላይ መናደድና መማረር ሊመጣም ይችላል። አብረናቸው መጫወት መሳቃችን እየቀነሰ ይመጣል። በትንሽ በትልቁ ልንጮህ፣ ፊታችንን ልናጠቁር፣ ትልቅ እድል ይኖረዋል።

ራሳችንን በጥሩ ሁኔታ መጠበቅ ያለብን ሌላኛው፣ ዋነኛ ምክንያት፣ ለልጆቻችንን ጥሩ ምሳሌ ለመሆን ነው። ልጆች ከናታቸውና አባታቸው ምሳሌነት፣ ስለሕይወት ይማራሉ። ራሳችንን ስናጎሳቁል፣ ሁልጊዜ ራሳችንን ወደኋላ ስናደርግ፣ ለልጆቻችን ተገቢ ያልሆነ መልእክትን እየሰጠን ነው። “ራስን መጠበቅ ስህተት ነው፣ ሁልጊዜ ራሳችሁን ዝቅ አድርጋችሁ ኑሩ” እያልናቸው ነው። በተቃራኒው ግን፣ ወላጆች ለራሳቸው ጊዜ ሲወስዱ፣ ተገቢ እረፍትን ሲያደርጉ ሲያዩ፣ ልጆችም ለራሳቸው ያንን ማድረግን ይማራሉ። ሁዋላ በትልቅነት እድሜያቸው፣በትዳር ጊዜ፣ከእናትና ከአባታቸው እንደተማሩት፣ ራሳቸውን ይንከባከባሉ፣ ተነቃቅተውም ይቆያሉ። ከራሳችንም በላይ ለቤተሰባችን ስንል፣ ደህንነታችንን እንጠብቅ።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ይህን እውነት ልብ እንበል፤ የጤንነት ሁኔታ መከታተል በጣም አስፈላጊ ነው። ምንስ ጥሩ ወላጆች

ብንሆንና፣ ለልጆቻችን ትልቅ አላማ ቢኖረን፣ ጤናችን ከተቃወሰ፣ ልናደርግ የምንፈልገውን እንዳናደርግ እጃችን ይያዛል። የጤናችን መቃወስ፣ ተዳክመን እንድንቆይ ሊያደርገን የአልጋ ላይ ቁራኛ እስከመሆንም ሊያደርሰን ይችላል። ያንን ለመከላከል፣ ህልማችንን ግብ መቶ፣ ለልጆቻችን ያለምነውን እንድናይ፣ ጤናችንን እንጠብቅ። ሀኪም ጋ ሄደን ተገቢውን ምርመራ ማድረግ፣ ህመም ሲሰማን መከታተል፣ ጤናን ከሚያቃውሱ ምግቦች እና መጠጦች መራቅ ልንወስደው የሚገባ እርምጃ ነው።

ውስጣዊ ቁስል፣ እንደ መጋረጃ ሆኖ፣ ከሀሴትና ፍቅር ሊለያየን ሀይል አለው። በውስጥ ያለ የጸጸት፣ የጉድለት ስሜት፣ ብቸኝነት፣ ሀፍረት ወይም ምሬት ካለ፣ ውጫዊው ሕይወታችን ያመረ ቢሆንም እንኳ፣ ሰውም ጥሩ ሕይወት አላቸው ብሎ ቢያስበን፣ እኛ ግን ሕይወት ጨልማብን እንኖራለን። በውስጣችን ሰላም እንዲወርድ በሩን እንክፈት። በሰላምና በደስታ መኖር የምንችለው ውስጣችን ሲፈወስ መሆኑን ተረድተን፣ ውስጣችንን ማደሱ ላይ እናተኩር።

ወደፈጠረን፣ እግዚአብሔር መዞር ዋነኛ ብልሀት ነው። በአለም ዋነኛ ሀብታም በሚባሉ አገሮች፣ ብዙዎቻችን እየኖርን አለን፤ አብዛኛው የዓለም ሰው፣ እነሱ ምን ችግር አለባቸው ብሎ ሊያስብም ይችላል። እዚሁ መጥተን እንዳየነው፣ ያማረው ፎቅ እና ወይ ጉድ! የሚያስብለው ልብስ፣ እውነተኛ ደስታን አልሰጠንም። ውስጣችን የተጨነቀብን ብዙዎች አለን። ለስጋ አስፈላጊው ሁሉ ሞልቶ ሳለ፣ በጭንቀትና በባዶነት ስሜት መሞላት ደግሞ ከሁሉም የከፋ ነው፤ "ከዚህ በላይ የት ልሂድ" የሚያስብል የባዶነት ስሜትን ይለቃልና። ሰውን ባየንበት መንገድ፣ እግዚአብሔርን ገምተን ጀርባችንን አንስጠው። ወደ እሱ ዞረን እንጥራው። ልባችንን ከፍተን፣ "አለህ ወይ? ምራኝ፤ ማንነትህን አሳየኝ ወዳንተ የምቀርብበትን መንገድ አሳየኝ" እንበለው። እሱ ያለንበትን እና የገጠመንን ፈተና፣ ከአእምሮ





በላይ የሆነብንን ሸክም ይረዳል፤ ልምዳችንን እና እውቀታችንን ተጠቅመን ልናስወግደው ያልቻልነውን ችግር ይረዳል። "በውስጤ ያለ የውጥረት፣ የባዶነት ስሜትን አስወግደህ ሰላምና ደስታና ዕረፍት ሙላኝ፣ ከባድ ሸክም የሆነብኝን የሀፍረት ስሜት አስወግድልኝ፣ ሕይወቴ ትርጉም ያላት እንድትሆን እርዳኝ፣ እንበለው። የፈጠረን እሱ ነውና፣ እጁን ይዘረጋልናል፤ እኛም ሆንን ቤተሰባችን፣ ያማረና የለመለመ ሕይወት እንድንኖር ይረዳናል።

# ምዕራፍ አስር

## ወላጆችን እና ልጆችን ለመርዳት የማኅበረሰቡ ሚና

የዚህች መጽሐፍ ዋነኛ ዓላማ የተጠቃለለው በዚች ምዕራፍ ውስጥ ነው:: ይህች መጽሐፍ ለተደቀኑ ችግሮች ሁሉ መልስ ትሆናለች ተብላ አልተጻፈችም፤ ለተለያዩ፣ ለሌሎች አዳዲስ ሀሳቦችና ዝግጅቶች ድልድይ እንድትሆን እንጂ:: በማህበረሰባችን ውስጥ ቤተሰቦቻችንን ለማነጽ የሚረዳ በቂ የሆነ ምንጭ/ዝግጅት/ የለንም፤ ልጆቻችንን የሚረዳ በቂ የሆነ የድርጊት ፕሮግራምም የለንም:: የልጅና የወላጅ ብሎም የቤተሰብና የማህበረሰብን ግንኙነት በጥሩ መሰረት ላይ የማኖርን ኀላፊነት፣ ቀላል አድርገን የምናየው አይደለም። ይህ ጉዳይ ስለ ወላጅና ልጅ ብቻ አይደለም:: ይህ ጉዳይ፣ ስለ ትውልድ ፣ ስለ ህዝባችን የወደፊት እጣ ነው:: ወደፊት ከ30-40 አመት በኋላ ወደ ኋላ መለስ ብለን ብንመለከት፣ዛሬ በማህበረሰባችን ውስጥ ብዙ የምንንቀሳቀስ ሰዎች በቦታችን አንኖርም፤ አላፊዎች ነንና::

አንድ ትውልድ ከሁሉ በፊት ማንነቱ የሚቀረጸው በቤተሰቡ ውስጥ ነው:: ዛሬ የሚያስፈልጋቸውን ፍቅር፣ ድጋፍና እርዳታ ያገኙ ልጆች፣ ነገ ትልቅ ቦታ የሚደርሱ ህዝባቸውን፣ አገራቸውን በትልቁ የሚለውጥ ቁም ነገር የሚወጣቸው ጤነኛ ትውልድ ይሆናሉ፤ አስተማሪ፣ ዶክተር፣ የታሪክ ሊቅ ሆነው ምኞታችንን፣ ከግቡ የሚያደርሱ፣ ህዝብና አገራችንን ቀና የሚያደርግ ነገር የሚያበረክቱ ሰዎች ይሆናሉ:: ዛሬ በተለያየ ምክንያት የሚያስፈልጋቸውን እንክብካቤ፣ ቁም ነገር ሳያገኙ ያደጉ ልጆች ግን እንኳን ለአገር ሊሆኑ ለራሳቸውም፣ የማይፈይዱ ይሆናሉ::





በተገቢው ካሰብንበትና ከወጠንን ቤተሰብንና ልጆችን መርጃ ብዙ መንገዶች አሉ፤ የሚያስፈልገውን እርምጃ ከወሰድን፣ የብዙ ልጆችን የወደፊት ሕይወት በአዎንታዊ መንገድ ለመለወጥ እንችላለን::
ቤተሰብና ልጆችን ለመርዳት መውሰድ ስለምንችላቸው እርምጃዎች እንቃኝ:: ከሁሉ በፊት ያለውን ችግር ግልጽ አድርገን እናስቀምጥ፤ ወላጆች እየተጋፈጡት ያሉትን ውስብስብ፣ ልጆቻችን እያጋጠማቸው ስላለው ፈተና፣ በቤተሰብና በልጅ መሀል እየተፈጠሩ ያሉትን ችግሮች፣ እንጋፈጣቸው:: ፍሬው ጭንቀትን በሚያፈራ "ውጥረትን በሚለቅ" መልክ ሳይሆን "ምን ምን ማድረግ እንችላለን" በሚል፣ መላ ላይ ባተኮረ መልክ፣ እንወያየው::

ችግራችንን በግልጽ መወያየቱ ምን ጥቅም አለው?

- ወላጆች ከችግራቸው ጋር፣ ብቻቸውን ታፍነው እንዳይቀሩ ያደርጋል:: በማህበረሰባችን፣ ብዙውን ጊዜ፣ ቤተሰብ ውስጥ ያለ ችግር በግልጽ አይወራም:: ብዙ ቤተሰቦች የብቸኝነት፣ " ችግሩ ያለው እኔ ቤት ብቻ ነው" የሚል የውጥረት ስሜት፣ እና ኀፍረት ሊሰማቸው ይችላል፤ ስላሉት ችግሮች በግልጽ መወያየታችን፣ እነዚህ ቤተሰቦች ብቻቸውን እንደሆኑ ተሰምቷቸው እንዳይቀሩ ያደርጋል::
- ችግሩን በግልጽ መወያየታችን፣ የዚህን ጉዳይ አጣዳፊነት ማኅበረሰባችን እንዲገነዘብ ይረዳል:: እጃችንን ዘርግተን ቁምነገር መሥራት እንዳለብን፣ የበለጠ እንድንረዳም ያበረክታል::
- መላ እንዲመጣም አስተዋጽኦ ያደርጋል:: ልጆችና ወላጆችን በተለያየ መንገድ ለመርዳት፣ ፍላጎቱ፣ ብቃቱ፣ ችሎታው ያላቸው፣ የተለያየ የዕርዳታ ጥሪ ያላቸው፣ በተለያየ ሙያ የሰለጠኑ፣ ብዙ ሰዎች አሉ፤ እነዚህ ሰዎች ወደፊት እንዲመጡ ያበረክታል::

ወላጆችና ልጆችን መርዳትን በተመለከተ፣ የሚከተሉትን ነጥቦች እንቃኝ

## 1) <u>ወላጆችን ለመርዳት</u>

ወላጆችን ልንደርስበት የምንችላቸው ሶስት ዋና ዋና መንገዶች

- *ልጅን በጥሩ ሁኔታ ስለማሳደግ ጠቃሚ ምክር/ ግንዛቤን ማስተላለፍ*
- *ወላጆች ኑሮዋቸው እንዲስተካከል፣ በአዲስ ህብረተሰብ፣ እንዲቋቋሙ፤ የሚረዳቸውን ድጋፍና ግንዛቤን መስጠት*
- *ችግርን በአዎንታዊ መንገድ ስለመፍታት፤ ፈተናን ለመቋቋም ስለሚያስችሉ መንገዶች አስፈላጊውን ምሪት ለወላጆች መስጠት::*

### 1.1<u>ስለ ልጅ አስተዳደግ ጠቃሚ ግንዛቤን መስጠት</u>

ወላጆችን ለመርዳት፣ ልጆች ችግር ውስጥ እስኪገቡ ወይም ወላጆች ችግር እስኪያጋጥማቸው፣ መጠበቅ የለብንም:: ወላጆች በልጅ አስተዳደግ ላይ ከወዲሁ ትክክለኛውን ምርጫ እንዲመርጡ የሚረዳቸውን ነገር ካበረከትን፣ የችግሩ ውስብስብነት በጣም ይቀንሳል:: ልጆቻቸውን ከልብ የሚወዱና የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ሊሰጡ የተዘጋጁ፣ ጠቃሚ ግንዛቤ ቢያገኙ፣ ብዙ ገንቢ ስራ መሥራትን የሚችሉ ብዙ ወላጆች አሉ:: ያበበ ነገር ለማፍራት እንዲችሉ፣እነዚህን ወላጆች ትክክለኛ ግንዛቤ እንደሚያስፈልጋቸው ተረድተን፣ ያለንን ጠቃሚ ምክር እናስተላልፍላቸው::

አዎንታዊ በሆነ መልክ ልጅን ለማሳደግ፣ ምን መንገድ ቢከተሉ እንደሚጠቅም የተረዳነውን እናካፍላቸው:: ምሳሌ ብንሰጥ፤ ከልጅ ጋር ትስስርን ለማዳበር ምን እንደሚረዳ፣ ልጅ ወደ ትልቅ ቦታ እንዲዘረጋ፣ ትልቅ ቦታ እንዲደርስ ለመርዳት ወላጅ ምን ምን ማድረግ እንደሚችል፣ ልጅ ራሱን እንዲችል አድርጎ ስለማሳደግ





ጠቃሚነት ወዘተ-- ለወላጆች የሚጠቅም እውቀትን መስጠቱ አስፈላጊ ነው:: ልጅን ስለተለያዩ ነገሮች በግልጽ ስለማውራት አስፈላጊነት፣ ሚዛን ባለው መንገድ ሥነ ሥነ ሥርዐት ስለማስያዝ ወዘተ-- ወላጆችን እናስተምር:: ልጅ ከትምህርት ቤት/ጓደኛ ዘንድ የሚመጣበትን ግፊት እንዲቋቋም አድርጎ ስለማሳደግ፣ ልጅ ራሱን እንዲያከብር በማንነቱ እንዲኮራ አድርጎ ስለማሳደግ ጠቃሚነት፣ እነዚህ እና የመሳሰሉ ረጂ አስተዳደግ ዘዴዎችን ለወላጆች ማስተላለፉ ትልቅ ጥቅም አለው::

በዚህ ጉዳይ ላይ በተለይ በትልቁ ሊያበረክቱ የሚችሉ በውጭ አገር ልጆችን ያሳደጉ እና በማሳደግ ላይ ያሉ ወላጆች ናቸው:: እነዚህ ወላጆች አልፈውበት አይተውታል፤ ወይም እያለፉበት ነው:: ወላጅ የሚያልፍበት ፈተና ይገባቸዋል:: በዛ ህብረተሰብ ባህል ውስጥ ልጅን ሲያሳድጉ፣ ልጅ ላይ ሊመጣ ስለሚችል ፈተናም ተረድተዋል:: ምን አይነት የአስተዳደግ ዘዴ እንደሚረዳ እና ምን እንደሚጎዳ ከስህተታቸውም ሆነ ከልምዳቸው ተምረውታል:: እነዚህ ወላጆች አዳዲስ ወላጆችን በትልቁ የሚረዳ ግንዛቤን በተለያየ መልክ ማስተላለፍ ይችላሉ::

### <u>1.2 በኑሮ እንዲቋቋሙ መርዳት</u>

በውጭ አገር ልጆቻቸውን የሚያሳድጉ ወላጆች፣ ብቁ ከመሆን የሚያግዳቸው፣ የግንዛቤ እጥረት ብቻ አይደለም:: በአዲስ አገር ውስጥ ሲኖሩ፣ ሊያጋጥሟቸው የሚችሉት የተለያዩ የኑሮ አቀባዎች፣ የወላጆችን እጅ ሊያስሩ የሚችሉ ናቸው:: ስራ አጥነት፣ የመኖርያ ፍቃድ ጋር የተያያዘ ችግር፣ የጤና የኢንሹራንስ ችግር፣ አዲስ ባህል ውስጥ ኑሮን የመመስረት ውጥረት፣ የመሳሰሉ ወላጆችን የሚፈትኑ ውስብስቦች አሉ:: ይህ በኑሮዋቸው ውስጥ የሚያልፉበት ውጥረት፣ እነዚህ ወላጆች ለልጆቻቸው ያሰቡትን እንዳያደርጉ፣ እንቅፋት ሊሆንባቸው ይችላል፤

በማህበረሰባችን ውስጥ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ እውቀትን ያካበትን፣ የተለያየ ግንዛቤ ያለን ብዙ ሰዎች አለን:: ባለን ጥሪ፣ ግንዛቤ፣ ችሎታ እነዚህን ወላጆች እንድረስ። በዚህ አገር ውስጥ እንዲቋቋሙ፣ ኑሮዋቸው እንዲስተካከል የሚረዳቸውን ሁሉ እናበርክትላቸው:: እኛ ግንዛቤያችንን ለማስተላለፍ፣ እርዳታ ለማቀበል ፍቃደኛ እንሁን እንጂ፣ ተሞክሯችንን ከወላጆች ቤት ልናስገባ የምንችልባቸው ብዙ መንገዶች አሉ፤

መልእክታችንን በምን መንገድ ልናስተላልፍ እንችላለን?

- ድረ ገጽ መክፈት እንችላለን፤ በዚህ ጉዳይ ከተለያዩ ባለሙያዎች አስፈላጊ እውቀትን ሰብስበን፤ ስራ፣ ኢንሹራንስ፣ የወረቀት ችግር ፣መኖርያ ቤት፣ የሞያ ስልጠና እና ሌሎችም አስፈላጊ አርእስቶችን በተመለከተ፣ ወላጆችን ረጂ ግንዛቤ በድረገጽ (ዌብ ሳይት) ማስተላለፍ ጥሩ መንገድ ነው።
- ወላጆችን ሰብስበን ትምህርት መስጠት፤ በአንድ ጉዳይ ላይ አተኩረንም ሆነ በተለያዩ ጉዳዮች፣ ውይይት ማዘጋጀት ሌላ ረጂ መንገድ ነው::
- መልእክታችንን በመገናኛ ጣቢያ ማስተላለፍ፤ በቪዲዮ ትምህርታዊ መልእክትን ማዘጋጀት እንችላለን
- በተወሰነ ጉዳይ ላይ ዕውቀቱ ያላቸውን ሰዎች ጋብዘን ወላጆች በሚገኙበት፣ ግንዛቤያቸውን እንዲያስተላልፉ ማበረታታት፤
- ወላጆች፣ በብዛት የሚገኙባቸው ቦታዎች ሄደን፣ ጠቃሚ ግንዛቤያችንን ማካፈል፤ እዚያ ላሉ መሪዎች ስለ ሀሳባችን ነግረን፣ ለወላጅ ትምህርታዊ ሴሚናር መስጠት፤ ወይም ጠቃሚ መልእክት ያለው ጽሑፍ መበተን እንችላለን:: እኛው ራሳችን ባናደርገው እንኳ፣ ረጂ ዕውቀታችንን በመሪዎቹ በኩል፣ ወደ ህዝብ ልናስተላልፍ እንችላለን።





## 1.3 ችግርን፣ በአዎንታዊ መልኩ መቋቋም

ለልጆቻቸው ሊሰጉ የሚችሉትን ያህል እንዳይሰጉ፣ ለወላጆች እክል የሚሆንባቸው ሌላኛው አቀባ፣ ቤተሰብ ውስጥ የሚደርስ ችግር/ፈተና ነው::

ልጆቻቸውን አስመልክቶ፣ ቤተሰቦቻችን የተለያዩ ችግሮች ሊያጋጥማቸው ይችላል፤ ለምሳሌ ያህል ብንጠቅስ፣ ልጆቻቸው በጤና ችግር፣ ከትምህርት ጋር በተያያዘ ችግር፣ የአእምሮ ጭንቀት፣ ሱስ ወዘተ-- ሊያልፉ ይችላሉ:: አንድ ልጅ፣ ችግር ውስጥ ሲገባ፣ የችግሩ ውላጅ የሆኑ የተለያዩ ፈተናዎች ሊመጡም ይችላሉ:: ልጅ ሲታመም ወይ ልጅ ችግር ውስጥ ሲወድቅ፣ በቤተሰብ መኻል መከፋፈልና ጥል ሊመጣ፣ የወላጅ ጤና ሊናጋ፣ ሌሎች ወንድምና እህቶች የችግሩ ገፈት ቀማሾች ሊሆኑም ይችላል:: ችግርን ለመቋቋም፣ ለመወጣት እንዲችሉ የሚረዳቸውን፣ ምሪትና እርዳታ ለወላጆች ማቅረባችን በጣም አስፈላጊ እርምጃ ነው::

በችግር ውስጥ እያለፉ ያሉን ቤተሰቦች ለመርዳት ስለምንችልባቸው ዋና መንገዶችን እንቃኝ፤

- ✓ ልጅ ስለሚያልፍበት ችግር ምንነት ወላጆች በጥልቀት እንዲያውቁ መንገድ ማዘጋጀት::
- ✓ ልጅ የሚያልፍበትን ችግር ለመቋቋም፣ በአሸነፊነት ለመወጣት ወላጅ ምን እርምጃ መውሰድ እንደሚኖርበት፤
- ✓ ልጆቻቸውን በበለጠ ለመርዳት የሚያስችሏቸውን፣ በማህበረሰቡ (አካባቢያቸው) ስላሉ የእርዳታ ምንጮች (resources)፤ ምሪት በመስጠት ነው

ስለ እነዚህ ሦስት ነጥቦች ከሥር እንመልከት:: ልጅ በችግር ውስጥ ሲያልፍ፣ ወላጅ ስለ ችግሩ በጥልቀት መረዳት አለበት፤ ስለ ችግሩ ምንነት ካላወቀ፣ የቱንም ያህል ልጁን ቢወድና ሊረዳ ቢፈልግ፣ በምን መንገድ ሊረዳ እንደሚችል ግንዛቤ አይኖረውም:: በተለይ በምእራብያውያን አገሮች፣ ብዙ ቤተሰብን ረጂ ጹሑፎችና ምሪቶች ቢኖሩም፣ በቋንቋ ችግር ምክንያት እና እነዚህ ጽሁፎች እንዳሉም ባለመረዳት፣ ብዙ ወላጅ ሊያነብ እድል አይኖረውም። ከዛም በተረፈ፣ ብዙዎቹ ጽሁፎች የተዘጋጁት ለተለየ ባህል ነው:: በቋንቋውና ሊገባው በሚችለው መንገድ ቢጻፍ ግን፣ የበለጠ ወላጅ ለማንበብ ይበረታታል፤ ግንዛቤውንም ለሌላ ወላጅ ለማስተላለፍ እድል ይኖረዋል:: በዚህ ጉዳይ ላይ፣ ጠቃሚ ግንዛቤያችንን እናስተላልፍ:: ስለተለያዩ የጤና፣ የአእምሮ ችግሮች ገልጸን፣ እንጻፍ፤ ልጅ ሊገባባቸው ስለሚችሉ ስለተለያዩ ሱሶችና ስላላቸው ተጽእኖ፣ለወላጅ በሚገባው መልክ አብራርተን እናዘጋጅ:: ባጠቃላይ፣ ስለሌሎችም ልጅን ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ ችግሮች ምንነት፣ ቤተሰቦች በጥልቀት እንዲረዱ እንትጋ::

ችግሩን ለመወጣት፣ ለመቋቋም ስለሚረዱ እርምጃዎች፣ ተንትነን እንጻፍ:: ወላጅ ከልጅ ጋር ባለው ግንኙነት፣ ምን ችግሩን እንደሚያብስ፣ ምን ወደ መላ መንገድ እንደሚመራ፣ ለወላጆች በሚገባ መልክ ግንዛቤን እንስጥ::

በችግር ጊዜ እርዳታ፣ ድጋፍ ሊሰጡ ስለሚችሉ፤ በማህበረሰቡ ውስጥ ስላሉ የእርዳታ ምንጮች ግንዛቤ ማግኘቱ፣ ወላጅን በትልቁ ሊረዳ ይችላል፤ እነዚህ የእርዳታ ቦታዎች፣ ከወላጅ አቅም ውጭ የሆኑ ብዙ ችግሮችን፣ ሊፈቱ/ሊያቃልሉ ይችላሉና። ስለ እነዚህ የእርዳታ ምንጮች ለቤተሰቦች እናስታውቅ::

- ✓ ልጆቻቸውን ለመርዳት የሚያስችል የገንዘብ እርዳታ
- ✓ (grant) እንዴት ሊያገኙ እንደሚችሉ፣
- ✓ በአካባቢያቸው ስላሉ የህክምና፣ ቴራፒ እርዳታ ቦታዎች፣





- ✓ እርዳታ፣ ጠቃሚ ግንዛቤን ለማግኘት ሊደውሉባቸው ስለሚችሉባቸው 1-800 የእርዳታ መስመሮች--ወዘተ

ወላጅ የሚያጋጥመው ፈተና፣ ከልጅ ጋር በተያያዘ ጉዳይ ብቻ አይደለም፤ በወላጅ ሕይወት ውስጥም፣ የሱስ ችግር፣ ከአይምሮ ጭንቀት ጋ የተያያዘ ፈተና፣ የጤና ችግር ወዘተ-- ሊመጣ ይችላል:: ይህ ፈተና፣ በጤነኛ መንገድ ካልተገታ፣ የብዙ ቅን አሳቢ ወላጆችን አቅም ሊበላ ሀይል አለው:: ስለእነዚህ ችግሮች በግልጽ መወያየት፣ ወላጆች በችግራቸው ብቻቸውን እንዳልሆኑ መልእክት ማስተላለፉ አስፈላጊ ነው:: ከዛም አልፎ፣ ወላጆች ከችግራቸው ነጻ ለመውጣት እንዲችሉ፣ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው፣ በሚኖሩበት አካባቢ ስላሉ የእርዳታ ምንጮች፣ ምሪት ልናቀርብላቸው ይገባል::

ወላጅ የሚያጋጥመው ሌላው ዋነኛው ፈተና፣ የትዳር ችግር ነው:: በባልና ሚስት መሀል ያለ መቃቃር የብዙ ቤተሰብን ሕይወት ያበላሻል፤ ልጆችም፣ የወላጆቻቸው ፈተና፣ የእነሱ ሸክም ይሆናል:: እንደዚህ አይነት መራራ ፍሬዎች በቤተሰብ ውስጥ እንዳይነግሱ፣ ወላጆች ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል:: ትዳርን በተመለከተ፣ ሊኖሩ የሚችሉትን ችግሮች በግልጽ መወያየታችን፣ ጥቅሙ ብዙ ነው:: ትዳርን ለማደስ፣ ጤነኛ ትዳር ለመምራት፣ ወላጆች ምን ምን ማድረግ እንደሚችሉ ጠቃሚ የሆነ ግልጽነትን ያዘለ ትምህርት/ግንዛቤን ልናስተላልፍ ይገባል/እያስተላለፉ ያሉትን ግለሰቦች በጣም ልናበረታታ ይገባል:: በትዳር ውስጥ ችግር ሲፈጠር፣ አንድ ሰው ሊወስዳቸው ስለሚችለው ጎጂ እርምጃዎች፣ ግንዛቤን እንስጥ:: በተቃራኒው፣ ችግርን በተቃና መንገድ ለመፍታት ስለሚረዱ ጠቃሚ ዘዴዎች በግልጽ ተንትነን ማስተማሩ ትልቅ ጠቀሜታ አለው:: ጥሩ የትዳር ትምህርትን እየሰጡ ያሉንም ሰዎች፣ በጥሩ ስራቸው እንዲቀጥሉ ልናበረታታቸው ይገባል:::

ከላይ የተጠቀሱትን ግንዛቤዎች፣ እነዚህንና የመሳሰሉ የእውቀት ምንጮች (Resources) ከላይ እንዳነሳነው፣ በድረ ገጽ ላይ

ማዘጋጀት እንችላለን። በመጽሐፍ ወይም በመጽሔት መልክም ማዘጋጀት እንችላለን። በአካባቢያችን ወላጆች ችግራቸውን በግልጽ የሚወያዩበት የወላጆች ቡድን (support group) ማቋቋም እንችላለን። ለወላጆች ትምህርታዊ ሴሚናር ማዘጋጀት፣ የእምነት ሥፍራዎች ላይ በመሄድ ያለንን ግንዛቤ ማስተላለፍ፣ በአካባቢያችን ባሉ ሌሎች የማህበረሰብ ማእከሎች ሄደን፣ እውቀታችንን ማስተላለፍ እንችላለን:: ከኛም አካባቢ አልፈን በሌላ ስቴት (አካባቢ) የሚገኙ የማህበረሰብ ማእከሎች፣ ለህዝባቸው እንዲያስተላልፉ፣ ግንዛቤያችንን ማካፈል እንችላለን:: እንደ እግር ኳስ ጨዋታ ባለው አመታዊ የህዝባችን ስብስብ ላይ ቲገኝተን በጽሑፍ መልክ መበተን እንችላለን:: የሚያስፈልጋቸውን ምሪትና ግንዛቤ አግኝተው ኑሮዋቸው የተስተካከለው ወላጆች በትልቁ ይጠቀማሉ፤ የነገ ትልቅ ሰውንም በትጋት ያሳድጋሉ።

## 2. ልጆቻችንን መርዳት

ውስጡ የተለወጠና የጠነከረ ሰው የእርሱ በሆነው ቁም ነገርና መልካምነት ታንጾ፣ ሌሎችንም ያንጻል:: ልጆቻችን እንዲሁም ወጣቶቻችን እንዲታደሱ፣ እንዲያብቡ፣ ወደ ተሻለ ግንዛቤ እንዲደርሱ፣ ማህበረሰባችን ትልቅ ነገር ሊያበረክት ይችላል:: ልጆችን ሆነ ወጣቶችን መርዳት የምንችልባቸው መንገዶች ምንድን ናቸው?

- *በተለያየ ችግር ውስጥ እያለፉ ያሉ ልጆችንና ወጣቶችን መድረስ፣ መደገፍ፣ ከችግራቸው ነጻ መውጣት የሚያስችላቸውን መንገዶች ማሳየት፤*
- ***ልጆቻችንን በልበ ሙሉነት ማስታጠቅ፤*** በየእድሜ ደረጃቸው፣ በቤትም ሆነ በውጭ ሊገጥሟቸው የሚችሉትን ፈተናዎች፣ እንዴት ጤናማ በሆነ መንገድ መቋቋም እንደሚችሉ ግንዛቤ መስጠት፤
- ***ልጆቻችን እንዲያብቡ መርዳት፤*** ሊደርሱ የሚችሉበት ቦታ መጥቀው እንዲደርሱ በተለያየ መንገድ መርዳት፣ መደገፍ





ከዚህ በታች ነጥቦቹን ለመቃኘት እንሞክር፤

### 2.1) ልጆችን ሆነ ወጣቶችን ከችግራቸው ነጻ እንዲወጡ መርዳት

የተለያየ ችግር ያጋጠማቸውን ልጆች መርዳት፣ ልጆችን ከፍ ማድረጊያ ዋነኛ መንገድ ነው:: ለቤተሰብ ግንዛቤ መስጠት ልጅን መርጃ ዋነኛ መንገድ ቢሆንም፣ በተለይ በእድሜ ተለቅ ያሉ ልጆችን፣ የሚያጽናና የሚያበረታታና አዲስ መንገድ የሚያሳይ ግንዛቤ ልናስተላልፍላቸውና፣ ድጋፍ ልንሰጣቸው እንችላለን::

በችግር ውስጥ እያለፉ ያሉ ልጆችን መርዳት ስንፈልግ፣ ሁለት ነጥቦችን ልብ እንበል:: ችግር ውስጥ ያሉ ወጣቶች ማለት፣ በውጫዊ ሁኔታ የሚጎዳቸውን ነገር እያደረጉ ያሉ ብቻ ማለት አይደለም፤ በውጭ የተስተካከለ ህይወት እየመሩ፣ በውስጥ ግን በተለያየ ጭንቀት፣ ውጥረት እና ሌላም ከአእምሮ ጋር የተያያዘ ችግር ውስጥ የሚያልፉ ብዙ ልጆች አሉ::

ሌላው ነጥብ ይህ ነው፤ "በጥፋት" ውስጥ እያለፉ ያሉ ወጣቶችን በማስመልከት፣ ብዙ ጊዜ ጉዳዩ፣ በውጭ ተገልጦ ከምናየው "ጥፋት" ብቻ አይደለም:: ከውጫዊ "ጥፋት" ጀርባ፣ ተደብቀው ያሉ፣ ጥፋቱን የሚያነሳሱ መንስኤዎችም ሊኖሩ ይችላሉ:: ምሳሌ ብንወስድ፣ ቤተሰብ ውስጥ ያለ ችግር፣ የጉድለት ስሜት፣ ጭንቀት፣ ጓደኛን ለመምሰል ሙከራ እና የመሳሰሉ ፈተናዎች፣ ከውስጥ ተደብቀው፣ የውጭ ጥፋት ነጸብራቅ ሆነው ይወጣሉ:: የልጆች ወይም የወጣቶች ውጫዊ ሁኔታ "ጥፋት" ብቻ እንዳልሆነ ስንረዳ፣

- እነዚህን ልጆች ሳንዳኝ፣ ሳንፈርድባቸው ለመቅረብ እድል ይኖረናል፤
- በትእግስት ተሞልተን እንድንረዳቸው ጽናቱ ይኖረናል፤

- በምን መንገድ ብንረዳቸው እንደሚጠቅም የበለጠ ግንዛቤም ይኖረናል፤

ልጆችና ወጣቶች በጥፋት ውስጥ ሲያልፉ፣ በቤተሰብ/ማህበረሰብ በኩል ሊገጥማቸው ስለሚችል መገለል፣ ያም በእነርሱ ላይ ስለሚያመጣው አሉታዊ ተጽእኖ በግልጽ እንወያይ:: ልጆች እንዲሁም ወጣቶች አንገት እንዳይደፉ፣ ተስፋ እንዳይቆርጡ እናበረታታቸው::

ባጠቃላይ እነዚህን ልጆች እና ወጣቶች ለመርዳት፣ ችግራቸውን ለመወጣት የሚያስችሏቸውን ጤነኛ መንገዶችን መማራቸው በጣም ይረዳቸዋል፤ ውስጣዊ ችግርን መጋፈጥ፣ ለራስ ህይወት ኀላፊነት መውሰድ፣ ተስፋ አለመቁረጥ፣ ችግርን ገልጦ ማማከር እና የመሳሰሉ፣ ወደ አሸናፊነት መንገድ ስለሚወስዱ ምርጫዎች በዝርዝር እናስተምራቸው፤ ወደ ተስፋ መንገድ እንዲጓዙ የሚረዷቸውን ጽሁፍና ትምህርቶችን እናዘጋጅ። በዚህ ጉዳይ እነዚህን ልጆች ሊደርሱ ከሚችሉ፣ ከተለያዩ ቡድኖች ጋርም አብረን እንስራ።

ወጣቶችን እና ልጆችን በተለያየ ጉዳይ ሊረዷቸው ስለሚችሉ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ስላሉ የእርዳታ ምንጮች፣ ለልጆቻችን ማስተላለፍ፣ አንድ በጣም ጠቃሚ መንገድ ነው። ለምሳሌ የምክር አገልግሎት፣ ቴራፒ፣ እርዳታ ሰጭ ስለሆኑ ቦታዎች ግንዛቤ ለማግኘት፣ ሊደውሉባቸው ስለሚችሉ ቦታዎች፣ መጥቀስ ይቻላል።

## 2.2) ልጆችንና ወጣቶችን ከወዲሁ ማስተማር

ይህ፣ ሌላኛው ልጆችን ልንረዳ የምንችልበት ትልቅ መንገድ ነው:: በዚህ ጊዜ ታዳጊ ልጆች/ወጣቶች፣ በየእድሜ ደረጃቸው የሚያጋጥሟቸው፣ የተለያዩ ፈተናዎች አሉ:: በእኛ ባህል፣ ብዙ ቤተሰብ፣ ስለእነዚ ነገሮች በግልጽ ከልጆቹ ጋር አይወያይም::





ቤተሰብ ውስጥ ይህ ጉዳይ በግልጽ ካልተወራ፣ የኛ ልጆች ከችግሮቹ ጋር የሚጋፈጡት ፊት ለፊታቸው ሲያፈጥባቸው ወይም ከጓደኛ በሚያዩትና በሚሰሙት ብቻ ሊሆን ይችላል:: በማህበረሰባችን ውስጥ፣ ልጆቻችንን አስፈላጊ ግንዛቤ ለማስገኘት የሚያስችል ነገር ቢዘጋጅ ግን፣ ብዙ ልጆች ከአደጋ ሊጠበቁ፣ ባገኙት እውቀታቸው ተመርተው በጎዺ ፋንታ ትክክለኛ ምርጫ ሊመርጡ ይችላሉ:: ለዚህም ስንል፣ ልጆቻችንን በአስፈላጊና ተገቢ እውቀት እናስታጥቅ::

ባሉበት ማህበረሰብና ባህል ውስጥ፣ ሊመጡባቸው ስለሚችሉ ግፊት፣ ጫናዎች (የጓደኛ ግፊት፣ ስለ ትምህርት ቤት ውስጥ ችግር፣የተቃራኒ ጾታ ጉዳይ፣ ስለ ሱስ) ወዘተ በግልጽ እናስተምር:: እነዚን የመሳሰሉ ግፊቶች ሲመጡ፣ በጤነኛ መንገድ እንዲቋቋሙ ስለሚረዷቸው ዘዴዎች፣ በግፊቱ ሳይሸነፉ እንዴት ወደ ድል ሰፈር ሊደርሱ እንደሚችሉ ጠቃሚ ግንዛቤን እንስጥ:: እነዚን፣ ልጆችን የሚረዱ ምክሮችን፣ በተለያዩ መንገዶች ማስተላለፍ እንችላለን::

- ✓ ይህንን መፍትሄ በጽሁፍ ማስፈር እንችላለን:: ልጆች የሚገኙባቸው አካባቢዎች ሄደን፣ ተመክሯችንን ማቀበል፣ ትምህርታዊ ሴሚናር ማዘጋጀት፣ ሌላኛው መንገድ ነው::
- ✓ ልጆቻችንን በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ጥሩ ግንዛቤ የሚሰጥ ድረ ገጽ ማዘጋጀት በጣም የሚረዳ መንገድ ነው:: በእንግሊዘኛ የተጻፉ፣ በተለያየ እድሜ ለሚገኙ ልጆች የተዘጋጁ፣ ጥሩ ትምህርትና ምክር አዘል ድረ ገጾች አሉ:: ከእነዚህ ድረ ገጾች ሁሉን እንወስዳለን ለማለት ሳይሆን፣ ጥሩ ምሪትን ልናገኝባቸው እንችላለን::
- ✓ እኛ በፊት ለፊት ልናገኛቸው የማንችላቸው ብዙ ልጆች ይኖራሉ:: አንድ ጥሩ መንገድ፣ ልጆች የሚመጡባቸው ቦታዎች፣ ሌሎች መልእክታችን እንዲያስተላልፉ፣ ማቀበል ነው። ለምሳሌ አንድ ቤተክርስያን ሄደን " ለልጆች የሚጠቅም ይህ ሀሳብ አለኝ፤ እናንተ አካባቢ የሚመጡ

ልጆችን ይህን ማስተማር ከፈለጋችሁ ይኸውና" ብለን ግንዛቤያችንን በእነሱ በኩል ማስተላለፍ እንችላለን:: መልእክትን ማስተላለፍን በተመለከተ፣ አንድ ልብ ልንለው የሚገባ አስፈላጊ ነጥብ አለ:: ልጆችን ለመሳብ እንዲያስችለን፣ ከምክራችንም በላይ አቀራረባችን ትልቅ ቦታ አለው:: የቱንም ያህል ትልቅ እውቀት ቢኖረን፣ አቀራረባችን ልጅን በሚሰብ መልክ ካልሆነ፣ ግንዛቤ/ምክራችን ልጆች/ ወጣቶች ልብ ሊደርስ አይችልም። አቀራረባችን ልጆችን በሚስብ መልክ እንዲሆን ምን ማድረግ እንችላለን?

በእዚህ ባህል ያደጉ ልጆች፤ ወጣቶች፣ በዚህ ጉዳይ ላይ በብዙ መንገድ ሊረዱን ይችላሉ:: ከተለምዶዋቸው እኛ የማናውቀውን ያውቃሉና፣ በተለያየ መንገድ፣ ረጂ ሀሳብ ይሰጡናል፤ ለወጣቶች እና ለልጆች አመቺ አድርገን እንዴት እንደምንጽፍ ሊያስተምሩን ይችላሉ። ሴሚናር ለማዘጋጀት ብንፈልግ እንዴት አድርገን ወጣቶችን መሳብ እንደምንችል ጥሩ ግንዛቤንም ይሰጡናል:: ከዚህም በተጨማሪ ልጆችንና መድረስ ስለምንችልባቸው፣ ስለተለያዩ ረጂ መንገዶች ሊያሳውቁን ይችላሉ::

## 2.3) ልጆችና ወጣቶቻችን እንዲመጥቁ መርዳት

ልጆችና ወጣቶቻችን መካከለኛ ከሆነ ማንነት አልፈው፣ በራሳቸው በሆነው ተፈጥሮዋዊ ስጦታ እንዲመጥቁ፣ ወደ ተሻለ አዲስ ቦታ እንዲሻገሩ ድልድይ መሆን፣ ሌላው ልጆችን መርጃ ትልቅ መንገድ ነው:: ትንሽ ዕገዛ ቢያገኙ፣ ሊመጥቁ ሊመነጠቁ፣ የሚችሉ ብዙ ልጆች አሉ:: ለዚህ ቅዱስ አላማ፣ በተለያየ መልክ እርዳታችንን ማቀበል እንችላለን::

ሀ) ትምህርት የብዙ ልጆችና ወጣቶችን የወደፊት እጣ ፈንታ የሚለውጥ፣ እንዲያብቡ፣ እንዲለመልሙ የሚረዳ መሰላል ነው:: መማር እየፈለጉ፣ ባጋጠማቸው እክል ምክንያት ያልተማሩ ወጣቶች፣ የቱንም ያህል ትልቅ ራእይ እና ችሎታ ውስጣቸው ቢቀመጥ ያለሙት ቦታ እንዳይደርሱ ሊታቀቡ ይችላሉ:: እድል ያገኙ ልጆች ግን፣ ብዙ በር ይከፈትላቸዋልስለ ኮሌጆች፣ ስለተለያዩ የእውቀት መስኮች ጥሩ ግንዛቤ ያለን፣ ብዙ ሰዎች አለን:: በዩኒቨርሲቲ እያስተማርን ያለን ብዙ ኢትዮጵያውያን አለን:: አገራችን ሄደን ለማስተማር ሁኔታ ባይመቻችልን እንኳ፣ በአካባቢያችን ያሉ ወጣቶቻችን ትምህርት ቤት የመሄድ እድሉ እንዲኖራቸው፣ በምናውቀው መንገድ መርዳት እንችላለን፤ ይህም የተቀደሰ አላማ ነው፤ ያ ማለት አገራችንን፣ ህዝባችንን መርዳት ነውና::

ትምህርትን በተመለከተ ልጆች/ወጣቶችን እንዴት ልንረዳ እንችላለን?

- ✓ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ያሉ ልጆችንና፣ ከአገር ቤት የመጡ ስለዚህ አገር ትምህርት ቤት አሰራር የማያውቁ ወጣቶችን ሰብስበን ለኮሌጅ እንዴት ሊዘጋጁ እንደሚችሉ ግንዛቤን እንስጥ:: በኮሌጅ ውስጥ ሊያጠኗቸው ስለሚችሏቸው ስለተለያዩ የእውቀት መስኮች (majors)፣ ትምህርት ሲጨርሱ ስለሚከፈቱላቸው አዳዲስ እድሎች፣ ግንዛቤ በመስጠት እናበረታታቸው፤
- ✓ ትምህርትን በተመለከተ፣ የገንዘብ እርዳታ (financial aid)፣ ነጻ የትምህርት ዕድል (ስኮላርሺፕ) ለማግኘት ምን ማድረግ እንዳለባቸው ፣ ግንዛቤን እንስጥ፤
- ✓ በተለይ ትላልቅ ከተማዎች ያሉ፣ ትምህርት ቤት መሄድ መማር እየፈለጉ የሚኖሩበት አካባቢ ለትምህርት ምቹ ስላልሆነ እና ሌላ የት ሊሄዱ እንደሚችሉ ባለመረዳት፣ የማይፈልጉትን ትናንሽ ስራ በመስራት ተወስነው ያሉ ከአገር ቤት የመጡ ብዙ ወጣቶች አሉ:: ጥሩ ኮሌጅ ያለበት አካባቢ የምንኖር ኢትዮጵያውያን፣ ሄደን ትላልቅ ከተማ ለሚኖሩ ልጆች/ወጣቶች፣ ስላለንበት አካባቢ፣ ትምህርት ቤት

እንንገራቸው፤ ትምህርታዊ ሴሚናር እንስጥ፤ ቦታውን መጥተው እንዲያዩትም መንገድ እንፍጠርላቸው::

- ✓ ምሳሌ ብንወስድ፣ ትላልቅ ከተማ ውስጥ በአመት አንድ ጊዜ የሚካሄድ ትምህርትን ተያይዞ የተዘጋጀ አንድ ሴሚናር ቢኖረን፣ ብዙ ወጣቶችን መሳብ፣ ጥያቄያቸውን መመለስ እንችላለን:: ከትምህርት ቤት ጋር ተያይዞ ያሉ የተለያዩ ጉዳዮችን አንስተን እየተወያየን፣ አስፈላጊ ግንዛቤ ለልጆችና ወጣቶች ማቀበል እንችላለን::
- ✓ ለሁሉ ወጣት ምርጫው፣ አራት አመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የኮሌጅ ትምህርት ላይሆን ይችላል:: በስድስት ወር፣ አንድ አመት፣ ሁለት አመት ትምህርት የሚገኙ፣ ብዙ የሞያ ስልጠናዎች አሉ፤ ስለእነዚህ የሞያ ስልጠናዎችና፣ እንዴት ሊያገኟቸው እንደሚችሉ፣ ግንዛቤን ማስተላለፍ እንችላለን::

ለ) ልጆችን/ወጣቶቻችን ወደ ላይ እንዲመጥቁ የሚረዳቸው ሌላው ነገር የአስተሳሰባቸው መታደስ ነው:: ግንዛቤያቸው የጠበበ ልጆች/ወጣቶች፣ የቱንም ያህል ትልቅ ቦታ ለመድረስ ችሎታና እድሉ ቢኖራቸው እርምጃቸው ግን ያጠረ ይሆናል፤ የሰው ልጅ እርምጃው የሚመራው በአስተሳሰቡ ነውና:: በአዳዲስ አዳሽ ግንዛቤ እንዲሞሉ፣ ነገሮችን በአዲስ መንገድ እንዲመለከቱ መንገዱ ከተጠረገላቸው ግን፣ የነገ መሪዎችና ታሪክ ለዋጮች ብቅ ብቅ ማለት ይጀምራሉ፤ በውስጣቸው በተሞላው አዲሱ ግንዛቤ ተመርተው፣ ከራሳቸው አልፈው ህዝብን የሚደርስ ነገር ለማውጣት ይነሳሳሉ::

የተለያየ አዳሽ እውቀት ያለን፣ ልጆቻችን አስተሳሰባቸው እንዲታደስ በትልቁ ልናበረክት የምንችል ብዙ ሰዎች አለን። በእድሜያችን ክልል ከሚገኙ ሰዎች ጋር ብቻ ጊዜያችንን ማሳለፍ አቁመን፣ የነገን ተረካቢ ትውልድ ብናድስ፣ ለህዝባችን ትልቅ ነገር እናበረክታለን:: ወጣት አስተሳሰቡ





እንዲታደስ እንርዳ ብለን ስናስብ፣ አንድ አስፈላጊ ነጥብ ልብ ልንል ይገባል፤

ወጣትን በግንዛቤ እንዲለመልም መርዳት ማለት፣ እንደ እኛ የሚራመድ ፣ ልክ እንደ እኛ የሚያስብ፣ ሌላ ሰው ለመፍጠር መሞከር ማለት አይደለም:: እንደ እኛ እንዲያስቡ፣ እኛ የምናየውን እንዲያዩ አድረገን ልንቀርጻቸው ከፈለግን፣ ወጣቶች ከወዲሁ ገብቷቸው ይሸሻሉ፤ እነርሱ ያሉበት ጊዜ፣ ልምምዳቸውና ባህላቸው የተለየ ነውና። ወጣቱን ማነጽ ማለት እንዳይለመልም፣ በሮ እንዳይወጣ ማነቆ የሆኑበት እስራቶች ምን እንደሆኑ ተረድተን፣ ከዛ እንዲላቀቅ መርዳት፣ ስላለው እምቅ ሀይል (ፖተንሺያል) እንዲገነዘብ መርዳት፣ በውስጡ ያለው ሊወጣ ያለው እምቅ ሀይል ፈክቶ እንዲወጣ ድጋፍ መሆን ማለት ነው:: በዚህ መንገድ ወይም በዚያ መንገድ ሁኑ ሳንላቸው ደጋፊ እጃችንን ካቀበልናቸው፣ ወጣቶች በራሳቸው መንገድ ፈክተው ይወጣሉ፤ሌላንም ያፈካሉ፤ውስጡ የበራ ሰው የሚያፈልቀው ብርሀንን ነውና::

☞ የወጣቶችን ግንዛቤ የምናለመልምባቸው የተለያዩ መንገዶችን እንቃኝ::

- ✓ ውስን አስተሳሰብ የወጣትን እርምጃ ያሳጥራል:: ውስን አስተሳሰብን ከወጣቶቻችን ለማስወገድ ጥረት ልናደርግ ይገባል:: ትልቅ ህልም ስለማለም፣ እኔ ከማንም አላንስም ብሎ ስለ መወሰን፣ ተስፋ ሳይቆርጡ ስለመጓዝ፣ ሌሎችም ከፍ ወዳለ ቦታ ወጣቶች እንዲመለከቱ የሚረዷቸውን ግንዛቤዎች እንስጥ። በአለማችን ታሪክ ውስጥ በተለያየ መስክ ስለመጠቁ፣ ህልማቸውን እውን ስላደረጉ፣ ለውጥ ስላመጡ፣ ለየት ብለው ስለወጡ ስለተለያዩ ሰዎች ታሪክ ለልጆች፣ለወጣቶች እናቅርብ:: እንዲህ አይነት እውነት ውስጣቸውን ሲዘልቅ፣ ልጆቻችን ወደ

ትልቅ ቦታ ያነጣጥራሉና፤ሳይገቱ ያለሙት ቦታ ተራምደው ይደርሳሉና።

- ✓ ጠባብ አስተሳሰብ ያላቸው ልጆች ለጠባብ ነገር ኖረው ያልፋሉ።ጠባብ አመለካከትን ከልጆች ከወጣቶቻችን ለማስወገድ ጠንክረን ልንሰራ ይገባል፤ ሌላው ያደረገውን በጭፍን በመከተል ፈንታ የራስን ልዩ መንገድ ስለመከተል፣ ከቁሳቁስ አልፎ ስለ ማሰብ አስፈላጊነት፣ አላማና ራእይ ያለው ህይወት ስለመኖር፣ "ስለራስ ብቻ በማሰብ ፋንታ ለህዝብ ስለማሰብ አስፈላጊነት፣ ለወጣቶቻችን ግንዛቤን እንስጥ። የመገናኛ ብዙኀንና የከበባቸው ጓደኛ ከሚነግራቸው መልእክት ሰፋ ባለ ሁኔታ እንዲያዩ የሚረዳቸው መልእክት እናስተላልፍ። እውነተኛ የወንድነት መለኪያ፣ የሴትነት መለኪያ ምን እንደሆነ፤ለልጆቻችን/ለወጣቶቻችን አዳዲስ ግንዛቤን እንስጥ።
- ✓ ታሪክን ፣ምንጭን አለማወቅ፣ በራስ ማፈር፣ ትልቅ ራእይ የተሰነቀባቸውን የብዙ ወጣቶች አንገት አስደፍቶ ሊያስቀር ሀይል አለው። ይህ የአእምሮ እስራት ውስጣቸውን ከሰረጸ፣ የወጣቶቻችን ብቸኛ ህልማቸው፣ ሌላን መምሰል፣ ከራስ መሸሽና ደንዝዞ መቅረት ብቻ ይሆናል። ራስን፣ ባህልን ፣ ምንጭን ፣ ስለ ማክበር አስፈላጊነት እናስተምር፤በራሳቸው፣ በባህላቸው፣ በህዝባቸው እንዲኮሩ፣ ቀና እንዲሉ የሚረዳቸውን ግንዛቤ እናቅርብላቸው።

ለልጆች፣ ለወጣቶች አዳዲስ ግንዛቤን ለማስተላለፍ የተለያየን ሰዎች፣ እንደየችሎታችን የተለያዩ አርእስቶች ላይ ልናተኩር እንችላለን።"የልጆች አስተሳሰብ እንዲታደስ ይረዳል" ብለን፣ በምናስበው አርእስት ላይ ግንዛቤያችንን ማስተላለፍ እንችላለን። ልጆችን የሚያስደስት የስፖርት፣ የጥበብ፣ ...ወዘተ ስብሰባ





አዘጋጅቶ ያንን እድል ተጠቅሞ አነቃቂ ዕውቀትን ማካፈል፣ በጽሁፍ ማዘጋጀት፣እንዲሁም በፌስ ቡክ መልቀቅ ይቻላል።

ልጆች ወጣቶችን ልንደርስበት የምንችልበት ሌላው ዋናው መንገድ፤ ራእይ ያላቸው፣ ሌላን ለመድረስ ፍላጎቱ ያላቸው ልጆች/ወጣቶች ወጥተው ሌላን ወጣቶች እንዲደርሱ ድልድይ በመሆን ነው። ውስጣቸው በአዳዲስ ግንዛቤ የበራ እነዚህ ልጆች፣ ብዙ ወጣቶችን በሚያነቃ፣ አዲስ ግንዛቤ በሚሰጥ መልክ፣ መልእክታቸውን ማስተላለፍ ይችላሉ።

## 2.4) ሊወጡ ሊያብቡ የደረሱ ወጣቶች መርዳት

ይህ ወደ መጨረሻው ነጥብ ያመጣናል። በተለያየ መስክ ለውጥ ለማምጣት ራእይ ያላቸው ልጆች/ወጣቶች በመካከላችን አሉ። እነዚህ ልጆች/ወጣቶች ወደ ላይ እንዲነሱ ድጋፍ ቢያገኙ፣ የብዙ ሰው ህይወትን በትልቁ የሚለውጥ ነገር ይወጣቸዋል። ነገ አገራችን ገብተው ሆስፒታል ከፍቶች፣ ህዝብን አዳሽ መሪ፣ ወላጅ የሌላቸውን ህጻናትን አሳዳጊ፣ ህዝብን አነቃቂ ይሆናሉ። እነደዚህ አይነት ልጆች ከተደገፉ፣ አገራችን ሌላን መለመን ታቆማለች፤ በራስዋ ልጆች ታብባለች። (በ14 አመቷ 400 ሺህ እርሳስ ሰብስባ የአገሯን ልጆች ልትረዳ ኢትዮጵያ የሄደችው፣ (በዚህ መጸሀፍ ምእራፍ 4 ታሪኳ የተጻፈው ልጅ) አንድ ጥሩ ምሳሌ ነች። ዋናው ማየት ያለብን እነዚህ ልጆች ነገ የት ሊደርሱ እንደሚችሉ ነው፤ ራቅ አድርገን እናስብና፣ የነገን መሪዎች እንደግፍ። እኚህ አይነት ልጆች አብበው እንዲወጡ ስንፈልግ የሚከተሉትን ነጥቦች ልብ እንበል፡

- ✓ እኔ በምራመድበት ካልተራመዱ አልደግፍም ማለትን እናቁም። ዋናው ነገር ላገራችን የሚሆን ራእይ በውስጣቸው መሰነቁ መሆኑን አስታውሰን፣ የነገን ተስፋዎቻችንን ባለን ሁሉ እንደግፍ። "ብቻ ለአገሬ እጅ ሁኑላት እንጂ ይኸው እደግፋለሁ" እንበላቸው። "ለወገኔ ተስፋ የሚሆን ነገር አምጡ እንጂ ባለኝ ሁሉ እደግፋችኋለሁ" ብለን መልእክታችንን

እናስተላልፍላቸው፤ እነዚህ ልጆች ወደላይ ከፍ ብለው እንዲወጡ መሰላል እንሁናቸው።

- ✓ ወደ ድል ሰፈር መውሰጃ ብቸኛ ድልድዩ ተስፋ ነች:: ልጆች/ወጣቶቻችን ስለ አገር ሊሰሙ በፈለጉ ቁጥር፣ ስላለው ችግርና ስለጠፋው ጥፋት ብቻ አናውራላቸው። ከዚህ ጋር ተያይዞ፣ አሉታዊ ህዝብን ዝቅ አድራጊ ንግግሮችን ለማቆም ጥረት እናድርግ፤ "የኛ ነገር አያልፍልን፤ ያበሻ ነገር-የሚሉት ቃላቶች ህዝብን ሰባሪዎች ናቸው:: ልጆቻችን ፊት ሁልጊዜ ስለ አሉታዊ ነገር የምናወራ ከሆነ፣ "ልንለወጥ ተስፋ የለንም" እያልናቸው መሆኑን ልብ ልናደርግ ይገባል፤ በውስጣቸው ያለው ተስፋ እንዲነቃቃና ቀና እንዲሉ፣ ለውጥን ማምጣት እችላለሁ ብለው እንዲያስቡ እናበረታታቸው:: ራእይ ካላቸው፣ ጠንክረው ከሰሩ ተስፋ እንዳለ፣ አገራቸው ህዝባቸው ላይ ለውጥን ማምጣት እንደሚችሉ እንንገራቸው:: በህዝባቸው ውስጥ ስላሉ፣ ቁም ነገር ስለሚሰሩ፣ ጎበዝ ጀግና ሰዎችም እንንገራቸው
- ✓ በተለያየ መልክ እየመጠቁ ያሉን ፣ በማህበረሰባችን ውስጥ ያሉ ልጆች/ ወጣቶቻችንን ለሌላው እናስተዋውቅ:::በትምህርት ትልቅ ደረጃ የደረሱን፣ ያለሙት ህልም ያሳኩን፣ ሌላን የሚጠቅም ስራ እየሰሩ ያሉ ልጆችን፣ ስለ አኩሪ ድርጊታቸው እንግለጽላቸው፤ የሽልማት ጊዜ ብለን ብናዘጋጅ፣ በጽሁፍ ብናስተዋውቃቸው፣ ለብዙ ልጆች ምሣሌ ይሆናሉ:: ሌሎች ልጆችም፣ "እኔም ለውጥ ማምጣት፣ ህዝብን የሚረዳ ነገር ማድረግ እችላለሁ የሚል ነበልባል በውስጣቸው ጭል ጭል ማለት ይጀምራል::





## ወላጅና ልጆችን ለመርዳት፣ የማህበረሰብ ማእከሎች ተሳትፎ፤

### የሃይማኖት ተቋማት

የኢትዮጵያ ህዝብ፣ የተለያየ ሀይማኖት አለን:: ነገር ግን ሁላችንም፣ "ልጆቻችን በፍቅር ማደግ አለባቸው፤ ቤተሰቦቻችንን መርዳት አለብን" በሚለው ሐሳብ ተሳስረናል:: የሀይማኖት ተቋማት ህዝባችንን ለመርዳት፣ ልጆቻችንንና ቤተሰቦቻችንን ለማነጽ በትልቁ ሊያበረክቱ ይችላሉ::

- ➢ ብዙ ለማድረግ፣ ብዙ ለማበርከት ችሎታው፣ ሀይሉ ያላቸው ታዳሚዎች ወደእነዚህ ቦታዎች ይመጣሉ:: ስለ አገልግሎት አስፈላጊነት በየችሎታችን ወንድም እህታችንን መድረስ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ፣ ለታዳሚ ግንዛቤን መስጠት አስፈላጊ ነው:: ከእሁድ እሁድ ጸሎት ስላለፈ.፣ በተግባር ስለተገለጠ የእምነት እርምጃ፣ ሁሌ ሌላን በመጠበቅ ሌላው እንዲህ አላደረገም በማለት ፈንታ ወይ ትልቅ ነገር እስኪሆንልኝ ምንም አላደርግም በሚል ውስን አስተሳሰብ ፈንታ ባለን የማበርከትን አስፈላጊነት፣ ለታዳሚው ማስተማር ትልቅ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል:: ሰዎች ሊሳተፉባቸው የሚችሉትን የተለያዩ የአገልግሎት ሀሳቦችን ማቅረብ፣ የአገልግሎት መስኮችን መክፈትም በትልቁ ሊረዳ ይችላል::
- ➢ ልጆችን ለመርዳት፤ በየሳምንቱ ለልጆች ተብሎ የሚዘጋጀው የልጆች ትምህርት፣ ቁም ነገሩን ሳይለቅ፣ ግን ልጆችን በሚስብ መልክ አድርጎ ማዘጋጀቱ ትልቅ ጥቅም አለው፤ ከልጅነታቸው አልፎ ለወደፊታቸው ህይወት የሚቆይላቸው ግንዛቤ፣ በውስጣቸው ስር የሚቀረጸው ተነቃቅተው ደስ ተሰኝተው ሲማሩ ነውና:: አሳምሮ ማቅረቡ፣ ልጆች

እንዳይሰለቹ፣ ተነቃቅተው በየሳምንቱ እንዲመጡ፣ ከማበርከቱም በላይ እድሜያቸው ከፍ ሲል፣ "አሁን ማንም አያስገድደኝም" ብለው ተሰላችተው እንዳይቀሩ፣ ያኔም ቢሆን ተነቃቅተው እንዲመጡ፣ በእምነታቸው እንዲጠነክሩ ይረዳል::

- በእዚህ ባህል፣ ህብረተሰብ ውስጥ የሚያድጉ ልጆች ሊገጥማቸው የሚችለውን ፈተና ተረድተን፣ ልጆች በጤነኛ መንገድ እንዲቋቋሙ የሚረዳቸውን ግንዛቤ፣ ለእነርሱ በሚገባ መንገድ ማስተማር፣ ብዙ ልጆችን ከብዙ አደጋ ሊጠብቅ ይችላል::
- ከቤተሰብ ጋ ባለ ግንኙነትና ባጠቃላይ በሕይወት ውስጥ ስለሚያልፉበት ውጥረት፣ ልጆች በግልጽ እንዲወያዩ የሚረዳ መድረክ መክፈት፣ (ስፖርት ግሩፕ ማቋቋም) ወዘተ; በእንደዚህ ሁኔታ፣ ከእውነተኛ ህይወታቸው ጋር የተያያዘ ትምህርት ለወጣቶች ማቅረባችን፣ ጥሩ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ከማድረጉም በላይ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ትስስር እንዲጨምር ያበረክታል፤ ለእነርሱ ሕይወት እውነተኝነት ያለው እርዳታን፣ ከእግዚአብሔር እንደሚያገኙ ሲረዱ፣ ፈጣሪያቸውን የበለጠ ለመቅረብና ለማወቅ ጉጉት እያደረባቸው ይመጣል::
- ወጣቶች ፣ በአስራዎቹ እድሜ ያሉ ልጆች፣ የትምህርት እርዳታ ሊያገኙባቸው ስለሚችሉ የተለያዩ መስኮች መጠቆም፣ ትምህርት ቤቶችን (ኮሌጅ፣ የገንዘብ ድጋፍ ተቋማትን) በተመለከተ ልጆችን የሚረዳ አስፈላጊ ምንጮችን፣ በተመለከተ አስፈላጊ ግንዛቤ መስጠት በተለያየ መንገድ እያበቡ ያሉ ልጆችን ማበረታታት፣ ከዚህ ጋር ተያይዞ ህዝብን በአቅም ችሎታ ስለመርዳት አስፈላጊነት ለልጆች/ወጣቶች ማስተማር፣ የብዙ ልጆችን አእምሮ ሊያድስ ይችላል::





- ወላጅን መርዳት፤ ወላጆችን ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ ስለተለያዩ ችግሮች በግልጽ መወያየት፣ ወላጆች ብቻቸውን እንዳልሆኑ መንገር፣ ማበረታታት፣ በልጅ አስተዳደግ፣ ከልጅ ጋ ያለ ግንኙነትን በተመለከተ ለወላጆች ጠቃሚ ግንዛቤ መስጠት፣
- ትዳርን በተመለከተ በተለይ በአዲስ ህብረተሰብ ውስጥ ሊኖር ስለሚችል ፈተና፣ ጫና፣ በግልጽ የሚያወያይ፣ የሚያስተምር መድረክ መክፈት ከልጅ ጋር የተያያዘ ፈተና፣ የጤና ችግር፣ ትዳር፣ እነዚህንና የመሳሰሉ ጉዳዮች ወላጆች በግልጽ እንዲወያዩ፣ ከእርስ በእርስ እንዲማሩ የሚረዳ ስብስብ፣ ( ግሩፕ ማዘጋጀት)
- ለወላጆች፣ የእርዳታ ምንጮችን ማዘጋጀት፤ የወረቀት ጉዳይ፣ የገንዘብ ጉዳይ፣ የስራ ጉዳይ የጤና ጉዳይ-- ወዘተ በተመለከተ ወላጆችን ሊረዳ የሚችል ትምህርታዊ ሲሚናር ማዘጋጀት፣ ጠቃሚ ምንጮች ያላቸው ጽሁፎችን መበተን፤ የሀይማኖት ተቋማት ሊሳተፉበት የሚችሉት ጠቃሚ መንገድ ነው።

## 2) *የማህበረሰብ ማእከል (community center)*

የማህበረሰብ ማእከል፣ ወላጆችና ልጆችን የሚረዳ ነገር ትልቅ ነገር የማበርከት፣ ሀይል አለው:: የማህበረሰብ ማእከል ሊያደርገው የሚችለው ዋናው ነገር፣ የተለያዩ እርዳታ ምንጮችን አቅፎ መያዝ ነው::

- ልጆችን ቤተሰቦችን ሊረዱ ፍላጎት ያላቸውን ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች አሉ:: ምንም እንኳን ከተለያየ እምነትና አሰራር የሚመጡ ቢሆን፣ ይህ ቅዱስ ዐላማ ያገናኛቸዋል:: ዐላማውም እነዚህን ሰዎች ማሰባሰብ፣ እርስ በእርስ ማስተዋወቅ፣ ወጥተው ሌላውን እንዲደርሱ መሰላል መሆን፣ ስራቸውን ማስተዋወቅ፣ የሚያስፈልጋቸው እርዳታ መስጠት ነው።

## *ለወላጅ፤ ከታዳጊ ወጣቶች (teenagers) ጋ ለተያያዘ ጉዳይ*

parentdrugfree.org ልጆቻችንን ከተለያዩ ሱሶች (መጥፎ ልምምዶች) ለመጠበቅ፣ ለማዳን፣ (በየእድሜያቸው ደርጃ ምን፣ እንዴት ልናወራቸው ልንመክራቸው እንደሚገባ በጣም ጥሩ ምክር ይሰጣል
www.theantidrug.com የሚለው ዌብ ሳይት ልጆቻችን ስላለባቸው የተለያዩ ግፊቶች ጥሩ ግንዛቤ ይሰጠናል። እንዴት ልንረዳቸው እንደምንችል ከእነሱ ጋር ባለን የንግግር ልውውጥ (communication) ወደ ድል እንዲሸጋገሩ ረጂ መንገድ ምን ጥሩ ገለጻን ያደርግልናል።
www.parentingteensonline.com ገብተው Resource የሚለውን ቢጫኑ፣ ከልጆቻችንን ጋር በተያያዙ የተለያዩ ጉዳዮች (ስፖርት፣ ትምህርት ቤት፣ ህክምና መጠጥ፣ ድራግ፣ ወዘተ--) በተመለከተ፣ ጥያቄያችንን ሊመልሱልን፣ ግንዛቤ ሊሰጡን ስለሚችሉ የተለያዩ የእርዳታ ምንጮች (resources) በዝርዝር ያሳያል።
**መጸሀፍ፤** Queen Bees Wannabes; Rosaland Wiseman (ሴት ልጆቻችንና በትምህርት ቤት ያለባቸውን ግፊትን በተመለከተ)

## *ልጅን ችግር ሲያጋጥም እርዳታ ጠቋሚ*

1-800=662-4357 treatment referral (የአይምሮ ህክምናን በተመለከተ እና ለድራግ ሱስ እርዳታን በተመለከተ፣እኛ በምንኖርበት አካባቢ ስላሉ የህክምና (treatment) ቦታዎች ይነግሩናል። (ልጆቻችን እዛው ቆይተው እርዳታ የሚያገኙበት፡(in patien treatment ) ሆነ ወይ እየተመላለሱ (out patient treatment) ቦታዎች የት እንዳሉ፣ በመጠቆም ያገለግሉናል። ከዛም በተረፈ፣ በምንኖርበት ስቴት፣ ካውንቲ ውስጥ ዋጋ ቅናሽ፣ ክፍያ እርዳታን ለማግኘት የት እንደምንደውል ይጠቁሙናል።
ከስልኩ ሌላ በአካባቢያችን ስላሉ የእርዳታ ቦታዎች ሊጠቆመን የሚችለው findtreatment.samhsa.gov የተባለ ዌብ ሳይት ነው።
Drugfree.org ልጆቻችን በመጥፎ ልምምድ ውስጥ ከገቡ ወይ በሱስ ከተጠመዱ በኂላ ከእነሱ ጋር ያለንን ግንኙነት በተመለከተ፣ የሚያስፈልጋቸውን ውጫዊ እርዳታ በተመለከተ ምን አይነት እርምጃ ልንወስድ እንደሚገባን ደረጃ በደረጃ ጥሩ ግንዛቤን ይሰጠናል።
National suicide prevention life line
1-800-273-8255
Gambling referral to outpatient and inpatient facilities and support groups in our area
1-800-522-4700
ከቁማር ጋር በተያያዘ ግንዛቤን የሚሰጥ ዌብ ሳይት ncpgambling.og





## *ለወላጅ፤ የልጆች በትምህርት ቤት ጥቃት ለመከላከል*

stopbullying.gov ፣ www.jodeeblanco.com ልጆች በትምህርት ቤት የሚደርስባቸውን ጥቃት በተመለከተ በብቁ ሁኔታ ለመርዳት እንድንችል ጥሩ ግንዛቤን ይሰጠናል።
መጸሀፍ፤ "The Bully, the Bullied and The bystander; How parents and teachers can help break the cycle of violence;" "Odd Girl out; The hidden culture of aggression in girls;" Rachel Simmons

## *ልጆችን ከኮምፒዩተር አደጋ ለመጠበቅ*

www.enough.org ልጅን ከአደጋ ለመከላከል ረጂ ግንዛቤ ይሰጠናል
internetsafety101.org

## *ልጆችና ቴሌቭዥን አጠቃቀማቸውን በተመለከተ*

Commonsensemedia.org ወላጆች ሊያዩት የሚገባ በጣም ጥሩ ዌብ ሳይት ነው Reviews and advice የሚለውን ብንጫን ስለተለያዩ በቴሌቭዥን ስለሚታዩ (shows), ፊልሞች, ቪዲዮ ጌም፣ መጸሀፎች ለልጆቻችን (እንደየእድሜያቸው) ተገቢ ይሁኑ አይሁኑ በግልጽ ያሳየናል።
Parentstv.org ሌላ ጥሩ ድረ ገጽ ነው።

## *ልጆችን በተናጥል ስናሳድግ*

Moreforkids.info/single parenting
Singledad.com
Singlemothers.org

## *የትዳር ባልደረባችንን ልጆች ማሳደግን፤ በተመለከተ*

Step-parenting.com
More4kids.info/step parenting

## *ልጆችና ትምህርታቸው*

*Tutor.com (ትምህርትን በተመለከተ በኮምፕዩተር ለልጆች እርዳታ የሚሰጡ ሰዎች ለማግኘት)*
Brainfuse; offers tutoring help for kids.
*Infoplease.com ፤* (Encyclopedias, dictionaries, atlases, almanacs
*Homeworkspot.com* (Online resources organized by subject and grade level.

## *ለወላጅ ግላዊ ሕይወት*

Helpguide.org (ወላጅ በግል ሕይወቱና በትዳሩ ላሉት የተለያዩ ጥያቄዎች)
Troubledwith.com (ወላጅ በግል ሕይወቱ ለሚኖረው የተለያዩ ጥያቄዎች)

## *የቤተሰብ መንፈሳዊ ሕይወት*

Familyministries.com; ልጆች/ቤተሰብ በመንፈሳዊ ሕይወት ታንጸው እንዲቆዩ፤ ለወላጅ ጥሩ ግንዛቤ የሚሰጥ ድረ ገጽ ነው
Anointedyouth.org፤ ለታዳጊ ወጣቶች
Churchofchrist.org; ለልጆች





# ዋቢ መጻሕፍት


- Carson Ben (1996) <u>Think Big</u>, Zondervan Publishing Co
- Carson Ben (2009) <u>Gifted Hands; The Ben Carson Story</u>, Zondervan Publishing
- Cline and Jim Fay (2006) <u>Parenting teens with love and logic,</u> Nava Press Publishing
- Crockenberg, S., & Litman, C. (1990) <u>Autonomy as competence in 2 year olds; Maternal Correlates of child defiance, compliance and self-assertion.</u>
- <u>Drug free.org</u>
- Dyer Wayne (1985) <u>what do you really want for your children</u>, Addison Wesley publishing company.
- Fitzgerald Helen; (1992) <u>The Grieving Child: A Parent's Guide</u> , Touchstone publishing
- <u>Epstein 2010 Robert Epsteing Scientific American Mind Novem ber 2010 issue page</u>
- Gregory S. Smith; (August 30, 2007) <u>How to Protect Your Children on the Internet</u>: A Road Map for Parents and Teachers, Praeger publisher
- <u>Howtostopbullying.com</u>
- Huston, A. C., Donnerstein, E., Fairchild, H., Fashbach, N. D., Katz, P. A., Murray, J. P., Rubinstein, E. A., Wilcox, B. L., Zuckerman, D., (1992). <u>Big world, small screen; The role of television in American Society.</u> Lincoln, NE: University of Nebraska.
- (Internet safety 101.org)

- Jing Zhou, M.S, BCBA Decreasing problem behaviors through good teaching www.brightfeats.com/articles
- Maccoby, E. E., & Martin, J. A. (1983). Socialization in the context of the family: Parent–child interaction. In P. H. Mussen & E. M. Hetherington, Handbook of child psychology: Vol. 4. Socialization, personality, and social development (4th ed.). New York: Wiley
- Murray J.P (1997) Media violence and youth; children in a violent society J. Osofsky (Ed),New York , Guilfor Press
- (National Center for Missing and Exploited Children, 2008).
- Obama, Barack. (2004) Dreams From My Father, Three Rivers Press, New York City
- Obama, Michelle; (December 2011-Jan 2012) Readers Digest
- Online Victimization of Youth: Five Years Later. (2006) National Center for Missing & Exploited Children, Crimes Against Children Research Center, Office of Juvenile Justice and Delinquency Prevention. December 4, 2006. http://www.unh.edu/ccrc/pdf/CV138.pdf)
- Rigby Jill (2008) Raising unselfish children in a self absorbed world, Howard books.
- Sheras Peter, (2002) Your Child: Bully or Victim? Understanding Fireside; Sumon and Schuster.
- Smith A Charles (1999) The encyclopedia of parenting theory and research
- Spelling Tori (2008) sTORI telling , Simon Spotlight
- Steinberg Laurence (2011) you and your adolescent, Simon and Schuster







- Victoria Rideout, Donald F. Roberts. Ulla G. Foehr. March 2005. Generation M: Media in the Lives of 8-18 Year-Olds. The Henry J. Kaiser Family Foundation. 17 November 2006, http://www.kff.org/entmedia/up...f-8-18-Year-olds-Report.pdf).
- Wolf Liz (1992) The beauty myth; How images of beauty are used against women ,publisher--Anchor
- (www. Parenthood.com ) Wolf Liz